አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝም ና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# “የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የስራ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ህይወታቸው”

በ

ሀብታም ግዛት

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

“የዳባት ወረዳ  ገበሬዎች የስራ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ህይወታቸው”

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝም ና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

*በ*

**ሀብታም ግዛት**

2006 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| አማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________ | ______________________ |
| ______________________ | ______________________ |
| **ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** |
| ______________________ | ______________________ |
| ______________________ | ______________________ |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ርዕስ ከመምረጥ ጀምሮ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው አቅጣጫ በመጠቆም፣ የጐደለውን በመሙላት፣ የተጣመመውን በማቃናት ገንቢ ሙያዊ ምክራቸውን በመለገስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጥናታዊ ጽሁፉን ላረሙልኝ አስተማሪዬና አማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ እግዚያብሄር እድሜና ጤና ይስጥልኝ፡፡

ትምህርት በተከታተልኩባቸው ዓመታት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍቅራችሁን በመቸር ትምህርቴ ከግብ ይደርስ ዘንድ፣ የገንዘብና የሀሳብ ድጋፍ በማድረግ፣ ማቴሪያል በማባዛት ላልተለያችሁኝ የክፍል ጓደኞቼ መኮነን አስማማውና የኔዓለም ካሣሁን፣ ቤተሠቦቼ እናንየ አንባቸው፣ ጀግናው አንባቸውና መለስ ምህረት ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ እግዚያብሄር ውለታችሁን ይክፈላችሁ፡፡

ካሜራ ከማዋስ ጀምሮ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝና ጥናቴ በታቀደው ጊዜ ታርሞ ይጠናቀቅ ዘንድ ኮምፒውተር በማዋስ ፣ የማስተካከያ ሀሳብ በመስጠትና የተጣመመውን በማቃናት እገዛ ላደረገልኝ ወንድሜ ዮሐንስ አቸነፈ ላቅ ያለ ምስጋናየ ይድረሰው፡፡ እንዲሁም የተለያየ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝና በፀሎታችሁ ለምታስቡኝ ቤተሰቦቸና የክፍል ጓደኞቸ በሙሉ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በመስጠትና በጥሩ መስተንግዶ ለተቀበሉኝ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች፣ መረጃ በምሰበስበበት ወቅት ስራ ፈትታችሁ ከእኔ ጋር ለተንከራተታችሁት የመስክ ረዳቶቸ አቶ አድን ዱቤ፣ አደራጀው ዱቤ፣ ደጀን ንጉሴና ሃይለ ሚካኤል መንግስቱ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት የሚሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ ሃድጉ ተካ፣ ብሩክታዊት ተስፋዬ፣ ሰሚራ ሙሃመድ፣ ፍፁም ብርሃኑ፣ ቴዎድሮስ አለበል አመሰግናለሁ፡፡ ይህን የትምህርት እድል ለሠጠኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ በመጨረሻም ፅሁፉን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል እስከመጨረሻው ታግሳ የተየበችልን ፍሬህይወት ዳኜን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

# አበርክቶ

ይህ ጥናት ቀን ፀሃዩ ፣ ማታ ጨለማው ሳይገድባት ፣ አቀበት ወጥታ ፣ ቁልቁለት ወርዳ ላስተማረችኝ ፣ ዳዴ እያልኩ ውለታዋን ላልከፈልኳት ስኬቴን ለማየት ለምትናፍቀውና በተስፋ ለምትጠብቀኝ አንደበቷ ሰላሜና ምግቤ፣ ፀሎቷ ጤንነቴ ሆኖ ለዚህ ላደረሰችኝ ውድ እናቴ ፀሀዬ አዳነ ይሁንልኝ፡፡ እናቴ የደከምሽበትን ፍሬ ትበይ ዘንድ እድሜና ጤና ይስጥልኝ ፡፡

ማውጫ ገፅ


ምስጋና ........ I

አበርክቶ ........ ii

ማውጫ ........ iii

ሙዳዬ ቃላት ........ vii

አጠቃሎ ........ viii

1. መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 1

1.2. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 3

1.5. የምርምር ጥያቄዎች ........ 4

1.6. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የናሙና አመራረጥ ........ 4

1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 4

1.6.1.1. ምልከታ ........ 5

1.6.1.2. ቃለ መጠይቅ ........ 6

1.6.2. የናሙና አመራረጥ ........ 7

1.7. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 8

1.8. የጥናቱ ዘዴ ........ 8

1.9. የጥናቱ ወሰን ........ 8

1.10. በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች ........ 9

1.10.1. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 9

1.10.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 10

1.11. የመስክ ተሞክሮ ........ 11

2. ክለሳ ድርሳን ........ 14

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 14

2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 18

2.2.1. የስራ ቃል ግጥሞች ........ 18

2.2.2. ክዋኔ ........ 19

2.2.3. አውድ ........................................................................................ 22
2.2.4. ደረሳ ........................................................................................ 24
2.2.5. ተስተላልፎ ........................................................................................ 26
2.2.6. የስራ ላይ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ........................................................................ 27

3. የዳባት ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ ........................................................................ 28
3.1. የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ማህበራዊ ህይወት ........................................................ 31
3.1.1. በኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች ................................................ 31
3.1.2. በእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ................................................ 33
3.1.3. በኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ................................ 35
3.2. የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ ................................................ 36
3.2.1. የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች ................................................ 37
3.2.2. የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ................................................ 40
4. የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም አደራረስ አከዋወንና ተስተላልፎ 43
4.1. የቃል ግጥሞች አደራረስ ........................................................................ 43
4.2. የቃል ግጥሞች ክዋኔ ........................................................................ 47
4.2.1. በተናጠል የሚከወኑ ቃል ግጥሞች ................................................ 50
4.2.2. በጥንድ /በቅብብሎሽ/ የሚከወኑ ቃል ግጥሞች ................................ 51
4.2.3. በቡድን የሚከወኑ ቃል ግጥሞች ................................................ 52
4.3. የቃል ግጥሞች ተስተላልፎ ........................................................................ 53
4.4. ቃል ግጥሞች የተከወኑባቸው የስራ አጋጣሚዎች ........................................ 54
4.4.1. የአውድማ አውድ ........................................................................ 55
4.4.2. የአጨዳ አውድ ........................................................................ 57
4.4.3. የእርሻ አውድ ........................................................................ 59
4.4.4. የጉልጓሎ አውድ ........................................................................ 60
4.4.5. የአረም አውድ ........................................................................ 61
5. የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና ........................................................................ 62
5.1. የአውድማ ቃል ግጥሞች ........................................................................ 62

5.1.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ........ 62
5.1.2. እናትን የሚያወድሱ ........ 65
5.1.3. ምክር የሚሰጡ ........ 66
5.1.4. የወንድምን አስፈላጊነት የሚገልፁ ........ 70
5.1.5. ስለ በሬ የተዜሙ ........ 72
5.1.5.1. የበሬን አስፈላጊነት የሚገልፁ ........ 72
5.1.5.2. በሬን የሚያወድሱ ........ 74
5.1.5.3. የበሬን ዳተኝነት የሚገልፁ ........ 76
5.1.5.4. በበሬ ላይ የሚደርስን በደል የሚገልፁ ........ 76
5.1.6. ፀፀትን የሚገልፁ ........ 77
5.2. የአጨዳ ቃል ግጥሞች ........ 78
5.2.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ........ 78
5.2.2. የውዳሴ ቃል ግጥሞች ........ 81
5.2.2.1. ገበሬን የሚያወድሱ ........ 81
5.2.2.2. አገርን የሚያወድሱ ........ 84
5.2.3. ትችትን /ስድብ/ የሚገልፁ ........ 86
5.2.4. ምክር የሚሰጡ ........ 87
5.2.5. ፀፀትን የሚገልፁ ........ 89
5.3. የእርሻ ቃል ግጥሞች ........ 90
5.3.1. ትችትን /ስድብ/ የሚገልፁ ........ 91
5.3.2. ገበሬን የሚያወድሱ ........ 94
5.3.3. ምክር የሚሰጡ ........ 98
5.3.4. የገበሬን ተስፋ የሚገልፁ ........ 100
5.4. የአረም ቃል ግጥሞች ........ 101
5.4.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ........ 101
5.4.2. ትችትን /ስድብ/ የሚገልፁ ........ 103
5.4.3. ምክር የሚሰጡ ........ 104
5.4.4. ገበሬን የሚያወድሱ ........ 105

5.4.5. ፍቅርን የሚገልፁ ....107

5.4.6. ፀፀትን የሚገልፁ ....108

5.5. የጉልጓሎ ቃል ግጥሞች ....109

5.5.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ....109

5.5.2. ገበሬን የሚያወድሱ ....110

5.5.3. ምክር የሚሰጡ ....112

6. ማጠቃለያ ....114

የተጠቀሱ ምንጮች ....117

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል ....119

አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች ....123

አባሪ ሶስት፡- ከመስክ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ....125

አባሪ አራት፡- ካርታ ....175

አባሪ አምስት፡- ፎቶ ግራፎች ....176

## ሙዳዩ ቃላት

1. ማንጨህጨህ = እህሉን በእንቅብ በማንዘርዘር ከገለባው በነፋስ መለየት
2. ማቶት = በዛፍ ልጥና በእሳር ገመድ የሚሰራ ጠላ በእንስራ የሚቀመጥበት
3. ማጭድ = ለእህል ማጨጃ የሚያገለግል የብረት መሳሪያ
4. ምጎጎ = የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ
5. ቁና = ከእሳር የሚዘጋጅ አነስተኛ መጠን ያለው የስፌት አይነት
6. ቡቡኝ = ያለ ጌሾ የሚዘጋጅ የሙስሊሞች የመጠጥ አይነት
7. አቁማዳ = ከቆዳ ቁርበት የሚዘጋጅ የእህል መቋጠሪያ
8. አንጣር = አንፃር
9. አገልግል = የተለያየ አገልግሎት ያለው ክብ የስፌት አይነት
10. አግማስ = በረከት ረድኤት
11. አጐዛ = ከእንሰሳት ውጤት የሚዘጋጅ ምንጣፍ
12. እንቅብ = የተለያየ አገልግሎት ያለው ከእሳር የሚዘጋጅ የስፌት አይነት
13. እፉታ = የበሬ ድምፅ
14. ኮረፌ ጠላ = የሚጠመቅ የጠላ አይነት
15. ወሰን = (ሰን) ይጠብቃል ውሳኔ ማሳረፍ
16. ወገዳ = ወገዳ (ረገዳ) ማለት ገበሬው ጃሎ ብሎ ግጥሙን ሲጨርስ ለማጨድ የሚደረግ ፉክክር ነው፡፡
17. ዋንጫ = ከከብት ቀንድ የሚዘጋጅ የጠላ መጠጫ
18. ዋዳት = የሊጥ ማቡኪያ እቃ
19. ጥሩ ጠላ = ከኮረፌ ጠላ የተለየ አዘገጃጀት ያለው የጠላ አይነት
20. ጩልዳ = እርሻ ሲታረስ ለበሬ መግረፊያ የሚያገለግል መሳሪያ(ጅራፍ)
21. ፉጨት = እህያ ለመንዳት ከጉሮሮ የሚወጣ ድምፅ
22. ፌጦ = ለተለያየ አገልግሎት የሚውል የፍሬ አይነት

# አጠቃሎ

ከዚህ በፊት በመጀመሪያም ሆነ ሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ በዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል-ግጥም ክዋኔና ማህበራዊ ህይወት ላይ ጥናት አልተደረገም፡፡ በገበሬዎች ቃል ግጥም ላይ የተለያዩ አጥኝዎች በተለያዬ ቦታ ጥናት ቢያደርጉም ቃል ግጥም ከቦታ ቦታ፣ ከከዋኝ ከዋኝ ሊለያይ የሚችል በመሆኑና የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን እንደሚመስል መገለፅ አለበት በሚል እምነት ይህ ጥናት የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም ክዋኔና ማህበራዊ ህይወት ላይ የተደረገ ነው፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ የስራ አይነቶች(አጋጣሚዎች) ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን ቃል ግጥሞች በአውዳቸው በመሰብሰብ የሚያነሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፣ የግጥሞቹን ማህበራዊ ፋይዳ መግለፅና ገበሬዎች ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ማሳየት ነው፡፡

ጥናቱ በዋናነት በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ የተቀነበበ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱም በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የጥናቱ አቀራረብ በገላጭ የምርምር ዘዴና ይዘት ትንተና ላይ ተመስርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችም ከቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎችም በምልከታና ቃለ መጠይቅ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ሲሆን እንደአስፈላጊነታቸውና እንደ መረጃ ሰጭዎቹ ፍላጎት በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ካሜራ፣ በመቅረፀ ድምፅና በማስታወሻ ደብተር ተሰንደዋል፡፡

ጥናቱ ከወረዳዋ 30 ቀበሌዎች መካከል በተመረጡ ሰባት ቀበሌዎች ላይ የተደረገ ሲሆን መረጃዎችም ከ33 ቁልፍና ከ15 ረዳት መረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት በውቂያ፣ በአጨዳ፣ በእርሻ፣ በአረምና በጉልጓሎ የስራ አጋጣሚዎች በአውድ ውስጥና ከአውድ ውጭ ሲሆን ከ580 በላይ ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ገበሬዎች በተደጋጋሚ ያነሷቸው 54 ቃል ግጥሞች ተመርጠው በተከወኑበት አውድ መሰረት በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተከፋፍለው ገለፃና የይዘት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

ከመረጃ ትንተናው ግኝት መረዳት እንደሚቻለው የዳባት ወረዳ የኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ጥብቅ ግንኙነት የሚፈጥሩት በጋብቻ፣ በተዝካር፣

በዓመታዊ ክብረ በዓላት፣ በሰንበቴ፣ በለቅሶ፣ በክርስትና፣ አበልጅነትና በሆበራ ስራ ጊዜ መሆናቸው በጥናቱ ተገልጿል፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች በእምነታቸው የማይፈቀደውን በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከባድ ከባድ የሚባሉትን የቅዱስ ሚካኤል፣ ማሪያም፣ ባለእግዚያብሄርና ሰንበት (እሁድ) በዓላትን ያከብራሉ፡፡ የሚያከብሩበትም ምክንያት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች አዝዕርታቸውን በረዶ ሲደበድበውና አንዳንድ ችግሮች ሲያጋጥሟቸው የችግሩ መንስኤ አድርገው ስለሚቆጥሯቸው ከአገር ባህል ሳይወጡ ግንኙነታቸውን በማጠናከር ተቻችለው በሰላም ለመኖር መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

እነዚህ ገበሬዎች በአዘቦት ቀን፣ በሰንበት ቀን (እሁድና ቅዳሜ)፣ በዓመታዊ ክብረ በዓላት ቀንና በመንግስት በዓላት ቀን የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ የስራ ድርሻቸውንም ስንመለከት ሴቶች ከቤት ስራቸው በተጨማሪ የውጭ የግብርና ስራ በማከናወን ሰፊውን ቦታ ሲይዙ ወንዶች በመስክ ስራ ብቻ ስለሚሳተፉ በሴቶች ላይ የስራ ጫና እንደሚፈጠርባቸው ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው የሰሙትን ቃል ግጥም ከነዜማ አወራረዱ በመሸምደድ፣ የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀምና አውድን መሰረት አድርገው የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝና የይዘት ለውጥ በማድረግ፣ ለውጥ ሳያደርጉና ሙሉ ለውጥ በማድረግ ይከውናሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜም በሽምደዳ እንደሚያቀርቡና የሚከውኑትም በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን ስልት እንደሆነ በጥናቱ ታይቷል፡፡

ገበሬዎች በእርሻ፣ በውቂያ፣ በአጨዳ፣ በአረምና በጉልጓሎ የስራ አጋጣሚዎች ባዜሟቸው ቃል ግጥሞች ብሶትና ምሬትን፣ ትችትን (ስድብ)፣ ውዳሴን፣ ምክርን፣ የወንድምን አስፈላጊነት ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ስለበሬ፣ ስለፍቅር፣ ስለተስፋና ስለፀፀት የሚያወሱ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስተዋል፡፡ ገበሬዎች ቃል ግጥሞቹን ያለፈና የወደፊት አኗኗራቸውን፣ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ በአጠቃላይ ስለ ህይወት ያላቸውን ፍልስፍና ለመግለፅ እንደሚጠቀሙባቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ ስድስት ምዕራፎች አሉት፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችና የናሙና አመራረጥ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፈትሄዎች እንዲሁም የመስክ ገጠመኝ ይቀርባል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝትና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ይቀርባል፡፡

በምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ገፅታ፣ የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ ተካተዋል፡፡

በምዕራፍ አራት የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም አደራረስ፣ አከዋወንና ተስተላልፎ፣ እንዲሁም የቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች ይገኙበታል፡፡

በምዕራፍ አምስት የስራ ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና የሚደረግበት ሲሆን በምዕራፍ ስድስት የጥናቱ ማጠቃለያ የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዳራ

ስነ-ቃል ከፎክሎር ዘውጎች አንዱ ነው፡፡ ቃል ግጥም ደግሞ ከስነ-ቃል ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ ቃል ግጥም በመዜምና በመንጎርጎር በቃል የሚፈጠር ሲሆን የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ፣ ከዋኝና ታዳሚ አለው፡፡ በዚህ ፈጠራ ህዝብ አመለካከቱን፣ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ ድጋፍና ተቃውሞውን ይገልፅበታል፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎችም እምነትና ታሪካቸውን፣ ስሜትና ፍላጎታቸውን፣ ድጋፍና ተቃውሟቸውን፣ ወግና ልማዳቸውን የሚገልፁበት የተለያዩ ስነ-ቃል አላቸው፡፡ ካሏቸው የስነ ቃል አይነቶችም አንዱ ቃል ግጥም ነው፡፡

ከቃል ግጥም አይነቶች የስራ ግጥም አንዱ ሲሆን በውስጡ ከሚያካትታቸው ዘሮቹ የገበሬዎችን የስራ ግጥም እናገኛለን፡፡ "በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጠል የተለያዩ ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራትና ራሱን ከድካም ነፃ ለማድረግ እንዲያግዘው ግጥም እየደረደረ ያንጐራጉራል፣ ይዘፍናል፣ ይጨፍራል፡፡" /ዘሪሁን፣ 2004፣ 46/፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎችም በጋራም ሆነ በተናጠል ስራቸውን ሲያከናውኑ ይዘፍናሉ፣ ይጨፍራሉ፣ ያንጐራጉራሉ ፡፡

በቃል ግጥም ላይ በአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በኤምኤ ዲግሪና ባችለር ዲግሪ ደረጃ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ እነዚህን ጥናቶች ስንመለከት የሴቶችና የወንዶችን የስራ ክንውን መሰረት በማድረግ የተጠኑ ናቸው፡፡

በኤምኤ ደረጃ ከተደረጉ ጥናቶች ብርሃኑ አሳዬ "በባንጃ ና አንካሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ግጥሞች"(1999ዓም)፣ Getie Gelaye "Peasant Poetics and State Discourse in Ethiopia: Amharic Oral Poetry as a Response to the 1996-1997 Land Distribution Policy" (1999) ፣ የማሞ ተፈራ "በመኸር ወቅት የሚፈፀሙ ሀገረ ሰባዊ እምነቶች ፋይዳ እና የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና በዳንግላ ወረዳ እና አካባቢው" (2002 ዓ.ም)፣ የቀለመወርቅ ተክሌ "የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና" (2004 ዓ.ም) ፣ ጋሻው አሻግሬ "በእብናት ወረዳ ባህላዊ ወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና" (2005 ዓ.ም) ይገኛሉ፡፡ በኤምኤ ደረጃ ጌቴ ገላዬ መረጃውን የሰበሰበው በግብርናና ሌሎች አውዶች ጭምር ሲሆን ትኩረቱም የገበሬዎች ፖለቲካዊ ግጥሞች ላይ ነው፡፡ የማሞ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱ ሀገረ ሰባዊ እምነቱ ላይ ሲሆን የገበሬዎችን ቃል ግጥም በአጨዳ፣ ውቂያና ክምር የስራ አይነቶች በአውድ ላይ ሰብስቦ የይዘት ትንተና በማድረግና የብርሃኑ ጥናት ሴቶች በአጨዳና ውቂያ የመስክ ስራ ያላቸውን ተሳትፎ አሳይቷል፡፡ የቀለመወርቅ ተክሌና የጋሻው አሻግሬ ጥናትም በሴቶች ስራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም የስነ ቃል ዘሮች በመሆናቸው ሊመሳሰሉ ቢችሉም ቃል ግጥም ከቦታ ቦታ፣ ከከዋኝ ከዋኝና ከአውድ አውድ ልዩነት ማሳየቱ አይቀርም፡፡ የገበሬዎች ቃል ግጥምም ከማህበራዊ ህይወታቸውና የዕለት ተዕለት ውሏቸው ጋር ተያይዞ መጠናት አለበት፡፡

በአጠቃላይ የጥናቶቹ ትኩረት ሀገረሰባዊ እምነት ላይ፣ የአጨዳ፣ ውቂያና ክማሮና ሌሎች ከግብርና ውጭ ያሉ የስራ አይነቶችና በሴቶች ስራ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ የቃል ግጥም አደራረስና ተስተላልፎ እንዲሁም የገበሬዎች ማህበራዊ ህይዎትና የዕለት ተዕለት ውሎ አልተገለፀም፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመሙላት በዳባት ወረዳ ገበሬዎች የአረም፣ የእርሻ፣ የጉልጓሎ፣ የአጨዳና የውቂያ የስራ አጋጣሚዎች ወቅት ቃል ግጥሞችን ከማህበራዊ አውዳቸው በመሰብሰብ በሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች የይዘት ትንተና ማናድረግ፣ የቃል ግጥሞቹን አደራረስ፣ ተስተላልፎ፣ ማህበራዊ ፋይዳ፣ የገበሬዎችን ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን እንደሚመስል መግለፅ ላይ ያተኩራል፡፡

### 1.3. **የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት**

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዳጠና ጥቆማ በማድረግ አቅጣጫ ያሳዩኝ መምህሬ ዘሪሁን አስፋው ናቸው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ትኩረቴን ስለሳበው እና ከዚህ በፊትም በትውልድ ቦታየ በገበሬዎች የስራ መስክ በመሳተፍ ቃል ግጥሞችን ሲደረድሩ እሰማቸው ስለነበር በፎክሎር ትምህርት ባገኘሁት እውቀት ምክንያት ጉዳዩን ተጠግቶ የማጥናት ፍላጎት አደረብኝ፡፡

በገበሬዎች ቃል ግጥም ላይ የተለያዩ አጥኝዎች በተለያዬ ቦታ ጥናት ቢያደርጉም በዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም ክዋኔና ማህበራዊ ህይወት ላይ በመጀመሪያም ሆነ ሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ከዚህ በፊት የተጠና ጥናት አለማግኘቴ ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

በተጨማሪም ቃል ግጥም ከቦታ ቦታ፣ ከከዋኝ ከዋኝ ሊለያይ የሚችል በመሆኑ እና የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን እንደሚመስል መገለፅ አለበት በሚል እምነት ጥናቴን የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም ክዋኔና ማህበራዊ ህይወታቸው በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማድረግ ተነሳስቻለሁ፡፡

### 1.4. **ጥናቱ ዓላማዎች**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ የስራ አይነቶች /አጋጣሚዎች/ ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን ግጥሞች በአውዳቸው በመሰብሰብ የሚያነሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፣ የግጥሞቹን ማህበራዊ ፋይዳ መግለፅና ገበሬዎች ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ማሳየት ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ገበሬዎች ግጥሞችን የሚደረድሩባቸውን የስራ አይነቶች ለይቶ መግለፅ፣
- ገበሬዎች እያንዳንዱን የስራ አይነት ሲያከናውኑ የሚያዜሟቸውን ግጥሞች ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፣
- ገበሬዎች እርስ በርስ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት እና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን እንደሚመስል መግለፅ፣
- የቃል ግጥሞቹን አደራረስ፣ ተስተላልፎ ና በማን፣ ለማን፣ ለምን፣ እንዴት እንደሚከወኑ መግለፅ፣

- የስራ ቃል ግጥሞች ከዋኝና ተሳታፊዎች በክዋኔ ወቅት ያላቸውን ሚና መግለፅ፣
- ሴቶች በግብርና ስራ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ መግለፅ፡፡

## 1.5. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የተነሳበትን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች መልሷል።

- ገበሬዎች የሚያከናውኗቸው የስራ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
- ገበሬዎች በስራ ዘፈኖቻቸው ምን ምን ርዕሰ ጉዳዮችን ያነሳሉ? ልዩነትስ አላቸው ወይ?
- በስራ ላይ መዝፈን ለገበሬዎች ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?
- ገበሬዎች የስራ ዘፈናቸውን እንዴት ይደርሱታል? እንዴትስ ያስተላልፉታል?
- ገበሬዎች እርስ በርስ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል? የዕለት ተዕለት ውሏቸውስ ?
- ሴቶች በግብርና ሙያ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ምን ይመስላል?

## 1.6. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የናሙና አመራረጥ

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች እንዴትና በምን ዘዴ እንደተሰበሰቡና እንደተመረጡ ይቀርባል፡፡

### 1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ስነ-ቃሉ በሚከወንባቸው ባህላዊና ማህበራዊ አውዶች፣ በክዋኔ ላይ የተሳተፉት ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ ለክዋኔው መንስኤ የሆኑት የክዋኔ አጋጣሚዎች ናቸው። ቀዳማይ መረጃዎቹም ወደ መስክ በመውጣት በገበሬዎች የስራ ክዋኔ ወቅት በአውዱ የሚገኙትን ከዋኝና ታዳሚዎች፣ በመመልከትና በመጠየቅ፣ የስራ ቃል ግጥሞችን የተመለከቱ መረጃዎች በተፈጥሯዊ መቼት ተሰብስበዋል፡፡ የገበሬዎች የስራ ግጥም ወቅታዊ ስለሆነ ክዋኔውን ማግኘት ያልተቻለውንና የገበሬዎችን ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ የተመለከተውን መረጃ ከክዋኔ ውጭ አርቲፊሻል መቸትን እንደሁኔታው በመጠቀም በቃለ መጠይቅ ሰብስቤያለሁ፡፡

ርዕሰ ጉዳዩን የተመለከቱ ንድፈ ሀሳቦችና ፅንሰ ሀሳቦችን ከተለያዩ መፃህፍት፣ መጣጥፎች፣ ከቤተ መፃህፍትና ኢንተርኔት እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ ይህ ጥናት የተነሳበት አላማ ግብ ይመታ ዘንድ ሁለቱንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም ምልከታና ቃለ መጠይቅ በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

1.6.1.1. **ምልከታ**

ምልከታ በተለያዩ የክዋኔ አጋጣሚዎች በአካል በመገኘት መረጃን ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ ተሳትፏዊ፣ ፅሞናዊና ህቡዕ ተብሎ በሶስት ይከፈላል፡፡ ከእነዚህም የምልከታ ዘዴዎች ተሳትፏዊና ፅሞናዊ ዘዴዎች ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉ ሲሆን ህቡዕ የምልከታ ዘዴ በድብቅ መረጃን ለመሰብሰብ የሚደረግ በመሆኑና ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ አልተጠቀምኩበትም፡፡

ተሳትፏዊና ፅሞናዊ የምልከታ ዘዴዎች የየራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው፡፡ ተሳትፏዊ የምልከታ ዘዴ ክዋኔውን ለመገንዘብ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም ማስታወሻ ለመያዝና ለመቅረፅ አያስችልም፡፡ በሌላ በኩል ፅሞናዊ ዘዴ በተሳታፊዎች ላይ መነቃቃትን ለመፍጠር፣ ማስታወሻ ለመያዝ፣ በቴፕ ለመቅዳትና ፎቶ ለመያዝ ያስችላል፡፡

በመሆኑም የገበሬዎች የስራ ቃል ግጥሞች በተለያዩ ወቅቶችና ማህበራዊ አውዶች የሚፈጠሩ ሲሆን ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑበትን ማህበረ ባህላዊ አውድ፣ የገበሬዎችን የቃል ግጥም አደራረስና ማህበራዊ ፋይዳ በመመልከት ለመተንተንና የዕለት ተዕለት ውሏቸው፣ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ምን እንደሚመስል ለመቃኘትና ለመረዳት፣ የከዋኞችና ታዳሚዎችን ተሳትፎ፣ የክዋኔውን ሂደት፣ የከዋኞችን እንቅስቃሴና ሚና፣ ያላቸውን የእርስ በርስ መስተጋብር በጥልቀት በማስተዋል መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሳትፏዊ የምልከታ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ተሳትፏዊ ዘዴን ከመስክ ረዳቴ ጋር ከሰዎቹ ጋር በደንብ እስከምለማመድ ሳካሂድ እቆይና ከዚያ መረጃወቹን በማስታዎሻ ደብተርና በመቅረፀ ድምፅ ለመያዝ ፅሞናዊ ዘዴን እያፈራረኩ ተጠቅሜያለሁ፡፡

ዳባት ተወልጄ ያደግሁበት አካባቢ በመሆኑ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ የአኗኗር ስርዓቱንና የስራ ክዋኔውንም በመሳተፍ ስላሳለፍኩት ወደ ማህበረሰቡ ዘልቆ በመግባት

ግልፅና ትክክለኛውን ፎክሎራዊ ገፅታ ለማግኘት ስለሚያስችለኝ ተሳትፏዊ የምልከታ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡

ፅሞናዊ የምልከታ ዘዴም የክዋኔውን ሂደትና ጥቃቅን ጉዳዮች ዳር ሆኖ በመመልከት በማስታወሻ ለመያዝ፣ በቴፕ ለመቅዳትና ተሳታፊዎችን ለማበረታታት እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

### 1.6.1.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በዚህ ጥናት ከምልከታ በኋላ ተከናውኗል፡፡ በመሆኑም ለቃለ መጠይቅ ከተዘጋጁት ጥያቄዎች በተጨማሪ በምልከታ ወቅት የሚፈጠሩትን ጥያቄዎች ለመመለስና ክፍተቶቹን ለመሙላት ስለሚያስችለኝ ቃለ መጠይቅ ተጠቅሜያለሁ፡፡ ቃለ መጠይቅ የመረጃ ሰጭዎችን እውቀት፣ እምነት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ደርጊት፣ ገለፃና ምክንያት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስችላል /Goldstien 1964፡104/፡፡ በዚህ ዘዴ መረጃ የተሰበሰበው በክዋኔ ወቅት ከሚገኙት ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ የፆታ፣ የእድሜና የሙያ ስብጥር በማድረግ ነው፡፡ ስብጥር የተጠቀምኩት የተለያዩ እውቀት፣ ክህሎት፣ ችሎታና አመለካከት ካላቸው መረጃ ሰጭዎች ጥልቅ መረጃ ለማግኘት ያስችለኛል ብዬ በማሰብ ነው፡፡

ለመረጃ ሰጭዎች የቀረበው የቃለ መጠይቅ ጥያቄ ክፍትና ዝግ ጥያቄ ሲሆን፣ ክፍት ጥያቄ ለጠያቂውም ሆነ መረጃ ሰጭው ነፃነት የሚሰጥ በመሆኑ ከዚያው ላይ ጥያቄ በመፍጠር አስፈላጊውን በቂ መረጃ ለማግኘት አስችሎኛል፡፡ ዝግ ጥያቄ አጭርና ማብራሪያ የማያስፈልጋቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ክፍተት ለመሙላት፣ ለማዳበርና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች በመጠየቅ የመረጃዎችን ተጣጣሚነት ለማረጋገጥ አስችሎኛል፡፡ /Goldstien፣ 1964:113/ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለተመሳሳይ መረጃ አቀባዮች እንዲሁም፣ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች መጠየቅ፣ የቀደምት ቃለ መጠይቆችን መረጃ ወጥነት አለመኖር ለመመርመር፣ የመረጃ አቀባዮችን ውስብስብ ሁኔታና ስሜት ግልፅ ለማድረግ፣ የተለያዩ ጉዳዮችን ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች በመጠቀም መረጃዎች እንደ አስፈላጊነታቸው በማስታወሻ ደብተርና በመቅረፀ ድምፅ ወምስል ተሰብስበዋል፡፡

እነዚህን መሳሪያዎች መጠቀም አጠቃላይ የክዋኔውን እንቅስቃሴ ለመቅረፅ ና መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስችሎኛል፡፡

### 1.6.2. የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ ታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን መሰረት ያደረገ ሲሆን በዳባት ወረዳ ከሚገኙ ሰላሳ ቀበሌዎች መካከል ለጥናት የተመረጡት ሰባት ሲሆኑ እነሱም ቃርሃ፣ ዳራ፣ ጭላ፣ በንከር፣ ጫርቢጣ፣ አብጠራና ታላቅ መስክ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት በርካታ ቃል ግጥም ደርዳሪ ገበሬዎች የሚገኙባቸው በመሆኑና መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ወቅት የስራ ክዋኔያቸው ያላለፈ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

ገበሬዎች ከሚያከናውኗቸው የስራ አጋጣሚዎች እርሻ፣ አጨዳ፣ ውቂያ፣ አረም፣ ጉልጓሎ ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡበትም ምክንያት እነዚህን የስራ አይነቶች ለማከናወን ገበሬዎች ራሳቸውን ለማነቃቃትና ስራውን ለማፋጠን በርካታ ቃል ግጥሞችን የሚያቀነቅኑባቸው መሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ ቀበሌዎች የሚኖሩ ከ12-70 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሴትና ወንድ፣ እስልምናና ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ 48 መረጃ አቀባዮች ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች በዋናነት ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ ቃል ግጥሞችን ያቀነቀኑ፣ ትንታኔ የሰጡ፣ ስለገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የቃል ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳና ክዋኔ መረጃ የሰጡ ናቸው፡፡ የተመረጡትም ቃል ግጥሞችን በመደርደር ባላቸው እውቀት፣ ብቃትና ችሎታ እንዲሁም በሚሰጡት የመረጃ ጥልቀት በአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጣቸውና የሚታመንባቸው ናቸው፡፡

መረጃዎች የተሰበሰቡት በክዋኔ ውስጥና ከክዋኔ ውጭ በቃለ መጠይቅና በምልከታ ነው፡፡ የተሰበሰቡት ግጥሞች ከ580 በላይ ሲሆኑ የአጨዳ፣ የአረም፣ ውቂያ፣ የእርሻና የጉልጓሎ ግጥሞች ናቸው፡፡ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ገበሬዎች በተደጋጋሚ የሚያነሷቸውን 54 ቃል ግጥሞች በመምረጥ አውድን መሠረት ያደረገ ገለፃና ትንታኔ አድርጌያለሁ፡፡ ቀሪዎቹ ቃል ግጥሞች በተከወኑበት የስራ አጋጣሚ የገበሬዎችን ትንታኔ መሰረት በማድረግ በርዕሰ ጉዳይ ተከፋፍለው በአባሪ ቀርበዋል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- በወረዳው የገበሬዎች ስነ- ቃል፣ ባህል፣ አመለካከት፣ የስራ ክንውን ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ለሚያካሂዱ፣ የባህል፣ የስነ-ሰብ፣ የስነ ፅሁፍ፣ የፎክሎርና ታሪክ አጥኚዎች መረጃ ይሆናል፡፡
- የወረዳውን ገበሬዎች የአኗኗር ዘይቤ፣ እምነት፣ የህይወት ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ የዕለት ተዕለት ውሎና ማህበራዊ ግንኙነት ማወቅ ለሚሹ ፍንጭ ይሰጣል፡፡
- በወረዳው ያሉ በግብርና ሙያ ላይ ያተኮሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የገበሬዎችን አመለካከት፣ ፍላጎትና አኗኗር ማዕከል ያደረገ እቅድ፣ ድጋፍና የስራ ማሻሻያ ስልቶችን ለመንደፍ በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

## 1.8. የጥናቱ ዘዴ

ለጥናቱ መቀንበቢያ የተጠቀምኩት ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብም በተግባር ላይ ውሏል፡፡ ክዋኔ በአንድ በተወሰነ አውድ (ቡድን ውስጥ) ያለውን ጥበባዊ ገለፃ የሚያጠና ነው /Sims and Stephen 2005:140/፡፡ /Bauman 1983/ አንድ አጥኚ በመስክ ሲያጠና በማህበረ ባህላዊ አውድ ላይ ማተኮር አለበት፡፡ አውድ ሲፈጠር አንዳች አገልግሎት ኖሮት ነው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ውጤታማ የሚሆነው በአውድ ከተጠና ነው ብለዋል፡፡

ስለዚህ የክዋኔውን ጠቀሜታ ለመግለፅ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብም ይተኮርበታል፡፡ በመሆኑም ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በአውድ ላይ የገበሬዎች የስራ ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ወቅት ያላቸውን ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ፋይዳ፣ ከዋኞችም ሆነ ታዳሚዎች፣ መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደሚጠቀሙበት ጠቀሜታና አገልግሎትን ለማጥናት ያስችላል፡፡ ቃል ግጥሞቹን ከአውዳቸው ለመሰብሰብ፣ የከዋኝና ተሳታፊዎችን አይነት ለመለየት፣ ክዋኔን ተጠቅሜያለሁ፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰበውን መረጃ በመግለፅ ለመተንተን ገላጭ የምርምር ዘዴና የይዘት ትንተና በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

## 1.9. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሰሜን ጎንደር ዞን ዳባት ወረዳ ከሚገኙት 30 ቀበሌዎች መካከል በሰባት ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እነርሱም ቃርሃ፣ ዳራ፣ ጭላ፣ ጫርቢጣ፣ በንከር፣ አብጠራና ታላቅ መስክ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት አንደኛ

ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት የተነሳ ሁሉንም ቀበሌዎች ለማካተት አስቸጋሪ ስለሆነ ሲሆን፣ ሁለተኛው በእነዚህ ቀበሌዎች በርካታ የቃል ግጥም ደርዳሪ ገበሬዎች የሚገኙባቸው በመሆኑና መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ወቅት ክዋኔያቸው መገኘት መቻሉ ነው፡፡ ጥናቱ ከቃል ግጥም አይነቶች የገበሬዎችን ቃል ግጥም ክዋኔ ሲመለከት የዕለት ተዕለት ውሏቸውንና ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ይጨምራል፡፡

ጥናቱ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን ከሚያቀነቅኑባቸው የስራ አጋጣሚዎች በአጨዳ፣ ውቂያ፣ አረም፣ ጉልጓሎና እርሻ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በጥናቱ ሁለቱም የፆታ ክፍሎች ሴት ወንድ፣ ህፃን፣ ወጣት፣ አዛውንት የተሳተፉ ሲሆን እምነታቸው የእስልምናና ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች ናቸው፡፡

ጥናቱ ከተነሳበት ዓላማ አንፃር ብዙ ጊዜና ገንዘብ ስለሚጠይቅ ሌሎች የስራ አጋጣሚዎችን፣ ሀገረሰባዊ እምነቱንና የቃል ግጥሞቹን ቅርፃዊ መዋቅር አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም ክዋኔና ማህበራዊ ህይወታቸው ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## 1.10. በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች

ለጥናት ግብአት የሚሆኑትን መረጃዎች በመስክ ላይ በምሰበስብበት ወቅት በርካታ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ነገር ግን ወደፊት ለሚያጠና ሰው መረጃ ይሆናሉ ያልኳቸውን ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን እገልፃለሁ፡፡

### 1.10.1. ያጋጠሙ ችግሮች

በመስክ ስራ ክንውን ወቅት ካጋጠሙኝ ችግሮች አንዱና ዋነኛው የካሜራ ባለሙያ ማግኘት አለመቻል ነው፡፡ የዳባት ወረዳ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ የካሜራ ባለሙያ እንዲሰጠኝ ቢያዙም ባለሞያው በመስክ ስራ ምክንያት ሊገኝ አለመቻሉና ቀረፃ በሚካሄድበት ጊዜም የመቅረፀ ድምፅ ብልሽት መከሰቱ አስቸጋሪ ነበር፡፡

በመስክ ቆይታዬ እንደ ተመለከትኩት የአካባቢው ገበሬዎች በአጨዳ ወቅት ተጠቃለው ወደ ስራ የሚገቡት ከሶስት ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ ቃል ግጥሞችንም የሚከውኑት ከስድስት ሰዓት በኋላ ምሳና ጠላ መጥቶ በልተው ጠጥተው ሞቅ ሲላቸው ነው፡፡ ከዚያ በፊት የመግጠም ተነሳሽነት አለመኖራቸው፣ ካልጠጡ፣ ጠጥተውም ሞቅ ካላላቸው የማይገጥሙ መሆኑ ችግር ሆኖብኝ ነበር፡፡ እንዲሁም ጫርቢጣ፣ ታላቅ መስክና አብጠራ ቀበሌዎች ገበሬዎች በሚከውኑበት ጊዜ መቅረፅ ድምፅና ካሜራ

ተጠቅሜ ቃል ግጥሞችን በምሰበስብበት ጊዜ ድምፃችን አያምርም፣ የተበላሸ ድምፅ ይዘን፣ ልብሳችን ሳንቀይር አይቻልም በማለት ከፊሉ ፈቃደኛ ሲሆኑ ከፊሉ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የድምፅም ሆነ የምስል ቀረፃ ለማካሄድ ችግር አጋጥሞኛል፡፡

በቃርሃ ቀበሌ ሽሃ ጎጥ ከሙስሊሞች መንደር መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ በምሰበስብበት ወቅት ጥያቄውን ስሰነዝር ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻልና መቅረፀ ድምፅና ማስታወሻ ደብተር ለመጠቀም ስሞክር የተናገሩትን ሀሳብ በመቀየር ትክክለኛውን መረጃ የመደበቅ ችግር አጋጥሞኛል፡፡ እንዲሁም ጉራሬ ማሪያም በተባለ ጎጥ በአውድማ አውድ ላይ በጥዋት ተገኝቼ ቃል ግጥሞችን መቅረፀ ድምፅና ካሜራ በመጠቀም በመሰብሰብ ላይ እያለሁ የአውድማው ባለቤት እናት ምሳና ጠላ ይዘው መጥተው ይህችማ ብዙ ገንዘብ ይኖራታል በማለት አንድ አንድ ሺህ ብር እየተከፈለው ነው የሚገጥም ክፈይው፣ ትክፈልህ አትዝፈን በማለት ገንዘብ በመጠየቅ ግፊት ማድረጋቸውና እሳቸውም እንዲከፈላቸው በመፈለግ ደክሞኛል ሲሉ ስራውን ማቋረጥ መቻላቸው ችግር ፈጥሮብኛል፡፡ በተጨማሪም በዳራ ቀበሌ በለስ ባድማ የተባለ ጎጥ በጤፍ አጨዳ ላይ ተሰባስበው እየገጠሙ ሲያጨዱ የነበሩት እኔ ስደርስ ፀጥ በማለት ለመግጠም ፈቃደኛ አለመሆን ችግር አጋጥሞኛል ፡፡

### 1.10.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመረጃ ስብሰባ ወቅት በመቅረፀ ድምፅ ብልሽት ምክንያት የተፈጠረውን የመረጃ ክፍተት ከሁለት የመስክ ረዳቶቼ ጋር በመሆን ቪዲዮ ካሜራና ማስታወሻ ደብተር በመጠቀም ማሟላት ችያለሁ፡፡

ገበሬዎች አጨዳ እስከ ሚጀምሩ አንደኛ ገበሬዎች የአውድማ ቃል ግጥሞችን የሚከውኑት በጥዋት ስራውን ለመጀመር በሮችን እርስ በርስ በገመድ አጠላልፈው ወደ አውድማው ማስገባት ሲጀምሩ በራሳቸው ተነሳሽነት ስለሆነ እስከ ቀኑ ስድስት ሰዓት የአውድማ ቃል ግጥሞችን ስሰበስብ እቆያለሁ፡፡ ከሰባት ሰዓት ጀምሮ ወደ አጨዳው በመሄድ ጠላ በመቅዳትና በማስተባበር፣ ከበሉና ከጠጡ በኋላ ያለማንም ቀስቃሽ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ሁለተኛ የአካባቢው ገበሬዎች የተማረ ሰው ስለሚያከብሩ የተማሩና ተሰሚነት ያላቸውን የአካባቢው የተማሩ ወጣቶች በመውሰድ ተነሳሽነት እንዲፈጥሩ በማድረግ መረጃውን በቀላሉ ማግኘት ችያለሁ፡፡

በምስልና በመቅረፀ ድምፅ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑትን ገበሬዎች የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ቀድሞ

የተቀረፀውን በማሰማት፣ የሌሎችን ምስል በማሳየት፣ የራሳቸውን ድምፅ በማሰማትና ምስላቸውን በማሳየትና ምንም ችግር እንደሌለው በማስረዳትና በማሳመን ነው፡፡ እንዲሁም ፍፁም በምስልና በመቅረፀ ድምፅ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑትን ማስታወሻ ደብተር በመጠቀም ሰብስቤያለሁ፡፡ በተጨማሪም መረጃው በማስታወሻ ደብተርም ሆነ በመቅረፀ ድምፅ መያዙ በእሱ ላይ የሚያመጣው ምንም ችግር እንደሌለው በማስረዳት፣ ዓላማውን ደጋግሜ በመግለፅና በማሳመን የተደበቀውን መረጃ ማግኘት ችያለሁ፡፡ መረጃውንም ከሌላ መረጃ ሰጭ በመጠየቅ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮችን የቀረፃውን አላማና ጥናቱም ለእነሱ በምን መልኩ ሊጠቅም እንደሚችል በማስረዳትና በማሳመን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ለማያውቁት ሰው መረጃ በቀላሉ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑትን ገበሬዎች በአካባቢው ታዋቂ የሆነውን የተማረ ገበሬ ይዤ በመሄድ እና በአጨዳው እየተሳተፈ፣ እራሱ በመፎከርና የነሱንም ስሜት ለፉከራ በማነሳሳት፣ እኔም የታጨደውን በመሰብሰብና ጠላ በመቅዳት መረጃውን ማግኘት ተችሏል፡፡

## 1.11. የመስክ ተሞክሮ

ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታህሳስ 24 ቀን 2006 ዓ.ም ከአዲስ አበባ የዞኑ ዋና ከተማ ጐንደር ከተማ ገብቼ ሆቴል ይዤ አደርኩ፡፡ ታህሳስ 25/2006 ዓ.ም ቀን በጥዋት ተነስቼ ዳባት ከተማ ደረስኩና ወደ ወረዳው ዋና አስተዳደር በመሄድ የትብብር ደብዳቤ አስፃፉኩኝ፡፡ ከዚያም ከባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፣ ትምህርት ጽ/ቤት ባለሞያዎች ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ደብዳቤውን በማሳየት አንዳንድ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡

ታህሳስ 30/2006 ዓ.ም ከወረዳው የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ዳራ ቀበሌ በለስ ባድማ የተባለ ጎጥ ከሃያ በላይ ገበሬዎች የተሳተፉበት የአቶ አስማረ መልሴ የጤፍ አጨዳ ሆበራ ላይ በመገኘት ቃል ግጥሞችን ለመሰብሰብ ከመስክ ረዳቴ አድን ዱቤ ጋር ስንሄድ እየፎከሩ ሲያጭዱ የነበሩት እኛ ስንደርስ መፎከራቸውን አቋርጠው ፀጥ አሉ፡፡ ከዚያም የመስክ ረዳቴ በአጨዳው በመሳተፍና በመፎከር የእነሱን የመፎከር ተነሳሽነት በመፍጠር መረጃዎችን መቅረፀ ድምፅ ወምስል በመጠቀም መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በመጨረሻም የተቀረፀውን በማሳየትና በማሰማት አመስግነን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

ታህሳስ 30 ቀን ነው ጋሎ የተባለ ቦታ የጤፍ አጨዳ ሆበራ እንዳለ የተሳተፉትም በመግጠም ችሎታቼው የታወቁ በርካታ ገበሬዎች መሆናቼውን አቶ አድን ዱቤ ጠቁሞን ከመስክ ረዳቴ ደጀን ንጉሴ ጋር ሄድን፡፡ ስንደርስ ከደብሩ ሁለት ሰው ሞቶ ስለነበር ከተለመነው 20 ሰው አምስት ሰው ብቻ በመምጣቱ ባለቤቷ ወ/ሮ ሙሉ አለበል ሁለት ቢጫ ጀሪካ ጠላና አስር ሙሉ የምጣድ ዳቦ አምጥታ ያቀደችው ስራ ባለመሳካቱ በጣም ተናደደች፤ "ሞቻለሁ ቅበሩኝ" አለች፡፡ ያሉት ገበሬዎችም በሁኔታው ተናደው ጥሩ ስሜት ስለሌላቸው መዝፈን አልቻሉም ነበርና አይዟችሁ ብለን በማስተዛዘን ተመለስን፡፡

ጥር 06/2006ዓ.ም ከመስክ ረዳቴ አደራጀው ዱቤ ጋር ወደ መሰክ ስንወጣ ዳራ የቄስ ቢምረው ጥላዬ የተባሉ ገበሬ የጤፍ አውድማ ሆበራ እንዳለ ተነገሮን ሄድን፡፡ ቄስ ቢምረው በቃል ግጥም ችሎታቸውና በድምፃቸው የተመሰከረላቸው እንደሆኑም ነግረውናል፡፡ ከዚያም ቄስ ቢምረውና ሌሎች ተሳታፊዎች ሆበሬ እያሉ መረጃዎችን በድምፅና በምስል ሰበሰብኩ፡፡ የመስክ ረዳቴም እነሱን ለማበረታታት ሆበሬ በማለት መረጃዎችን በመሰብሰብ ላይ እያለን እናታቸው ምሳና ጠላ ይዘው ዘው አሉ፡፡ እናም ቀረፃውን ሲያዩ ሽህ ብር እየተከፈለው ነው የሚገጥም ክፈይው፤ አሁን ብዙ ብር ይኖራታል፣ ትክፈልህ፣ ክፈይኝ በላት ካልሆነ አትቀረፅ አሉዋቸው፡፡ እርሳቸውም ይበቃኛል ደክሞኛል ሲሉ ገለፁልኝ፡፡ ከዚያም መረጃውን የምሰበስብበትን ዓላማና ጥቅም በመግለፅ የመረጃውን አሰሳሰብ ሂደት ከቀጠልን በኋላ መጨረሻ ላይ ጠላና ቆሎ ሰጡን በልተን ጠጥተን በማመስገን ወደ ሌላ የጤፍ አጨዳ ሄድን፡፡

ጥር 06/2006 ዳራ ቀበሌ ጋሎ የተባለ ጎጥ በቃል ግጥማቸው ታዋቂ የሆኑ 22 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ እልልታና ሆታው ከርቀት ይሰማል፡፡ ባለቤቷ ወ/ሮ ሙሉ አለበል ባለቤቷ ታስሮባት ያለች የሴት ወንድ ናት፡፡ ወገቧን በነጠላዋ ታጥቃ ጤፉን በአህያ በመጫን፣ በመሰብሰብና በማጨድ በፉከራና ቀረርቶው፣ በእልልታ ትሳተፉ ነበር፡፡ ከመስክ ረዳቴ ጋር ጤፉን ጨርሰው አብሸ ሲያጭዱም በአጨዳውና በእልልታው በመሳተፍ እስከ ምሽት አንድ ሰዓት መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ ሙሉ አለበል ቃል ግጥሞችን በመደርደር አዚማለች፡፡ የምታዜማቸው ግጥሞች በሙሉ ብሶትን የሚገልፁ ነበሩ፡፡ ተሳታፊዎችም ሴቶች በአብዛኛው በሆበራ ላይ ሲፎክሩ ስላልተለመደ በመገረም ያበረታቷት ነበር፡፡ ግዛት አሰፋ የተሰኘ ገበሬም በስራውም ሆነ በቀረርቶ ችሎታዋ በመደነቅ ከዚያው ላይ ያዜምላት ነበር፡፡

ጥር 12 ቀን ነው ከሙስሊሞች መንደር ከአቶ ኑርልኝ ኢሳና አቶ ተበጀ በየነ ጋር ስለ ገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ መረጃ ሰበሰብኩ፡፡ ከዚያም አቶ ተበጀ በየነ ድረስ ግርማው የሚባል ገበሬ ከዚያው ቀበሌ መረጃ ሊሰጠኝ እንደሚችል ጠቆሙኝና ሄድን፡፡ እርሱም አስፈላጊውን መረጃ ሰጥቶኝ በጭዋታ ጭዋታ የሴት ገበሬዎችም አሉኮ ያስፈልጉሻል ሲል ጠየቀኝ፡፡ እኔም ያስፈልጉኛል ስለው ብትወጣ ኪዴ የተባለች የሴት አራሽ ገበሬ ቤት ወሰደን፡፡ ብትወጣ ከድረስ ጋር የስጋ ዝምድና ያላቸው በመሆኑ እሱን በማክበር ፎቶና ቀረፃ ከመከልከሏ በስተቀር የስራዋን ሁኔታ እያሳቀች ነገረችን፡፡ ብትወጣ የአምስት ልጆች እናት ናት፡፡ ባለቤቷ ገበሬና ነጋዴ ነው፡፡ እሷም በትርፍ ጊዜዋ ትነግዳለች፡፡ ከባለቤቷ ጋር እኩል ወጥተው ይገባሉ፡፡ አብዛኛው ሴቶች የማይደፍሩትን እርሻ በማረስ ትታወቃለች፡፡ የቤትም ሆነ የውጭ ስራ ስትሰራ እያዜመች ነው፡፡

ጥር 13/2006/ ከሙስሊሞች መንደር ተመልሸ ስሄድ የስንዴ ውቂያ አገኘሁ፡፡ ባለቤቱ ሰይድ መሳነር ይባላል፡፡ እየገጠመ የነበረው ስንደርስ ፀጥ አለ፡፡ ድምፄ የተበላሸ ነው በማለት ቢለመንም እሽ አላለም፡፡ ድረስ ግርማውና አደራጀው ዱቤ አብረውኝ ነበሩ፡፡ እኛን ሲያይ ስሜቱ ይነሳሳል በሚል በየተራ ሆበሬ ማለት ጀመሩ፡፡ ከዚያም ግጠም ብለው ቢሰጡት ድምፄ አያምርም በሚል ድምፁን ሳያሰማ ያዜማል፡፡ ድምፁ ለቀረፃ ሊሰማ ባለመቻሉ በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን እንዲሰጠን ስንጠይቀው ፈቃደኛ ሆኖ ጀመርን፡፡ ስለ ገበሬዎች ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ መረጃ ለመሰብሰብ ሀሳቤን ስሰነዝር መረጃውን መስጠት ጀምሮልኝ እያለ ማስታወሻ ደብተርና መቅረፀ ድምፅ መጠቀም ስጀምር እየተናገረ የነበረው በፍርሀት መናገሩን አቆመና ሌላ ሀሳብ መቀየር ጀመረ፡፡ ከዚያም የጥናቱን ዓላማና ጥቅም በማስረዳት፣ በእሱ ላይ የሚያመጣው ችግር እንደሌለ በማሳመን ወደ ነበረበት ሀሳብ በመመለስ መረጃውን እንዲሰጠኝ አድርጌያለሁ፡፡

የመስክ መረጃው አሰባሰብ ሂደት እስከ ጥር 16 የቀጠለ ነበር፡፡ ከዚያም ጥር 17 ቀን ከሰዓት በኋላ ጉዞዬን ወደ አዲስ አበባ አደረኩ፡፡ ከመስክ መልስም በመቅረፀ ድምፅ ወምስል የተሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ ማስታወሻ ደብተር በመገልበጥ በተሰበሰቡበት አውድ መሠረት በርዕሰ ጉዳይ ምደባ አደረኩ፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ አንደኛ ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ስራዎች ቅኝት ሲሆን ሁለተኛ ከገበሬዎች ቃል ግጥም ጋር ዝምድና ያላቸው የስራ ቃል ግጥም ምንነትና ፋይዳ፣ ክዋኔ፣ አውድ፣ ደረሳና ተስተላልፎ የንድፈ ሀሳብ ስራዎች ቅኝት ይቀርባሉ፡፡

## 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አንድ መጣጥፍና አንድ የኤምኤ ጥናት ላይ ሰፋ ያለ ቅኝት አድርጌያለሁ፡፡ ሌሎች ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች በኤምኤም ሆነ በቢኤ ዲግሪ ደረጃ ያሉ ቢሆንም በሌሎች ስራዎች አንዱ በአንዱ ቅኝት ስለተደረገባቸው መድገሙ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ቅኝት እንደተደረገባቸው በመግለፅ መካተት ነበረባቸው ያልኳቸውን ሀሳቦች በመጠቆም ቅኝቱን አድርጌያለሁ፡፡

ብርሃኑ አሳዬ “በባንጃና አንካሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ግጥሞች” (1999 ዓ.ም) በሚል ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም ኤ ዲግሪ ጥናት አቅርቧል፡፡ በጥናቱም ሴቶች በአጨዳና በጉልጓሎ ያላቸውን ተሳትፎ አመልክቷል፡፡ በጥናቱ ቅኝት ካደረገባቸው ጥናቶች በዚህ ጥናት የተካተቱት የያዜ ወርቁ “የደንቢያ አውራጃ የስራ ላይ ዜማ ይዘት ትንተና” (1984 ዓ.ም)፣ ህዝበ አዳም ገላ “የደጀን ሴቶች የስራ ላይ ዘፈን ይዘት ትንተና” (1986 ዓ.ም)፣ አባቡ ሽመልስ “በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን በሚዳን ኦሮሞ ወረዳ የሚዜሙ የስራ ላይ ግጥሞች” (1997 ዓ.ም)፣ አብርሃም አለሙ “የግራዋ ወረዳ አካባቢ ገበሬዎች የደራሼ የስራ ዘፈን ግጥሞች ይዘት ትንተና” (1987 ዓ.ም) ጥናቶች ይገኙበታል፡፡ በእነዚህ ጥናቶች ላይ ቅኝት አድርጎባቸዋል፡፡ ስራዎቹም በቢኤ ዲግሪ ደረጃ የተደረጉ ጥናቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ስራዎችም የአጠናን ዘዴያቸውን፣ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶቻቸውን፣ ጭብጦችን ለመመደብ የተጠቀሙበትን አቅጣጫ፣ እንዳላሳዩ ገልጿል፡፡

የስራ ቃል ግጥሞችን የሰበሰቡት ከአውዳቸው ውጭ ያውቃሉ ከሚባሉ ሰዎች፣ ከራሳቸው እውቀት፣ በተማሪዎችና መምህራን እገዛ፣ ከጓደኞቻቸውና ወዳጆቻቸው ጋር በፖስታ በመላላክ እንደሆነ ጠቅሷል፡፡ ብርሃኑ ጥናቱ ከእነዚህ ጥናቶች ጋር ያለውን ዝምድናና ልዩነትም አሳይቷል፡፡ በጥናቱ ላይ የተወሰነ የሀሳብ መምታታት

ይታይበታል፡፡ ይህም የጥናቱ ወሰን ላይ የቃል ግጥሞችን ስልታዊ፣ ቅርጻዊና መዋቅራዊ ገጽታ አልመለከትም በማለት አስቀምጧል፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ጥናቶች ልዩ ከሚያደርገው ነገር አንዱ የቃል ግጥሞቹን ስልታዊ፣ መዋቅራዊና ቅርጻዊ ገጽታዎች ግምት ውስጥ አስገብቶ መተንተኑ እንደሆነ ገልጿል፡፡

የብርሃኑ አሳዬ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በአጠናን መንገዱ፣ ሴቶች በአጨዳና ጉልጓሎ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በማሳየቱ ይመሳሰላል፡፡ የእኔ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ አጋጣሚዎቹ ፣ የገበሬዎችን የእለት ተዕለት ውሎና ማህበራዊ ህይወት፣ የቃል ግጥም አደራረስ፣ ተስተላልፎና ማህበራዊ ፋይዳ በማካተቱና በትኩረት አቅጣጫው ይለያል፡፡

Getie Gelaye“Peasant Poetics and State Discourse in Ethiopia: Amharic Oral Poetry as a Response to the 1996-1997 Land Distribution Policy” (1999) በሚል ርዕስ መጣጥፍ አቅርቧል፡፡ ጥናቱም በኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ ወዲህ የምስራቅ ጎጃም ገበሬዎች የገጠሟቸውን፣ ያዜሟቸውን፣ ያንጎራጎሯቸውን የሀዘን፣ የብሶት፣ ፍትህ ማጣት፣ መበደል፣ ቁጭት፣ ድህነትና ፖለቲካዊ ግጥሞች የተመለከቱ ናቸው፡፡ መጣጥፉ የመሬት ሽግሽጉን የደገፉትም ሆነ የተቃወሙት አካላት ድጋፍም ሆነ ተቃውሟቸውን እንዴት በቃል ግጥማቸው አማካይነት እንደሚገልፁ ያሳያል፡፡

ጌቴ መረጃውን ከምስራቅ ጎጃም ወረዳዎች ዲጀ ማሪያምና ገደብ-ጊዮርጊስ ላይ ከ32 መረጃ አቀባዮች 2000 ቃል ግጥሞችን እንደሰበሰበና ወደ እንግሊዝኛ እንደ ተረጎማቸው ገልጿል፡፡ መረጃውንም በሁለት ገበሬ ማህበረሰቦች ውስጥ በተከሰቱ 6 ልዩ ልዩ የክዋኔ አጋጣሚዎች ላይ ተገኝቶ ቃል ግጥሞቹን በመቅዳት ሰብስቧል፡፡ እነዚህ ማህበራዊ አጋጣሚዎች የግብርና ስራዎች፣ ህዝባዊ በዓላት፣ የልቅሶ ስርዓት፣ ሰርግ፣ የከብት እገዳ ወቅትና ዓመታዊ የሀይማኖት በዓላት መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡

አጥኚው መረጃውን ያሰባሰበው ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ምልከታ በማድረግና ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡ ቃል መጠይቁንም ያደረገው በተለያዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ሁኔታዎች ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ቄሶች፣ የዕድሜ ባለጸጎች እና ህጻናት እንደሆነ ገልጿል፡፡ የሰበሰባቸውን ቃል ግጥሞች ከሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር ተንትኖ አቅርቧቸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ለገበሬው የሚሰጡ ስያሜዎች (ቢሮክራት፣ ፊውዳልና ጨቋኝ) የሚመለከቱ፣

የመሬት ሽግሽግ ፖሊሲውን የሚደግፉ ግጥሞች፣ የመሬት ሽግሽግ ፖሊሲውን የሚቃወሙ ግጥሞች፣ የአካባቢውን ባለስልጣናት ሙስና፣ ኢ-ፍትሃዊነትን የሚመለከቱ፣ ዘመኑን የሚቃወሙ፣ በገበሬውና በሹማምንቱ መካከል ያለውን ግጭት የሚመለከቱ ናቸው፡፡

የጌቴ ገላዬ መጣጥፍ በዘመን የተገደበና በፖለቲካዊ የገበሬዎች ቃል ግጥም ማተኮሩ፣ ግጥሞቹን በሰበሰባቸው ማህበራዊ አጋጣሚዎች፣ በሰበሰባቸው ቃል ግጥሞች ብዛትና አቀራረብ ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡ ርዕሰ ጉዳዩ የገበሬዎች ህይወት ላይ በመሆኑ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅ መጠቀሙ፣ የይዘት ትንተና በማድረጉ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የእኔ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ አጋጣሚ የግብርና ስራ ክዋኔ ላይ መሆኑ የገበሬዎችን የዕለት ተዕለት ውሎና ማህበራዊ ህይወት፣ የግጥም አደራረስ፣ ተስተላልፎ፣ ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ በመግለፁ ይለያል፡፡

ማሞ ተፈራ "በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳና ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና በዳንግላ ወረዳና አካባቢው" (2002 ዓ.ም) በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ አቅርቧል፡፡ የማሞ ጥናት ዋና ዓላማ የሀገረሰባዊ እምነቶችን ፋይዳ መግለፅና የቃል ግጥሞችን አበይት ጭብጦች ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ በአጨዳ፣ ውቂያና፣ ክምር ቃል ግጥሞች ላይ የተወሰነ ነው፡፡ አጥኚው መረጃውን በበራይ፣ በወበራ፣ በአጨዳ፣ በአውድማ ልቅለቃ፣ ክምር፣ ማሽላ መላጥና ማሸላ መደብደብ አውዶች ላይ መሰብሰቡን ገልጿል፡፡

ማሞ ተፈራ የመስክ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ በፎቶ ካሜራ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በመቅረፀ ድምፅና ማስታወሻ ደብተር በመጠቀም ሰብስቧል፡፡ በስራ ላይ የሚፈፀሙት ሀገረሰባዊ እምነቶች እየጠፉ እንዳሉ በመመልከቱ በአርቲፊሻል መቸት በቃለ መጠይቅ መረጃውን እንዳሟላ ጠቅሷል፡፡ ጥናቱ በ15 ቀበሌዎች የተካሄደ ሲሆን 152 ቃል ግጥሞችንና 22 ሀገረሰባዊ እምነቶችን በክዋኔና አልፎ አልፎ ከክዋኔ ውጭ መሰብሰቡን ገልጿል፡፡ በ15 ሀገረሰባዊ እምነቶችና 46 ቃል ግጥሞች ላይ ትንታኔ አድርጓል፡፡ የሀገረሰባዊ እምነቶችን ፋይዳ ከእንስሳት ጋር የተያያዙ፣ በሬ መመረቅ፣ በሬ መጥራት፣ ከሚበሉና ከሚጠጡ ነገሮች ጋር፣ ከተተከሉ ነገሮች ጋር፣ ከቀናት ጋር፣ ከጥላ ማደር መከልከል ጋር፣ ከአቅጣጫ ጋር፣ ከቁጥሮችና ሴቶች ጋር የተያያዙ በማለት ተንትኗል፡፡

ማሞ የቃል ግጥሞችን ይዘትም ስለ በሬ የተዜሙ፣ የበሬ ጥቅም፣ በበሬ ላይ የሚደርሱ በደሎች፣ ስለ ጠንካራና ዳተኛ በሬ፣ ገበሬዎች ስለራሳቸው፣ ስለ ምርጥ ዘር አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታ፣ ተባብሮ መስራት፣ የብድር አገልግሎት፣ ቢሮክራሲያዊ አሰራር፣ የአባላዘር በሽታ፣ ጉቦ (ሙስና)፣ ክፉ ቀን በሚሉ መደቦች ከፋፍሎ ተንትኗል፡፡ ማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነቶችን የሚፈፅመው በመናፍስት ሀይል አማካይነት በምርትና በስራ ተሳታፊዎች እንስሳትና ሰዎች ላይ ችግር ያደርሳል በሚል ስጋት እንደሆነ ገልጿል፡፡ ስጋቶቹን ለመከላከልም የተለያዩ እምነታዊ ድርጊቶች በመፈፀም መናፍስቱን መለማመን፣ መናፍስቱን ማታለል፣ በመናፍስቱ ሀይል ላይ የበለጠ ሀይል ያሏቸውን ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የሚፈጸሙ መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡ የሴቶችን ተሳትፎ በተመለከተም በአጨዳም ሆነ ውቂያ ስራዎች በሙሉም ሆነ በከፊል እንደማይሳተፉ ገልጿል፡፡

የማሞ ጥናት ትኩረቱ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳ ላይ መሆኑ፣ ሴቶች በአጨዳም ሆነ ውቂያ ተሳትፎ እንደሌላቸው መግለፁ፣ በአጨዳ፣ ውቂያና ክማሮ የስራ አጋጣሚዎች ላይ መወሰኑ፣ ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የገበሬዎችን ቃል ግጥም ሰብስቦ የይዘት ትንተና በማድረጉ፣ በአጠናን መንገዱ፣ ከስራ አጋጣሚዎች የአጨዳና ውቂያ አውድ መጠቀሙ ነው፡፡ የእኔ ጥናት የአረም፣ አጨዳ፣ ውቂያ፣ እርሻና ጉልጓሎ የሥራ አጋጣሚዎችን በማካተቱ፣ የገበሬዎችን የዕለት ተዕለት ውሎና ማህበራዊ ህይወት፣ የቃል ግጥሞችን አደራረስና ተስተላልፎ፣ በተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መጠን፣ ሴቶች በአጨዳ፣ ውቂያ፣ አረምና ጉልጓሎ እንደሚሳተፉ ማሳየቱ ለየት ያደርገዋል፡፡ ማሞ በጥናቱ በ15 ሀገረሰባዊ እምነቶች ላይ ትንተና እንዳካሄደ ገልጿል፡፡ ነገር ግን ትንተናውን ያካሄደው በ10 ሀገረሰባዊ እምነቶች ላይ እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል፡፡

ጋሻው አሻግሬ “በእብናት ወረዳ ባህላዊ ወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና” (2005 ዓ.ም) በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤምኤ ዲግሪ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ በጥናቱም ቅኝት ካደረገባቸው መካከል “የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና” (2004 ዓ.ም) በሚል የቀረበው የቀለመወርቅ ተክሌ የኤምኤ ዲግሪ ጥናት ይገኝበታል፡፡ የጋሻው አሻግሬና ቀለመወርቅ ተክሌ ጥናት የስራ ዘፈን ላይ በማተኮርና በአጠናን መንገዱ ከእኔ ጥናት ይመሳሰላል፡፡

የሴቶች የስራ ዘፈን ላይ በማተኮራቸው ከእኔ ጥናት ይለያሉ፡፡ በመቀጠልም የምሁራን ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ይቀርባል፡፡

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ስር ጥናቱ የሚቃኝባቸው ንድፈ ሀሳቦች የቀረቡ ሲሆን በውስጡም  የስራ ቃል ግጥም ምንነት፣ ክዋኔ፣ አውድ፣ ድረሳ፣ ተስተላልፎና የስራ ቃል ግጥም ፋይዳ ተካተዋል፡፡

### 2.2.1. የስራ ቃል ግጥሞች

"ቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎውና አቀራረቡ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ በዘፈን፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው፡፡" /ፈቃደ 1991፣ 86 /፡፡ ይህ ህዝባዊ ግጥም በአንድ ሰው ተደርሶ በመዜም፣ በመከወንና በመተላለፍ የህዝብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንም /Okpewhu 1992፣ 69/ "…a piece of oral literature may be initially composed by one person but presented by a different person…" በማለት ቃላዊ ስነ ፅሁፍ መጀመሪያ በአንድ ሰው ተደርሶ በተለያዬ ሰው ሊከወን እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል /ዘሪሁን 1992፣ 46/ በዜማና በግጥም ከሚቀርቡት ባህላዊ የዘፈን አይነቶች አንዱ የስራ ዘፈን ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ከስራ ዘፈን ውስጥም የገበሬዎችን የስራ ዘፈን እናገኛለን፡፡ የስራ ዘፈን ስራን ለማቀላጠፍ፣ ራስንና ታዳሚን ለማዝናናት፣ ባህልና ታሪክን፣ ድጋፍና ተቃውሞን፣ ስሜትና ፍላጐትን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመግለፅ ያስችላል፡፡ እንዲሁም ለማስተማር፣ ለመተቸት፣ ስርዓትን ለመገንባት፣ መልዕክትን ለማስተላለፍ በጥቅሉ ገበሬዎች ስለ ህይወት ያላቸውን ፍልስፍና የሚገልፁበት ህይወታቸው የተቀረፀበት የማንነታቸው መገለጫ ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ነው፡፡

/Finnegan 1977፣ 218/ የስራ ቃል ግጥሞች ተሳታፊዎችን በማስደሰት፣ መነቃቃትን በመፍጠር ጥበባዊ በሆነ መንገድ ስራን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ሀገረሰባዊ የዘፈን ግጥሞች ያለዳንስ፣ እስክስታ፣ ጭፈራ፣ ወገዳ ወዘተ ብቻቸውን የሚከወኑበትን ጊዜ ማሰብ ያስቸግራል /ፈቃደ 1991፣12 /፡፡ ፈቃደ አንዳሉት የስራ ዘፈኖች በሚከወኑበት ጊዜ በእንቅስቃሴ ታጅበው ነው፡፡ በእንቅስቃሴ ታጅበው

ከሚከወኑትም በአብዛኛው በቡድን የሚከወኑት ስራዎች ናቸው፡፡ ክዋኔው በጭፈራ፣ በወገዳ (ረገዳ) ፣ በእስክስታ፣ ቁጭ ብድግ፣ ከፍ ዝቅ በማለት፣ በማጨብጨብ፣ ወደ ላይ በመዝለል፣ በመወራጨት በድምፅና በዜማ የታጀበ ነው፡፡ የስራ ዘፈኖችን የመዝፈን ችሎታ በመደበኛ መንገድ ጊዜና ቦታ ተዘጋጅቶለት በመማር የሚገኝ ሳይሆን መደበኛ ባልሆነ መንገድ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚማሩት ነው ፡፡ ይህንም /Sims and Stephen 2005፡ 6/ "Folklore is informally learned and unofficial, part of everyday experience." በማለት ፎክሎር መደበኛ ባልሆነ ሂደት የሚማሩት ይፋ ያልሆነ የዕለት ተዕለት ተግባራችን አካል ነው ብለዋል፡፡

### 2.2.2. ክዋኔ

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የሚከወነውን ነገር ከሚከወንበት አውድ ጋር የሚያጠና ነው፡፡ /Sims and Stephen 2005፣28/ "Performance is still at the center of the study of folklore" ሲሉ ክዋኔ በአሁኑ ሰዓትም የጥናት መስክ ሆኖ በማገልገል ላይ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰ ሀሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው፡፡ "The performance approach helped to establish the core of the discipline as the study of artistic expression in groups and specific contexts." /Sims and Stephen 2005፣26/፡፡ ክዋኔ በአንድ በተወሰነ አውድ ወይም ቡድን ውስጥ ያለውን ጥበባዊ ገለፃ ለማጥናት ቁልፍ ነገር ነው፡፡ በጥቅሱ እንደገለፁት ክዋኔ በአንድ አውድ ውስጥ ያለውን የከዋኝና የታዳሚዎች ጥበባዊ የሆነ የቃል ግጥም የአከዋወን ስልት፣ የከዋኝና ታዳሚዎች መስተጋብር ምን እንደሚመስል ቃል ግጥሙን እንዴት እንደሚፈጥሩትና እንደሚጋሩት ለማጥናት ያስችላል፡፡

ክዋኔ ለቃል ግጥም ህልውናው ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ /Finnegan 1977፣ 28/ "Since an oral poem is an essential emphemeral work of art, and has no existence or continuity apart from its performance" ሲሉ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ለቃል ግጥም ህያው ሆኖ መኖር ክዋኔ ወሳኝነት አለው፡፡ ክዋኔ ለቃል ግጥም የልብ ትርታውና የደም ስሩ ነው፡፡ ቃል ግጥሙ ሲከወን ካልታየና ካልተደመጠ የማሳዘንም ሆነ የማስደሰት፣ ስሜትን የመኮርኮርና የማነሳሳት ሃይል አይኖረውም፡፡ የሚያሳዝነው፣ የሚያስለቅሰው፣ የሚያስቀውና የሚያስከፋው ሲከወን ነው፡፡

> Performance is an expressive activity that requires participation, heightens our enjoyment of experience, and invites response. In order for a performance to “happen,” a recognized setting must exist (we have to know a performance is taking place) and participants (performers and audience) must be present.” /Sims and Stephen 2005፣ 128-129/

ክዋኔ ገላጭ ድርጊት ሲሆን ክዋኔው ህያውና የተሳካ እንዲሆን የሚከወንበት የተደራጀ መቸት (ጊዜና ቦታ)፣ ከዋኝና ታዳሚ፣ በልምዳቸው የማዝናናትና ምላሽ የመስጠት ብቃት መኖር የግድ ነው፡፡ በጥቅሱ እንደተገለፀው አንድ ቃል ግጥም በሚከወንበት ጊዜ ክዋኔው የሚዘጋጅበት ጊዜና ቦታ፣ ክዋኔውን የሚመራው ከዋኝ፣ ክዋኔውን የሚያስተባብሩት ታዳሚዎች ሰንሰለታዊ ግንኙነት አስፈላጊ ነው፡፡ “የቃል ግጥም ክዋኔ ሁለት ጠቃሚ ማህበራዊ ሁኔታዎች ከዋኝና ታዳሚ በተመሳሳይ ሁኔታ በቀጥታ እርስ በርስ በመገናኘት ገፅ ለገፅ እየተያዩ የሚከወን ድርጊት ነው” /Ben-Amos 1971፣12-13/፡፡ የታዳሚዎችም ሚና የተለያዩ ሲሆን ክዋኔውን ሳቢ ያ ያደርገዋል፡፡ የከዋኙና ታዳሚው ስሜታዊ ምላሽ፣ በአውድ ላይ የሚገኙት ቁሶች ከክዋኔው ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ የክዋኔውን፣ ከዋኙንና ታዳሚውን ምላሽ ለመተርጐም የታዳሚዎችንና ከዋኞችን ግንኙነትና መስተጋብር መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ቃል ግጥሙ በሚደረደርበት ጊዜ ተናጋሪውና አድማጩ ያላቸው መስተጋብር እንዴት ነው፣ የከዋኙን ቃል፣ እንቅስቃሴ፣ የንግግር ሁኔታ፣ የድምፅ አወራረድና ዜማ እንዴት ይከተላሉ የሚሉት ይቃኛል፡፡ የቃል ግጥሙ ህያውነት የሚታየው ገላጭ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ ቃልግጥሞቹና ዜማው አብረው ሲገኙ ነው፡፡

ክዋኔ ቃል ግጥሞች በግልም ይከወኑ በቡድን ለመኖራቸው ወሳኝ ነው፡፡ ቃል ግጥሞች በቡድን ወይም በተናጠል ሊከወኑ ይችላሉና፡፡ ታዳሚዎች ክዋኔውን የሚገመግሙትና የሚለኩት የከዋኞችን ብቃትና ክህሎት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የከዋኞች የአከዋወን ስልትና ችሎታ ለክዋኔው መሳካት ወሳኝ ነው፡፡ /Sims and Stephen 2005፣133/ የቡድኑ አባል ሆኖ ክዋኔውን መረዳትና መተረጐም ካልተቻለ ክዋኔው የተሳካ ገለፃ አለው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ተሳታፊው በክዋኔው ምላሽ መስጠት ካልቻለ ክዋኔውን መረዳትና መተርጐም አልቻለም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የከዋኞች ችሎታና ብቃት የሚለካው በታዳሚው ግንዛቤና በክዋኔው ደረጃ ነው፡፡ ክዋኔ ተኮር

ንድፊ ሀሳብ ታዳሚው በገለፃዊ ድርጊቱ ስለሚሳተፉ ክዋኔውን ለመተንተን፣ ለመተርጎም፣ ፍች ለመስጠትና ብሎም ከክዋኔው ለመማር ያስችላል፡፡

ፎክሎር ሲከወን፣ ሲጨፈር፣ ሲተረት፣ ሲነገር፣ ሲዘመር አጥኝው ሊያተኩረባቸው የሚገቡ የክዋኔ አላባዊያን የሚባሉት ከዋኝ፣ አድማጭ፣ ቴክስት፣ አውድ፣ ቀመር፣ መልዕክት፣ መቸትና ደንብ ናቸው፡፡ እነዚህም እርስ በርስ እንደ ሰንሰለት የተያያዙና የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ከዋኝ ድርጊቱን የሚከውነው አካል ነው፡፡ “They may be acting singly; in pairs; in a small or large group; interacting or exchanging with other single or collective performers as leader, follower, or equal; overlapping or interchanging with more audience-like roles. /Finnegan 1992፣ 89/፡፡ ክዋኔውም እንደየሚናቸው በተናጠል፣ በጥንድና በትንሽ /ትልቅ/ ቡድን መስተጋብርና ልውውጥ ከሌሎች የተናጠልና የቡድን ከዋኞች ጋር መሪ አቀንቃኝ፣ ተከታይበመሆንና እኩል በመከወን፣ ሚናቸውን ከታዳሚው ጋር በመለዋወጥ በመከተልና በጋራ ሊከወን ይችላል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ቃል ግጥም በተናጠል፣በጥንድና በቡድን አንዱ አቀንቃኝ ሌላው ተከታይ በመሆንና ሚናቸውን በመለዋወጥ በጋራ የሚከውኑ መሆኑን ነው፡፡

የቃል ግጥም ክዋኔ በዜማ፣ በቅብብሎሽና በምልልስ በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን ሊከወን ይችላል፡፡ በተናጠል የሚከወኑ ሲባል አንድ ሰው በግሉ ወይም በቡድን ክዋኔ ብቻውን የሚያንጎራጉራቸውን ቃል ግጥሞች ይመለከታል፡፡

በጥንድ የሚከወኑት ቃል ግጥሙን በመቀባበል በፉክክር በየተራ በማዜምና በማንጎራጎር ነው፡፡

በቡድን የሚከወኑት ደግሞ በማጨብጨብ፣ በሆታና በልልታ በእንቅስቃሴ ታጅበው የሚቀርቡ ናቸው፡፡ እንደየቃል ግጥሙ ባህሪይና አይነት ክዋኔውም የተለያዩ ነው፡፡ Sims and Stephen /Bauman 1984፣ 37/ን ጠቅሰው ሲገልፁት “every performance differs from every other, depending on the context and the group in which the folklore occurs.” ይላሉ /Sims and Stephen 2005፣ 149/፡፡ ማንኛውም ክዋኔ ከማንኛውም ሌላ ክዋኔ አውድና የፎክሎሩን መፈጠሪያ አጋጣሚ መሰረት አድርጎ ይለያል በማለት ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የስራ ቃል ግጥሞች ከከዋኝ ከዋኝ፣ ከገጣሚ ገጣሚ፣ እንደየችሎታቸውና ስልታችው የተለያዩ ናቸው፡፡ በሚከወኑበት

ጊዜም የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝና የሀሳብ አገላለፅ መለያዬት ይታያል፡፡ በሌላ በኩል /Okpewho 1992፣ 42/

> Performance differ one from the other depending on such factors as the age and energy of the performer, the nature of the occasion, (death or merriment) the type of setting (cult enclave or open square), whether or not any musical accompaniments are used especially by the performer, and whether it is a solo or a group act.

አንድ ክዋኔ በተለያዩ ምክንያቶች ከሌላኛው ክዋኔ ይለያል፡፡ ልዩነቱም ከከዋኙ እድሜና ጉልበት፣ የክዋኔው ባህሪይና ሁኔታ (ሀዘን ወይም ደስታ) ፣ የሚከወንበት ጊዜና ቦታ ሃይማኖታዊ መሆንና አለመሆን፣ ሙዚቃዊ መሆንና አለመሆኑ፣ የተናጠል ወይም የቡድን ክዋኔ መሆንና አለመሆን የተነሳ ነው፡፡ ከጥቅሶቹ መረዳት የሚቻለው አንድ ክዋኔ ከሌላኛው ክዋኔ የሚለይበት የራሱ ባህሪያት ያሉት መሆኑን ሲሆን ይህንም ልዩነት በመስክ ቆይታየ ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ቃል ግጥሞች የሚከወኑበትን አውድ እንመለከታለን፡፡

### 2.2.3. አውድ

አውድ ለአንድ ክዋኔ ድረሳ፣ ቅርፅና መዋቅር እንዲሁም የሚተላለፈው መልዕክት መሰረት ነው፡፡ "Context is foundational concept in performance studies /Hufford 1995፣ 531/፡፡ አውድ ለክዋኔ ጥናት መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ክዋኔ ደግሞ ስሜትን የሚስብ የአውድ አካል ነው፡፡ "Context refers to anything and everything that surrounds a text and performance." /Sims and Stephen 2005፣137/፡፡ አውድ ማለት ቃል ግጥም በሚከወንበት ጊዜ የሚፈጠረውን አጠቃላይ ድባብ የሚያመለክት አንድ የማህበረሰብ ቡድን ህዝባዊ ጥበቡን የሚለዋወጥበትና ግንኙነት የሚፈጥርበት ተፈጥሯዊ ቦታና ማህበራዊ ሁኔታ ነው፡፡ አውድ የከዋኙ ማንነት፣ የታዳሚው ፈጠራና ተሳትፎ፣ የሚከውነው ነገር፣ ጊዜና ቦታ፣ ቁሳቁሶች በቅንጅት በደንብ ተደራጅተው፣ ገላጭና ጥበባዊ በሆነ መንገድ የሚቀርብበት፣ የእርስ በርስ ግንኙነትና መስተጋብር የሚፈጠርበት ተፈጥሯዊ መቸትና ማህበራዊ አውድ ነው፡፡

"The text, of course, is extremely important, but with out the context it remains life less." /Bascom 1954፣ 335/፡፡ ቃል ግጥም ያለ አውድ ህይወት

የለውም፡፡ Bascom እንዳሉት ቃልግጥም ህይወት ኖሮት ነፍስ የሚዘራው በአውድ ውስጥ ሲከወን ነው፡፡ ቃል ግጥሙን ከአውድ ነጥሎ ማጥናት የሚቻል ቢሆንም እንኳን ለቃል ግጥሙ ትክክለኛ ትርጉም መስጠትና የቃል ግጥሙን አይነት መለየት የሚቻለው በአውድ ውስጥ ሲነገር፣ ሲዘመር፣ ሲፈከር፣ ሲያሳዝንና ሲያስለቅስ ስናገኘው ነው፡፡ ይህንም /Ben Amos 1993፣ 211-212/ "The meaning of a text is its meaning in context. A valid interpretation is an interpretation of a text in context." ለይዘቱ ትክክለኛ ትርጉም መስጠት የሚቻለው በአወዱ ውስጥ ነው፡፡ የአውዱ ፋይዳም የፎክሎሩን ይዘት ለመተርጐም ነው ብለዋል፡፡ የሚከወነውን ቃል ግጥም መልዕክት ማወቅ ፣መተንተን፣ መተርጐምና ትክክለኛ ፍች መስጠት የሚቻለው በአውድ ውስጥ ነው፡፡ የአውዱን አጠቃላይ ድባብ በመመልከትና አዳምጦ በመገንዘብ መሆን አለበት የሚተረጐመው ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ቃል ግጥም የሚከወንበት አጋጣሚ ሠፊ ነውና፡፡ እንዲሁም አውዱን መመርመር ይዘቱን ከመተርጐም አልፎም በአውድ ውስጥ ያሉትን አጠቃላይ ጓዞች ለመረዳት ያስችላል፡፡

/Bauman 1983፣ 367/ እንደገለፁት አንድ የፎክሎር መስክ ተመራማሪ መረጃ በሚሠበስበት ጊዜ መታየት ያለባቸው በአውድ ውስጥ የሚጠቃለሉ ስድስት ነገሮችን አስቀምጠዋል፡፡ የአውዱ ፍች /ትርጉም/፣ የማህበራዊ አውዱ የትነት፣ ከሌላው የፎክሎር አይነት ያለው ዝምድና፣ የሚከውኑት ሰዎች ማህበራዊ ደረጃ፣ የግለሠብ አውድና ሁኔታዊ አውድ ናቸው፡፡ ከጥቅሱ መረዳት የሚቻለው በፎክሎር መስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት ክዋኔው የሚደረግበትን ጊዜና ቦታ ማወቅ፣ ከሌሎች ዘውጐች የሚዛመድበትን መንገድ፣ ምን አይነት ሰዎች ይሉታል? በግለሰብና ማህበራዊ አውድ ውስጥ እንዴት ይተገበራል የሚለውን ማጥናት አለበት፡፡ አውድ ተጨባጭና ማህበራዊ አውድ ተብሎ በሁለት ይከፈላል /Sims and Stephen 2005፣137/፡፡

> "It is important to know where the performance takes place, both in terms of geography and the specific setting. The physical environment also includes who is present–performers and audience members as well as any observers (of course, that includes the folklorist )" / 2005፣138/፡፡

ተጨባጭ አውድ ክዋኔው የሚካሄድበትን ጊዜና ቦታ ለማወቅ ያስችላል፡፡ ጊዜ ሲባል ቃል ግጥሙ የሚከወንበትን ወራትና ሰዓት ሲሆን ቦታ ደግሞ ክዋኔው የሚደረግበትን አካባቢ መልካም ድራዊ ገፅታና ውስን መቸት ነው፡፡ ከዋኝና ተሳታፊን እንዲሁም ሌላ ተመልካቾችን ለመለየት ያስችላል፡፡ የከዋኙና ታዳሚው መስተጋበርም

በዚሁ የሚታይ ነው፡፡ የከዋኙን የአከዋወን ስልት፣ ምት፣ የድምፅ አቀያየርና መለዋወጥ፣ እንቅስቃሴ፣ የታዳሚውን ምላሽ ያጠቃልላል፡፡ ይህ አውድ በክዋኔው ላይ ተገኝቶ በቴፕ በመቅዳትም ሆነ ማስታወሻ በመያዝ ትክክለኛ መረጃ ለመሰብሰብ የላቀ ሚና ይጫወታል፡፡

ማህበራዊ አውድ የክዋኔውን አጠቃላይ ድባብ፣ የከዋኞችን ማንነት ማህበራዊ ደረጃ፣ የታዳሚዎችን ሁኔታ /በእድሜ፣ በፆታ፣ በጐሳ፣ በመደብ፣ በሙያ፣ በሃይማኖትና በባህል ምክንያት የሚፈጠረውን ጠቅላላ አውድ ይመለከታል፡፡ ከዋኝ፣ ተሳታፊና መቸትም በክዋኔው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ በሌላ በኩል / Bascom/ እንዲህ ይላሉ፡-

> "The social context of folklore, including the time and place for the telling of specific forms; the identity of the narrators and the composition of the audience, as well as the relationship of the narrator to the text; the use of dramatic and rhetorical devices in performance; audience participation; folk classification of traditional genres and the people’s attitudes toward them / 1954:334/.

ማህበራዊ አውድ የታዳሚው ፈጠራ፣ የከዋኝና ይዘቱ ግንኙነት፣ የክዋኔውን ሁኔታ፣ የሚቀርበው ነገር፣ የሚቀርበበት ጊዜና ቦታ፣ የታዳሚውን ፈጠራ፣ ተሳትፎና አቋም ከከዋኝ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያጠቃልል መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይህም የክዋኔውን ማህበራዊ አውድ መመልከቱ ማን፣ ምን፣ ለምን፣ ለማን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደ ተከወነ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቃል ግጥም አደራረስ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

### 2.2.4. ድረሳ

ቃል ግጥም እንዴት ይደረሳል? ስንል ከገጣሚው ወይም ከከዋኙ አንደበት የሚፈጠርበትን ስልት ነው፡፡ ቃል ግጥም በቃል አጥንቶ በመሸምደድ፣ ከክዋኔ በፊት ከሰው የሰሙትን በማስታወስና በክዋኔው ላይ እዚያው በመፍጠር ሊከወን ይችላል፡፡ በደረሳውም የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝ፣ የዓረፍተ ነገርና የሀሳብ ለውጥ ይፈጠራል /Finnegan 1970፣373-374፣ ዘሪሁን 1992፣28/፡፡ Finneganና ዘሪሁን እንደ ገለፁት በደረሳ ወቅት የይዘትም ሆነ የቅርፅ ለውጥ የሚከሰተው የከዋኙ የአከዋወን ስልት፣ ድምፀት፣ የማስታወስ አቅም ልዩነት፣ የከዋኙና ታዳሚው እድሜ፣ ፆታ፣ የሚከወንበት ጊዜና ቦታ የተለያዬ መሆን የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም በመርሳት፣ የራስን ሀሳብ

በመጠቀም፣ በአዳዲስ ቃላት ከአውዱ ጋር ተስማሚ አድርጎ ለማቅረብ በሚደረግ ጥረት ይሆናል፡፡ የለውጡ መፈጠርም በራሱ ድረሳውን ሳቢ ያደርገዋል፡፡

ግጥሞች ከመፍጠር ይልቅ በማስታወስና ማሻሻያ በማድረግ ላይ ሲያተኩሩ በቡድን የሚከወኑት ግን በአብዛኛው በመፍጠር ላይ ያተኩራሉ፡፡ የፈጠራ ችሎታ የሚመነጨውም ብዙ ጊዜ በቡድን ክዋኔ ከዋኙ ስሜታዊ ሆኖ ሲሳተፍ ነው፡፡ አንድ ከዋኝ የራሱን ቃል ግጥም ሊፈጥር ሌላ ሰው ሊያስገጥመውና ከዚህ በፊት የነበረውን ቃል ግጥም አዳዲስ ቃላት ተጠቅሞ በማሻሻል ከአውዱ ጋር ተስማሚ አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ /Finnegan 1977፣53/ እንደሚያስረዱት ቃል ግጥሞች በክዋኔ ወቅት በሶስት መንገድ ሊደረሱ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ሽምደዳ፣ እዚያው በዚያውና ተመስጦ ናቸው፡፡

በሽምደዳ አደራረስ ስልት ከዋኙ ቀድሞ ሲከወን የነበረውን ቃል ግጥም ይዘቱን ሳይለቅ ትውፊቱን ጠብቆ እንዳለ የሚያቀርብበት መንገድ ነው፡፡ የዚያው በዚያው አደራረስ ስልት ደግሞ ከዋኙ የክዋኔውን ድባብ ተመስርቶ የነበረውን ቃል ግጥም የራሱን አዳዲስ ቃላትና ሀሳቦች በመጨመር አሻሽሎ በማቅረብና እዚያው ላይ አውዱን መሰረት አድርጎ በመፍጠር የሚያቀርብበት ነው፡፡

ሌላው ተመስጦ አደራረስ ስልት ከዋኙ በተለያዩ ስሜት ቀስቃሽ ነገሮች ተነሳስቶ ሳያስበው የሚያዜማቸውን ግጥሞች ይመለከታል /Finnegan 1977፣ 52-87/፡፡ በመሆኑም ቃል ግጥም የተፃፈን አንብቦ ወይም ከሰው ሰምቶ በማጥናትና በመሸምደድ፣ እዚያው ላይ በመድረስ እና በአንዳንድ ድንገት ደራሽ ቀስቃሽ ነገሮች ምክንያት ሊደረስ ይችላል፡፡ በደረሳውም አውዱን መሰረት ያደረገ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለውጥ ተደርጎበት ወይም እንዳለ ለውጥ ሳይደረግበት ሊቀርብ ይችላል፡፡

የቃል ግጥም ደረሳ የመደጋገም ባህሪ አለው፡፡ ከዋኔው ድግግሞሽን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ጊዜ የመደጋገም እድላቸው የሰፋ ነው፡፡ እናም በቃል ግጥም ደረሳ የድግግሞሽን መኖር ማወቅ የሚቻለው በክዋኔው ሲገኙ ነው፡፡ ድግግሞሹ ከክዋኔ ውጭ በሚነገሩ ቃል ግጥሞች ሊኖር ቢችልም ድግግሞሹን ነፍስ ዘርቶ የምናገኘው ግን ሲከወን ስናየው ነው፡፡ ድግግሞሹም በቃል፣ በሀረግ፣ በስንኝ ብሎም በይዘትና ቅርፅ ደረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ የድግግሞሹንም ፋይዳ /Finnegan/ “Repetition has real point in such circumstance ;it makes it easier for the audience to grasp what has been said and gives the speaker/singer confidence that it has understood  the message he is trying to communicate.” /1977፣129/፡፡

የቃል ግጥም ድግግሞሽ ለከዋኙ በራስ መተማመን ስሜትን ለመፍጠር፣ ተሳታፊዎችም የከዋኙን መልዕክት በቀላሉ ለመያዝ፣ ለመረዳትና መልሰው በመሞከር መግባባትን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ እንዲሁም በድረሳ ወቅት ክፍተት ሲፈጠር የግጥም መስመር ለመሙላት፣ ቃል ግጥሙ ስሜት እንዲኖረው ለማድረግ፣ ለግጥሞቹ መልዕክት አጽንኦት ለመስጠት፣ የተሳታፊዎችን ትኩረት ለመሳብና የመልዕክቱን አሳሳቢነት ለማረጋገጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ድግግሞሽና ተለዋዋጭነትም በቃል ግጥም ደረሳ ወቅት የማይቀሩ ባህሪያቱ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የቃል ግጥም ድረሳን ካየን ቃል ግጥሞቹ እንዴት እንደሚተላለፉ ደግሞ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 2.2.5. ተስተላልፎ

ተስተላልፎ ሲባል ቃል ግጥም በቃል ተደርሶ ከጊዜ ጊዜ፣ ከቦታ ቦታ፣ ከባህል ባህልና ከትውልድ ትውልድ ሊተላለፍ የሚችልበትን ዘዴ ይመለከታል፡፡ ቃል ግጥሞች ይህን ሽግግር ለማድረግ አጋጣሚዎችን ይሻሉ፡፡ ምክንያቱም ቃል ግጥሞች አውድን መሰረት አድርገው በመከወን እንደሚፈጠሩ ሁሉ የሚተላለፉትም በአውድ ላይ ሲከወኑ ነው፡፡ የመከወኛ አጋጣሚ ካላገኙ የመኖር ህልውናቸው ሊቀንስ ብሎም ሊያከትም ይችላል፡፡ /Finnegan 1977፣ 135/ የቃል ግጥምን ተስተላልፎ የቦታን ድንበር ሰባሪነት ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም ቃል ግጥሞች በተለያዩ መልኩ ከቦታ ቦታና ከዘመን ዘመን ለውጥ እየተደረገባቸው ሊተላለፉ እንደሚችሉ ሁሉ በቅርጽም ሆነ በይዘት ለውጥ ሳይደረግባቸው ከቦታ ቦታ እና ከጊዜ ጊዜ የሚሸጋገሩ ናቸው፡፡ በቃል ግጥም ተስተላልፎ ወቅት በቃል፣ በሀረግ፣ በስንኝ፣ በዋና ሀሳብና በዓረፍተ ነገር ላይ ለውጥ ይከሰታል፡፡ ለቃል ግጥም ተስተላልፎ የከዋኙ የአከዋወን ስልትና የማስታወስ ችሎታም ወሳኝ ናቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ቃላዊ ከመሆኑ የተነሳ “በቃል ያለ ይረሳል በጽሁፍ ያለ ይወረሳል” እንዲሉ የመረሳት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ በቃል ግጥም ተስተላልፎ ጊዜ በመረሳት የሚከሰተውን ክፍተት ለመሙላት የደረሳ ተስተላልፎ ይፈጠራል፡፡ የቃል ግጥሞችን ሙሉ በሙሉ ማስታወስ እንደማይቻልም /Finnegan 1977፣144-145/ ይገልፃሉ፡፡ እናም የቃል ግጥም ተስተላልፎ ቀድሞ ይባል የነበረውን በመሸምደድ እና አስታውሶ በመከወን፣ እዚያው ላይ በመድረስ እና በመከወን ሊሆን ይችላል፡፡ ተስተላልፎውም የመግጠም ልዩ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ሊሆን ይችላል፡፡

### 2.2.6.የስራ ላይ ቃል ግጥሞች ፋይዳ

የስራ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ሲባል ቃል ግጥሞቹ ለገበሬዎችም ሆነ ለስራው መፋጠን ያላቸውን ጠቀሜታ የሚመለከት ነው፡፡

/Finnegan 1977፣233-239፣ 1970፣ 239/ በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች በቡድን የሚከወኑ የስራ ላይ ቃል ግጥሞች ስራውን በማፋጠን፣ የሰራተኞችን ስሜት በማነቃቃትና በማስተሳሰር፣ ከግጥሙ ዜማና አወራረድ፣ ከሰውነት እንቅስቃሴ ጋር እኩል እንዲራመዱ፣ የፉክክር ስሜት በማጫር ምላሽ እንዲሠጡ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ ይህንም /Okpewho 1992፣ 111/ “Each of these songs clearly reveal, same spirit of competion.” ሲሉ የስራ ቃል ግጥሞች የፉክክር ስሜት በመፍጠር ስራውን ለማፋጠን የሚረዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል / ዘሪሁን 1992፣ 46/ የስራ ዘፈኖች ግጥምና ዜማ ስራው አሰልች እንዳይሆን ለማለዘብ፣ ተሳታፊዎች ድካም እንዳይጫጫናቸው፣ ለስራው እንዲተጉ፣ እንዲበረቱ ለማድረግ ያስችላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም የስራ ቃል ግጥሞች ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወንና በከዋኙም ሆነ ታዳሚዎች መካከል መልካም መስተጋብርና ቅንጅት በመፍጠር ትልቅ ሚና ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች የሚደረደሩት ቃል ግጥሞች ከሚከወነው የስራ አይነት ጋር ተግባራዊ ግንኙነት እንዳላቸውና ይህን ግንኙነታቸውን ለማረጋገጥም የሚከሰቱበትን አውድ መመርመር የግድ መሆኑን / /Finnegan 1977፣ 231 / ገልፀዋል፡፡

በተለያዩ የስራ አይነቶች የሚገጠሙት ቃል ግጥሞች ከስራው አይነት ጋር የተጣጣሙና ተግባራዊ ግንኙነት ያላቸው ቢሆንም የዜማ አወራረድና እንቅስቃሴያቸው እንደየስራ አይነቱ ለየቅል ነው፡፡ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ከስራው አይነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ግጥሞችም እንዳሉ መዘንጋት የለብንም፡፡ በዚህ ጥናት በመስክ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች የዜማ አወራረድና ክዋኔ ከአውድ አውድ ቢለያይም ግጥሞቹ ከስራው አይነትና ገበሬዎች ስሜት ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ እነዚህ የስራ ቃል ግጥሞች የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊና ባህላዊ አመለካከትና ስሜት ለመግለፅ ያስችላሉ፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ  ጥናቱ የተካሄደበት ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

# 3. የዳባት ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለ ዳባት ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳዩ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ በውስጡም የዳባት ወረዳ ስያሜ አመጣጥ፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት፣ የህዝብ ስርጭትና መተዳደሪያ ኢኮኖሚ፣ የመሰረተ ልማት አውታሮች፣ የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ ትንታኔ ተካተዋል፡፡

የዳባት ወረዳ በሰሜን ጐንደር ዞን ከሚገኙ 24 ወረዳዎች /የከተማ አስተዳደሮች/ አንዷ ስትሆን ወረዳውን በሰሜን ደባርቅ፣ በምስራቅ ወገራና ደባርቅ ፣በደቡብ ወገራ፣ በምዕራብ የጠገዴና የታች አርማጭሆ ወረዳዎች ያዋስኑታል፡፡ ወረዳው ከአዲስ አበባ በ814 ኪ.ሜ፣ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ባህርዳር በ255 ኪ.ሜ፣ ከዞኑ ከተማ ጐንደር ደግሞ 75 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳው በ30 ቀበሌዎች በአራት የከተማና በ26 የገጠር ቀበሌዎች የተከፈለ ነው፡፡

የዳባት ወረዳ በ1476 ዓ.ም ገደማ "ደባ" በተሰኘ ንጉስ እንደተቀረቀረ በአፈ ታሪክ ይነገርለታል፡፡ በአፈ ታሪኩ መሰረትም  የደባ አባት ደጃች ሰርፀ ሱልስ አራት ልጆች ክፍሎን፣ ገላውዲዎስ፣ ኪሮስና ራሱ ደባንን ወለዱ፡፡ በግዛት ክፍፍል በጐንደር ላይ ሆነው "ደባ" የተባለው ልጅ ዳባትን እንዲገዛ ደረሰው፡፡ በዚህም ይገዛ ስለነበር ከልዑል ንጉስ ስም በመውሰድ ከተማውን "ዳባት" ብለው ጠሩት፡፡ /የዳባት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት  2005ዓ.ም የፅሁፍ መረጃ/፡፡

በሌላ በኩል አቶ ጀጃው ደርሶ ዳባት የሚለው ስያሜ የተሰጣት አንዲት ለአቅመ አዳም ያልደረሰች ሴት ልጅ አሁን ዳባት በተሰኘው ቦታ ላይ በመደፈሯ ምክንያት "ደባት"አሏት፡፡ ትርጉሙም "ደፈራት፣ ጣላት፣ ወደቀች ማለት ነው፡፡ ከዚህ ስያሜ በመነሳት "ዳባት" እንደተባለ በአፈ ታሪክ ይነገራል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 10/2006/ [1]

---

[1]በዚህ ጥናታዊ ስራ ዉስጥ የመረጃ አቀባዮች ምንጭ አጠቃቀስ አራት አይነት ነው፡፡ መረጃው በክዋኔ አውድ ላይ ከተሰበሰበ ስም፣ ቀን፣ ካሴት ቁጥር በማለት ተገልጿል፡፡ መረጃው በክዋኔ አውድ ላይ ተሰብስቦ በካሴት ያልተቀረፀ ከሆነ ሰምና ቀን ተገልጿል፡፡ ከክዋኔ ውጭ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ በካሴት የተቀረፁ መረጃዎች ቃለ መጠይቅ፣ ስም፣ ቀን፣ ካሴት ቁጥር የተጠቀሰ ሲሆን ከክዋኔ ውጭ በቃለ መጠይቅ መረጃ ሰጥተው በካሴት ያልተቀረፁት ቃለ መጠይቅ፣ ስም፣ ቀን በማለት ተገልጿል፡፡

የወረዳው የቆዳ ስፋት በጠቅላላ 173, 285 ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 10% ወጣ ገባ፣ 30% ሜዳማ ፣ 55% ተራራማ፣ 5% ሸለቋማ ነው፡፡ ወረዳው ከባህር ወለል በላይ ከ1500-3200 ሜ ከፍታ አለው፡፡ ወረዳው 52% ደጋማ፣ 14% ወይናደጋ፣ 34% ቆላማ፣ የአየር ንብረት ሲኖረው በአማካይ ከ800-1400 ሚ.ሜ የሚደረስ አመታዊ የዝናብ መጠን ያገኛል፡፡ በወረዳው ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ አብዛኞቹ ደጋማና ቆላማ ናቸው፡፡ የወረዳው አፈር 60% ቡናማ፣ 35% ጥቁር አፈር፣ 5%ቀይ አፈር መሆኑን የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት 2006 የፅሁፍ መረጃ ያመላክታል፡፡

ወረዳው የተለያዩ አዝዕርቶችን ለማብቀል ተስማሚ የአየር ንብረት ያለው መሆኑን ተከትሎ በአካባቢው ሲኖሩ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ብሉልኝ፣ ጠጡልኝ፣ ወጋቸው በሞቴ፣ አፈር ስሆን ልማዳቸው መሆኑን የተረዱ እግር የጣላቸው አልፎ ሂያጅ እንግዶች ይቅርና ንጉሶችም በቋሚነት ለመኖሪያ እንደመረጡት ለመግለፅ በስነ ቃላዊ ግጥሞች እንዲህ በማለት ሲያሞካሹት የቆዩ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች በአፈ ታሪካቸው ይገልፃሉ፡፡

አገሯ ወገራ የምትበላው ገብስ
ግርም ያደርገኛል የእጇ አለሳለስ
አገሬ ወገራ እልበቱ ሽንኩርቱ
ተልባው ትዝ ይለኛል ያ የጠላሁቱ
የተዘፈነላት ብዙ የተዜመላት
የአያሌው ብሩ አገር እንደምን ናት ዳባት
/የዳባት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2005 የፅሁፍ መረጃ/

እነዚህና የመሳሰሉት ስነ ቃላዊ ግጥሞች ስለ ወረዳው ልምላሜና የአየር ነብረት ተስማሚነት የሚመሰክሩ በተለያዩ ጊዜያት ይኖሩ የነበሩ የአካባቢው የማህበረሰብ ክፍሎች፣ በአውድማ፣ በአረሙ፣ በአጨዳ፣ በእርሻው እየተቀባበሉ ለብዙ ዘመናት በመቻቻልና በመከባበር በአብሮነት ዘይቤ ኑሯቸውን ይገፉ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ብርቄ ጫኔ ፣ ታህሳስ 25/2006፣ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2005 የፅሁፍ መረጃ/ ፡፡

የወረዳው ህዝብ በከተማ ወንድ 9,512፣ ሴት 11,716 ድምር 21,228 ሲሆን በገጠር የሚኖረው የህዝብ ብዛት ወንድ 74,154፣ ሴት 69,891 በድምሩ 144,045 ነው፡፡ በወረዳው የወንድ ብዛት 83,666 እና የሴት ደግሞ 81,607 ሲሆን የወረዳው የህዝብ

ብዛት በአጠቃላይ 165,273 ደርሷል፡፡ የወረዳው ህዝብ 97% የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሲሆን 3% የእስልምና እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ በፍቅርና በሰላም ተከባብረውና ተባብረው ይኖራሉ፡፡ /የዳባት ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት 2006 የፅሁፍ መረጃ/፡፡

የዳባት ወረዳ ህዝብ በአብዛኛው በግብርናው የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚስተዳደር ነው፡፡ ወረዳው ዘርፈ ብዙ የእርሻ ኢኮኖሚ፣ በርካታ የቀንድና የጋማ ከብት፣ ከፍተኛ የማዕድን ሀብት አለው፡፡ የወረዳው ህዝብ በግብርና፣ በንግድ፣ በእደ ጥበብና በቀን ስራ ይተዳደራል፡፡ በወረዳው ከሚገኙት የገጠር ቀበሌዎች አብዛኞቹ ደጋማና ቆላማ ሲሆኑ በደጋ ቀበሌዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች ከሚያመርቷቸው የብዕርና የአገዳ ሰብሎች መካከል አተር፣ ባቄላ፣ ቢራ ገብስ፣ ስንዴ፣ ምስር፣ አብሽ፣ ጓያና ጤፍ በብዛት ይመረታሉ፡፡ በተለይም ደግሞ በደጋማው የቢራ ገብስ ሲመረት፣ በቆላማው የወረዳ ክፍል ከሚመረቱ የሰብል ውጤቶች ዳጉሳና ማሽላ የበላይነቱን የሚይዙ ቢሆንም እንደ ሰሊጥና ኑግ የመሳሰሉት የቅባት እህሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬ በብዛት ይመረታሉ፡፡ የወረዳው ህዝብ ከእርሻ በተጨማሪ ከብቶችን በማድለብም ይጠቀማል፡፡ የዳልጋ፣ የቀንድ ከብቶች፣ በጐችና ፍየሎች በብዛት ያረባል፡፡ በንብ ምርትም በዘመናዊ ፣ የሽግግር ና ባህላዊ ቀፎ በመጠቀም ተጠቃሚ ናቸው፡፡

የዳባትን ወረዳ የመሰረተ ልማት አውታሮች ስንመልከት ወረዳው ለመሰረተ ልማት ግንባታ ምቹ እንደመሆኑ መጠን በጤናው ዘርፍ 31 ጤና ኬላዎች፣ 6 ጤና ጣቢያዎች፣ ሁለት የግል ክሊኒኮችና 5 መለስተኛ ክሊኒኮች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም የወረዳውን የትምህርት ተቋማት ስንመለከት አንድ መሰናዶ፣ አንድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ 2 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 75 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 150 ተግባር ተኮር የጐልማሶች ጣቢያ፣ ሁለት አፀደ ህፃናት ትምህርት ቤቶች፣ ሁለት የልዩ ፍላጐት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በዚህም የትምህርት ሽፋን 1ኛ ደረጃ ት/ት ቤት 89.7% ፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 92%ና መሰናዶ ት/ት ቤት 76.3% ደርሷል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን በሚመለከት ወረዳው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለህዝብ አገልግሎት በመስጠት፣ የተንቀሳቃሽና መደበኛ ስልክ ተጠቃሚ ሲሆን፣ 24 ሰዓት የመብራት አገልግሎት ያገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር ደባርቅና ወገራ አጐራባች ወረዳዎች መብራት የሚያገኙት ዳባት ላይ ከተገነባው ማሰራጫ መስመር ነው፡፡ ወረዳው ከፍተኛ

የሆነ የውሃ እጥረት አለበት፡፡ በወረዳው በቅርቡ ከጐንደር ደባርቅ ደረጃውን የጠበቀ የአስፓልት መንገድ ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ በመሆኑና ከደባርቅ ጃናሞራ መንገድ እየተሰራ 95% ደርሷል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ አደራጀው ጌታቸው፣ ታህሳስ 25/2006፣ የዳባት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም 2005 የጽሁፍ መረጃ/፡፡

በዚህ ክፍል የወረዳውን አጠቃላይ ገፅታ ካየን በውስጡ ያሉት ገበሬዎች ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን፣ በምን፣ ለምንና እንዴት እንደሆነ ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 3.1. የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ማህበራዊ ህይወት

በወረዳዋ የኦርቶዶክስና የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ገበሬዎች በአንድ አካባቢ /አገር/ አብረው ሲኖሩ የተለያዩ ማህበራዊ መስተጋብሮችን ይፈጥራሉ፡፡ ያላቸውን መስተጋብርም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ፣ የእስልምና እምነት ተከታይና ኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ያላቸው ማህበራዊ መስተጋብር በማለት በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

### 3.1.1.በኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች በበርካታ ጉዳዮች እርስ በርስ መስተጋብር ይፈጥራሉ፡፡ "ግንኙነታችን በሰንበቴ፣ በቅዱሳን ዝክር፣ በክርስትና፣ በትዝካር፣ በጋብቻ፣ በጉርብትና ፣አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ በክብረ በዓላት፣ በለቅሶ፣ በሆበራ፣ በምዝነትና አበልጅነት ወዘተ ነው" /ቃለ መጠይቅ፣ ድረስ ግርማውና ደሴ ውበት ጥር 12/2006 /፡፡ ገበሬዎች እምነታቸውን፣ አንድነታቸውን ግንኙነታቸውን ለማጠናከር እነዚህን የግንኙነት ሰንሰለቶች ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ የግንኙነት መስካቸው ገበሬዎች ግንኙነት ከሚፈጥሩበት ጉዳይ አንዱ የቅዱሳን ዝክር ነው፡፡ መረጃ አቀባዬ ድረስ ግርማው እንዲህ ይላል፡-

> አብዛኛው ገበሬ ቢያንስ የአንድ አንድ ቅዱሳን ስም በመጥራት ይዘክራል፡፡ ዝክር አንድ ሠው በመንግስት ደረጃ የሆነ ጥፋት ሠርቶ ከተገኘ ዋስ አምጣና ትለቀቃለህ እንደሚባለውና ዋስ ካመጣ እንደሚለቀቀው እኛም ጥፋት ሠርተን ስንገኝ ዋስ ጠበቃ የሚሆኑን መሆናቸውን ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ባህል በመጠበቅና ከሃይማኖት አባቶች እንማራለን፡፡ በዚህ ምክንያት በዝክሩ ከሩቅም ከቅርብም ያለውን ዘመድ በመጥራት ተገናኝተን እርስ በርስ እንወያያለን፤ ችግር ካለ እንፋታለን፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡

"በሞት ጊዜ ያዘነውን በማፅናናት፣ የገንዘብም ሆነ የእህል መዋጮ በማድረግ፣ አቅም ካነሰው ከ10 እስከ 20ብር አዋጥተን ፍታት በማስፈታት፣ የተቸገረውን በመርዳት፣ የደከመውን በማገዝ፣ ከሳቀው ስቀን ካለቀሰው አልቅሰን ችግርም ሆነ ደስታችን እንጋራለን" /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡

የገበሬዎች ግንኙነት /መስተጋብር/ የሚፈጠርበት ሌላው አመታዊ ክብረ በዓል ፣ጋብቻ፣ ተዝካርና ሌሎችም ናቸው፡፡ በእነዚህ ተቋማት እርስ በርስ በስራ የመደጋገፍ፣ የመረዳዳት /ከጌሾ ወቀጣ ጀምሮ/ ሴት ወንድ ሳይሉ በአንድነት ይሰራሉ፡፡ አብረው በመበላትና በመጠጣት ሀዘንም ሆነ ደስታቸውን ይካፈላሉ፡፡ የገንዘብም ሆነ የሀሳብ ድጋፍ ይለግሳሉ፡፡ ከተለያዬ አቅጣጫ የሚጠራው ቤት ዘመድም ከሁለት ቀን ያላነሰ እስከ ሳምንት ባለው ሲጫወት፣ ሰንብቶ ይሸኛል፡፡ /ቃለመጠይቅ፣ የማታው አስናቀው ፣ጥር 06/2006 ዓ.ም/፡፡ ይህንም ግንኙነታቸው በጥር አስራ ሁለት ቅዱስ ሚካኤል ዓመታዊ ክብረ በዓል፣ በሰንበቴ፣ በተዝካር፣ በጋብቻ፣ በለቅሶና በጉርብትና አብሮ በመብላትና መጠጣት ያላቸው ግንኙነት በመስክ ቆይታዬ ተመልክቻለሁ፡፡

ገበሬዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሩት በቡድን ተሰባስበው ነው፡፡ ሆበራውም በአጨዳ፣ ውቂያ፣ ክምር፣ አረም፣ ጉልጓሎና እርሻ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደ መረጃ አቀባየ ግዛት አሰፋ ማብራሪያ፡-

ገበሬዎች ግንኙነታቸው የተመሰረተበት ሆበራ ሁለት አይነት ነው፡፡ አንዱ አሰና ግብር ሲባል ሌላኛው ደግሞ በደቦያት የሚደረግ ሆበራ ነው፡፡

የአሰና ግብር ሆበራ አንድ ሰው ሴትም ሆነ ወንድ ስራውን ለማከናወን አቅም ሲያጥረውና አቅም እያለውም ብቻውን ሊከውነው የማይችል ሰፊና ብዛት ያለው አዝመራ ከሆነ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሰውየው ለሌላ የቅርብ ቤተሰቡ ወይም ጓደኛው አሰና ግብር ቁምልኝ ይለዋል፡፡ ይህም ሰው ከሌሎች ሰዎች ስራ ደበያት በማውጣትና በመለመን በርካታ ስዎችን ይሰበስባል፡፡ የስራውን ቀን ይነግራቸዋል፡፡ ከባለቤቱ ጋር ምን ያህል ሰው እንዳገኘለት ተነጋግሮ አስፈላጊው የምግብና የጠላ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ በአሰና ግብር የሚመጣው ወጣትም ይሁን አዛውንት ሽማግሌ እርስ በርስ በመፎካከር፣ በመወገድ፣ በዘፈን፣ በፉከራና በቀረርቶ፣ እየተነቃቃ የታቀደውን ስራ ሳይጨርስ አይሄድም፡፡ እስከ ምሽትም ቢሆን ሰርተው ባለቤቱን በማስደሰት ሽልማት የሚያገኙበት አጋጣሚም አለ፡፡ ሽልማቱም የሌላ አይደለም የጠላና የበግ ነው፡፡ በመብላትና በመጠጣት በዘፈን ሙሉ ሌሊቱን ያሳልፋሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 06/2006 ዓ.ም/፡፡

በሌላ በኩል አታክልት ዳምጤ "አሰና ግብር አቅም ለሌላቸው ባል የፈቱና የሞተባቸው ሴቶች ና በሰፊው ለሚያመርት አራሽ ገበሬ በአንድ ጊዜ በመተባበር ተጋግዞ በፉከራና ቀረርቶ እያቀለጡ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚተገበር ነው" በማለት ይገልጻሉ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 09/2006ዓ.ም/፡፡

> ደበያት አንድ ሰው ከተለያዩ ሰዎች ስራ በመሄድና በመስራት ብድር የሚያወጣበት ነው፡፡ የእሱው አዝመራ ወደ ኋላ መቆየት የሚችል ከሆነ የሌሎችን የደረሰ አዝመራ በማተጫጨድ፣ በማተራረም፣ ወዘተ ይሣተፋል፡፡ የእራሱ አዝመራ ሲደረስ ደግሞ ቀን አውጥቶ ባልደረባዎቹን በመሰብሰብ ያሳጭዳል ፤ያሳርማል ፤ያስወቃል ወዘተ፡፡ ይህም በሆበራ የሚደረግ የስራ ክንውን ስራውን ያቀላጥፋል፡፡ ግማሹ አጫጅ፣ ግማሹ ሰብሳቢ በመሆን በእልልታና በሆታ፣ በፉከራና ቀረርቶ ሆኖ ይሳተፋል /ቃለ መጠይቅ፣ ግዛት አሰፋ፣ ጥር 06/2006 ዓ.ም/፡፡

በመስክ ቆይታዬም በዳራ ቀበሌ አስማረ መልሴ የተባለ ጠንካራ ገበሬ በልመናና በደበያት የጤፍ አጨዳ ሆበራ የሳተፉት ከሃያ በላይ ገበሬዎች የታቀደውን አጨዳ በፉክክር ባልታሰበ ሰዓት ጨርሰው ተሸክመው በመከመራቸው ባለቤቱ አስማረ አንድ ጋን ጠላና እንድ በግ ሊሰጣቸው ቃል ሲገባ ሰምቻለሁ፡፡ በጥቅሉ የወረዳው ገበሬዎች በተለያዩ ጉዳዮች የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በመቀጠልም የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት እንመለከታለን፡፡

### 3.1.2. በእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች

የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ግንኙነት አላቸው፡፡ ይህንም መረጃ አቀባዬ ተበጀ በየነ እንዲህ ይላሉ፡-

> በዓመታዊ ክብረ በዓላት፣ በስግደት ሰዓት፣ በሆበራ፣ በጋብቻ ወዘተ እርስ በርስ እንገናኛለን፡፡ ወደ መስጊድ በመሄድ የስግደት ስርዓት ስናከናውን እርስ በርስ በመማማርና በመወያየት ግንኙነታችን እናጠናክራለን፡፡ ስለ መንግስት ድጋፍ፣ ስለ ኑሮ፣ ስለ አካባቢው፣ ስለ መልካም ስራ፣ የሰው ገንዘብ አለመመኘት፣ የደከመ ማሳረፍ፣ የራበው ማብላት፣ የጠማው ማጠጣት፣ ለበረደው ማልበስ እንዳለብን እንወያያለን፡፡ ይህንም በተግባር እናሳያለን /ቃለ መጠይቅ፣ ተበጀ በየነ፣ ጥር 12/2006/፡፡
> ሌሎችም ሰይድ መሳነርና ተገኘ አማን ይህን ሀሳብ ገልፀዋል፡፡

ሙስሊሞች ያላቸውን መስተጋብር ከሚገልፁባቸው ተቋማት አንዱ ዓመታዊ ክብረ በዓላት ናቸው፡፡ በዓል ከሆነ አብሮ በመብላትና መጠጣት በሳቅና ጨዋታ ተደስተው ይውላሉ፡፡

ዓመታዊ የመውሊድና የአረፋ በዓል ሲሆን እህል ያለው እህል ብር ያለው ብር ያዋጣል፡፡ ፍሪዳ ይገዛና ይታረዳል፡፡ የሌላቸው ድሆች ይመለመሉና ተሰብስበው ከታረደው ፍሪዳ ተቆርጦ ይሰጣቸዋል፡፡ ያለው ለሌለው ይሰጣል፡፡ "በዚህ ቀን ከባድ በዓል ስለሆን በኛ በመጣፋችን የበኩር ልጅህን እረድ" ይላል፡፡ ልጃገረዲቱ ምን አድርጌ ልውል ነኝ ስትል ልጅሽን አቅርቢው ልጅሽን እረጅ ይላታል ነብያችን፡፡ ከሌለኝማ ልጄን ላቅርብ እንጅ ምን ላድርግ ስትል ልጇን ትቶ ቀይ በግ ደከረላት፡፡ በዚህም የአረፋ በክር ልጅህን እረድ እየተባለ ይተረታል /ቃለ መጠይቅ፣ ተበጀ በየነ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡

በሌላ በኩል ኑርልኝ ኢሳ "በበዓል ቀናት ሁሉም ሰው ሳይከፋ ተደስቶ ያለው ለሌለው አካፍሎ በአንድነት ተከባብሮ፣ በሰላም ሀዘንና ደስታውን በመጋራት ይውላል" /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡

ሙስሊሞች ግንኙነት ከሚፈጥሩባቸው ጉዳዮች ሌላው የሆበራ ስራ ነው፡፡ "ስራችን አንተ ትብስ አንች ትብሽ ተባብለን እርስ በርስ በመረዳዳትና በመተጋገዝ በአጭር ጊዜ እናከናውናለን፡፡ የደከመውን ፣ለመስራት አቅም ያነሰውን ሰው ስራ ተባብረን እንሰራለን" /ቃለ መጠይቅ፣ ሰይድ መሳነር፣ ጥር 13/2006 ዓ.ም/፡፡ ሙስሊሞች በጋብቻም እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅር በማሳየት ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ፡፡

ስራው ከተጀመረ እስከ መጨረሻው አንለያይም፡፡ ስራ በማገዝ፣ እንግዳ በማስተናገድ፣ የጎደለ በመሙላት፣ እንጀራና ገንዘብ በማዋጣት እንሳተፋለን፡፡ አብረን እንበላለን እንጠጣለን፤ ደስታችን እንካፈላለን፡፡ ከቅርብም ከሩቅም ያለው ወገን ዘመድና አበልጅ ይጠራል፡፡ አብልተን አጠጥተን በደስታ ይሸኛሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ተገኘ አማን፣ ጥር 13/2006 ዓ.ም/፡፡

በጥቅሉ የእስልምና እምነት ገበሬዎች በስራ፣ በሀዘንም ይሁን በደስታ እጅና ጓንት ሆነው በመረዳዳት፣ በመተዛዘን የሚኖሩ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ሁለቱም የእምነት ተከታዮች እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት እንመልከታን፡፡

### 3.1.3. በኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች

የኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች በተለያዩ ጉዳዮች መስተጋብር አላቸው፡፡ ሁለቱም በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የተሳሰሩ ናቸው፡፡ መረጃ አቀባዩ ደሴ ውበት ሲገልፁት "በክበረ በዓል፣ በጋብቻ፣ በተዝካር፣ በስራ /ሆበራ፣ በለቅሶ፣ በአበልጅነት[2] ወዘተ እርስ በርስ እንገናኛለን:: ልዩነታችን ስጋ መብላት ላይ ብቻ ነው፡፡" /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡

እንዲሁም እንደ መረጃ አቀባዮች ተበጀ በየነና ደሴ ውበት መብራሪያ የኦርቶዶክስና የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች በተለያዩ ዝግጅቶች ይጠራራሉ፡፡ ለሙስሊሞች ለብቻ ከራሳቸው ቤተሠብ አንድ ወይም ሁለት ሴት በማምጣት ቡቡኝ የተባለ መጠጥ ያደርሳሉ፤ እንጀራ ይጋግራሉ፡፡ እንደሰዎቹ ብዛት ከደሮ ጀምሮ በግና ከብት እንኩ ራሳችሁ እወቁበት ተብሎ ይሰጣቸውና ራሳቸው አዘጋጅተው እርስ በርስ ይስተናገዳሉ፡፡ ባለቤቱን ለመርዳትም ለበግ መግዣ የሚሆን ብለው ብር ያዋጣሉ፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮችም እንዲሁ ከኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሴቶች ወሰደው ጠላና ምግብ እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ፡፡ ዋና ዋና ቀንድ ቀንድ ሰዎችን ጠርተው እንደ ብዛታቸው ከዶሮ እስከ ከብት ይሰጣቸውና ራሳቸው አርደው በራሳቸው ይስተናገዳሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡

በተለያዩ የስራ አይነቶችም በደቦ‌ያት ስራ ይሳተፋሉ፡፡ እርስ በርስ በመተጋገዝና በመረዳዳት ተባብረው ይሰራሉ፡፡ ሙስሊሞች ከኦርቶዶክስ ገበሬዎች ጋር ሆበራ ሲይዙ የስራ ቀናትን ለይተው በመጠቀም ነው፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ሰይድ መሳነር፣ ጥር 13/2006 ዓ.ም/፡፡

ሰይድ መሳነር መረጃውን የሰጡኝ ቤታቸው በመሄድ ሲሆን ሽማ እየሰሩ ነበር፡፡ ስለ ኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ማህበራዊ ግንኙነት ስጠይቃቸው ያላቸውን ግንኙነት ሲነግሩኝ ማስታወሻ ደብተርና መቅረፀ ድምፅ መጠቀም ስጀምር ስለ ግንኙነታቸው ምክንያት የተናገሩት መረጃ ስጋት ፈጠረባቸውና ለመደበቅ ሲሞክሩ የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት እንዲረጋጉ አደረኳቸው፡፡ እንዲህ ሲሉ ነበር የተናገሩት፡፡

---

2 እንደ መረጃ አቀባየ ተበጀ በየነ ጥር 12/2006/ ገለፃ አበልጅነት የሚመሰረተው ዝምድና ለመፍጠር፣ ወዳጅ ለመሆን ሲባል የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች የሙስሊሙን ልጅ ወሽላ ሲገረዝ በማቀፍ ነው፡፡ ልጁን ካቀፈው አባቱ ነው፡፡

በጣም ከባድ ናቸው የሚባሉትን በዓላት እነማሪያም፣ እነሚካኤልና ባለእግዚያአብሔርን አንሰራም፡፡ አክብረን እንውላለን፡፡ እሁድም እንደዚያው፡፡ በረዶ ሲጥልና አዝመራ ሲደበደብ የሚያመሃኙት በእኛ ነው፡፡ ቅዳሜ እንሰራለን፡፡ በእኛ እምነት እኛ ከምናከብራቸው በዓላት ውጭ ሌላውንም እንድናከብር አይፈቀድልንም፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 13/2006/፡፡

በሌላ በኩል ተበጀ በየነ መረጃውን የሰጡኝ ቤታቸው በመሄድ ሲሆን ሰይድ መሳነር የተባሉት ገበሬ ስለ ሁለቱም የእምነት ተከታይ ገበሬዎች ሲገልፁ ሊደብቁ የፈለጉትን መረጃ እንዲህ ሲሉ አረጋግጠውልኛል፡፡

የአገር ባህልን በተመለከተ ያለንን ግንኙነት በማጠናከር ተመሳስለን እንኖራለን፡፡ ከበድ ከበድ ያሉትን በዓላት እነማሪያም፣ እነሚካኤልና ባለእግዚያአብሔርንና እሁድን አንሠራም፡፡ አዝዕርቶች ላይ በረዶ ሲጥልና ሌሎች አደጋዎች ሲያጋጥሙ እናንተ ናችሁ በበዓሉ ሁሉ እየሰራችሁ የምታስጨፈጭፉን ይላሉ፡፡ እኛም ሀሳባቸውን ተቀብለን በእምነታችን ያልተፈቀደውን ስራ በመስራትና በመተግበር ተመሳስለንና ተከባብረን እንኖራለን፡፡ በእነዚህ ቀናት ንብረት በመከወን በስራ ቀን የታጨደውን በመሸከም፣ በመከመር፣ በስራ ቀን የተወቃውን በማፈስና መጫን ነው የምንውለው፡፡ በዚህም ከጐረቤቶቻችንና ከሀገር ጋር ተስማምተን በሰላምና በፍቅር እንኖራለን፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር12/2006/፡፡

በመሆኑም የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ከኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር በእምነታቸው የማይፈቀደውን ድርጊት ሁሉ ይፈፅማሉ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሁለቱም የእምነት ተከታዮች በክበረ በዓል፣ በጋብቻ፣ በተዝካር፣ በስራ /ሆበራ/፣ በለቅሶ፣ በክርስትና ወዘተ ጥብቅ ግንኙነት አላቸው፡፡ ስለ ገበሬዎች ማህበራዊ ግንኙነት ይህን ያህል ካልን ቀጥለን ድግሞ የዕለት ተዕለት ውሏቸውን እንመለከታለን፡፡

## 3.2. የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ ስንል ገበሬዎች ከጧት እስከ ማታ ዓመቱን ሙሉ ጊዜያቸውን እንዴት ያሳልፋታል፤ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበት ነው፡፡ የገበሬዎችን የዕለት ተዕለት ተግባርም በአዘቦት ቀን፣ በሰንበት ቀን /እሁድና ቅዳሜ/፣ ዓመታዊ ክብረ በዓላትና በመንግስት በዓላት ቀን በማለት ከፋፍለን ገበሬው እስከ ቤተሰቦቹ ምን ይሰራል የሚለውን

እንመለከታለን፡፡ ይህም የኦርቶዶክስና የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ ተብሎ ቀርቧል፡፡

### 3.2.1. የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች በአዘቦት ቀናት፣ የአጨዳ፣ ውቂያ፣ አረም፣ ጉልጓሎ፣ እርሻ ተግባራትና የመሳሰሉትን ያከናውናሉ፡፡ ገበሬው በጥዋት ተነስቶ ከብቶችን ፈትቶ ለከብቶች ሳር ከሰጠ በኋላ ወደ መስክ ስራው ይሰማራል፡፡ በተሰማራበት ስራም ከጥዋት እስከ ማታ ሲሰራ ይውላል፡፡ ሚስትም ሌሊት ስትፈጭ አድራ በጥዋት ተነስታ ወለል ጠርጋ ምግብና ቡና ታዘጋጃለች፡፡ በልተው ጠጥተው ባል ወደ መስክ ሲሄድ ልጆች ወደ ከብት፣ ወደ ቁጥቋጦና ሌሎች የአጨዳ፣ አረም፣ ሸክም ስራዎች ይሰማራሉ፡፡ ሚስት ሁሉንም ሸኝታ ወደ መስክ ትወጣለች፡፡ በአጨዳው ስታጭድ፣ ስትሰበስብ፣ ስትሸክም፣ በአህያ ስትጭን፣ አረም ስታርም፣ አራሙቻ ሰታወጣ፣ በጉልጓሎ ወገቧን አደግድጋ ሰትጐለጉል፣ ስርዶውን መንጥራ ስታራግፍ፣ በውቂያም ስትቆሰቁስ፣ በሮችን ስታሄድ ትውላለች ሲሉ ጎሌ ደርሶ ገልፀውልኛል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 08/2006 ዓ.ም/፡፡

> ሚስት ያላት ተግባርና ሃላፊነት ከወንዶች የበለጠ ነው፡፡ በአሁኑ ስዓት ሰፊውን የስራ ድርሻ እየሸፈነች ያለች እሷ ናት፡፡ ባሏ እርሻ ሲያርስ ጠላና ምግብ በመውሰድና ስራውን በማገዝ ትሳተፋለች፡፡ እንደ ወንድ የሚያርሱ ሴቶችም አሉ፡፡ ከጐረቤት እንኳን ስማቸውን መጥራት አልፈልግም እንጅ ከባላቸው በላይ የሚሰሩና የሚያርሱ ሴቶች አሉ፡፡ ለከብቶች ሳር አጭደው ተሸክመው ውርጭ፣ ዝናብ፣ ጭቃ ሳይፈሩ የሚመግቡ ናቸው፡፡ አንድ ጊዜም መስከረም ወራት ወደ ደባት ዙሪያ ለቅሶ ስሄድ ባሏ ቁጭ ብሎ ምሳ እየበላ እሷ ግባ ስትልና ስትተልመው አይቻለሁ፡፡ ልጅ ከማሳደግና ከቤት ስራ በተጨማሪ የግብርና ስራውን በእኩልነት ትሰራለች፡፡ እኔ ልጅ አላዳረስኩም ሚስቴ ግን እኩል ከእኔ ጋር ውጭ ውላ የቤቱንም ስራ ትሰራለች፡፡ የከብቶችን ሁኔታም ታውቃለችና እርሻ ውየ ስገባ በሮቹን አይታ ዛሬ በጥሩ ሁኔታ ውለዋል ሰውነታቸው አልደነገጠም ትለኛለች፡፡ በዚህ ሙያዋም ጠምዳ እንዳረሰች እቆጥረዋለሁ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ግዛት አሰፋ፣ ጥር 06/2006 ዓ.ም/፡፡

በሌላ በኩል ድረስ ግርማው "አብዛኛው ሴቶች በእርሻ ብቻ አይሳተፉም እንጅ በሌላው ሙያ ይበልጥ የሚሳተፉ እነሱ ናቸው፡፡ የማይሳተፉትም የበሬ እፉታ ስለሚያስፈራቸው ነው፡፡" /ቃለ መጠይቅ ፣ ጥር 12/2006/

የወረዳው ሴቶች ከቤት ውስጥ ስራ በተጨማሪ በመስክ የግብርና ስራ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ "ጥዋት ተነስቸ ምሳ አዘጋጃለሁ ከባለቤቴ ጋር ጥዋት የወጣሁ ልጅ

በጀርባዬ አዝዬ ማታ እመለሳለሁ፡፡ ሁሉንም ስራ አብረን ነው የምንሰራ፡፡ ተመልሰን እሱ ሲያርፍ እኔ እራት አዘጋጃለሁ ሌላም ስራ ሁሉ ስሰራ አመሻለሁ" /ቃለ መጠይቅ፣ አበባ እንየው፣ ጥር 09/2006/፡፡ እንዲሁም ብትወጣ ኪዴ "ከባለቤቴ ጋር እኩል ነው የምንሰራ እሱ ቢኖር ባይኖር ከስራው አልቀርም፡፡ የቤቱንም ስራ እሰራለሁ ጠንክረን ስለምንሰራ ቤታችን ሙሉ ነው አይቸግረንም" /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006ዓ.ም/፡፡

እኔም በመስክ ምልከታዬ ወቅት ሴቶች በግብርና ስራ ያላቸውን ተሳትፎ ተመልክቻለሁ፡፡ የቤቱን ስራ ሰርተው ምሳ አዘጋጅተው ይዘው በመምጣት አጨዳ ሲያጭዱ ፣ ሲሸከሙ፣ በአህያ ሲጭኑ፣ በውቂያ ሆበሬ ሲሉ፣ ሲቆሰቁሱ ውለው ተመልሰው የቤቱን ስራ ሲያከናውኑ አይቻለሁ፡፡

የመንግስት በዓላት በሚከበሩበት ቀን የገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ ምን ይመስላል የሚለውን አደራጀው ዱቤ ሲገልፁት "ገበሬዎች የመንግስት በዓል ሲሆን ፈረስ፣ በቅሎ ሸልመው፣ መሳሪያ ይዘው፣ በእልልታ፣ በሆታ፣ በዘፈን፣ በፋከራ፣ በሰልፍ፣ ባንዴራ ይዘው ጥሩምባ እየነፋ በመዞር የወረዳው ከተማ ዳባት ላይ በድምቀት ያከብራሉ፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 06/2006 ዓ.ም/፡፡

እንደ መረጃ አቀባዮቸ ድረስ ግርማውና ደሴ ውበት ማብራሪያ የመንግስት በዓላት በዓመት ሁለት ሶስት ጊዜ ይከበራሉ፡፡ በዚህ ቀን የመንግስት በዓል ነው ያላችሁን ተሞክሮ ለማሳየት ተዘጋጁ ይባላል፡፡ ፈረስ፣ በቅሎ፣ መሳሪያ ያለው ያዘጋጃል፡፡ የበዓሉ ዕለት በቀበሌ ተጠርንፎ፣ እርስ በርሰ ተቀሳቅሶ ይሄዳል፡፡ ፈረሱና በቅሎው ተሸልሞ ፊት ለፊት እየዞረ ሰውም ተሰልፎ በእልልታና በሆታ ያከብረዋል፡፡ ዝግጅቱ ሲያልቅ ከተመረቀ በኋላ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ልጆቻቸውን፣ ከብቶቻቸውንና አዝመራቸውን ይንከባከባሉ፣ ይቆጣጠራሉ፡፡ ልጆችም ከብቱን፣ አዝመራውን ሲጠብቁ፣ ሸክም ሲሸከሙ ይውላሉ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006 ዓ.ም/፡፡ ሌሎችም ምህረት ካሴና ጀጃው ደርሶ ይህን ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡

> በመንግስት በዓላት እኛ በፉከራና ቀረርቶ ፈረሳችን ሸልመን እንውላለን፡፡ ሴቶችም ወኔ ያላቸው ይሄዳሉ በአብዛኛው ግን ከቤት የሚውሉት ይበልጣሉ፡፡ በተለይ አሮጊቶች፡፡ ነገር ግን በዚህ ቀን በዓሉን የማያከበሩ ገበሬዎችም አሉ፡፡ እነዚህ ገበሬዎች ሚስታቸውን ወደ ገበያ በመላክ እነሱ አዝመራ ሲጠበቁ፣ ከብቶችና ልጆችን ሲቆጣጠሩ ይውላሉ፡፡ እኔም በአብዛኛው ሳልሳተፍ ነው ቀኑን የማሳልፈው ሲል ግዛት አሰፋ ገልፆልኛል፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ ጥር 06/2006 ዓ.ም/፡፡

ስለዚህ በመንግስት በዓላት ቀን አብዛኛው ገበሬ በፉከራና ቀረርቶ መሳሪያ ይዞ ፈረስና በቅሎ ሽልሞ ሲውል የማይሳተፉ ገበሬዎችም አሉ፡፡

በሰንበት ቀናት /እሁድ ቅዳሜ/ የገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ ሸክም በመሸከም፤ የከብቶች ሳር በማጨድ፣ ክምር በመከመር፣ ገበያ በመገብየት፣ ቤተክርስቲያን በመሳምና ሰንበቴ መጠጣት፣ ጥሪ ቤት በመሄድ፣ ከብቶችና አዝመራን በመጠበቅ፣ እንጨት በመፍለጥ፣ አራሙቻ በማውጣት፣ ገለባ በመከመር፣ በስራ ቀን የተወቃውን በማፈስ፣ በመጫን ነው፡፡ ቅዳሜ ቀን በገበያ፣ በመሸከም፣ በመከመር፣ አዝዕርትና ከብቶችን በመጠበቅ፣ ልብስ በማጠብ፣ እንጨት በመፍለጥ ይውላሉ፡፡ ባልም ሆነ ሚስት፣ ልጅ እነዚህን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ ሚስት ገበያ የምትሄድ ከሆነ ባል ሁሉንም ነገር ከውኖ ይቆያል፡፡ ባል ወደ ገበያ የሚሄድ ከሆነ ሚስቱ በጥዋት ተነስታ ወለል ጠርጋ ቁርስ አዘጋጅታ፣ ቡና ጠጥቶ ፣ጤፍ፣ ባቄላ፣ ምስር፣ አብሽ ወይም በግ ግልገል በመውሰድ ሸጦ ገበያ ያደርጋል፡፡ በዚህ ቀን አብዛኛው ገበሬዎች ባህላቸው ያደረጉትን የፀሀይ ማብረጃ የከተማ ጠላ ቀምሰው ይመለሳሉ፡፡ ሚስትም ከብቶችና ልጆችን ተቆጣጥራ ትውላለች፡፡ ባል የገዛውን እቃ ለሚስቱ ሰጥቶ ቡና ጠጥቶ ወደ ከብቶችና አዝመራው ብቅ ይላል በማለት ገልፀዋል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ አስናቀው ካሴ ፣ ጥር 05/2006/፡፡

> በሰንበት ቀን ስራ አይሰራም፡፡ ጥዋት ቤተክርስቲያን ይሳማል፡፡ ዝክር ካለ ይኬዳል፡፡ የማይሰራውም በሀይማኖት አባቶች ሰንበት የስጋችን መዳኛ የነፍሳችን መጠገኛ ነው፡፡ በዚህ ቀን መርፌ ቢሆን ማንሳት አይቻልም /አይፈቀድም/ ሲሉ ያስተምራሉ፡፡ ገበሬው ከቤተክርስቲያን መልስ የሰንበቴም ሆነ ሌላ ዝክር ጥሪ ካለው መሄድ፣ ከብቶችና ልጆችን በማቋጠር ይውላሉ፡፡ ሴቶችም የቤት ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡ ልጆችም ከብት ይጠብቃሉ፣ ለከብቱ ሳር ያጭዳሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ድረስ ግርማው፣ ጥር 13/2006/፡፡

ስለዚህ ገበሬዎች በሰንበት ቀን ንብረታቸውን ሲቆጣጠሩ ጥቃቅን የሆኑ ልብስ ማጠብ፣ ገለባ መከመርና ሌሎች ተግባራት ሲያከናውኑ አርፈው ይውላሉ፡፡

በዓመታዊ ክብረ በዓላት ገበሬዎች ያላቸውን የዕለት ተዕለት ውሎ ስንመለከትም ቤተክርቲያን መሳም፣ ከብትና አዝመራ በመጠበቅ፣ ጥሪ ቤት በመሄድ እንግዳ በማስተናገድ፤ ፍሪዳ በማረድ፣ በግ በማረድ ስራ ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ሴቶችም የቤቱን ስራ ያከናውናሉ፡፡ ዓመታዊ የእመቤታችን ወይም ሌሎች በዓላት ሲሆኑ ጥዋት ቤተክርስቲያን ስመው ተመልሰው የተጠራውን እንግዳ ለማስተናገድ አጐዛ አንጥፈው

ለምለም ሳር /ጨፌ/ ይጐዘጉዛሉ፡፡ እንግዶች ሲመጡ በማቶት ኮረፌ ጠላ ይወርድና በዋንጫ ይቀዳል፡፡ ሚስት ምሳ ታቀርባለች ይበላል፡፡ ከዚያ በኋላ ኮረፌውን ትተው ጥሩ ጠላ ይወርድና በብርሌና በብርጭቆ ይቀዳል፡፡ እንግዶች ይስተናገዳሉ፡፡ መሸት ሲል በሞቅታ ዘፈን ይጀመራል፡፡ ከዚያም ሲዘፍኑ ያድራሉ፡፡ በዓመታዊ ክብረ በዓላት እርስ በርስ በመጠራራት በዚህ ሁኔታ ቀኑን ያሳልፉታል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ግዛት አሰፋ፣ ጥር 01/2006/፡፡

ይህንም በመስክ ቆይታዬ በቃርሃ ቀበሌ ጉራሬ ሚካኤል ኅዳር ጥር 12 ቀን የሚከበረው በዓል ተሳታፊ በመሆን፣ ታህሳስ 29 ቀን የአካባቢው ገበሬዎች ፍሪዳ አርደው ሲከፋፈሉና ሌሎችም ተግባራት ተመልክቻለሁ፡፡

ዓመታዊ የጥምቀት በዓል ሲሆንም አብዛኛው ገበሬዎች ወደ ጥምቀት የሚሄዱና ታቦቱን በመከብከብ ሲጨፍሩ የሚውሉ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ከብትና አዝመራ ሲጠብቁ ከቤታቸው ይውላሉ፡፡ ልጆች አዲስ ልብስ ለብሰው፣ ሎሚና ከረሜላ ይዘው በመሄድ ሲጨፍሩ ውለው ይመጣሉ፡፡ ሴቶችም ትንንሽ ልጆችን ይዘው ተኩለው፣ ተቀብተው ጃንጥላቸውን ይዘው ዳር ላይ በመቆም "በወት ያግባሽ በወት" እያሉ በማጨብጨብ ታቦቱን ሲያጅቡ ውለው ይመጣሉ፡፡ ሲመለሱ ልጆች ወደ ከብቶች ጥበቃ ይሄዳሉ ወንዶች ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ ሚስትም ቡና ታፈላለች፡፡ የቤት ስራዋን ትሰራለች /ቃለ መጠይቅ፣ ጀጃው ደርሶ፣ ጥር 10/2006/፡፡

"ጥምቀት ሲሆን አዲስ ልብስ ለብሸ ተኳኩዬና ተቀባብቸ ልጆቸን ይዠ ስናጨበጭብ፣ ስንዘፍን ውለን እንመለሳለን፡፡ ባለቤቴ ብዙ ጊዜ ጥዋት ፀበል ተረጭቶ መጥቶ ቤትና ከብት ሲጠብቅ ይውላል" (ቃለ መጠይቅ፣ ቢምር እንየው፣ ጥር 12/2006)፡፡ በመስክ ቆይታዬ ጥር 11 እና 12 የጥምቀት በዓል በመሳተፍ እንደ ተመለከትኩት አብዛኛው ገበሬ፣ ሴቶችና ልጆች ጥምቀቱን ሲያከብር የሚቀሩና ቤት ሲጠብቁ የሚውሉ ገበሬዎችም አሉ፡፡

በጥቅሉ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች ሴትም ሆነች ወንድ የተለያዩ ጉዳዮችን በማከናወን ይውላሉ፡፡ በውሏቸው አብዛኛውን ስራ የሚያከናውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ በመንግስት በዓላት ቀን የሚሳተፉ እንዳሉ ሁሉ የሚቀሩም አሉ፡፡

### 3.2.2. የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች

የእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎችን የዕለት ተዕለት ውሎ ስንመለከትም በአዘቦት ቀናት የአጨዳ፣ አረም፣ ውቂያ፣ እርሻ፣ ጉልጉሎና ሌሎች ስራዎችን

ያከናውናሉ፡፡ በእነሱ እምነት የማይሠራው ጁማ ቀን ሲሆን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከሚያከብሯቸው ከባድ በዓል ናቸው የሚባሉትን እሁድ፣ በየወሩ ቅዱስ ሚካኤል፣ ማሪያምና ባለእግዚያብሔርን ያከብራሉ፡፡ እነዚህን በዓላት የሚያከብሩትም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች በረዶ አዝመራቸውን ሲጨፈጭፈው እናንተ በዓል ስለማታከብሩ ነው ሲሉ ስለሚያማርሩ ከአገር ባህል ሳይወጡ ተቻችለው ለመኖር ነው፡፡ ከእነዚህ ውጭ ያሉ ቀናትን ይሰራሉ፡፡ በስራ ቀናትም ጥዋት ተነስተው ስግደት ይሰግዳሉ፡፡ ከዚያም ቁርስ በልተው፣ ቡና ጠጥተው ወደ መስክ ስራ ይሄዳሉ፡፡ በመስክ ስራው ላይ እያሉም የስግደት ሰዓት ሲደርስ እዚያው ላይ ይሰግዳሉ፡፡ ልጆችንና ሚስታቸውን ወደ ሰራ ያሰማራሉ፡፡ ልጆች ቤተሰብ በመርዳት፣ ከብት በመጠበቅ ይረዳሉ፡፡ ሚስትም ከባሏ እኩል ከቤቱ ስራ አልፎ የውጭ የመስከ ስራውን ታከናውናለች፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ተገኝ አማን፣ ጥር 13/2006/፡፡

> በጁማ ቀን አንሰራም፡፡ በዚህ ቀን ውሏችን ጥዋት፣ ሰባት ሰዓት፣ 11 ሰዓት፣ ማታ ደግሞ "መቅሪብ" ይባላል እንሰግዳለን፡፡ ሙሉ ቀን ስግደት ነው፡፡ በዚህ ቀን ራስ ክብር ነው፡፡ ቀኑ "ውጥባ" ይባላል፡፡ ይህ ማለት የተለየች የመሰብሰቢያ ቀን ናት ማለት ነው፡፡ ተከብሮ ሲውል "በረካ አለው" ይባላል፡፡ ማለትም ሌላው የተሰራው በረከት፣ ረድኤት አለው ማለት ነው፡፡ ቀኑን ሙሉ መስጊድ ቁራን ስንማር፣ ስንወያይ፣ እንውላለን፡፡ ሰባት ሰዓት ምሳ በልተን ተመልሰን እንሄዳለን፡፡ በዚህ ቀን ልጆች ከብት ሲጠብቁ፣ ሴቶች ገበያ ያደርጋሉ፡፡ ሲመለሱ ይሰግዳሉ፡፡/ቃለ መጠይቅ፣ ተበጀ በየነ፣ ጥር 12/2006/፡፡

በሌላ በኩል ኑርልኝ ኢሳ ጁማ አዝመራ የሚሻር ከሆነና በሬ የሌለው የቸገረው ገበሬ በሬ ለምኖ የሚጠቀም በአብዛኛው በዚህ ቀን ነው፡፡ ከችግር የተነሳ አንዳንድ ሰዎች ይሰራሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2006/፡፡

በእስልምና እምነት ተከታዮች ዓመታዊ ክብረ በዓላት ሲሆኑ ስለተለያዩ ጉዳዮች ሲወያዩ፣ የተራበ ሲያበሉ፣ የተጠማ ሲያጠጡ፣ ለድሆች፣ ሲረዱ፣ በጋራ በመተዛዘን ይውላሉ፡፡ ድሆችን መልምለው በራሳቸው መዋጮ አድርገው ከገቡት ፍሪዳ በማካፈል፣ ሲሰግዱ፣ ቁራን ሲማሩ ይውላሉ፡፡ ልጆችም ንብረትን አዝመራ ይቆጣጠራሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ተበጀ በየነና ኑርልኝ ኢሳ፣ ጥር 12/2006/፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱም የእምነት ተከታይ ገበሬዎች በተለያዩ ጉዳዮች እርስ በርስ እንደ ሰንሰለት የተጠላለፉ ናቸው፡፡ ሀዘንም ሆነ ደስታቸውን ይካፈላሉ፡፡ በሰላምና በፍቅር ተከባብረውና ተቻችለው ይኖራሉ፡፡ ሁለቱም የእምነት ተከታዮች እምነታቸው

በሚፈቅደው መሰረት ግንኙነት አላቸው፡፡ የዕለት ተዕለት ውሏቸውም እንደየእምነታቸው የተወሰነ ነው፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች በተለያዩ መልኩ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ከእምነታቸው አልፎ ያሉ በዓላትን በማክበር ተሳስበው ይኖራሉ፡፡

## 4. የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም አደራረስ አከዋወንና ተስተላልፎ

በዚህ ክፍል የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም አደራረስ፣ የደረሱትንም የሚከውኑበት ስልት (አፈፃፀም) እና ከትውልድ ትውልድ የሚያሸጋግሩበትን ዘዴ ወይም ተስተላልፎ በመግለፅ ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡

### 4.1. የቃል ግጥም አደራረስ

ዋና ትኩረቴ ወደ ሆነው የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም አደራረስ ስመለስም በምዕራፍ ሶስት ከተብራራው የቃል ግጥም አደራረስ ስልት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን በቃል አጥንቶ በመሸምደድ፣ ከክዋኔ በፊት ከሰው የሰሙትን በማስታወስና በክዋኔው ላይ እዚያው በመፍጠር ይከውናሉ፡፡ እነዚህን አደራረስ ስልቶች ተከትለውም በርካታ ቃል ግጥሞችን ይገጥማሉ፡፡ ገበሬዎች በሸምደዳ ጊዜ በተለያዬ ከዋኝ ፣ጊዜና ቦታ እንዲሁም በተለያየዬ ከዋኝ ፣በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ከእዚያው ላይ በመስማት ሙሉ በሙሉ ሸምድደው የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ሠፊ ነው፡፡ እኔም በመስክ ቆይታዬ በተለያዩ የክዋኔ ቦታዎች፣ ከዋኞችና ጊዜ የሰማኋቸው ቃል ግጥሞች ከተሰበሰበው ቃል ግጥም አብዛኞቹ በሽምደዳ የተገኙ ናቸው፡፡ ግጥሙንም ከአውዱ ለማስማማት የራሳቸውን ፈጠራ ተጠቅመው ማሻሻያ በማድረግ መልሰው ይገጥሙታል፡፡

የወረዳው ገበሬዎች እዚያው ላይ አውድን መሰረት በማድረግ የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝና የይዘት ለውጥ በመፍጠር የታዳሚውን ፍላጐት መሠረት ያደረገ ግጥም ይፈጥራሉ፡፡ እንዲሁም አንዱ አንዱን በማስገጠምና ራሱም በመግጠም የራሱንና የቅርብ ጓደኞቹን ስም፣ ሙያ፣ አገር፣ ጀግንነት እያነሳ ሲገጥም የሌላውን ስሜት ይነካል፡፡ በዚህ ግጥም ስሜቱ የተነካ ስሙ ያልተጠራ፣ ጀግንነቱ ያልተወሳ ገበሬ ድንገት ተነሳስቶ በፉክክር ስሜት መግጠም ይጀምራል፡፡ ይህንም በመስክ ቆይታዬ የተመለከትኩ ሲሆን ለአብነትም ቀጣዩቹን ቃል ግጥሞች እንመልከት፡፡

217 [3]:- አረ ደኑ አረ በለው/2 /ከነብርቱ ጋራ ከነ አባባው ጋራ

አብረው ቢሠደዱ

ከየማታው ጋራ ከነሲሴ ጋር አብረው ቢሰደዱ /2/

ከግብርና ጋራ አብረው ቢሰደዱ

ቢያገኝም ያበላል ቢያጣም ያዝናል ሆዱ /2/

/የማታው አስናቀው፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

ይህን ቃል ግጥም ጋሎ የተባለ ቦታ ጤፍ አጨዳ ላይ ግዛት አሰፋ የተባሉት ገበሬ ያዜሙት ሲሆን ግዛት በቃል ግጥሙ የሚያውቋቸውን አበባው፣ ብርቱ፣ የማታውና ሲሳይን በማንሳት አቀንቅነዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ስሙ ያልተነሳው አበራ ብርሃኑ በስሜት የሚያውቋቸውንና ስማቸው ያልተነሳውን የሽበርና ክንዱ የተባሉትን ገበሬዎች በማሞገስ እንዲህ ሲሉ ቀጣዩን ቃል ግጥም አቀንቅነዋል፡፡

218. ኧረ በለው /2/ እነ ወጣት እነ ሽበር እነ ክንዱን ይኸ

እንኳን ጤፍ አጨዳ በበላሁ እጅ ይገፉ

/አበራ ብርሃኑ፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 1ሀ/

በመቀጠል የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም ለመዳ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

የተለያዩ በርካታ ቃል ግጥሞችን በአጨዳ፣ በአረም፣ በጉልጓሎ፣ በአውድማ፣ በእርሻ፣ በሰርግና ከብት ጥበቃ ላይ ሲፎክሩ፣ ሲያቅራሩ፣ ሲዘፍኑና በሆታ መልክ ቤተሰቦቻችን፣ ጓደኞቻችን ሲከውኑ እንሰማለን፡፡ የሰማነውንም በመሸምደድ ከብት ስንጠብቅ፣ ሳር ስናጭድ፣ ስናርም፣ ስንጎለጉል፣ ስናርስና ስንወቃ መልሰን እንገጥመዋለን፡፡ ሲጠፉንም የራሳችን ፈጠራ እንጨምርበታለን፡፡ / ቃለ መጠይቅ፣ ድረስ ግርማው፣ ጥር 12/2006፣ ካሴት ቁጥር 1ሀ/

በሌላ በኩል አበባ እንየው "በደበያት ከሰው ስራ ስንሄድና ከራሳችንም ስራ ከቤተሠቦቻችን እንሰማና የራሳችን ጨምረን እንገጥማለን፡፡" /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 09/2006/፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየን ገበሬዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው ቃል ግጥሞችን በመስማት፣ በማስታወስና በመሸምደድ እንደሚገጥሙ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚገጥሙት በሽምደዳ ነው፡፡

[3] የተሰጠው ቁጥር በአባሪ ሶስት መስክ ላይ ለተሰበሰቡት ግጥሞች የተሰጠ ተራ ቁጥር ነው፡፡

39፡- በሬ በሬ ብየ የምወዘወዘው
እንጀራ አይበላም አምላክ ካላዘዘው
1፡- ወንድም የሌለው ሰው የወንድም አባሪ
ከትክሻው ቀረ የዱላው ስባሪ
/የሽበር ካሣው፣ ጥር 08/2006፣ ካሴት ቀጥር 4ሀ/

ከላይ በተራ ቁጥር 54 እና 21 የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች በአውድማ አውድ ላይ በተመሳሳይና በተለያዩ ጊዜ፣ በተለያዩ ከዋኝ፣ ሲቀነቀኑ ሰምቻለሁ፡፡ በዳራ ቀበሌ የሽበር ያቀነቀኗቸውን በቃርሃና ጭላ ቀበሌዎች ያለ ምንም ለውጥ አቀንቅነዋቸዋል፡፡ ከአንድ አውድ ላይ ያሉ በርካታ ገበሬዎችም እዚያው ላይ በመሸምደድ አዚመዋል፡፡ በምልከታዬም ዳራ ቀበሌ ጤፍ ውቂያ ላይ የሽበር የገጠሙትን ወዲያውኑ ግዛት፣ ዋሴና አደራጀው መልሰው ሲገጥሙት ሰምቻለሁ፡፡ እነዚህን ቃል ግጥሞች በቃርሃ ቀበሌ ተካ የማታውና አዳነ የማታው አዚመዋቸዋል፡፡ በተለይም ተራ ቁጥር 54 በሁሉም ቦታ ሲዜም አሰማለሁ፡፡ “እነዚህ ቃል ግጥሞች ጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ሲባሉ የነበሩ ናቸው፡፡” /ቃለ መጠይቅ፣ ግዛት አሰፋ፣ ጥር 06/2006/፡፡ ከዚህም ቃል ግጥም ከቦታ ቦታ ብቻ ሳይሆን ከዘመን ዘመን የሚሸጋገረው በሽምደዳ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህን ጉዳይ የሚያሳዩ ተጨማሪ ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ በተራ ቁጥር 3፣ 10 ፣14፣ 27፣ 30፣ 41፣ 48፣ 71፣ 88፣ 89፣ 97፣ 98፣ 179፣ 198 ወዘተ ይመልከቱ፡፡

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥምን በመሸምደድ እንደሚያቀርቡ ሁሉ የተለያዩ ለውጦችን በማድረግም ያቀርባሉ፡፡ ለውጡም የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝ፣ የይዘት ለውጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ሀሳብ ግዛት አሠፋ ሲገልፁት፡-

> አብዛኛውን ጊዜ የምንገጥመው በሽምደዳና ከልብ ወለድ አንጣር ነው፡፡ ከአያት ቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላችን ስለሆነ የእነሱን እግር ይዘን በመስማትና ከቤተሠብም ሆነ ከሰው ደቢያት ስንሄድ የሰማነውን መልሰን እንለዋለን፡፡ አንዳንድ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ፣ ከሀዘንና ከደስታ ስሜት የተነሳ ከራሳችን ፈጥረን እንገጥማለን፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 08/ 2006፣ ካሴት ቁጥር 5ሀ/

እንዲሁም ቄስ ቢምረው ጥላዬ “በተለያየ ስራ ስንሳተፍ በመስማትና በመሸምደድ እንደ ትምህርቱ እንቀስመዋለን፡፡ ራሳችንም እንፈጥራለን፡፡ ከሌሎች የስራ አይነቶች ይልቅ የሆበሬ ግጥም በጣም ይያዛል “በማለት ገልፀዋል /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር

06/2006/፡፡ በሌላ በኩል አዳነ የማታው "ግጥሞችን ሰምተን እንሽመድዳለን፡፡ የሚሽመደድ ግን ግጥሙ ብቻ አይደለም የዜማ አወራረዱ፣ አሰባበሩ፣ የድምፅ ቅላፄው ጭምር ነው" ይላሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 13/2006/፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን በመስማት ሸምድደው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አጋሚዎች እዚያው ላይ በመፍጠርም ይከውናሉ፡፡ የሚሸመድዱት ግጥሙን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የግጥሙን አወራረድ፤ አሰባበርና ዜማ ነው፡፡ አንዱ ያለውን ሌላኛውም የእሱን አውድ መሰረት አድርጐ በመፍጠር የተለያዩ የቃል፣ የሀረግ፣ የስንኝ ለውጥ በማድረግ የይዘት ለውጥ ሳያደርጉ እንደሚከውኑ በመስክ ቆይታዬ በቃርሃ፣ ዳራ፣ ጭላ፣ አብጠራና ተንሰዬ ማሪያም ቀበሌዎች ባደረኩት ምልከታ አስተውያለሁ፡፡ ለአብነት ቀጣዩቹን ቃል ግጥሞች እንመልከት፡-

501፡- ማረስ ነው እንጅ እጅ እስኪቆስል

ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል

/ቃለ መጠይቅ፤ ሰምሙ ነጋሽ፣ ጥር 07/2006/

ይህ ቃል ግጥም ተንሰዬ ማሪያም ቀበሌ ስምሙ ነጋሽ እርሻ ሲያርሱ ያዜሙት ነው፡፡ ይህንኑ ቃል ግጥም አብጠራ ቀበሌ አስናቀው ካሴ የቃል ለውጥ ብቻ በማድረግ ርዕሰ ጉዳዩን ሳይቀይሩ እንዲህ ሲሉ አዚመውልኛል፡፡

502፡-ማረስ ነው እንጅ ሽንጥ እስኪቆስል

ምንድን ነው ስርቆት ውሻ ይመስል

/ቃለ መጠይቅ፣ አስናቀው ካሴ፣ ጥር 05/2006/

እነዚህን ሁለት መንቶ ቃል ግጥሞች ስንመለከት የቃል ለውጥ እናያለን፡፡ በቃል ግጥማቸው "እጅ" ና "ሽንጥ" የሚሉትን ሁለት የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች የሚገልፁ ቃላት ተመስርተው ማረስ የተለካው እጅና ሽንጥ እስኪቆስል በመስራት ነው፡፡ በመሆኑም በብርታትና በጥንካሬ ችግርን፣ ህመምን ፣ስቃይን ተቋቁሞ ማረስ እንደሚያስፈልግ "ማረስ ነው እንጅ እጅ እስኪቆስል" እና "ማረስ ነው እንጅ ሽንጥ እስኪቆስል" በማለት የቃላት ለውጥ በማድረግ ተመሳሳይ ሀሳብ አንስተዋል፡፡ "ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል" በማለት የስርቆትን አላስፈላጊነት፣ መጥፎነት በተግሳፅ ይመክራሉ፡፡

40. አንች የእናቴ ልጅ ነይ እንሂድ ትግሬ

አንች ወጠ ሰሪ እኔ ወንዝ አሻግሬ

/ተካ የማታው፣ ጥር 13/2006 /

ይህን ቃል ግጥም ተካ የማታው ቃርሃ ቀበሌ አብሽ ሲወቁ ያዜሙት ሲሆን የሃረግ ለውጥ በማድረግ ይዘቱን ሳይቀይሩ ምህረት ካሴ በዳራ ቀበሌ እንዲህ ሲሉ ሲያዜሙት ሰምቻለሁ፡፡

41. አንች የእናቴ ልጅ ነይ እንሂድ ትግሬ

አንች ወጠ ሰሪ እኔ ጋሻ ጃግሬ

/ ምህረት ካሴ፣ ጥር 07/2006 ዓ.ም/

በቃል ግጥሙ ወንዝ አሻግሬና ጋሻ ጃግሬ የሚሉትን ሁለት የተለያዩ ሃረጋት በመጠቀም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ቃል ግጥም አቀንቅነዋል፡፡ በቃል ግጥሙ "አንች የእናቴ ልጅ ነይ እንሂድ ትግሬ" በሚለው ስንኝ ከአገራችን ወጥተን ሰርተን እንብላ ሲሉ ይመክራሉ፡፡ "አንች ወጠ ሰሪ እኔ ወንዝ አሻግሬ" እና "አንች ወጠ ሰሪ እኔ ጋሻ ጃግሬ" በሚሉት ስንኞች ከሄዱ ወዲያ የሚሰሩት ወንዝ ማሻገርና ጋሻ ጃግሬ ሆኖ መስራት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ገበሬዎች ለራሳቸው በሚመቻቸው መንገድ በመድረስ እንደሚያቀርቡ ነው፡፡

በአጠቃላይ ገበሬዎች ከሌላ ሰው የሰሙትን ቃል ግጥም ከነዜማ አወራረዱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለውጥ በማድረግና በመሸምደድ፣ የራሳቸውን አዳዲስ ቃል በመጠቀም የክዋኔውን ድባብ መሰረት አድርገው ከአውዱ ጋር ለማስማማት ጥረት እንደሚያደርጉ ያመለክታል፡፡ በመቀጠልም ደረሳ የሚካሄድበትን የጥናቱ መቀንበቢያ ክዋኔን እንመለከታለን፡፡

## 4.2. የቃል ግጥም ክዋኔ

በመስክ ቆይታዬ ባደረኩት ምልከታ ገበሬዎች ቃል ግጥም የሚከውኑት ከምንም ተነስተው አይደለም፡፡ ለመግጠም አነሳሽ ምክንያቶችን ይፈልጋሉ፡፡ ይገጥሙ ዘንድ ሌላ አነሳሽ አካል ጃሎ በል የሚል፣ የሚጠጡት ጠላና የራሳቸውም ለመግጠም በስራው አጋጣሚ መፈንዳት ያለበት አንዳች የውስጥ ስሜት መኖር እንዳለበት ተመልክቻለሁ፡፡ ገበሬዎች የሚገጥሙት እንዲገጥሙ ሲጠየቁ፣ ጃሎ በል ላስገጥምህ ሲባሉ፣ አስገጥሙኝ በማለት፣ ተቀበል ሲባሉ፡፡ አልፎ አልፎም በራሳቸው ወኔያቸው

ሲቀሰቀስና ጠላ ከጠጡ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ ጃሎ ብሎ ሲፎክር የመጀመሪያውን ስንኝ ሲገጥም ሌሎች እንዲያበል፣ ተውተው፣ እልል እያሉ ሲያበረታቱ ይቆዩና የመጨረሻውን ስንኝ ሲገጥም በጋራ በአንድ ድምፅ ይደፉና አሆ፣ ያዝ በለው፣ እም እም፣ እያሉ በፉክክር ያጭዳሉ፡፡ ከላይ ተነስተው አጨዳውን ዳር ካደረሱ በኋላ ወደ መነሻቸው ሲመለሱ አንድ ሰው አቀንቃኝ ሌሎች ተቀባይ በመሆን በቡድን ቆመው ይጨፍራሉ፡፡ እየጨፈሩም ከተነሱበት ቦታ ይደርሱና ተቀምጠው አንዱ በማቀንቀን ሲጨፍሩ ቆይተው ጃሎ ማለት ይጀምራሉ፡፡ እየተቀባበሉ በመፎከር ያጭዳሉ፡፡

የገበሬዎች የስራ ቃል ግጥም የራሱ የሆነ የአጀማመር ስርዓት አለው፡፡ ስርዓቱም ከስራ ስራ ይለያያል፡፡ "ገበሬዎች በእርሻ፣ በአረምና በጉልጉሓሎ በቀረርቶና በፉከራ ሲከወኑ፣ በአውድማ ላይ ደግሞ በማንጐራጐር፣ በማዜም እንደሚከውኑ ጎሌ ደርሶ ገልጸውልኛል" /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 05/2006/፡፡

ገበሬዎች የአጨዳ ቃል ግጥሞችን ሲከውኑ ከቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ከሆታ ወደ ዘፈን /እስክስታ/ ተመልሰውም ወደ ቀረርቶና ፉከራ እንደሚሸጋገሩም በነበረኝ የመስክ ቆይታዬ አጨዳ አውድ ላይ ተመልክቻለሁ፡፡ መስክ ላይ እንደ ተመለከትኩት የአጨዳ ቃል ግጥሞችን ብንመለከት ገበሬዎች ከስድስት ሰዓት በፊትና በኋላ የሚከወኑት ግጥም አንድ አይደለም፡፡ ተነሳሽነታቸው ይለያያል፡፡ ከስድስት ሰዓት በፊት ተሰባስበው ሲያጭዱ በሌላ ቀስቃሽ አካል በል ተብለው፣ ተለምነው፣ በሌላ አስገጣሚ ተነግሯቸውና አልፎ አልፎም መግለፅ የሚፈልጉት ጉዳይ ካለ በራሳቸው ተነሳሽነት ይገጥማሉ፡፡ ስራውም የሚጠበቀውን ያህል አልተፋጠነም፡፡ ነገር ግን ከምሳ ሰዓት በኋላ ጠላ ጠጥተው ሞቅ ሲላቸው ያለማንም ቀስቃሽ አካል እርስ በርስ ተደራርበው ይፎክራሉ፣ ያቅራራሉ፡፡ ያንጐራጉራሉ፡፡ ሰራውንም በስሜት በተቀላጠፈ ሁኔታ ሲያከናውኑ ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ለቃል ግጥሞች መገጠም፣ መከወን ለገበሬዎች መነቃቃትም ሆነ ስራው መቀላጠፍ ጠላ መጠጣት ያለውን አስተዋፅኦ ነው፡፡ ከዚህም ገበሬዎች ውሃ ቢቀርብላቸው ተነቃቅተው እንደ ማይንቀሳቀሱና ስራውም እንደማይፋጠን እንረዳለን፡፡ ጠላ ምን ያህል ለስራው መፋጠን አስፈላጊ እንደሆነም የማታው አስናቀው እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡፡

305፡-ጠላ የለም እንጅ ጠላማ ቢኖር
ይህ አጨዳ ተርፎ አያድርም ነበር
/ ጥር፣ 06/2006/

በተለይ አስር ሰዓት ላይ ቀሪውን ጠላ እረፍት አድርገው ከጠጡ በኋላ ያለው ምሽት እጅ ለእጅ የሚቆራረጡበት ጊዜ ነው፡፡ እርስ በርስ አይተያዩም፡፡ በጥድፊያ እየዘለሉ፣ እም እም እያሉ፣ ስራውን ያራውጡታል፤ በልልታና በሆታ ይደምቃል፡፡ ክዋኔውም ከአውድ አውድ ይለያያል፡፡ የአውድማን አውድ ስንመለከት መግጠም የሚጀምሩት በል ተብለው ተጠይቀው፣ ወይም ጠላ እስኪጠጡ ድረስ ጠብቀው አይደለም፡፡ ስራ ከጀመሩበት ሰዓት አንስተው በራሳቸው ተነሳሽነት ይገጥማሉ፡፡ የሚገጥሙበትን ምክንያትም መረጃ አቀባዬ ቄስ ቢምረው ጥላዬ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡-

> አንድ ገበሬ ልጁን ሲድር ካልተፈከረለት፣ ካልተጨፈረለት፣ ካልተንጨበጨበ አይደምቅም፡፡ ዳሱ እንደ ዳስነት አይቆጠርም፡፡ ዳሱ ዳስ የሚሆነው ሲጨፈረ፣ ሲፎከር ና በጭብጨባ ነው፡፡ ገበሬ ደግሞ ሆበሬ ካላለ፣ ካላንጐራጐረ በዙሪያው መንሽ ይዞ የሚቆሰቁሰው ሰራተኛም ሆነ በሬው ፍዝ ሆነው አይንቀሳቀሱም፡፡ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ አያከናውኑም፡፡ ጤፍም ይሁን ገብስ የሚወቃው ባህልና የአባት ሰለሆነ ሲፎክር፣ ሲንጐረጎር፣ ዜማ ሲወርድ በሬውም ገበሬውም በሞራል ይንቀሳቀሳል፡፡ ስራውን በማፋጠን ሁለት ቀን የሚያውለው በአንድ ቀን ተከውኖ ተግባራዊ ምርት ይመረታል፣ ለምግብነት ይውላል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 06/2006 /፡፡

በሌላ በኩል አታከልት ዳምጤ “በሬ ሆበሬ ካልተባለለት አይዞርም፣ ደንቆሮ ማለት ነው፡፡ ቢደበድቡትም አይሰማም አይሄድም፡፡ ሆበሬ ሲባልለት ነው በራሱ የሚሽከረከረው የሚሰራው፡፡” /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 09/2006፣ ካሴት ቁጥር 1ሀ/

ከላይ እንደተገለፀው ቃል ግጥም ለመግጠም ዋናውና ትልቁ አነሳሽ ምክንያት ጠላ ነው፡፡ ጠላ ከሌለ ምንም እንኳን ከአውድ አውድ ቢለያይም የመገጠም እድሉ ጠባብ ነው፡፡ “ጠላ ካልጠጣን ክንዳችን ይፈዛል፤ ተነቃቅትን አንሰራም፤ ሞራላችን የሚቀሰቀሰውና ስራው የሚፋጠነው ስንጠጣ ነው” /ቃለ መጠይቅ፣ የማታው አስናቀው፣ ጥር 06/2006/፡፡ ይህም የሚሆነው ገበሬዎች ሰራተኛውም ሆነ በሬው የሚንቀሳቀሱት በዜማው አማካይነት እንደሆነ ካላቸው እምነት የተነሳ ነው፡፡

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን የሚከውኑት ከላይ በምዕራፍ ሶስት የቃል ግጥም ክዋኔ እንደተብራራው በሶስት አይነት መንገድ በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን ነው፡፡ እነዚህንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.1. በተናጠል የሚከወኑ ቃል ግጥሞች

በተናጠል የሚከወኑት ቃል ግጥሞች አንድ ገበሬ በግሉ ወይም በቡድን ክዋኔ ብቻውን የሚያዜማቸውን ግጥሞች ይመለከታል፡፡ ይህንም ወጣት አደራጀው ዱቤ ሲገልፀው "ግጥሞችን በግል የምናንጐራጉረው በተለያዩ በርካታ አጋጣሚዎች በእርሻ፣ አረም፣ አጨዳ፣ ውቂያና ጉልጓሎ ብቻችን ስንሰራና በቡድን ስንሰራም ለብቻችን አንድ አንድ እየሆን እንዘፍናለን፣ እናንጐራጉራለን" (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 13/2006)፡፡ እኔም በመስክ ምልከታዬ ለብቻቸው በተለያዩ አጋጣሚ እንደሚያንጐራጉሩ ለማየት ችያለሁ፡፡ ለአብነት የሽበር ካሳውና አድን ዱቤ የገጠሟቸውን ቃል ግጥሞች እንመልከት፡፡

42፡- በሬው ዙርልኝ በሬው ዙርልኝ
አዟሪም የለኝ በርባሪም የለኝ
አንተው ቀልስልኝ አንተው ዙርልኝ
/አድን ዱቤ፣ ጥር 08/2006/

አድን ዱቤ ዳራ ቀበሌ ከቤታቸው አጠገብ ጤፍ እየወቁ አገኘኋቸው፡፡ ብቻቸውን ነበር ሲወቁ ያገኘኋቸውና ለምን ብቻዎትን ይሰራሉ ረዳት የለዎትም ብዬ ስላቸው ልጆች ትምህርት ቤት ሂደው እስኪመለሱ ነው አሉኝ፡፡ ከዚያም ልጆች ከትምህርት ቤት ተመልሰው አገዙዋቸው፡፡ እናም ይህንና ሌሎችም መሰል ቃል ግጥሞች ብቻየን ነኝ እረዳት የለኝም ሲሉ አንጎራጉረዋል፡፡

149፡- አረ በለው /2/የሰው አገር ውሃ ብጠጣው መረረኝ
ኧረ አገሬ ጭላ መጣሁ ተቀበለኝ
/የሽበር ካሳው ፣ ጥር 08/2006፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

የሽበር ካሳው አገራቸው ጭላ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜ የአቅመ ደካማ ዳራ ቀበሌ የሚኖሩ እያታቸውን አዝመራ ሊከውኑ መጥተዋል፡፡ ይህን ቃል ግጥም የገጠሙት ጤፍ ሲወቁ የተለመኑት ሰዎች ዘግይተው ጥዋት ብቻቸውን በመስራት ላይ እያሉ ነው፡፡

ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 42 እና149 የተጠቀሱት ቃል ግጥሞች ገበሬዎች አብዛኛውን ጊዜ በተናጠል ከሚያንጐራጉሯቸው ለአብነት የቀረቡ ናቸው፡፡ ለብቻቸው በሚያዜሙበት ጊዜ የሚገጥሟቸው ግጥሞችም በአብዛኛው ግላዊ ጉዳይን የሚያነሱ

ናቸው፡፡ ገበሬዎች በተናጠል ሲከወኑ የታፈነውን ስሜታቸውን፣ ፍላጐታቸውን፣ ምኞት፣ ተስፋ፣ ብሶትናምሬት፣ ሀዘንና ደስታቸውን ይገልፃሉ፡፡ "ስራ ላይ ሆነን ጠላታችን ሲያልፍ ስናይም እሱን ለመንካት እንገጥማለን፡፡ ነገር ግን ቢሰማም ባይሰማም ከገጠምነው ልክ የሰማንን ያህል በመናገር ያልገለፅነውን በግጥማችን ገልፀን እንደሰታለን፡፡ ከስራ ውጭም በጠላ ቤት ሆነን መንገር የምንፈልገው ውስጣችን ያለውን ስሜት በግጥም እናስወጣዋለን" /ቃለ መጠይቅ፣ አታክልት ዳምጤ ፣ጥር 09/2006/፡፡

### 4.2.2. በጥንድ /በቅብብሎሽ/ የሚከወኑ ቃል ግጥሞች

በጥንድ የሚከወኑት ቃል ግጥሙን በመቀባበል በፉክክር በየተራ በፉከራ፣ ቀረርቶ፣ በማዜምና በማንጐራጐር ነው፡፡ ይህንም በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ይከውኑታል፡፡ በመስክ ቆይታዬም በአጨዳ ጊዜ በፉከራና ቀረርቶ፣ ግጥሞችን በቅብብሎሽ በየተራ ሲከውኑ ተመልክቻለሁ፡፡ ለአብነትም የሽበር ካሳውና ግዛት አሰፋ በፉክክር እየተቀባበሉ በአጨዳ ላይ ያቀረቧቸውን ግጥሞች እንመልከት፡-

150፡-አረ አይጣል አያድረስ /2/ የጅል ጐረቤት /2/
ፍርሃት ይመስልለዋል ንቀው ሲተውት
/የሽበር ካሳው፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

የሽበር ካሳው ግጥሙን ያቀነቀኑት ጋሎ የተባለ ቦታ ጤፍ አጨዳ ላይ ነው፡፡ ሁለቱም የማቀንቀን ችሎታ ያላቸው ሲሆን በፉክክር ይገጥሙ ነበር፡፡ የሽበር በማማረር ግዛት ጅል ጎረቤት እንደሆነ ሲገጥሙ ግዛት ተቀብለው ቀጣዩን ቃል ግጥም አቀንቅነዋል፡፡

151፡- አንተም እኔን ንቀህ እኔም አንተን ንቄ እንዲህ ተናንቀን
እንገናኛለን ከአንዱ ጐራ ታንቀን
/ግዛት አሰፋ፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

አጨዳው ከ20 በላይ ሰዎች የተሳተፉበት የጤፍ አጨዳ ነው፡፡ በአጨዳው አንዳንድ እርስ በርስ የማይተዋወቅ ሰው ስለነበር ስለ እርሱ ማንነት ለመግለፅ ያስቸግራል፡፡ በዚህም የተነሳ አንዱ የራሱን ሀገር ገበሬዎች ፣ ጀግንነት፣ አይበገሬነት፣ ስነ-ምግባር፣ የዋህነት፣ አገሩን ወዘተ በማንሳት ያንጐራጉራል፡፡ ይህ ዝርዝር ያልተመለከተውና የነደደው ገበሬ ሌሎች የሚያውቃቸውን ጓደኞቹን፣ ሀገሩን፣ ደብሩን፣ ጀግንነት በማንሳት የራሱን ለማሞገስ ከማን አንሳለሁ በሚል ስሜት በፉክክር

ይገጥማል፡፡ በግጥም ችሎታዬም አይችሉኝም የሚል ስሜት ያድርባቸውና ጉን ለጉን ሆነው በየተራ ይገጥማሉ፡፡ ይህንና መሰል ቃል ግጥሞች ለተጨማሪ መረጃ በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 291-303 ይመልከቱ፡፡

### 4.2.3. በቡድን የሚከወኑ ቃል ግጥሞች

በቡድን የሚከወኑት የገበሬዎች ቃል ግጥሞች በእንቅስቃሴ የታጀቡ ናቸው፡፡ በፉከራ፣ በቀረርቶ፣ በማጨብጨብ፣ በዘፈን፣ በሆታና በልልታ፣ መሬት በእግር በመምታት፣ በመዝለል፣ ከፍ ዝቅ በማለት፣ በእንቅስቃሴ ታጅበው የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በዚህ ክዋኔ ከሁለት በላይ ገበሬዎች ይሳተፋሉ፡፡ በአንድ ከዋኝና ሌሎች ተቀባይ ይከወናል፡፡ እንደ መረጃ አቀባዮቸ ግዛት አሰፋና ጀጀው ደርሶ ማብራሪያ የሆታና የእልልታ ግጥሞች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች የሚከውኑ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ የሚከውኑት በአጨዳ አውድ ላይ ነው፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 6ና 10/2006/፡፡

አጨዳ አብዛኛውን ጊዜ በቡድን የሚከናወን የስራ አይነት ስለሆን ገበሬዎች ተሰብስበው በፉከራ፣ ቀረርቶ፣ በልልታና በሆታ በወገዳ እየተሸቀዳደሙ ይከውኑታል፡፡ አጨዳውን ከላይ ከጀመሩበት ቦታ ወደ ታች አድርሰውት ሲመለሱ እየጨፈሩ ነው፡፡ ሲጨርሱም እዚያው ላይ ቆመው በደስታ አንዱ ሲያቀነቅን ሌላው በመቀበል በልልታና በሆታ፣ እስክስታ እየመቱ፣ ሞቅና ደመቅ ባለ ሁኔታ ላባቸው ጠብ ጠብ እስኪል ድረስ ይጨፍራሉ፡፡ ሲደክማቸውም እርስ በርስ ይተዋወቃሉና ይቀባበላሉ፡፡ የሚቀባበሉትም በመግባባት ክዋኔውን ሳያደናቅፉ አንዱ ማቀንቀን ሲጀምር በፊት ያቀነቅን የነበረው ተቀባይ በመሆን ነው፡፡ ይህንም በመስክ ምልከታዬ በአጨዳ አውድ ላይ ተመልክቻለሁ፡፡ ለማስረጃነት ያህል ካቀረቧቸው ግጥሞች እንመልከት፡-

287፡- አበባ ያፈራል ገና
አዲስ አበባ
አበባ ያብባል ገና
አዲስ አበባ

/የማታው አስናቀው፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 5ሀ/

በማለት ጋሎ በተባለ ቦታ ጤፍ በሚያጭዱበት ጊዜና አጭደው ሲጨርሱ በደስታ ስሜት ጨፍረዋል፡፡ የማታው ዋና አቀንቃኝ ሆነው ሲመሯቸው ሌሎች እየተከተሉ ይቀበሏቸዋል፡፡ በጭብጨባ፣ በእልልታ፣ በሆታና በዘፈን /እስክሰታ/፣ አጃቢ

በመሆን ተሳትፈዋል፡፡ በዚህም የማታው “አበባ ያፈራል ገና” ብለው ሲጨርሱ “አዲስ አበባ” በማለት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በድምቀት ይዘፍናሉ፡፡ አቀንቃኝ ለመሆንና የደከመውን ለማሳረፍ  ይተጋገዛሉ፡፡ በዚህ ክዋኔም የማታው ሲያቀነቅኑ ከቆዩ በኋላ ግዛት ተቀብለው ጭፈራውን እንዲቀጥል አድርገውታል፡፡

288፡- አበባ ሸው አዲስ አበባ

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

/ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 5ሀ/

ግዛት ከየማታው ተቀብለው አበባ ሸው አዲስ አበባ እያሉ ወደ ነበሩበት ቦታ ሲመለሱ ሁሉም አዲስ አበባ በማለት ግብረ መልስ ይሰጡ ነበር፡፡ በዚህ ቡድናዊ ክዋኔ በመተሳሰብ በሰላምና በፍቅር ከመደሰታቸው የተነሳ የሚከውኑት ስለሆነ በአቀንቃኙና አጃቢዎች መካከል ያለው መስተጋብር ጥብቅ እንደሆነም በመስክ ምልከታዬ ማየት ችያለሁ፡፡ እነዚህን መሰል ተጨማሪ ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 289ና 290 ይመልከቱ፡፡ በዚህ ክፍል የቃል ግጥሞች ክዋኔ ምን እንደሚመስል ከተመለከትን በመቀጠል ደግሞ ግጥሞቹን ተስተላልፎ እንመለከታለን፡፡

## 4.3. የቃል ግጥም ተስተላልፎ

ተሰተላልፎ ስንል ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን ከትውልድ ትውልድ ከቦታ ቦታና ከዘመን ዘመን የሚያስተላልፉበትን ስልት የሚያሳይ ነው፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ግጥሞችን በተለያዩ መንገድ ይለምዳሉ የለመዱትንም እንደገና መልሰው በመግጠም ያስተላልፋሉ፡፡ በመስክ ምልከታዬ እንዳየሁት የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የቃል ግጥም ተስተላልፎ ቀድሞ ይባል የነበረውን በመሸምደድ እና አስታውሶ በመከወን፣ እዚያው ላይ በመድረስ እና በመከወን ነው፡፡ እንዲሁም በአንድ አውድ የክዋኔውን ድባብ መሰረት አድርገው የቃል፣ የሀረግና የስንኝ ለውጥ በማድረግ፣ ለውጥ ሳያደርጉና ሙሉ ለውጥ በማድረግ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ቃል ግጥሞች በመግጠም ያስተላልፋሉ፡፡ ለአብነትም ቀጣዮቹን ቃል ግጥሞች እንመልከት፡፡

43፡- እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ

አንዱን ለእኔ ወንዱም አንዱን ለእግዜር ፈንታ

/ግዛት አሰፋ፣ ጥር፣ 08/2006፣ ካሴት ቁጥር 4ሀ/

ይህን ቃል ግጥም ግዛት አሰፋ ዳራ ቀበሌ ጥር 08/2006 በጤፍ አውድማ ላይ ሆበሬ እያሉ ያቀነቀኑት ሲሆን የሽበር ካሳው ግዛትን ለማገዝ ሆበሬ በሚሉበት ጊዜ አውዱን ሳይለቁ የስንኝ ለውጥ በማድረግ ቀጣዩን ቃል ግጥም አቀንቅነዋል፡፡

304፡- እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ

ቀኝ እጄ ሲመክት ግራ እጄ ተመታ

/የሽበር ካሳው፣ ጥር፣ 08/2006/፣ ካሴት ቁጥር 4ሀ/

የሁለቱን መንቶ ቃል ግጥሞች ይዘት ስንመለከት የተለያዩ ነው፡፡ "እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ" በሚለው ስንኝ አውዱን ሳይቀይሩ ሁለቱም ሁለት ልጅ በአንድ ጊዜ እንዲወለድና ወንድም እንዲያገኙ ለእናት የሚደረግን ልመና ፣ተማፅኖ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ከአውዱ እንዲስማማ በማድረግ "አንዱን ለእኔ ወንድም አንዱን ለእግዜር ፈንታ" የሚለውን "ቀኝ እጄ ሲመክት ግራ እጄ ተመታ" በማለት የስንኝ ለውጥ በማድረግ የተለያዩ ይዘት ያላቸው ግጥሞችን አቅርበዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳዩን ገበሬዎች በተለያዩ አጋጣሚ የሰሙትን ግጥም ሙሉ በሙሉ በመሸምደድ እንደሚያቀርቡ ሁሉ የተለያዩ ለውጦችን በማድረግ ከአውዱ በማስማማት እንደሚያስተላልፉ ነው፡፡

በአጠቃላይ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን በሽምደዳ፣ እዚያው ላይ በመፍጠርና ከአውዱ ተስማሚ በማድረግ ያስተላልፋሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን የሚከውኑባቸው የተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ይቀርባሉ፡፡

## 4.4. ቃል ግጥሞች የተከወኑባቸው የስራ አጋጣሚዎች

በዚህ ክፍል የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በግል፣ በጥንድም ሆነ በቡድን ሆነው የሚያከናውኗቸው የስራ አጋጣሚዎች ማለትም አጨዳ፣ አውድማ፣ እርሻ፣ አረምና ጉልጓሎ የስራ አከዋወን ሂደት ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

### 4.4.1. የአውድማ አውድ

አውድማ በዶማ ተቆፍሮና ተጠርቦ በክብ ቅርፅ እንደሚወቃው የእህል መጠን ስፋቱ ተመጥኖ ይዘጋጃል፡፡ እህሉ ወደ ውጭ እንዳይወጣና እንዳይባክን በዙሪው በድንጋይ ይከተራል፡፡ ከዚያም ውሃና እበት በማምጣት ከአውድማው መሃከል ላይ እበት ዳር ለዳር ተከትሮ ይበጠበጣል፡፡ አንድ ሰው ከፊት ለፊቱ ውሃ መሬቱን ሲያርከፈክፍ አንድ ሰው ከኋላ በመከተል ይለቀልቃል፡፡ በውሃ የሚርከፈከፈውም እበቱን እንዲይዘውና እንዳይሰነጣጠቅ ነው፡፡ የሚለቀለቀው ደግሞ ምርቱ ከአፈሩ ጋር እንዳይቀላቀል ነው /ቃለ መጠይቅ አለማየሁ ተዘራ፣ ጥር 01/2006/፡፡

በመስከ ቆይታዬ ጥር 07/2006/ ዳራ ቀበሌ እንደተመለከትኩት አውድማውን ያለቀለቁት ሁለት ወንድና አራት ሴቶች ናቸው፡፡ አበባ እንየው፣ ሙሉ አለበል፣ ገነት ጨርቆስ፣ ደጀን ንጉሴ እና የሽበር ካሳው ናቸው፡፡ የሽበር ውሃ ሲያርከፈክፉ፣ አበባ ይለቀልቁ ነበር፡፡ ሙሉ፣ ገነትና ደጀን ውሃ ያመላልሳሉ፡፡ ሴቶቹ ባለትዳር ሲሆኑ ወንዶቹ  አላገቡም፡፡ አውድማው የጤፍ አውድማ ሲሆን የተካሄደው ጥር 8/2006 ነው፡፡ ክዋኔው በአውድማው ባለቤት ወ/ሮ ሙሉ አለበል ልጅ ኪሮስ ቄስ አዳነና ቤተሰብ የሆነው የሽበር ካሳው ጥዋት 2 ሰዓት ተጀመረ፡፡ እኔም በዚህ ሰአት ተገኘሁ፤፤ የሽበር በመጀመሪያ ጤፉን ከክምሩ ቀንሰው አውድማው ላይ ነሰነሱት፡፡ ከዚያም ፌጦ ረጭተው የሚታሄዱትን ሶሰት በሬ፣ አንድ ላም ና ጥጃ ሁሉንም አፋቸውን በገመድ ለጉመውና አንገታቸውን አጠላልፈው ኋላ ሆነው ገመዱን በመያዝ ሆበሬ እያሉ በመግጠም በአውድማው አዞሯቸው፡፡

በአውድማው የተሳተፉት 6 ሆነው ነው፡፡ ግዛት አሠፋ ከጉራሬ ማሪያም፤ የሽበር ካሳው ከጭላ፣ ጥጋቡ ካሴ፣ ዋሴ ፈንቴ፣ ሙሉ አለበልና ኪሮስ ቄስ አዳነ ከዳራ ቀበሌ ናቸው፡፡ ገበሬዎቹ ከ9-60 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ሁሉም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይና አለባበሳቸው ከጉልበቱ የተቀዳደደ፣ የተጣጣፈ አሮጌ የስራ ልብስ ነው፡፡ ከራሳቸው ፎጣቸውን ጠምጠም አድርገው የሚሰሩም ነበሩ፡፡

ግዛት መሀል ሆነው ሆበሬ እያሉ ሲያሄዱ ባለቤቷ ሙሉ አለበልና ሌሎች በዙሪያው ሆነው ሁለትና ሶስት ጣት ባለው መንሽ ከተከመረው ጤፍ እየቀነሱ በመጨመር ይቆሰቁሳሉ፡፡ እያራገፉ ወደ ዳር በማውጣት ዳር ላይ ቆልለው ሁሉም ሲልም መልሰው በማስገባት ያስጠቀጥቁታል፡፡ በአብዛኛው ሆበሬ እየሉ በማንጐራጐር

የሚያሄዱት ግዛት አሰፋና የሸበር ካሳው ናቸው፡፡ ዋሴ ዳር ላይ ሆኖ ገለባውን እያራገፈ ያስገጥም ነበር፡፡ ሲዘፍኑ ድምፃቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ፣ በዜማ፣ አንዱ የአንዱን በመሸምደድና እዚያው ላይ በመፍጠር ነው፡፡ የግጥም እጥረት ሲያጋጥማቸው እስከሚፈጥሩ አስገጥሙን በማለት፣ ሌሎችም ላስገጥምህ እንዲህ በል ሲሏቸው ይገጥማሉ፡፡ በፍላጎታቸው ሆበሬ ልበል ሲባሉ ወይም የደከመው የሚያግዘኝ ሲል በመቀያየር በማሄድ ይዘፍናሉ፡፡

በምልከታዬ ወቅት እንደ ሰማሁት አንድ ገበሬ የገጠመውን ግጥም ሌላ ሰው መልሶ እንዲገጥመው ሲነግረው እንደ ተገጠመ ተናግሮ የራሱን ግጥም ያቀርባል፡፡ ለምሳሌ ግዛት አሰፋን ዋሴ ፈንቴ “እኔና በርዬ እንሂድ ምናኔ” በል እስኪ ሲላቸው ተገጥሟል በማለት የገጠሙት መሆኑን በመግለፅ የራሳቸውን ግጥም ይገጥማሉ፡፡ ዳር ላይ የሚቆሰቁሱትም ስለ ኑሮ፣ የመንግስት እዳና ሌላም የቆጥ የማገሩን ያወራሉ፡፡

ግዛት አሰፋ የተባሉትን ገበሬም “አያልቅበት አዝማሪ እኮ ነው” በማለት ይስቃሉ፡፡ ስድስት ሰዓት ሲሆን ጠላ በቢጫ ጀሪካን፣ እንጀራ በኑግና ተልባ ተቀብቶ /አነባብሮ/፣ ስንዴና ሽንብራ ቆሎ በማር ተቀብቶ፣ ኑግ ተንቦልቡሎ ተደርጎ መጥቷል፡፡ በሮቹን ፈቱና ተቀምጠው ከመሃከላቸው በእድሜ የሚበልጡት ጥጋቡ ካሴ እንዲህ ሲሉ መርቀዋል፡፡ “የሰላም የደስታ ያድርገው፣ በሰላም ታፍሶ የሚገባ፣ የቸር ቀለብ ያድርገው፣ የታሰሩትን ያስፈታቸው ለቤታቸው ያብቃቸው” ሲሉ ሌሎች “አሜን” ይላሉ፡፡ ከዚያም ለአግማስ ቆርሰው አስቀመጡና ወደ አውድማው ጠላና ምግብ በመርጨትና በመጣል መመገብና መጠጣት ጀመሩ፡፡ ከዚያ መልሰው በሮቹን በመለጐም አስገቡና አሄዱ ፡፡

ምርቱ ከገለባው ሲለይ በሮቹን አውጥተው በመንሽ ገለባውን ከምርቱ በነፋስ ለይተው በእንቅብ በማንጨህጨህ ጠርገው ወደ አንድ ጐን ይቆልሉታል፡፡ ከዚያም በወንፊት ለሁለት ይነፉታል፡፡ ምርቱን በለምለም የባህር ዛፍ ቅጠል አልብሰው ከመታፈሱ በፊት የመጣውን እንጀራ በዱባ፣ ድንችና ክክ ወጥ፣ ዳቦ፣ አነባበሮ ከመቅመሳቸው በፊት ለአግማስ አስቀምጠው ወደ አውድማው ቆርሰው በመጣል መብላት ጀመሩ፡፡ የሚያፍሰው በእድሜ የሚበልጠው አቶ ጥጋቡ ነበር፡፡ ቅጠሉን ገለጥ ሲያደርገው በስማም ብለው ማፈስ ሲጀምሩ “ስጭን እመቤቴ፣ ስጭነ፣ ሰራተኛው ትንሽ ነው፣ በላተኛው ብዙ ነው፣ ስጭን እባክሽ የቅዱሳንን ስም የምንጠራበት፣ የምንድርበት የምንኩልበት፣ የመንግስት እዳ አይቀርምና የምንከፍልበት ስጭን፣ ሞልቷል፣ አፈሰሰው”

በማለት አፍሰው እስኪጨርሱ በፀሎት እየለመኑ ነው፡፡ በቀኝ በኩል የሽበር በያዙት አቁማዳና ጆንያ ሁለት ሁለት እንቅብ እየተሰፈረ ይቋጠራል፡፡

እህሉ የተጫነው በአህያ ሲሆን የጫኑት ባለቤቷ ሙሉና ወንዶች ሲሆኑ እኔና የሙሉ ልጅ ኪሮስ አህያው እንዳይሮጥ በመያዝ እገዛ አናደርግ ነበር፡፡ እየነዱ ሲሄዱ የከበደውን አህያ እንዳይጥል በመደገፍ ስለ ምርቱ የነበራቸውን አስተያየት በርክቷል አልበረከተም ይባባላሉ፡፡ ባለቤቷ ሙሉ አለበል ጐተራውን አዘጋጅተው ስለነበር እንደ ደረሱ በትብብር ሴትም ሆነ ወንዱ ከአህያው አውርደው ሴቶች በእንቅብ እየተቀነሰ፣ ወንዶች ሙሉ የጆንያውን እህል በትከሻቸው እየተሸከሙ ተገለበጠ፡፡ ከዛያም ከቤት ቡናና ጠላ ስንጠጣ አምሽተን የቅርቦቹ ሲሄዱ ከርቀት ቦታ የመጡት የሽበር አድረዋል፡፡ እኔም ከመስክ ረዳቴ አደራጀው ዱቤ ጋር ስለነበርኩ በልተን ጠጥተን እንድናድር ቢለምኑንም አመስግነን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

## 4.4.2. የአጨዳ አውድ

በዳባት ወረዳ ከ7 ዓመት ጀምሮ ያለ ልጅ ሴትም ይሁን ወንድ በተለያዩ የአዝእርት አይነቶች አጨዳ ይሳተፋል፡፡ /ቃለ መጠይቅ አድን ዱቤ ታህሳስ 30/2006/፡፡ በመሆኑም በመስክ ቆይታዬ እንደ ተመለከትኩት የጤፍ፣ አብሽ፣ ምስርና ሽንብራ አጨዳ ያካሄዱት በርካታ ገበሬዎች ናቸው፡፡ የጤፍ አጨዳ ካከናወኑትና ከመስክ ረዳቴ አድን ዱቤ ጋር ከተሳተፍኩባቸው ገበሬዎች መካከል ታህሳስ 30/2006/ የተከናወነው የአቶ አስማረ መልሴና ሙሉ አለበል በጋራ የዘሩት ጤፍ አጨዳ አንዱ ነው፡፡

በአጨዳው የተሳተፉት ሃያ ሁለት ገበሬዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ምህረት መልሴ ፣ ምርኩዝ በለጠ፣ መከት ትዛለ፣ ነጋ ብርቁ ከዳራ ቀበሌ፣ ግዛት አሰፋ ከጉራሬ ማሪያም፣ የማታው አስናቀው፣ ሲሳይ ጐንጠ ከቃርሣ፣ የሽበር ካሳው ከጭላ፣ እና ሌሎችም ስማቸው ያልተጠቀሱት ገበሬዎች ይገኙበታል፡፡ በስራው የተሳተፉት ገበሬዎች በልመና፣ በደቦና በቤተ ዘመድነት የተሰባሰቡ መሆናቸውን አስማረ መልሴ ገልፀውልኛል፡፡ እነዚህ ገበሬዎች በተለያዩ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህፃን፣ ወጣትና ሽማግሌ፣ ሴትና ወንድ ናቸው፡፡ መከትና ሙሉ የታጨደውን በመሰብሰብ፣ በአህያ ጭነው በማመላለስ እስከ 10 ሰዓት ከተሳተፉ በኋላ በአጨዳው ተሰማርተዋል፡፡ አለባበሳቸው በአብዛኛው አሮጌ የስራ ልብስ ሆኖ ከጉልበቱ የተጣፈም አለ፡፡ ፎጣቸውን ከራሳቸው የጠመጠሙ ያሉ ሲሆን ሙሉ ደግሞ ነጠላቸውን ከወገባቸው አደግድገዋል፡፡

ገበሬዎች ሲያጭዱ የተወሰኑት በእጣታቸው ተንቆርጥጠው፣ የተወሰኑት ደግሞ ተንበርክከውና ተቀምጠው ነው፡፡ በመስክ እንደ ተመለከትኩት በአጨዳ ወቅት ከስድስት ሰዓት በፊት ለመፎከርና ጃሎ ለማለት ወኔው አልነበራቸውም፡፡ የሆድ የሆዳቸውን በየአቅራባቸው ያወራሉ፡፡ ለመፎከር "አንተበል" አንተ በል ተባብለው፣ አስገጥሙኝ ካለም ላስገጥምህ በማለት፣ ተቀበል ከዚህ፣ እንዲህ በል እስኪ፣ ጃሎ በልማ በማለት ግጥሙን ያቀብሉታል፡፡ ተቀባዩም የሚያውቀው ግጥም ሲሆን በአብዛኛው በራሱ ይጨርሰዋል፡፡ የመግጠም ችሎታ ያላቸውን ግዛት አሰፋ "በል እንጅ ጃሎ በል" በማለት ወዝውዘው ወዝውዘው በግድ ያስፎክሯቸው ነበር፡፡ ያለፉከራ ዝም ብለው እም እም እያሉ ይወግዱ ነበር፡፡ አንዱ ድንገት ደርሶ ጃሎ ሲል እንዲያበል፣ የግጥሙን ግማሽ መስመር ሲል ተው ተው ተው በማለት የመድፊያውን ግጥም የመጨረሻ ቃል በጋራ በማለት በእልልታና በሆታ፣ እም እም እያሉ፣ እስክስታ እየመቱ፣ መሬት እየደቁ፣ እየወገዱ አጭደዋል፡፡

ሰባት ሰዓት ላይ የአስማረ መልሴ ሚስት ከእህታቸው ጋር ሁለት ቢጫ ጀሪካን ጠላ በአህያ ጭነውና በሁለት እንቅብ እንጀራ በወጥ ተቀብተው ይዘው መጡ፡፡ ከሁለት ጎራ ተከፍለው ከመሃከላቸው በእድሜ ገፋ ያሉት ነጋ ብርቁ ሲመርቁ ሌሎች አሜን በማለት ተሳተፉ፡፡ የመስክ ረዳቴ አድን ዱቤም መርቀዋል፡፡ ከዚያም በልተው ጠጥተው ከጠገቡ በኋላ ስሜታቸው ግሎ ያለ ምንም ቀስቃሽ በራሳቸው ወኔ ጃሎ ብለዋል፡፡ ግዛት ጃሎ ሲሉ ምህረትና ሌሎች ተደርበው አብረው ጃሎ ብለዋል፡፡ ከዚያም ነጋ ብርቁ ምህረትን እንዲቆዩ በማድረግ ግዛት እድሉ ሲሰጣቸው ቀጣዩን ግጥም አቀንቅነዋል፡፡

216\. ጐራው ናና /2/ አስር ብር ገባ አሉ መራራው አብሽ
ከሙሉየ ሌላ ማን ብየ ልጥራሽ
/ግዛት አሰፋ፣ ጥር 06/2006፣ 2ሀ /

በፉክክር ጃሎ ሲሉ አገራቸውን፣ ጎጣቸውን፣ ቀበሌያቸውን፣ በውስጡ የሚኖሩትን ህዝቦች /ገበሬዎች/ በማሞገስ ነው፡፡ በግጥማቸው ስማቸውን በመጥራት፣ ጀግንነታቸውን፣ ስነ-ምግባራቸውን በመግለፅ፣ ወደ ፊት እንዲገሰግሱና እንዲነቃቁ አድርገዋል፡፡ ጃሎ ባዩ ግጥሙን ሲደፉት በጋራ ይቀበሉና በወገዳ በአብዛኛው እኩል፣ አልፎ አልፎ ፊትና ኋላ ሆነው ቁጭ ብድግ ከፍ ዝቅ እያሉ በእልልታና በሆታ አጭደዋል፡፡ አስር ሰዓት ላይ የተረፈውን ምግብና ጠላ በልተው ጠጥተው ወደ አጨዳው ሲገቡ ስሜታቸው ግሎ

ይበልጥ ለመግጠም ጊዜ ያጡትና እኔ እኔ በማለት ሽሚያ የገጠሙት ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ እጅ እስከ መቆራረጥ ሁሉ ደርሰዋል፡፡ አልፎ ሂያጅ አይዟችሁ ሲል ይበጀን "ይዟል" አይለቀውም ገና ሌላ ይጨምራል እያሉ ብርታታቸውን ይገልፃሉ፡፡

ግጥሞችን በጥንድ እየተቀባበሉ በፉክክር ሲገጥሙ በቡድንም አንዱ አቀንቃኝ ሌላው ተቀባይ በመሆን በእልልታና በሆታ ጨፍረዋል፡፡ ከዚያም ጤፉን እርስ በርስ በአህያ ጭነው፣ በምኝታ ምንጣፋቸውና በፎጣቸው ተሸክመው ሲሄዱ አህያውን በፉጨት እየነዱ ውሏቸው ምን ይመስል እንደ ነበር እያወሩ፣ እህሉ መቸ መወቃት እንዳለበት እየተወያዩ፣ እየሳቁና እየተጫወቱ ነው፡፡ እህሉን ወስደው ከቤቱ አጠገብ አውድማ ዳር ላይ በመከመር ተመስግነው ወደ የቤታቸው ተመለሱ፡፡

### 4.4.3. የእርሻ አውድ

በዳባት ወረዳ እርፍ ለመጨበጥ የደረሰ ህፃን ልጅ ከአባቱ ጐን እርፍ ላይ በመንጠልጠል እንዴት እንደሚታረስ እያዬ ያድጋል፡፡ እድሜው እየጨመረ ሲሄድ በተለያዩ አጋጣሚዎች ክፍተቶችን በመፈለግ አባቱ ለምሳ ሲቀመጥ አባቱን ለምኖ አንድ ፈሰስ ከዚያም ሲል ሲል አንድ ትልም እያለ ያርሳል፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች አባቱ እግር ሲያነሳው ጠምዶ ይሰጠውና ሲያርስ ይቆያል፡፡ ከዚያም በራሱ ጠምዶ ማረስ ይጀምራል፡፡ ወደ ሙያው እየተጠጋ ሲሄድም አባቱና ሌሎች ሰዎች የሚገጥሟቸውን ግጥሞች በመስማት ያንጐራጉራል፡፡ የእርሻ ስራ በቡድንም ሆነ በተናጠል ይከናወናል፡፡ ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉት መሳሪያዎችም ማረሻ፣ ሞፈር፣ ወገል፣ ቀንበር፣ ማነቂያ፣ ጀባ፣ ከርፈዝ፣ ምራን፣ ወስኮ፣ ድግርና ጅራፍ ናቸው፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ስምሙ ነጋሽ፣ ጥር 04/2006/፡፡

ጥር 04/2006/ ነበር ስምሙ በእርሻ ስራ የተሳተፉት፡፡ እርሻውን ያረሱት ከጥዋቱ ሶስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ነበር፡፡ ስምሙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ፣ እድሜያቸው 50፣ አለባበሳቸው አሮጌ የስራ ልብስ ነው፡፡ በተንሰዬ ማሪያም ቀበሌ የሚኖሩ የሶስት ልጆች አባት ጠንካራ ገበሬ ናቸው፡፡ እርሻውን በሁለት ትልልቅ በሮች ያረሱ ሲሆን በሚያርሱበት ወቅት ከድብ እስከ ድብ ድረስ በሮቹን እያቆላመጡ፣ ደግፈኝ ክንዴ፣ ቀናበል ክንዴ፣ በማለት በሮቹን በቃል ግጥም እያሞገሱ ነው፡፡ እርሻውንም ያረሱት ባቄላ ተዘርቶበት የነበረውን መሬት ለመከስከስ /ለማለስለስ/ እንደሆነ ነግረውኛል ፡፡

### 4.4.4. የጉልጓሎ አውድ

የጉልጓሎ አውድ በአብዛኛው ከሃምሌ እስከ ነሃሴ ወር ይካሄዳል፡፡ ጉልጓሎን የሚያከናውኑት በየትኛውም የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ለመጕልጐል አቅም ያላቸው ልጆች፣ ወጣቶች፣ አዛውንት ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ ሴቶችም ወንዶችም ይሳተፋሉ፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን የጉልጓሎ ድርሻ የሚሸከሙት ሴቶች ናቸው፡፡ ጉልጉሎን ለመጕልጐል ሴቶች እርስ በርስ ደቦ ያወጣሉ፡፡ ገበሬው በበሬ ወይም በፈረስ ሊያርስ ይችላል፡፡ በበሬ ከሆነ ጕልጓይ ሁለት ሰው፣ በፈረስ ከሆነ ሶስትና አራት ሰው መሆን አለባቸው፡፡ በፈረስ ጉልጓሎ ጕልጓይ የበዛው ፈረሱ ስለሚፈጥን ጕልጓይ እንዳይሸነፍና ስራው እንዳይጓተት ነው፡፡

ገበሬው ሲያርስ ጕልጓይና በሬ እንዳይደክሙ፣ ስራ እንዳይፈቱ፣ ከበሬው ኋላ እየተከተሉ የፊት የፊቱን በመጠቅጠቅ ሰርዶውን እያራገፉ በመውጣት እንዲሁም እንዳይፀድቅና እንዳይለመልም ከሾሩ እየደፉ ያጠብቁታል፡፡ አረሙን ለማራገፍ ሲጕነበሱ ወገባቸውን እንዳያማቸው በነጠላቸው፣ መቀነታቸው ግጥም አድርገው ያስሩታል፡፡ ለጉልጓሎም አሮጌ የስራ ልበስ ለብሰው ጭቃ እንዳይነካው ከፍ አድርገው ይታጠቁታል፡፡ ስራው እጅግ አድካሚና አሰልች በመሆኑ ጕልጓይ እንዳይደክም ገበሬው በርቱ፣ እስኪ እንደ ባህር አሳ ብቅ ዝልቅ በሉበት፣ አትፍሩት እያለ በግጥም፣ በዘፈን፣ ጕልጓዮችን፣ በሮቹን፣ ጤፍን፣ እያወሳ ይዘፍናል፡፡ ጕልጓይም በሳቅና በጨዋታ ሞራል እየተሰማቸው ድካማቸውን ይረሱታል፡፡ የስራውን አድካሚነት፣ ምን ያህል አሰልች እንደሆነ እያንጕራጕሩ እርሻው አልቆ በሮች እስኪፈቱ ድረስ ይቆያሉ /ቃለ መጠይቅ፣ አዳነ የማታው፣ ጥር 13/2006/፡፡

ጉልጓሎው ሲያልቅ ከመዝራቱ በፊት በበግ፣ አህያ፣ ፈረስ፣ ላምና በሬ ሁሉንም አስገብተው በማዟዟር፣ በማስጠቅጠቅ በደንብ እንዲጠብቅ መደብ እንዲመስል ያደርጉታል፡፡ ከዚያም ጤፉን በአገልግል ይዞ ለምለም ቅጠል ምልክት በማድረግ ይዘራል፡፡ ከጎልጓይ አንድ ሰው ቅጠሉን እየነቀለ ያልተዘራው መሬት ላይ እየተከለ ይዘራል፡፡ ከዚያም ጎልጓዮች ተመስግነው ይሄዳሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣አድን ዱቤ፣ ጥር 30/2006/፡፡

## 4.4.5. የአረም አውድ

በዳባት ወረዳ በአረም ስራ የሚሳተፉት እህልና ሌላውን ቅጠል ለይተው ያወቁ ሴት፣ ወንድ፣ ህፃን፣ ወጣትና አዛውንት ሁሉም ናቸው፡፡ በአረም ስራ ለመሳተፍ ልጆች ገና በህፃንነታቸው ከቤተሰቦቻቸው ጎን ተቀምጠው ይህን ንቀል ይህን አትንቀል እህል ነው እየተባሉ ማረም ይለምዳሉ፡፡ አረም ከሰኔ እስከ ታህሳስ ድረሰ እንደየአዝዕርቱ አይነት ይከናወናል፡፡ ገበሬዎች በአረም ስራ ሲሳተፉ እህሉ እንዳይሰባበር፣ እንዳይለወስ፣ ልብሳቸው ጭቃ እንዳይጨማለቅ፣ የተለያዩ ከእህሉ ጋር የሚገኙ አውሬዎች ወደ ገላቸው እንዳይገቡ ተንቆርጥጠው፣ አጐንብሰው ነው፡፡ የሚለብሱት አሮጌ የስራ ልብስ ነው፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ወይም ሚስቱ አራሙቻው እህሉን እንዳያደርቀው የፊት የፊቱን በማውጣት ድንበር ላይ ትቀልላለች፡፡ ስድስት ሰዓት ሲሆን ምሳ በእንቅብ ወይም በአገልግል ይመጣል፡፡ ከዚያም ከመሃከል አንዱ በእድሜ የሚበልጡት በስመ አብ ብለው በመባረክ ቆርሰው ይሰጧቸውና ይበላሉ፡፡ ጠላም ሲቀዳ አዝመራውን የቸር ያድርገው፣ ከአራዊት አፍ አውጥቶ በሰላም ወደ ቤት የሚገባ ይሁን፣ አረሙን የተልባ ማድ ያድርገው፣ እናንተም ጉልበታችሁ ይባረክ በማለት ሲመርቁ ሌሎች አሜን ይላሉ፡፡/ቃለ መጠይቅ፣ አዳነ የማታው፣ ጥር 13/2006/፡፡

ገበሬዎች ምግብ ሲበሉ እጃቸው ያለውን ጭቃ እርስ በርስ በማፋተግ ያራግፉታል፡፡ ከመብላትና መጠጣታቸው በፊት የቤተ ዘመድ ወሬ በማውራት ያርሙ የነበረው ከጠጡ በኋላ ወንዶችም ሴቶችም እየዘፈኑ፣ ለሴቶች እየገጠሙ፣ እያሞገሱ ሴቶችን እንዲበረቱ በማድረግ ያርማሉ፡፡ ከዚያም ምሽት 11፡30 ሰዓት ሲሆን ሴቶች ሂዱ ይባሉና ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ሲሄዱ ሚሰት ልጆቿንና ከብቶቿን ሸክፋ በራሷ አራሙቻ ተሸክማ ትሄዳለች፡፡ ወንዶችም እየዘፈኑ እስከ 12፡30 ድረስ ቆይተው ሳር ተሸክመው ይሄዳሉ፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ ፈንታ መንግስቱ፣ ጥር 14/2006/፡፡

ከዚህ በመቀጠል የጥናቱን ዋና ክፍል የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ያቀነቀኗቸው ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና እንመለከታለን፡፡

# 5. የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና

በዚህ ጥናት ከ580 በላይ ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚያነሱ በመሆናቸው ገበሬዎች በተደጋጋሚ የሚያነሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች መሰረት በማድረግ 54 ቃል ግጥሞች ተመርጠው ገለፃና ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ቃል ግጥሞቹ በእርሻ፣ አጨዳ፣ ውቂያ፣ አረምና ጉልጓሎ የስራ አጋጣሚዎች ላይ የተሰበሰቡ ሲሆን በቃል ግጥሞቹ የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮችም ምክር፣ ውዳሴ፣ ብሶትናምሬት፣ ትችት/ስድብ/፣ የወንድም አስፈላጊነት፣ ስለበሬ የተዜሙ፣ ተስፋ፣ ፍቅርና ፀፀትን የሚገልፁ ናቸው፡፡ የግጥሞቹ ይዘት ትንተናም ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

## 5.1. የአውድማ ቃል ግጥሞች

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የተለያዩ የአዝዕርት አይነቶችን ሲወቁ የቃል ግጥሞችን ያንጎራጉራሉ ያዜማሉ፡፡ በቃል ግጥሞቹም የብሶትና ምሬት፣ ትችት/ስድብ፣ የወንድም አስፈላጊነት፣ ስለበሬ የተዜሙ፣ እናትን የሚወድሱና ምክርን የሚገልፁ ጉዳዮች አንስተዋል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 5.1.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ብሶትና ምሬታቸውን ከሚገልፁባቸው አጋጣሚዎች አውድማ ትልቁን ቦታ ይይዛል፡፡ ገበሬዎች አውድማ ሲወቁ ስለ ብቸኝነት፣ የሰው ቤት እንጀራ መራራነት፣ የሚደርስባቸው ግፍና በደል ምሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

43፡-እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ
አንዱን ለእኔ ወንድም አንዱን ለእግዜር ፈንታ
/የሸበር ካሳው ፣ጥር 8/2006፣ ካሴት ቁጥር 4ለ/

በዚህ ቃል ግጥም የአንድን ወንድሙን በሞት እየተነጠቀ ብቸኝነት ያስመረረው ሰው ድምፅ እንሰማለን፡፡ እናቱ ደህና ወላድ እያለች በወለደች ቁጥር የፊት የፊቱን በሞት ትነጠቃች፡፡ ልጅ በእርግዝና ወራት ጀምሮ ተስፋ ያደርጋል፡፡ ወንድም ለማግኘት ሌት ተቀን ይመኛል፡፡ ሲወለድም ወንድም አገኘሁ ብሎ ሲደሰት በድንገት በሞት ይነጠቃል፡፡ አንጀቱ ተበጥሶ በስስት እንደባዘነ ይቀራል፡፡ ሞቱ የማይቀርና የማይገታ

መሆኑን በመረዳት አማራጭ ይፈልጋል፡፡ እናቱ መንታ መንታ እንድትወልድ ይለምናል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ የሽበር ካሳው፣ ጥር 08/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው በሞት ምክንያት ብቸኝነት የጎዳውና ያስመረረው ልጅ ወንድም ለማግኘት አማራጮችን ይፈልጋል፡፡ ይኸውም "እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ" በማለት ምሬት በተሞላ ድምፀት መንታ መንታ ብትወልድ አንድ ወንድም ሊያገኝ እንደሚችል ተስፋ በማድረግ እናቱን ይለምናታል፡፡ መንታ እንዲወለድ የፈለገውም አንድ ሲወለድ ምን ጊዜም መሞቱ አይቀርምና ሁለት ከተወለደ አንዱ ቢሞት አንዱ ይተርፍና ወንድም ይሆነኛል በሚል ፅኑ እምነት ነው፡፡ ለዚህም ነው "አንዱን ለእኔ ወንድም አንዱን ለእግዜር ፈንታ" በማለት የፈጣሪውን ትዕዛዝና ፈቃድ ሳይቃወም፣ ሁሉን ማድረግ፣ መስጠትም መንሳትም የሚችል የአለም ፈጣሪ መሆኑን ተገንዝቦ አንዱን ሲወስድ አንድ እንዲተርፍለት የለመነው፡፡ ልጁ መቸም ቢሆን አንድ አንድ የምትወልድ ከሆነ ወንድም እንደማያገኝ ተስፋ ይቆርጣል፡፡ ነገር ግን ልጁ እግዚአብሔር በሞት የሚነጥቅ እንጅ የሚፈጥር መሆኑን የዘነጋ ይምስላል፡፡

ልጁን የሚፈጥረው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ እናቱ መንታ ልውለድ ስላለች እሱም መንታ እንድትወልድ ስለፈለገ የሚሳካ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ካልፈቀደ እሷ የምትፈጥረው ይመስል "እባክሽ" ሲል ይማፀናል፡፡ ወንድም ካለ ደግሞ ይረዳዋል፣ ይመክረዋል፣ ዋስ ጠበቃ ይሆነዋል፡፡ "የወለዱት ካደገ የዘሩት ከበቀለ ሰው ድሃ አይሆንም" እንዲሉ፡፡ አንድ ሰው የዘራው ከበቀለ ምርት ያገኛል፡፡ በልቶ ጠጥቶ በደስታ ይኖራል፡፡ የወለደውም ካደገ እረዳት፣ መከታ፣ ጠበቃ ይሆነዋል፡፡ የወለደው ያላደገለት ሰው ግን የልጅ ድሃ ማለት ነው፡፡ ዋስ ጠበቃ የሚሆን ልጅ የለውም፡፡ ልጁ ብቸኛ ሆኖ ይንገላታበታል፣ ይሰቃያል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ የሽበር ካሳው፣ ጥር 08/2006/፡፡ ስለዚህ ልጁ ብቸኝነት እንዳማረረው፣ ያገኘ ሁሉ ሲደበድበው እንደሚውል፣ ሃይ ባይ ያጣ፣ ብሶተኛ መሆኑን እናቱ ሞትን መግታት ባትችልም መንታ መንታ ወልዳ ችግሩን እንድትፈታለት በመረረ ድምፅ ሲለምን ይስተዋላል፡፡

1 ፡- ተወይ ባለ ጠጋ ክፉ መናገርክን
አገሬን ሳልገባ ወንዙን ሳልሻገር
/ግዛት አሰፋ፣ ጥር 08/2006፣ ካሴት ቁጥር 4ለ/

በቃል ግጥሙ ከሰው ቤት ተቀጥሮ የሚሰራ ገበሬ(ሎሌ) በባለጠጋው እየደረሰበት ያለውን ግፍና በደል ምሬት በተሞላ ድምፅ ያሰማናል፡፡ ሎሌ የሚያገባ ሀብት ንብረት ያለው፣ ሀብታም ባለጠጋ ነው፡፡ ሎሌው ከቅርብ ወይም ከሩቅ ቦታ ሊመጣ የሚችል ቢሆንም ይህን የሚለው ሎሌ ግን ከማይታወቅ ሩቅ አገር የመጣ ነው፡፡ ሀብታም ደግሞ በሀብቱ ይኮራል፡፡ ወጥቶ ገብቶ መጨቃጨቅ፣ መሳደብ፣ ደፋ እስኪል ጉልበቱን መመዝበር ይፈልጋል፡፡ ስድቡም ቆማጣ ድሃ፣ ማራሪ፣ ችጋራም የሚሉት አንጀት የሚበጥሱ ናቸው፡፡ ማጣቱን፣ አገር ለቆ መሰደዱን ወጥቶ ገብቶ ይነግረዋል፡፡ እኔኮ ሌላ አመጣለሁ ከፈለክ ሂድም ይለዋል፡፡ ያለ እርሱ ሀብታም ያለ አይመስለውም፡፡ ቢሠራ የሠራ አይመስለው አያመሰግን ሌት ተቀን እንደ ውሃ ወራጅ ሲሄድ ቢያድር፣ ሲሰራ ቢውል ደስ ይለዋል፡፡ እረፍቱን አይፈልግም፡፡ ጭቅጭቅና ስድብ ያስመረረው ሎሌ ከፊቱ ላይ መናገር ያልቻለውን ያልደፈረውን ሆበሬ በሚልበት ጊዜ የታፈነውን ብሶቱን/ ምሬቱን ይተነፍሰዋል፡፡/ቃለ መጠይቅ፣ ግዛት አሰፋ፣ ጥር 08/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው ሎሌው ምሬቱን "ተውይ ባለ ጠጋ ክፉ መናገርክን" በማለት በምሬት ክፉ አትናገረኝ፣ ትዕግስት ይኑርህ ሲል ያስጠነቅቀዋል፡፡ ከድርጊቱ ካልተቆጠበ የለፋበትን፣ ቀን ፀሃይ፣ ማታ ብርድና ዝናብ እየተፈራረቀበት ያፈራውና ያመረተውን ንብረቱን ሳይወሰድ በከንቱ እንዳይቀር ይሰጋል፡፡ የሰራበትን፣ ጉልበቱን ያደከመበትን፣ ገንዘብ ሊያዝአይልም፡፡ አቃጥየው ፣ ለብልቤው ፣ አዋርጀው ልሂድ ነው የሚለው፡፡ ገበሬው (ሎሌ) የሚቆየው በውል እስከ ተቆረጠው ቀን አዝመራ እስኪሸከፍ ነው፡፡ አዝመራው ሲሸከፍ ንብረቱን ጠቅልሎ ይሄዳል፡፡ ለዚህም ነው "አገሬን ሳልገባ ወንዙን ሳልሻገር" በማለት በአገርህ ላይ አታዋርደኝ፣ አገሬ እሩቅ ነው ፈጅቸህ ልሂድ እችላለሁ ሲል ነው፡፡ ካልታገሰውና ሰላም ከሌለው ንብረቱን ጥሎ መሄድን ያሻል፡፡ ስለዚህ ገጣሚው በግጥሙ ሎሌ ማስገባት ክፉ ንግግር መዘዝ ያለው መሆኑን በመጠቆም ባለጠጋ ያካበተውን ንብረት ተቀምጦ ይበላው ዘንድ መልካም ስራ፣ ደግና ቅን ሰው መሆን የሚገባው መሆኑን አፅንኦት ይሰጣል፡፡ ይህን መሰል ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ 14፣ 16፣ 17 ይመልከቱ፡፡

2፡- ሆበሬ ሆበሬ /2/ እባክሽ እናቴ /2/ ጥሬ ቆልተሽ በገል
ታውቂዋለሽና የሰውን ቤት ነገር
/ዋሴ ፈንቴ፣ ጥር 08/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 4ሀ/

እንደ ቃል ግጥም ደርዳሪው ማብራሪያ የሰው ቤት እንጀራ ተበልቶ ጕን የማያነሳ መሆኑ ያሳያል፡፡ በሰው ቤት ተቀጥሮ የሚሠራ ገበሬ ምንጊዜም ምቾት የለውም፡፡ በውጭ ስራው ሲያሰቃየው ውሎ ሲገባ እንካ ብላ አፈር በላ በጭብጥ ቆሎ ይሸኛል፡፡ ጥሬ ቆርጥሞ አንጀቱን አስሮ ይውላል፡፡ በስራ ደፋ ቀና ሲል ውሎም ያችው ጭብጥ ጥሬ ትጠብቀዋለች፡፡ ጥዋት ውርጩ፣ ብርድና ዝናቡ፣ ቀን ፀሃዩ እየተፈራረቀ ከርሃብ ጋር በላዩ ላይ ይጋልብበታል፡፡ ስቃዩ ሲፀናበት የሚያደርገውን ያጣል፡፡ የሰውን እናት ስጭኝ ለማለት ለመለመን ይፈራል፡፡ ቢለምንም አትሠጥም፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ዋሴ ፈንቴ፣ ጥር 08/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው የሰው ልጅ ምንጊዜም ቢሆን በሌላ ሰው እጅ በእንጀራ እናት ብዙ ከሚሰጠው በእናቱ እጅ ጭብጥ ቢሰጠው ይጠግባል፡፡ የእንጀራ እናት ሞልታ ብታቀርብለት ትንሽ ይመስለዋል፡፡ የሚሰጠውን በስስት ስለሚበላ ቶሎ ቶሎ ይርበዋል፡፡ ቢርበውም የእንጀራ እናቱን ስጭኝ አይልም፡፡ ቢላትም የምትሰጠው አይመስለውምና፡፡ ሩህሩህ፣ አንጀቷ የማይጨክን እናቱን መለመን አማራጩ ይሆናል፡፡ "እባክሽ እናቴ /2/ ጥሬ ቆልተሽ በገል" በሚለው ስንኝ የእናት ስጦታ እጇ የነካው ትንሹ የሚያጠግብ፣ የርሃብ መድሀኒት መሆኑን ይገልፃል፡፡ እናት ለራሷ ተርባም ቢሆን ልጇ ቢበላ እንጅ ቢራብባት አትወድም፡፡ "ገል" የሸክላ ምጣድ ወይም ሸክላ ድስት ሰባሪ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሰባራ እቃም ቢሆን እንድትሰጠው መሻቱ እቃው ምንም እንኳን ብዙ ጥሬ ባይዝም እጇ የነካው አጥጋቢ መሆኑን ያሳያል፡፡ በገል ጥሬ መለመኑም ምን ያህል እርሃብ እንደ ፀናበት ያስረዳል፡፡ "ታውቂዋለሽና የሰውን ቤት ነገር" እናት የሰው ቤት እንጀራ ባድ የገመገመው ጕን የማያነሳ ይልቅስ ጉልበት የሚያደክም መሆኑን ታውቃለች፡፡ ሁል ጊዜም በሩህሩህ የወላድ አንጀቷ ስለ ልጇ በልቶ አድሮ ይሆን እያለች ትጨነቃለች፡፡ ሁል ጊዜም ያሙን ያደረ ይመስላታል፡፡ ስለዚህ የሰው ቤት እንጀራ ለማግኘት እንደ እሬት መራራ መሆኑን ነው በግጥሙ የገለፀው፡፡

### 5.1.2. እናትን የሚያወድሱ

በዚህ ክፍል እናትን የሚያወድስ ቃል ግጥም ተተንትኗል፡፡ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው እናት ደግ፣ ሩህሩህ፣ ቸር እንደሆነች በማወደስ ገልፀዋል፡፡ ትንታኔው ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

100 ፡-ሚስቴ ትፈጨውና እናቴ ትጋግረው
ይህን በላ ብላ ለሠው የማትነግረው
/አደራጀው ዱቤ፣ ጥር 06/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 4ሀ/

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ሲያብራራው እናት ምንጊዜም ቢሆን ገመና ከታች ነች፡፡ ሚስት እስከምትወልድ ድረስ ባዳ ማለት ናት፡፡ ያየችውን፣ የሰማችውን መልካም ይሁን መጥፎ ለባድ ለዘመድ ትናገራለች፡፡ እናት ግን ሩህሩህ ደግ ስለሆነች በእናትነት ፍቅሯ፣ ብትሰጥ የሰጠች አይመስላት፣ አትገመግም፣ አይነ ሙሉ ናት፡፡ ብዙ ጊዜ ወንድ ልጅ ጎጆ ካልወጣ ሚስት እንድትሰራ እንጅ እንድትሰጠው የሚፈልግ የለም ሲሉ ገልፀዋል /ቃለ መጠይቅ፣ አደራጀው ዱቤ፣ ጥር 06/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ መረዳት የሚቻለው ሚስት ብትሠራ እንጅ ብትፈትት አለመውደድን፣ የእናት እጅ የማይጠገብ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው "ሚስቴ ትፍጨውና እናቴ ትጋግረው" ሲል የገለፀው፡፡ የእናት እጅ የነካው ሁሉ የሚጣፍጥ፣ የሚያጠግብ፣ ያልተቆጠረ ያልተሰፈረ ነው፡፡ እናት የሰጠችውን ሰጠሁት አትልም፡፡ ስትሠጥም በጐድጉዳ እቃ በማያስገመግም ሁኔታ ነው፡፡ "ይህን በላ ብላ ለሠው የማትነግረው" ሲል እናት የወለደችውን ልጇን ገመና ከታች፣ ይህን ያህል በላ የማትል ይልቅስ በልቶ ጠሙን ውሎ ብላ የምትናገር ሩህሩህ ደግ መሆኗን ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ሚስት የእናት ተቃራኒ ሆና ቀርባለች፡፡ "የበላውን ሁሉ ይህን ያህል ይበላል ሆዳም ነው እንደ ጅብ ሲበላ ቢውል አይጠግብም፡፡ አምስት እንጀራም አይጠቅመውም" በማለት ለጐረቤት ስም ታስጠፋለች፡፡ ብትፋታም አገር ምድሩን በወሬ በመሙላት ትዳር ትከለክላለች፡፡ በሆዱ ነው የፈታሁት እስከ ማለት ትደርሳለች፡፡" ስለዚህ ገጣሚው እናት ለልጇ ምን የህል ደግ፣ ሩህሩህና እንከን የለሽ እንደሆነች በቃል ግጥሙ ያስረግጣል፡፡ በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 101ና 102 ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ግጥሞች ይመልከቱ፡፡

## 5.1.3. ምክር የሚሰጡ

በዚህ ክፍል ምክር የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ ገበሬዎች በቃል ግጥሞቻቸው ትዕግስት፣ መልካምስራ፣ የስደትን አስከፊነት፣ የገንዘብን ከንቱነትና መሰል ጉዳዮች በማንሳት አቀንቅነዋል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

44፡- ወንድም የሌለው ሰው ምነው ጠብ መውደዱ/2/ አይ በሬ በሬ
ወንድም የሌለው ሰው ምነው ጠብ መውደዱ
እንደ ጐዳና እሸት ቆርጠውት ቢሄዱ
/ዋሴ ፍንቴ፣ ጥር 08/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

ወንድም የሌለው ሰው ቻይ መሆን አለበት፡፡ አፉን አሳርፎ ካልተቀመጠ ያገኘው ሁሉ ይደበድበዋል፡፡ ጠባቂ የሌለውን እህል ያገኘው ሁሉ እየቆረጠው እንደሚሄደው እሱም አባሪ ስለሌለው ስድብና ዱላ ያርፍበታል፤ ሲሰቃይ ይውላል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ዋሴ ፈንቴ፣ ጥር 08/2006/፡፡

እንደቃል ግጥሙ ደርዳሪ ማብራሪያ ወንድም የሌለው ሰው እንደልቡ ሳይናገር ቢሰድቡት፣ ቢደበድቡት ሁሉንም ችሎ ማለፍ፣ በፀጋ መቀበል ይበጀዋል የሚል ነው፡፡ አልፎ የሚጋረድለት፣ የሚተማመነው ወንድም፣ የሚመክትለት አባሪ የሌለው ሰው ትግስተኛ፣ ቻይ፣ ሆደ ሰፊ መሆን እንደሚገባው ይመክራል፡፡ ምንም ጠብ መሻት፣ መጫር የለበትም፤ አርፎ መቀመጥ አለበት፡፡ የሚተማመነው ከጐኑ የቆመ ማንም ሠው የለውምና ነው፡፡ ነገር ግን ጠብ ከፈለገ፣ ከተደባደበ ያገኘው ሁሉ ወገቡን ቆርጦት፣ ራሱን ፈንክቶት ከመሄድ አልፎም ከመግደል ወደ ኋላ አይልም፡፡ ሮጦ የሚይዝ፣ ብድር የሚመልስ ተቆርቋሪ ወንድም የለውምና፡፡

በቃል ግጥሙ ወንድም የሌለው ሰው ጠባቂ ከሌለው የጐዳና እሸት ጋር ተነፃፅሮ ቀርቧል፡፡ የጐዳና ዳር እሸት ጠባቂ ስለሌለው አላፊ አግዳሚው፣ ያገኘው ሁሉ እየቆረጠ ይበላዋል፡፡ ይጠቀምበታል፡፡ ይቦርቅበታል፡፡ ወንድም የሌለው ሰው ጠብ መሻቱ ደግሞ እንደሚሸነፍ ይታወቃል፡፡ ልጁም አባሪ፣ መከታ፣ ጠበቃ የሚሆን ወንድም ከጐኑ ስለሌለው ያገኘ ሁሉ በማን አለብኝነት ሲደበድበው፣ ሲያደማው፣ ሲያቆስለው ይውላል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ወንድም ያለው ሠው ማንም ደፋሪ የለውም፡፡ ተከብሮ ይውላል፡፡ የጠቡ አነሳሽ ቢሆንም ወንድሙን ስለሚፈራ በወንድሙ ኮርቶ ይንጠራራል፡፡ ጠብ ሲነሳ ቶሎ ወንድሙን የመንገር፣ ብድርን የማስመለስ ነገር አለ፡፡ ለእናት አባቱ ሳይናገር ለወንድሙ ነው የሚናገረው፡፡ ስለዚህ ወንድም የሌለው ሰው ጠብ መሻት የለበትም፣ ጠብ መፈለግ ማንም በሌለበት ሊያስገድለው ስለሚችል መጠንቀቅና ትዕግስተኛ መሆን እንዳለበት አፅንኦት በመስጠት ይመክራል፡፡

45፡-ወዳጅ ወዳጅ አትዋል ይዋሉብህ /2/ አይ ይዋሉብህ
አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩ /2/

በሠው የመከሩ በአንተ የመከሩ እነማን ከበሩ
ከመከሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ /2/
/ግዛት አሠፋ፣ ጥር 08/2006፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

የዚህ ቃል ግጥም ተናጋሪ መልካም ስራ፣ ትዕግስት አስፈላጊ መሆኑን ይመከራል፡፡ በሰውየው ላይ ጥፋት ሊፈፅሙ፣ ሊያደኽዩት፣ ሊገድሉት፣ ሊያሳብዱት ሊመክሩ ይችላሉ፡፡ እንደ እነርሱ መሆንና ክፉ ማሰብ የለበትም፡፡ ይቻል፤ እነርሱን የእጃቸውን ይስጣቸው ብሎ መቀመጥ አለበት፡፡ የራሳቸው ክፉ ስራ ይጥላቸዋል፡፡ በቆፈሩት ጉድጓድ ራሳቸው ይገቡበታል /ቃለ መጠይቅ፣ ግዛት አሠፋ፣ ጥር 08/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ ሰው በስራው ሊመዘን እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ይኸውም ሰው ሰውን ለመጉዳት ብዙ ይጥራል፤ይለፋል ፤ይደክማል፡፡ ለጊዜው የጎዳው ሊመስለው ቢችልም እውነታው ግን ይህ አይደለም፡፡ "አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩ" በማለት እነርሱ ይበድሉህ፣ ይምከሩብህ ያሲሩብህ አንተ ግን መልካም ሁን ሲል ግፉና በደላቸውን በፀጋ መቀበል እንዳለበት ይመክራል፡፡ ይህ ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ክፉን በክፉ አትቃወም የሚለውን አምላካዊ ቃል የሚፀና ነው፡፡ ክፉ ሰው በስራው የሚመዘን ፣ የስራውን ዋጋ የሚቀበል መሆኑን "በሰው የመከሩ በአንተ የመከሩ እነማን ከበሩ" ሲል ቢመክሩም ለውጥ ያላመጡ ያልቅስ በራሳቸው ላይ ጥፋትን ያመጡ ናቸው፡፡ "በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም" እንዲሉ የስራቸውን ዋጋ ያገኛሉ፡፡ ሰውን መጉዳት ማጥፋት ሲያስቡ ራሳቸውን ይጎዳሉ፤ በገደል ይወረወራሉ፡፡ አንድ ሰው ለሰው መልካም፣ ቅን አሳቢ መሆን እንዳለበት ደጋግሞ "አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩ" በማለት በሰው ላይ መመቅኘት ተንኮል ማሰብ የማይጠቅም ከንቱ ድካም መሆኑን ይገልፃል፡፡ በሰው ላይ ተንኮል ያሰቡ ባጠመዱት ወጥመድ ራሳቸውን እንደሚያስገቡበት "ከመከሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ" በማለት "ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው" እንዲሉ የሰው ልጅ በሰራው እንደሚመዘን ያስገነዝባል፡፡ በጥቅሉ በግጥሙ ክፉ ስራ መጨረሻው ውድቀት መሆኑን በማስገንዘብ መልካም መስራት፣ ቅን መሆን እንደሚያስፈልግ በማስጠንቀቅ ምክር ይለግሳል፡፡

46፡- አወይ በርዬ ሆ /2/ አጐይ /2/ ይላል
አጐይ አጐይ ይላለ ጅብ እየጐተተው
አገሩ ያልቻለው ወንዙ ያልከተተው
/አዳነ የማታው፣ ጥር 13/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ አንድ ሠው ባህሪ ከሌለው፣ ከአገሩ ላይ ተስማምቶ ካልኖረ ከሰው አገር ሄዶ መቀመጥ አይችልም፡፡ ባህሪ የሌለውን ሰው እንኳን የሰው አገር ሰው ተወልዶ ያደገበት አገር ሰው ይጠላል፡፡ ከአገሩ ያላወቀበት፣ አገሩ ያልቻለው ከሰው አገር ሄዶ መስማማት አይችልም፡፡ "ከሰው አገር ሄዶ የከበረ ከህዝብ ዱር ገብቶ የዘፈነ ሁለቱ አንድ ናቸው" በሰው አገር ሄዶ ቢከብር፣ ቢደኸይ፣ ቢሰቃይ ተመልካች የለውም፡፡ ልክ ጫካ ዱር ውስጥ ወይም ሰው በበዛበት ጥምቀት በዓል ያለተመልካች የመዝፈን ያህል ነው፡፡ አገርን ለቆ መሄድ ጅብ መጐተት ነው፡፡ ቢታመም አስታማሚ፣ ቢሞት ቀባሪ የለውም፡፡ ጀብ ጐትቶ ይበላዋል፡፡ ከአገር ላይ መኖርን የመሰለ የለም፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ አዳነ የማታው፣ ጥር 13/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው በሰው አገር ከመሄድ ከአገር ላይ መቀመጥ የሚበጅ መሆኑን ነው፡፡ በሰው አገር መሄድ ልክ ጅብ ጠባቂ የሌለውን እንሰሳ በዱር ሲያገኝ ዘነጣጥሎ እንደሚበላው፣ ርህራሄ እንደሌለው ሁሉ በሰው አገር የሄደ ሰውም የአገሩ ሰው እንዴት እንደሚያሰቃየው፣ እንደሚጨክንበት ያሳያል፡፡ ለዚህም ነው "አጐይ አጐይ ይላል ጅብ እየጐተተው" በማለት የገለፀው፡፡ በጅብ የተመሰሉት የአገሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ ስቃይና እንግልት ሊደርስበት የቻለውም የተለየ ባህሪ ስላለው መሆኑን "አገሩ ያልቻለው ወንዙ ያልከተተው" በማለት በአገሩ ላይ መኖር ያልቻለ፣ ባህሪ የሌለው ሰው መጨረሻው ውድቀት መሆኑን ያስረዳል፡፡ በጥቅሉ በሰው አገር ሄዶ ከመንገላታት ፣ ከመሰቃየትና ወይኔ ብሎ በከንቱ ከመቅረት ከአገር ላይ ባህሪን አሳምሮ ሰርቶ መኖር የተሻለ መሆኑን ይመክራል፡፡

47፡-መካሬ መካሬ በሬው ሆየ
ህዳርና ታህሳስ ሁለቱ ነበሩ
ህዳር ሄደ ቤቱን /2/
ታህሳስ ሄደ ቤቱን /2/ ሄደ ቤቱን
እንደላም እረኛ አድርሶ ጊዜያቱን

/ቄስ ቢምረው ጥላዬ ፣ ጥር 06/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 4ሀ/

እንደ ቃል ግጥሙ ደረዳሪ ማብራሪያ ህዳርና ታህሳስ የአዝመራ መከወኛ ወቅቶች ናቸው፡፡ ህዳር ይታጨዳል፣ ይከመራል፣ ታህሳስ ይወቃል፡፡ ሁለቱም ወራቶች ሲያልፉ ወደ መጨረሻው የአዝመራ መከወኛ ወቅት ጥር ሽግግር ይደረጋል፡፡ በዚህ ወር ስራ ሲሸከፍ የሚዘፈን ነው፡፡ የሚዘፈነው ጊዜ ቆሞ እንደማይጠብቅ ገበሬው

እንዲያውቅና እንዲሰራ ነው፡፡ አሁን ላም እረኛ ስናስገባ ከተባለችው ቀን ውጭ አይቆይም፡፡ እህሉን ይዞ ይሄዳል፡፡ ቆይልኝ ትንሽ ቢባል እሽ አይልም /ቃለ መጠይቅ ፣ ቄስ ቢምረው ጥላዬ፣ ጥር 06/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው ህዳርና ታህሳስ አዝመራ የሚከወንባቸው ወራቶች ናቸው፡፡ ገበሬው ስራውን ለመሸከፍ ሁለቱ ወራቶች የነበሩት መሆኑን "ህዳርና ታህሳስ ሁለቱ ነበሩ" ሲል ገልጿል፡፡ እነዚህ ወራቶች ቆመው የማይጠብቁ አላፊ መሆናቸውንም "ህዳር ሄደ ቤቱን"፣ "ታህሳስ ሄደ ቤቱን" በማለት ከአንድ ተቀጥሮ የሚሠራ ላም እረኛ ጋር አነፃፅሮ አቅርቦታል፡፡ የላም እረኛ ሲቀጠር አዝመራው እስኪሸከፍ እስከ ጥር ድረስ እዚያው አብሮ በመኖር ወይም ቤቱ ቅርብ ከሆን በመመላለስ ሊሆን ይችላል፡፡ በጥር ያፈራውን ንብረት ይዞ ይሄዳል፡፡ ተመልሶ በአመቱ ይገባል፡፡ የተቀጠረው ቀን ቀን ጠብቆ ማታ ወደ ቤቱ ለመሄድ ቢሆንም ሰዓቱን አድርሶ ንብረቱን አስረክቦ ይሄዳል፡፡ ክረም ወይም እደር ቢሉት አያድርም፡፡ እነዚህ ወራቶችም ልክ እንደ ላም እረኛ ወራታቸውን፣ ሰዓታቸውን አድረሰው፣ ይሄዳሉ፣ ያልፋሉ እንጅ ቆመው አይጠብቁም፡፡ ላም እረኛ አዝመራው ተሸክፎ ባያልቅም በተባለችው እለት ንብረቱን ይዞ እንደሚወጣ፣ እነዚህ ወራቶትም ጠንካራው ገበሬው አዝመራውን ሲሸክፍ ሰነፍ ሲያንቀላፋ አይኑን እያስፈጠጡ ጥለውት ይልፋሉ፡፡ አያስቆማቸው የአምላክ ትዕዛዛት ናቸው፡፡ ቆዩልኝ አልጨረስኩም የሚባሉ አይደሉምና፡፡ ላም እረኛውም አዝመራው የለውም ክረምልኝ አይባልም፡፡ ቢባልም አይተውም የባለቤቱን አይን እያሰፈጠጠ ይወስዳል እንጅ፡፡ "ትልቅ ሰው እየሞተ ልጅ እየተተካ እንደ ሚሄድ ሁሉ ወቅቶችም አላፊ ናቸው፡፡" /ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ቢምረው ጥላዬ፣ 06/2006/፡፡ እናም ሁሉም በጊዜያቱ ታይቶ የሚጠፋ፣ ቆሞ የማይጠብቅ፣ ባለበት የማይገኝ፣ አላፊ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ገበሬው ይህን አውቆና ተገንዝቦ በሰዓቱና በወራቱ ሳይዘናጋ ጠንክሮ መስራት እንዳለበት ይመክራል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 87 ፣ 88 ፣ 89 ይመልከቱ፡፡

### 5.1.4. የወንድምን አስፈላጊነት የሚገልፁ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው ከሚያነሷቸው በርካታ ጉዳዮች አንዱ የወንድምን አስፈላጊነት፣ ጥቅም የተመለከቱ ግጥሞች ይገኙበታል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

95፡- ወንድም አልኩኝ እንጅ እናት የወለደው
የጥቃቱ ጊዜ እንደ ነሃሴ ጉም አልፎ እሚጋረደው
/የሽበር ካሳው ፤ ጥር 08/2006 ፤ ካሴት ቁጥር 4ሀ/

የዚህ ቃል ግጥም ተናጋሪ ወንድምነትን የለካው ከእናት ሆድ በመውጣት ከእናት በመወለድ ነው፡፡ ወንድም ሁለት አይነት ነው፡፡ የአባት ልጅና የእናት ልጅ ነው፡፡ የአባት ልጅ "የአባት ልጅ የደንደስ ስጋ" እንደሚባለው በጥቃት ጊዜ አልፎ የመመከት፣ ጠበቃ የመሆን ፍላጐት የለውም፣ ድንግጥ አይልም ጨካኝ ነው፡፡ የእናት ልጅ ወንድም ግን ከእናት ሆድ ከማይጨክነው፣ ከሩህሩህ አንጀት ስለወጣ ሆዱ ሩህሩህና የዋህ ነው ሲል የሽበር ካሳው ገልፆልኛል፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፤ ጥር 06/2006/፡፡

በቃል ግጥሙም እንደተገለፀው ወንድም ሁለት አይነት መሆኑን ነው፡፡ ሁለቱም የወንድም አይነቶች ተግባራቸው ይለያያል፡፡ የእናት ልጅ እናት ራሷን ጐድታ ለሌላው ቤዛ የምትሆን፣ ሳይመቻት የምታስመች፣ ሳይሞቃት የምታሞቅ፣ ከመውለዱ በፊት ዘጠኝ ወር ሙሉ በሆዷ ተሸክማ፣ ከተወለደ በኋላም ሶስት ዓመት ጡቷን እያጠባች ክፉ እንዳያገኘው ተንከባክባ ያሳደገችውን እናቱን ርህራሄና ቸርነት ተላብሶ ይወለዳል፡፡ ልጁም በእናቱ ልጅ ወንድሙ ላይ ጭካኔ የለውም፡፡ ለወንድሙ አልፎ መከታ፣ ዋስና ጠበቃ በመሆን ከክፉ ነገር ሁሉ ይታደገዋል፣ ራሱን አሳልፎ ይሰጥለታል፡፡ ለዚህም ነው "ወንድም አልኩይ እንጅ እናት የወለደው" በማለት የሚፈልገው እናቱ አምጣ የወለደችውን ወንድም መሆኑን የገለፀው፡፡ የአባት ልጅ ወንድም አያስፈልገውም፡፡ እንደ እናት ልጅ ወንድም ቢሳሳት አይመክረው፣ ጥቃት ቢደርስበት እይመክትለትምና፡፡ "የጥቃቱ ጊዜ እንደ ነሃሴ ጉም አልፎ እሚጋረደው" በሚለው ስንኝ የእናት ልጅ ጥቃት የማይወድ፣ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ፤ ራሱ ቢመታ እንጅ ወንድሙ ቢመታበት የማይወድ፣ አልፎ የሚመክት፣ መሆኑን ከነሃሴ ጉም ጋር አነፃፅሮታል፡፡ የነሃሴ ጉም ሳይታሰብ ጥቅጥቅ አድርጐ ሸፍኖ አካባቢውን ለማየት ያስቸግራል፡፡ ገበሬውም ጉም ሲጨፍን ስለማይታይ ሀብት ንብረቱን በአግባቡ ስለማይቆጣጠር የንብረት በከብት መሻርና የመውደም አጋጣሚ እንደሚከሰት ሁሉ የእናት ልጅ ወንድምም ማንም ሳያየውና ሳይሰማው፣ ጨለማን ተገን አድርጐ ደብድቦና የሚፈልገውን ጥቃት አድርሶ እንደሚመለስ ይገልፃል፡፡ በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 96 ፤ 97 ፤ 98 ፤ 99 ይህን ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡

### 5.1.5. ስለ በሬ የተዜሙ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች እህል ሲወቁ በቃል ግጥማቸው ከሚያነሷቸው ጉዳዮች አብዛኞቹ ስለ በሬ የሚዜሙ ናቸው፡፡ በግጥማቸው ስለበሬ ውዳሴ፣ ዳተኝነት፣ በደል፣ ጥቅም፣ ደግነት እያነሱ አቀንቅነዋል፡፡ ቀጥሎ ትንታኔውን እንመለከታለን፡፡

#### 5.1.5.1. የበሬን አስፈላጊነት የሚገልፁ

103 ፡- በርዬ አንተን አልባ /2/ በሬው ሆዬ
ወዳጄ አንተን አልባ /2/
አይኔም አያይልኝ ጀሮዬም አይሠማ
/ድረስ ግርማው ፣ ጥር 13/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ በሬ ለገበሬ አይንና ጥርሱ መላ ሰውነቱ ነው፡፡ አይንና ጆሮ ከሰውነት ክፍሎች ትልቅ ቦታ የሚሠጣቸው ናቸው፡፡ አንድ ሠው አይን ካለው የሚፈልገውን ሁሉ ይሠራል፤ የፈለገው ቦታ ይሄዳል፤ እንደፈለገው ይንቀሳቀሳል፡፡ አይን ከሌለው በጨለማ ስለሚሄድ የሚፈልገውን ያህል ላይሰራ ይችላል፡፡ ራሱን የተለየ ሰው አድርጐ ያስባል፡፡ በሬ አልባ መኖር እጅ ሰባራ ሆኖ መኖር ማለት ነው፡፡ አንድ እጁ የተሰበረ ሰው በአንድ እጁ ሰርቶ ማድማት አይችልም፡፡ በሬ የሌለው ገበሬም ያለ በሬ ቢሠራም ለእለት ጉርስ አይበቃም፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ በሬ የሌለው ሰው እንደ ድሃ ይቆጠራል፡፡ አንድ ገበሬ አንድ በሬ ካለው ሀብታም ነው፡፡ ከሌላ በሬ አቀናጅቶ ያርሳል፡፡ በሬ ስላለው ቢቸግረው መበደር ይችላል፡፡ በሰው አይናቅም፣ ከሸንጐ ይውላል፣ ማህበር ይጠጣል፣ እንደልቡ ይናገራል፡፡ በሬ ከሌለው ግን አያረስ፣ አያፍስ፣ አያመርትም ሰው አይውደውም፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ ድረስ ግርማው ፣ ጥር 13/2006/፡፡

ቃል ግጥሙ ገበሬ ያለ በሬ ህይወቱ ሙሉ አለመሆኑን ይገልፃል፡፡ በግጥሙ የበሬ ጥቅም የተላከው አይንና ጆሮ በሚሰጡት ጥቅም ነው፡፡ “በርየ አንተን አልባ” በማለት ድረስ ያለ በሬ ህይወቱ ሙሉ አለመሆኑን፣ መስራት አለመቻሉን ይገልፃል፡፡ አለመስራት ደግሞ ጉልበት ያደክማል፣ እንጀራ ያሳጣል፡፡ “አይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሠማ” ሲል በሬ ከሌለው ካልበላ፣ ካልጠጣ፣ ብቸኛ ሆኖ እንደሚኖር ያስባል፡፡ ለብቻ

ራስን አግልሎ መኖር በጨለማ እንደ መኖር ይመስለዋል፡፡ ያለ በሬ መንቀሳቀስ፣ መስራት አይችልም፡፡ ማህበር አይጠጣ፤ ከሸንጐ አይዝነቅ፣ ተገሎና ተነጥሎ ይኖራል፡፡ ከሰው እኩል መሆን የሚቻለው በሬ ሲኖር ነው፡፡ ስለዚህ በግጥሙ በሬ ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ከአይንና ጆሮ ጥቅም ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል፡፡ በሬ ለገበሬ ህይወት ትልቅ ዋስትና ያለው መሆኑን ያስረዳል፡፡

104፡- በርየ አንተን ያጡ ወዳጀ አንተን ያጡ
ከማህበር ወጡ ሸንጐ አይቀመጡ
/አለማየሁ ተዘራ ፣ ጥር 01/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ ማብራሪያ በሬ የሌለው ሰው ለምኖ ስለሚያርስ ጥሩ ኑሮ አይኖርም፡፡ በደንብ ስለማያርስና ከቀለብ የሚተርፍ እህል ስለማይኖረው ማህበር አይጠጣም፡፡ ከሰው ለመዘነቅ ይፈራል፡፡ የሚፈልገውን ነገር በቀላሉ ሰው አይሰጠውም፡፡ ምን ይከፍለኛል ይለዋል፡፡ አንድ በሬ ያለው ሀብታም ነው፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ አለማየሁ ተዘራ ፣ ጥር 01/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ የምንረዳው በሬ የሌለው ሰው ከሰው እኩል አለመሆኑን ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ማህበር የሚጠጣው፣ በሸንጐ የሚቀመጠው፣ ወደ አደባባይ የሚወጣው፣ አፉን ሞልቶ የሚናገርና ተናግሮም የሚሠማ በሬ ያለው ከሆነ ነው፡፡ ቤቱ ባዶ ሆኖ በሬ ካለው ሀብታም ነው፡፡ በሬ ካለው ያርሳል፣ ያመርታል፣ ቤቱ ባዶ አይሆንም፣ ችግር አያንቆፈቁፈውም ተብሎ ይታመናል፡፡ በሬ የሌለው ሰው ቢያርስም ለምኖ ነው፡፡ የልመና በሬ ዛሬ ቢገኝ ነገ አይደግምም፡፡ ያለውን መሬት የሚዘራበት፣ ያጣል፡፡ መሬቱ አፉን ከፍቶ ውሃ ሲጠጣ ይከርማል፡፡ አላፊ አግዳሚው መዘባበቻ ያደርገዋል፡፡ ከሰው ጋር መገናኘት አይፈልግም፡፡ ካላረሰ ካላፈሰ ፣ ካላመረተ ማህበር አይጠጣም፡፡ ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ ይሆንበታል፡፡ ራሱን ያገላል፡፡ "በርየ አንተን ያጡ ወዳጀ አንተን ያጡ" በማለት በሬ የሌላቸው ሰዎች የተናቁ፣ የተዋረዱ፣ ከሠው በታች ተደርገው የሚቆጠሩ ከሰው እኩል አለመሆናቸውን "ከማህበር ወጡ ሸንጐ አይቀመጡ" በማለት ማህበር የማይጠጡ፣ ለሸንጐ የማይመረጡ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሚኖሩ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ስለዚህ ህይወትን በትክክል ለመምራት፣ ሰርቶ ለመብላትና በማህበራዊ ህይወት ራስን ለማስተሳሰርና በሰላም ለመኖር በሬ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

#### 5.1.5.2. በሬን የሚያወድሱ

124፡- በሬ እንዳንተ እሚሆን የሚሸከረከር
አያ እንዳንተ እሚሆን የሚሸከረከር
እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር
/አለማየሁ ተዘራ ፣ ጥር 01/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

አለማየሁ ተዘራ በአካባቢው ከሚገኙ ባለፀጋ ሰዎች አንዱ ነው፡፡ አብሽ ሲወቃ አገኘሁትና ረዳቱ ጥጋቡ ካሴ እያዜመ ለመቅረፅ ስሞክር አልችልም ብሎ ወጣ፡፡ አለማየሁ ገባና ባልችልበትም ትንሽ ላንጎራጉርልሽ አለና ሆበሬ ሲል ዜማውን አወረደው፡፡ በርካታ የቀንድና የጋማ ከብቶች አሉኝ፡፡ ከንብረቶቸሁሉ በሮቼ ልዩ ናቸው፡፡ ከቤት ላም ተወልደው ያደጉና ለእርሻ ገና ጥጃ እያሉ ለመታረስ የቀኑ ናቸው፡፡ በሬው ሲሰራ ቅን ነው፤ እናት አይደል፡፡ የሰው ግፊት አያስፈልገውም፡፡ እንደ ሌላው በሬ በዱላ አይደበደብም፤ በራሱ ይዞራል፡፡ እንደዚህ ያለ በሬ መቸም ሌላ አላገኝም ሲል ነግሮኛል፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ አለማየሁ ተዘራ፣ ጥር 06/2006/፡፡

በዚህ ግጥም ባለቤቱ አለማየሁ ተዘራ በሬውን ሰልቶ ሲዞር፣ ሲሠራ ተወዳዳሪ የሌለው መሆኑን ሲያወድሰው፣ ሲያሞግሰው ይሰማል፡፡ የበሬውን ጥንካሬና ቅልጥፍና፣ አዟዟር እንኳን በሬ የደህና ፈታይ ሴት እንዝርትም የማይስተካከለው መሆኑን ይገልፃል፡፡ ፈታይ ሴት በእንዝርቷ ትታወቃለች፡፡ እንዝርቷ አንዴ ከተሰላ (ከደራ) ዳግመኛ አይሰላም፡፡ ሙሉውን ቀን ስታሽከረክረው ብትውል የቀረበውን ጥጥ አመድ ያደርገዋል፡፡ አይበጥስም፣ አያጕላድፍም፣ እንዝርቱ አንዴ ሲሽከረከር ካልከረረ መቆሚያ የለውም፡፡ ለማጠንጠን ዳግመኛ አታሽከረክርም፡፡ እዩት እንዝርቷ እንደ ውሃ ይፈሳል እየተባለች ትወደሳለች፡፡

የአለማየሁ በሬም እንዲሁ አንድ ጊዜ ከቀና፣ ከተገራ ዳግመኛ አይቀናም፡፡ ተስተካክሎ ይሰራል፡፡ ሙሉ ቀን ሲሰራ ቢውል የቀረበለትን ስራ አመድ ሳያደርግ አይውልም፡፡ ወደ ፊት ወደ ኋላ ሳይል ሰልቶ በጥንካሬና በቅልጥፍና ይሰራል፡፡ በቅንነት የሚሽከረከረው በሬ የታሰበውን አዝመራ ከቤት እንዲገባ ያደርጋል፡፡ የዚህ በሬ ስራ ግን ከደህና ሴት እንዝርትም የበለጠ እንደሆነ “እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር” ሲል የፈታይ ሴቶች እንዝርትም ሊወዳደርው እንደማይችል ያስረዳል፡፡

ስለዚህ ገበሬው በሬውን እንኳን ከበሬ ከፈታይ ሴት እንዝርትም የሚስተካከለው እንደሌለ፣ የተለዩ፣ ምርጥ፣ ትጉህ፣ የሚያኮራ በሬ መሆኑን ሲያወድሰው፣ ሲያሞግሰው ይደመጣል፡፡ እንዲሁም አለማየሁ በሬው በስራው ቀልጣፋና ቅን፣ ያየው ሰው ሁሉ የሚያደንቀው ነው ሲል ቀጣዩን ቃል ግጥም አቀንቅኖልኛል፡፡

125፡- በርየ ሲሰራ አያየ ሲሰራ
ጐንየ ሲሰራ ይመስላል ደብተራ
ቤተክርስቲያን ገብቶ ቅኔ የሚመራ
/አለማየሁ ተዘራ ፣ ጥር 01/2006፣ ካሴት ቁጥር 2ሀ/

በዚህ ቃል ግጥም አለማየሁ በሬውን ከደብተራ ጋር አመሳስሎታል፡፡ ከደብተራም ደብተራ ከቅኔ መሪ ጋር ነው፡፡ ደብተራና ቅኔ መሪ ደብተራ አንድ አይደሉም፡፡ ሙያቸው ይለያያል፡፡ ቅኔ የሚመራ ደብተራ ከትንሽ እስከ ትልቅ ብዙ ፈተናዎችን ተቋቁሞ በአባቶች ስር ተቀምጦ ትምህርቱን በሚገባ ተምሮ የጨረሰ ነው፡፡ ትምህርቱን ማጠናቀቅ ብቻ አይደለም ማዕረጉን ለማግኘት ስነ-ምግባርም ወሳኝ ነው፡፡ ቅኔን ሁሉም አይመራውም፣ ተሰጥኦውና ችሎታው ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

አለማየሁ በሬውን እያየ፣ ጐንየ፣ በርዬ በማለት ያቆላምጠዋል፡፡ ስራውንም ያወድሰዋል፡፡ በሬው ሲሰራ ሰልቶ የሚዞር፣ የማይደክም፣ ቅን፣ ወደ ፊት ወደ ኋላ የማይል፣ ቀልጣፋ፣ እንቅስቃሴው የሚማርክ መሆኑን በጥራትና በብቃት ተምሮ ወጥቶ ቅኔ ከሚመራ ደብተራ ጋር አመሳስሎታል፡፡ ቅኔ መሪ በደንብ ተምሮ ያወቀውንና ያገኘውን ትምህርት ያገለግልበታል፡፡ ራሱም ይገለገልበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቅኔ ሲመራ አንደበቱና እንቅስቃሴው ከማስተማር አልፎ ይማርካል፣ እርካታና ደስታ ይሰጣል፡፡ ያስተማረውን መምህር ያስመሰግናል፡፡ በሬውም እንደዚሁ እንቅስቃሴው ይማርካል፣ ለባለቤቱ ስራውን በማፋጠን እርካታና ደስታ እንዲሠማው ያደርጋል፡፡ ምርቱም በሰዓት ደርሶ ወደ ቤት ይገባል፡፡ ለታሰበው አገልግሎት ይውላል፡፡ በስራውም ባለቤቱን ያስመሰግናል፡፡ አላፊ አግዳሚው፣ ያየው ሁሉ አየህ ይህ በሬ ሲሰራ እያለ ያደንቀዋል፡፡ ይመኘዋል ሲል ነው የገለፀው፡፡ በግጥሙ በሬው በስራው የተመሠገነ ጠንካራ መሆኑን አስረግጦ ያስረዳል፡፡

### 5.1.5.3. የበሬን ዳተኝነት የሚገልፁ

140፡- እያየ በሬ ሆ /2/የበሬን ምስጋና ወስደው ፈረሱ
በኋላ ተነስቶ በፊት በመድረሱ
/አድን ዱቤ ፣ ጥር 30/2006/

በዚህ ግጥም የበሬ ዳተኛ መሆን ተገልጿል፡፡ መሬትን ከልቡ ለማረስ አብዛኛውን ጊዜ በሬ ይመረጣል፡፡ በፈረስ የሚታረሰው ስራውን ለማፋጠን ካልሆነ ሰርዶውን ገለባብጦ፣ አሰታሞ፣ ገጥሞ ለማረስ በሬ ይሻላል፡፡ በሬ ለእርሻ ፈረስ ለውቂያ ይመረጣል፡፡ በበሬ ሲታረስ ይከርማል፣ ከጥዋት እስከ ማታ ሲሰቃይ ይውላል፡፡ በእርሻ ወራት ነው የበሬው ምስጋና፣ በሬየን ገደልኩት፣ አንገላታሁት የሚባለው፡፡ ስቃዩና በደሉ የሚታሰበውና የሚመሰገነው የእርሻ ወራት አልፎ አዝመራው ሲወቃ ይረሳል ሲል ያብራራዋል፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ አድን ዱቤ ፣ ጥር 30/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው በሬ በእርሻ ሲሰቃይ ይከርማል፡፡ ውቂያ ላይ ፈረስ ይታሄዳል፡፡ ከታፈሰ በኋላም ተጭኖ ከቤት ያደርሳል፡፡ ስራውን በማፋጠን ያለምንም ድካም በሰዓት እንዲገባ ያደርጋል፡፡ በሬ ሲታሄድ የሚያሳድረው ፈረስ ሲታሄድ በአንድ ቀን ይገባል፡፡ በሬው ባረሰው ፈረሰ ስለወቃና ስለተጫነ ገበሬው የበሬውን ውለታ በመርሳት ፈረሱን ያመሰግናል፡፡ ያወድሳል፡፡ የበሬው ምስጋና ይረሳል፡፡ ጐታታ በሬ ተብሎ ይሰደባል፡፡ "የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ" በማለት በሬ በሰራው፣ በለፋበት፣ በደከመበት ፈረስ መመስገኑን ይገልፃል፡፡ "በኋላ ተነስቶ በፊት በመድረሱ" በሚለው ስንኝ ምስጋናውን ሊያገኝ የቻለውም በጥንካሬና ፍጥነቱ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ስለዚህ በውቂያ ወቅት የበሬው ተረሰቶ የፈረሱ ስለሚታወስ የሚመሰገነው ፈረስ እንጅ በሬ አለመሆኑን ያዘክራል፡፡

### 5.1.5.4. በበሬ ላይ የሚደርስን በደል የሚገልፁ

143፡- አወይ በሬ በሬ <u>አወይ በሬ መሆን /2/</u>
አስረው ደበደቡት ምን አርጓቸው ይሆን
/አራጋው ተሻገር ፣ ታህሳስ 26/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

በዚህ ቃል ግጥም ደርዳሪው በበሬ ላይ የሚደርሰው ስቃይና በደል ምን ያህል የከፋ እንደሆነ በመረረ ድምፀት ይገልፃል፡፡ በሬ በእርሻው በውቂያው ከጧት እስከ ማታ ሲሰራ የሚውል፣ የሚያመርት የገበሬ የህይወቱ መሰረት ነው፡፡ ገበሬ ያለበሬ

ህይወቱ ሙሉ አይደለም፡፡ እራሱ አይታረስ፤ አያመርትምና እንደ በሬ፡፡ ነገር ግን መልካም ስለሰራ፣ አፉ በማይናገረው እንስሳ ላይ ግፍና በደል ሲፈፅሙበት አላፊ አግዳሚው ይታዘባል፡፡ ትዝብቱንም "እወይ በሬ በሬ አወይ በሬ መሆን" /2/ በሚለው ስንኝ ደጋግሞ በበሬ ላይ ጭካኔ እንደሚፈፀምበት በሀዘንና ምሬት ገልጿል፡፡ በሬ ቢደክመው፣ ቢወድቅ፣ ቢተኛ ምን ሆኖ እንደተኛ፣ እንደ ወደቀ ምክንያቱን ማወቅ አልፈለጉም፡፡ ቢደክመው፣ ቢርበው፣ ቢታመም ስራውን ማቋረጥ እንደሌለበት ያስባሉ፡፡ "አስረው ደበደቡት ምን አርጓቸው ይሆን" በማለት በሬውን አፉን ለጉመው፣ በገመድ አስረው እንደሚደበድቡት፣ ዱላ እንደሚያወርዱበት ያስረዳል፡፡ በሬ ጠግቦ ካልበላ፣ ካልደከመ፣ ካልታመመ ከመስራት ወደ ኋላ አይልም፡፡ ነገር ግን ችግር ሲያጋጥመው መስራት አልችል ቢል ገበሬው ተው ስራ እያለ ምክንያቱን ሳይረዳ ዱላ ያሳርፍበታል፡፡ በዱላ በመደብደብ የሚሠራ ይመስለዋል፡፡ ስለዚህ በሬ እንዳይበላ ተለጉሞ፣ እንዳይሮጥ ታስሮ፣ በላዩ ላይ ሰንበር እስኪመስል ዱላ እያረፈበት፣ ስቃይና በደል እየደረሰበት የሚሠራ አፉ የማይናገር እንስሳ ምን ያህል እየተጨቆነ፣ እየተንገላታ እንደሆነ ትዝብቱን በጥልቅ ሀዘንና ምሬት ይገልፃል፡፡

### 5.1.6. ፀፀትን የሚገልፁ

ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው ሌሎችን እንደሚያወድሱና እንደሚተቹ ሁሉ ባሳለፉት ስራ ራሳቸውን በመኮነን በድርጊታቸው ትክክል አለመሆን ይፀፀታሉ፡፡

147፡- መኸር ተከውነ /2/ በሬው ሆዬ
መኸር ተከወነ ገባ በየቤቱ
አውኝ አለ ጅቡ እኔ ነኝ እራቱ
/አደራጀው ዱቤ፣ ጥር 06/2006 /

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ሰነፍ ገበሬ የጅብ እራት መሆኑን ይገልፃል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ በመኸር ወቅት ቤት ያለውም ይሁን የሌለው ወጣትና ሽማግሌ እህል ሲከመር እስከሚወቃ ድረስ ለመጠበቅ ተሰብስቦ ከገለባ ያድራል፡፡ የገለባ መኝታም ይመቻል፡፡ ቤት የሌለው ሰነፍ ገበሬ ቤት ልስራ ሳይል ከሞቀው እየበላ፣ ኑሮ ሳያስጨንቀው ሲስቅና ሲጫወት ያድራል፡፡ መኸር ሲሸከፍ ከጥር ወዲያ ማደሪያ ያጣል፡፡ ሰውም ይጠላዋል ጥሩ ፊት አያሳየውም፡፡ ባገኘው ሁሉ ሲሰቃይ ያድራል፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ አደራጀው ዱቤ ፣ ጥር 06/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው የመኸር አዝመራ ሁልጊዜ ውጭ አይኖርም ወቅቱን ጠብቆ እስከ ጥር ድረስ ይከወናል፡፡ ጀግናው ገበሬ አዝመራውን ሸክፎ ከመኸር ጋር ወደቤቱ ይገባል፡፡ ቤት ሳይሰራ፣ ሲዞር፣ ሲቀልድና የሰው ማጀት ሲያጐደጉድ የከረመው ሰነፍ ገበሬ ወቅቱ ሲያልቅ አዝመራው ተወቅቶ ገለባው ተሸክፎ ሲከመር የት እንደሚሄድ ግራ ይገባዋል፡፡ በዚህ ጊዜ "መኸር ተከወነ ገባ በየቤቱ" በማለት መኸር አላፊ እንጅ ህያው ሆኖ ሁልጊዜ የማይኖር መሆኑ የፈጠረበትን ድንጋጤ ይገልፃል፡፡ ውጭ ሲያድር የነበረው ለጊዜው አዝመራ እስከ ሚሸከፍ መሆኑን ዘንግቶታል፡፡ የገለባውን ምኝታ የዘላለም ቤት አድርጐታል፡፡ መኸር ከተከወነ ማደሪያ ገለባ ያጣል፡፡ ሰውም ይጠላውና ፊት ይነሳዋል፤ መጠጊያ ያጣል፡፡ ከባዶ ሜዳ ተኝቶ ጅብ እንደሚበላው ያምናል፡፡ "አውኝ አለ ጅቡ እኔ ነኝ እራቱ" ሲል የጅብ እራት እንደሚሆን ይገነዘባል፡፡ ጅብ የሰነፍ ገበሬ አህያና ፈረስ ካላገኘ ቀረጣጥሞት ማደሩ ነው፡፡ ጀቡ በጮኸ ቁጥር በፍርሃትና በድንጋጤ ከአሁን አሁን በላኝ ሲል ያድራል፡፡ የሰው ቤት ቢውሉበት የማያድሩበት፣ የማያኮራ መሆኑን የተገነዘበው መኸሩ ተከውኖ ማደሪያ ሲያጣ ነው፡፡ ስለዚህ በግጥሙ ጊዜውን በአግባቡ መጠቀምና መስራት ያልቻለ፣ በዋዛ ፈዛዛ ያሳለፈ ሰው መጨረሻው ወይኔ ፀፀት መሆኑን ይገልፃል፡፡

## 5.2. የአጨዳ ቃል ግጥሞች

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በአጨዳ ወቅት በቡድን ወይም በተናጠል ሆነው ይከውናሉ፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኛውን ጊዜ የሚከውኑት ተሰባስበው ነው፡፡ በአጨዳውም፣ ትችት/ስድብ/ ፣ ምሬትና ብሶት፣ ውዳሴ፣ ምክርና ፀፀትን የተመለከቱ ቃል ግጥሞችን አዚመዋል፡፡ የግጥሞቹን ትንታኔ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 5.2.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ

በዚህ ክፍል ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ገበሬዎች በሚደርስባቸው የስራ ጫና፣ የኑሮ መክበድ፣ ብቸኝነት፣ መድሎ፣ መከፋትና ሌሎችም መሰል ጉዳዮች የብሶትና የምሬት ቃል ግጥሞችን ያቀነቅናሉ፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔም ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

152፡-አባት አረገመኝ እናት አረገመኝ
ያምናው ክራሞቴ ዘንድሮም ደገመኝ
/ወ/ሮ ሙሉ አለበል ፣ ጥር 06/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

ይህ ቃል ግጥም ጥር 06 ቀን 2006 ዓ.ም በወ/ሮ ሙሉ አለበል የጤፍ አጨዳ ሆበራ ላይ የተዜመ ነው፡፡ ግጥሙን የደረደረችው ባለቤቷ ወ/ሮ ሙሉ አለበል ስትሆን ወንዶች ሲፎክሩ ሳይታሰብ ማንጎራጎር ጀመረች፡፡ የተናደደች ትመስላለች፡፡ ስትፎክር ብሶትና ሀዘንን በሚያስተጋባ ድምፅ ተኮሳትራ ነበር፡፡ ታሪኳንም እንዲህ ስትል ነግራኛለች፡፡ አስተዳደጓ በቤትም በውጭም ቤተሠቦቿን በስራ በመርዳት ነው፡፡ ከልጅነቷ ጀምራ የአባቷ ቀኝ እጅ ሆና የግብርና ስራን ስታከናውን፣ ተመልሳም እናቷን ውሃ በመቅዳት፣ እንጀራ በመጋገር፣ እንጨት በመልቀም ታግዛለች፡፡ እድሜዋ ለአቅመ አዳም ሲደርስ እናት አባቷ መርቀው ለባል ሰጧት፡፡ ሙሉ በትዳር ላይ ሆና ከባሏ ጋር እኩል ወጥታ በመግባት የቤቱንም ስራ ታከናውናለች፡፡ አሁን የሶስት ልጆች እናት ነች፡፡ በ2001ዓ.ም ህዳር ወር ላይ አራስ ቤት እያለች ባለቤቷ አዲስ አበባ በስልጠና ቆይቶ በገባ በሁለተኛው ቀን ባልታሰበ ሁኔታ በነፍስ ግድያ ተጠርጥሮ ይታሰርባታል፡፡ ወዲያውኑ 18 ዓመት ይፈረድበታል፡፡ አሁን 6 ዓመት ሆኖታል፡፡ ባሏ ከታሰረ ጀምሮ በቤትም በውጭም ስቃዩ በዛባት፡፡ አባት እናት አረገመኝ ግን ተሰቃየሁ ትላለች፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ ወ/ሮ ሙሉ አለበል ፣ ጥር 06/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው ሙሉ መሰቃየትና መከፋት ከእናትና አባት እርግማን ብቻ የሚመጣ ይመስላታል፡፡ ስቃይ እናት አባት ስለረገመ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የህይወት ውጣ ውረዶች ሊከሰት የሚችል መሆኑን አልተገነዘበችም፡፡ "አባት አረገመኝ እናት አረገመኝ" በማለት በእናት አባቷ ተመርቃ፣ ከአይኔ ብቀይ ብለዋት ያደገች መሆኑን ትገልፃለች፡፡ ሙሉ እናት አባት ባይረግሟትም ስቃየቷ ከአመት አመት አልቀነሰም፡፡ ለውጥ አላገኘችም፡፡ ለዚህም ነው "ያምናው ክራሞቴ ዘንድሮም ደገመኝ" ስትል ከዚህ በፊት ወጥታ ገብታ ለከብት ሳር አጭዳ ፣ አርማ፣ ጎልጉላ፣ አምርታ፣ ለልጆቿ ቀለብ አዘጋጅታ፣ ቀን ፀሃይ፣ ማታ ጨለማ ሳይገድባት ትሠራለች፡፡ አልፎ አልፎ መስራት ሲያቅታት ገንዘብ ከፍላ ወይም ለምና በሰው ታሠራለች፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ ሴት ልጅ ብቻዋን መንቀሳቀስ አትችልም፡፡ በተለይ የቁስ ሚስት ብቻዋን ወንዝ እንድትሻገር አይፈቀድም፡፡ ሙሉ የቁስ ሚስት ስለሆነች ብቻዋን ከቦታ ቦታ ስትንቀሳቀስ የሰው ነቀፌታና ትችት አልቻልሽ አላት፣ ከስቃዮዋ በላይ አስመረራት፡፡ ይህ ምሬቷ ከዓመት ዓመት እየተሸጋገረ አላልፍላት በማለቱ ከዚህ በፊት የተንገላታችው እንግልት፣ ስቃይ፣ በደል አሁንም እያማረራት ያለ መሆኑን አፅንኦት ትሰጣለች፡፡

153 ፡-መሬቱን አምሳ ክንድ በሬው የተውሶ

እንጀራው ሊበላ እንዲህ ብሎ ታርሶ

/የሽበር ካሣው ፣ ጥር 06/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

የቃል ግጥም ደርዳሪው የሽበር ካሳው በጤፍ አጨዳ ላይ ያዜመው ነው፡፡ የሽበር ታሪኩን እንዲህ ሲል አጫውቶኛል፡፡ አስረኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ወስጀ ተቀምጫለሁ፡፡ ውጤት ስላልሞላልኝ ትምህርቴን መቀጠል አልቻልኩም፡፡ ወደ ከተማ በመሄድ ሰርቼ መብላት እፈልጋለሁ፡፡ አባቴ ግን አርሰህ ብላ የምን ከተማ ነው ይለኛል፡፡ እኔ ደግሞ አባቴ ያለው መሬት ከቤተሰብ አልፎ ምኑ ሊተርፈኝ ነው ስል አልተስማማሁም፡፡ ከዚያም የሰጠኝ መሬት አንድ ክንድ የማትሞላ፣ አንድ ህፃን የማታጠግብ ቁራጣ ናት፡፡ ይችን መሬት ለማረስ ደግሞ በሬ ተለምኖ ነው ፡፡ የልመና በሬ ደግሞ አያኮራም፡፡ መንግስት ለወጣቶች ብሎ በጋራ ተደራጅቶ የሚታረስ መሬት ሰጥቶን ነበር፡፡ ነገር ግን መሬቱና የሰው ብዛት ስለማይመጣጠን ድካሙ በዝቶ ገቢው ከአንጀት የሚደርስ አይደለም፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ የሽበር ካሳው ፣ ጥር 06/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው በአሁኑ ሰዓት ያለው መሬት ለእለት ቀለብ የሚሆን አይደለም፡፡ የሚሠጠው መሬት አንድ ስንዝር የማትሞላ ናት፡፡ ይህችን መሬት ለማረስ የሚያስችል በሬም የለም፡፡ የልመና በሬ አንድ ጊዜ ቢገኝ ተመልሶ አይደግምም፡፡ በአንድ ጋት መሬትና በልመና በሬ ታርሶ ኑሮው ኑሮ ሊሆን እንደማይችል በማሰብ ብሶትና ምሬቱን፤ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልፃል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ አባት ለልጁ አንድ አንድ ጥማድ መሬት /በአንድ ቀን የምትታረስ/ ቤተሰብ ይሠጣል፡፡ ይችን መሬት አርሶ ቀስ በቀስ ኑሮውን ማሻሻል እንዳለበት ይታሰባል፡፡ የሚያርሰውም በልመና በሬ፣ ሊገኝም ላይገኝም በሚችል ተስፋ ባለ መቁረጥ ነው፡፡ "መሬቱን አምሳ ክንድ በሬው የተውሶ" በማለት የመሬቱን ማነስ ፣ አንድ እርምጃ የማትሞላ መሆኗንና ይህችን መሬት ለማረስም በሬው የሰው ፊት አይቶ በሰቀቀን የሚለመን እንጅ የራሱ በሬ የሌለው መሆኑን ይገልፃል፡፡ ከመሬቷ የምትገኘው ምርት ለዕለት ቀለብ አልበቃው ትላለች፡፡ አንድ ሰው መሬቱ ቢያንስም በሬ ካለው በሰዓቱ አለስልሶ በመዝራት ጥሩ ምርት ሊያገኝ ይችላል፡፡ በልመና በሬ ማረስ ግን ከሚቀር ይጥቆር አይነት ስራ ነው፡፡ በሰዓቱ መዝራት አይቻልም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ መሬቱ ሳይዘራ ውሃ ጠጥቶ የሚከርምበት አጋጣሚም እንዳለ መገመት አያዳግትም፡፡ በልመና በሬ ታርሶ ኑሮው ሊለወጥለት እንደማይችል ተስፋ መቁረጡን

“እንጀራው ሊበላ እንዲህ ብሎ ታርሶ” ሲል ኑሮ ያስመረረው፣ በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደማይችል ተስፋ በመቁረጥ ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ይወስናል፡፡ አታስቀም አታስዘረጋ ነገር ከንቱ ልፋትና ድካም ነው፡፡ አርሶ መብላት ይቅርብኝ እንዲህ በሰቀቀን የማገኘውን እንጀራ ከበላሁት አልቆጥረውም ሲል ኑሮውን በግብርና ሙያ ላይ የመመስረት ፍላጎቱ ያከተመበት መሆኑን ያስረዳል፡፡

### 5.2.2. የውዳሴ ቃል ግጥሞች

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በአጨዳ ወቅት ብሶትና ምሬታቸውን እንደሚገልፁ ሁሉ የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሱ ያደንቃሉ፣ያወድሳሉ፡፡ ከእነዚህም ገበሬንና አገርን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች ይጠቀሳሉ፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

#### 5.2.2.1. ገበሬን የሚያወድሱ

በዚህ ክፍል ገበሬን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ ገበሬዎች የተለያዩ አዝዕርቶችን ሲያጭዱ ስለ አካባቢውና የራሳቸው ጀግንነት፣ ስነ-ምግባር፣ ሙያ፣ መሳሪያ፣ ሴቶችና ሌሎች ጉዳዮችን በማንሳት ያደንቃሉ፣ ያወድሳሉ፣ ያሞግሳሉ፡፡ የግጥሞቹን ትንታኔ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

219፡- አረ በለው /2/ሴትም ጃሎ አለሽ የመባቻ ለታ የልደታ ለታ  
በነቀላው ገብታ ባጨዳውም ገብታ  
ሱሪም ባትታጠቅ ሽጉጥ ባይኖራት  
አረ ሙሉ አለበል የሴት ወንድ ናት  
/ግዛት አሠፋ፣ ጥር 01/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

ይህ ቃል ግጥም ጥር 01/2006 ዓ.ም ከወ/ሮ ሙሉ አለበል የጤፍ አጨዳ ሆበራ ላይ በግዛት አሠፋ የተዜመ ነው፡፡ በምልከታየም በአጨዳው ላይ ከሃያ በላይ ወጣቶ ተሳትፈዋል፡፡ ተሳታፊዎችም በልመናና በገንዘበ ክፍያ መሆኑን ነገራኛለች፡፡ ሙሉ ስድስት ሰዓት ምሳና ጠላ በአህያ ጭና ካመጣች በኋላ ወገቧን በነጠላዋ ታጥቃ ጤፉን እየሰበሰበች በአህያ እጫነች ወደ መንደር አውድማ ወስዳ ስትከምር ቆየች፡፡ ሰባት ሰዓት ሲሆን አጫጆች ተቀምጠው ምሳ በልተው ጠላ ጠጥተው ሲያበቁ ወደ አጨዳው አብራ ገባች፡፡ በአጨዳውም ከወንዶች እኩል ትራመዳለች፡፡ በፉከራ፣ በእልልታና

በጭፈራ እነሱን ትወዳደራለች፡፡ በአጨዳው ላይ የደረደረቻቸው ቃል ግጥሞች በሙሉ ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ናቸው፡፡ ይህም ሙሉ ህይወቷ በስቃይ፣ በበደል፣ በእንግልት የተሞላ መሆኑን ያሳያል፡፡ ውስጧ እፎይታን ያገኝ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ተጠቅማ ተንፍሳዋለች፡፡ ይህ ጀግንነቷ ያስደነቀው ግዛት አሰፋ "ሴትም ጃሎ አለሽ የመባቻ ለታ የልደታ ለታ" በማለት ሴት በአካባቢው ብቻዋን እንጅ እንዲህ ሰው በበዛበት ሆበራ ጃሎ ማለት አልተለመደም፡፡ የተለመደው ወንድ ጃሎ ሲል ነው፡፡ ከወንድም ሁሉ አይደለም፡፡ የሙሉ ግን በጣም የሚገርም ነው ድሮም አሁንም  እንደ ወንድ ናት፡፡ እንደ ወንድ የፎከረች መሆኑን ገልጿል፡፡

አጨዳው የተከናወነው ጥር አንድ ቀን ነበር፡፡ በግጥሙ የወሩ መጀመሪያ ቀን መባቻ ፣ ልደታ እየተባለ እንደሚጠራና በዚህ ቀን እንደፎከረች ነው የገለፀው፡፡ መጀመሪያ የፎከረችው በጤፍ አጨዳ ሲሆን ሲቀጥልም ጤፉን ጨርሰው ወደገቡበት አብሽ ነቀላ ገብታ ነው፡፡ ይህንም "በነቀላው ገብታ በአጨዳውም ገብታ"ሲል ያስረዳል፡፡ በግጥሙ ወንድነት የተለካው ሱሪ በመታጠቅና ሽጉጥ በመያዝ ነው፡፡ ደህና ጉበዝ የሚለካባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ሙሉ በሴትነት ባህሏ ቀሚስ ብታጠልቅ ነጠላ ብታደገድግም ታታሪ ጀግና ገበሬ መሆኗን "ሱሪም ባትታጠቅ ሽጉጥ ባይኖራት" በሚለው ስንኝ ወንድን ወንድ የሚያሰኙት ሱሪና ሽጉጥ ባይኖራትም የሴት ወንድ መሆኗን ይመሰክራል፡፡ ሊዚህም ነው "የሴት ወንድ ናት" ያለው፡፡ እንደ ገጣሚው ወንድ ሆኖ ሱሪ ካለበሰና ሽጉጥ ከሌለው ወንድ ሊባል አይችልም፡፡ ገጣሚው ሙሉ ተወዳዳሪ የሌላት፣ ጠንካራ፣ ታታሪ ገበሬ መሆኗን በቃል ግጥሙ ሲያሞግስ ፣ ሲያወድስ ታይቷል፡፡ በግጥሙ ከሴትም እንደ ወንድ በግብርና ሙያው የሚሣተፉ ታታሪ ሴቶች እንዳሉ አፅንኦት ይሠጣል፡፡

220፡-በማጭዱም ቢሆን /2/ አይቀድሙኝም ባይ ነው  
በጨልዳም ቢሆን /2/ አይቀድሙኝም ባይ ነው  
ያ ግዛት አሰፋ ወደረኛህ ማነው  
/የማታው አስናቀው ፣ ጥር 01/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 3ሀ/

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ በግጥሙ ግዛት አሰፋን ተስተካካይ የሌለው ታታሪ ፣ ጀግና ገበሬ መሆኑን ሲያወድሰው ፣ ሲያሞግሰው ፣ ሲያደንቀው ይታያል፡፡ ግዛት ሙሾ በማውረድና በዘፋኝነቱ ይታወቃል፡፡ በሰርግ ፣ ክብረ በዓል፣ ጥምቀትና ሌሎችም አጋጣሚዎች ይዘፍናል፡፡ በግብርናውም አገር የመሠከረለት "በሬ በትንፋሽ የሚሄድለት" ፣ሙሉ ቀን ሲገጥም ቢውል የማይደክመው ፣ በዚህ ሙያው በርካታ

ገበሬዎች የተለያዩ ጉዳዮችን ሲያዘጋጁ እንዲሳተፍላቸው ይጋብዙታል፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ የማታው አስናቀው፣ 01/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው ግዛት በአጨዳው ሲገባ በስሉ ማጭድ ጤፉን እያጐመደ ወጣቱን ሁሉ እየቀደመ፣ በፉከራና ቀረርቶ እያቀለጠው ይሄዳል፡፡ ማንም የማይቀድመው ፣ በራሱ የሚተማመንና የሚኮራ ጀግና ገበሬ ነው፡፡ ለዚህም ነው "በማጭዱም ቢሆን አይቀድሙኝም ባይ ነው" በማለት በራሱ የሚተማመን፣ ጠንካራ፣ ትጉህ ገበሬ መሆኑን የገለፀው፡፡ ይህንም ጀግንነቱን በተሳተፎ ተመልክቻለሁ፡፡ ግዛት ጀግንነቱ በዚህ አያበቃም በእርሻም ይመሰገናል፡፡ ደህና ገበሬ የሚለካው በእርፍ አጨባበጥና በሬ አነዳድ፣ በሞፈር ቀንበር አያያዝና አስተካክሎ መገኘት ነው፡፡ ሲያርስ በሮቹ ተስተካክለው እንዲሄዱ ሽንቆጥ የሚያደርገው በጩልዳው ነው፡፡ የጐበዝ ገበሬ ጩልዳ በሬውን ሳይገርፉ ይነዳዋል፡፡ ለዚህም ነው "በጩልዳም ቢሆን /2/ አይቀድመኝም ባይ ነው" በማለት በእርሻውም ታታሪ ተወዳዳሪ የሌለው ገበሬ መሆኑን፣ በሙያውም እንደሚኮራ የገለፀው፡፡ ሠፊውን መሬት በአንድ ጊዜ ሸፍኖ የሚውል ተስተካካይ የሌለው ምርጥ ገበሬ መሆኑን "ወደረኛህ ማነው" በማለት አራሽ አንደፋራሽ መሆኑ አፅንኦት ይሰጣል፡፡ ፡

221፡-ሄደ ነጐደ ሄደ ወረደ
ማጭዱ እንደ እሳት እየነደደ
የቆመውን ጤፍ እየጐመደ
/ቃለ መጠይቅ ፣ ጐሌ ደርሶ ፣ ጥር 08/2006/

ቃል ግጥሙ የገበሬውን ፈጣን አጫጅነት፣ ታታሪነት ያሳያል፡፡ እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ ቃል ግጥሙ ለጠንካራ ገበሬ የሚገጠም ነው፡፡ ገበሬው ጤፉን በሰላ ማጭድ ይዞ እየቆረጠው ርቆ መሄዱን ገልጿል፡፡ የማጭዱን ስለት ከሚነድ እሳት ጋር አነፃፅሮታል፡፡ የነደደ እሳት ያገኘውን እንደሚበላ፣ አመድ እንደሚያደርግ፣ ገበሬውም በሰላው ማጭድ ጤፉን እየጐመደ፣ ለጥ አድርጐት መሄዱን ነው "ማጭዱ እንደ እሳት እየነደደ" በማለት የገለፀው፡፡ "ጤፍን በጥንካሬ የሚያጭደው፣ የሚከምረው ሰውየው ነው፡፡ ሰውየው ጠንካራ ካልሆነ ማጭድ ብቻውን አይንቀሳቀስም፡፡ ለጠንካራ ገበሬ ዱልዱም ማጭድም ስሉ ነው፡፡ የአጨዳው ፍጥነት የሚወሰነው በገበሬው ጥንካሬ ነው፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ጐሌ ደርሶ ጥር 08/2006/፡፡

በዚህም የገበሬውን በአጨዳ ላይ እያርገፈገፈው፣ ነዶውን በነዶ ላይ እያቆላለፈው፣ ሰፊውን መሬት የተወለወለ አውድማ አስመስሎ የሚውል ገበሬ መሆኑን ያሞግሰዋል፣ ያወድሰዋል፡፡ ይህን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆነውን ቀጣይ ግጥም እንመልከት፡፡

222፡- አልቢኑማ እጅን አለው ፈንጅ

ሰውየው ነው እንጅ ጠምዝዞ ቆራጭ

/የማታው አስናቀው፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 1ሀ/

በማለት የማታው ከላይ የቀረበውን ግጥም መልዕክት ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ግጥሞልኛል፡፡ ማጭዱ መሳሪያ ስለሆነ በራሱ መንቀሳቀስ፣ መስራት አይችልም፡፡ ሰውየው ነው የሚያሠራው፣ የሚቆርጠው፣ በማለት ትልቁን ሚና የሚጫወተው ገበሬው መሆኑን ይገልፃል፡፡ ማጭዱ ከእጁ የተሰማማው ገበሬ ፍጥነቱና አስተጫጨዱ የተዋጣለት፣ የተመሰከረለት መሆኑን በቃል ግጥሙ በማሞገስ፣ በማወደስ ገልፆታል፡፡

### 5.2.2.2. አገርን የሚያወድሱ

በዚህ ክፍል አገርን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

291፡-አገሬ ቃርሃ አገሬ አዲስ አለም /2/

አገሬ ዋልካው ጐጥ ለዚችማ ምና

ተዛዝኖ ይበላል ጤፉንም በዝና

/አበራ ብርሃኑ ፣ ጥር 06/2006 ፣ ካሴት ቁጥር 5ሀ/

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ አገራችን ቃርሃ በስራ አትታማም፡፡ በቃርሃ የሚኖር ገበሬ ጠንካራ ነው፡፡ ጀግኖች ስለሆን ማንም አይስተካከለንም፡፡ ቦታው ኮረኮንች ቢሆንም ቁጥቋጦና ድንጋዩን ፈነቃቅሎ በማረስ ማምረት የሚችል ነው፡፡ ሁሉም ያለውን ተሳስቦ ይበላል፣ ለቸገረው ያበድራል ሲል ገልፆልኛል /ቃለ መጠይቅ ፣ አበራ ብርሃኑ፣ 06/2006/፡፡

አበራ ብርሃኑ ቃል ግጥሙን የገጠመው ከየማታው አስናቀው ጋር በመፎካከር ነው፡፡ የማታው ኸረ አገሬ ዳራ አያለ አገሩን ሲየወድስና ሲያሞግስ እኔስ ከማን አንሳለሁ በሚል ይገጥም ጀመር፡፡ በግጥሙ የቃርሃን ቀበሌ በተለያየ የጐጥ ስም እየጠራ ያወድሳል፤ያሽሞነሙናል፡፡ የአገሩ ሰዎች በፍቅርና በሰላም የሚተሳሰቡ፣ በሙያቸው ጠንካራ፣ ለተቸገረ የሚረዱ፣ በአጨዳው ሲገቡ መጡብን የሚባሉ አይነት

አጫጅ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው "ለዚችማ ምና" በሚለው ስንኝ አጨዳውን አንድ ጊዜ ለጥ የሚያደርጉት መድህኒቱ መሆናቸውን የገለፀው፡፡ ገበሬው በስራው ብቻ አይደለም የሚረዳዳው የሚተሳሰበው ያመረተውን ምርትም ተካፍሎ በመብላት ጭምር ነው፡፡ አንዱ እየተቸገረ ሌላው አይበላም፡፡ በስራው ማን ችሎን፣ ተወዳዳሪ የለንም፣ ለእኛ ይህች ቀላል ናት ሲል ጀግንነታቸው ከሌላው የበለጠ መሆኑን ያስረዳል፡፡ በአንድነት፣ በህበረት ያመረተውን ምርት ተዛዝኖ በፍቅር ያለው ለሌለው እያበደረ የሚበላ መሆኑን "ተዛዝኖ ይበላል ጤፍንም በዝና" ሲል ጨካኝ አለመሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡

292፡- ኧረ አገሬ ዳራ አገሬ ዳራቦ ወይን ያብቅልብሽ

ወጣት እንደ እንቦሳ የሚዘልብሽ

/የማታው አስናቀው፣ 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 5ሀ/

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ዳራ አየሯ የሚመች ነው፡፡ በሠፊ ሜዳዋ ላይ ወጣት ልጆቿ እንደ እንቦሳ ይዘላሉ፡፡ የዳራ ወጣቶች በስራ፣ በዘፈን፣ በሳቅና ጭዋታቸው የተመሰከረላቸው ፈጣን ናቸው፡፡ ማንም አይወዳደራቸውም፡፡ አገራችን ለምለም ትሁን ለፍሬ ያብቃት፡፡ /ቃለ መጠይቅ ፣ የማታው አስናቀው፣ 06/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ የማታው አገሬ ዳራ፣ ደራቦ እያለ ያወድሳል፡፡ "ወይን ያብቀልብሽ" ሲል ይህች አገር እንደ ወይን ሲያዩት የሚማርክ፣ መልካም መዓዛ ያለው ፍሬ እንድታፈራ ይመኛል፡፡ ዳራ አየሯ ለኑሮ የሚመች፣ መልካ ምድራዊ አቀማመጧ የሚስብ ለምለም አገር ነች፡፡ በቃል ግጥሙ በውስጧ የሚኖሩትን ወጣቶች ከእንቦሳ ዝላይ ጋር አነፃፅሮታል፡፡ እንቦሳ ከተወለደ በኋላ እናቱን ልጥባ አይልም በሠፊው ለምለም ሜዳ ላይ ሲፈርጥና ሲሮጥ ይውላል እንጅ፡፡ ቢርበውም ከለምለሙ መስክ ለመንጨት ይሞክራል፡፡ እንደፈለገው ይቦርቃል፤ ይጫወታል፤ ያገኘውን ላም ሁሉ ጡት ይጠባል፡፡ የዳራ ወጣቶችም እንደ ፈለጉት ወጥተው፣ ገብተው፣ እርስ በርስ ተጫውተው፣ ተወያይተው፣ ተረድተው፣ ሀዘንና ደስታቸውን ተካፍለው የሚኖሩባት ቦታ ናት፡፡ ወጣቱ ተጫዋችና ዝና ወዳድ ነው፡፡ በስራቸው ፈጣንና ቀልጣፍ ፣ በቀላሉ የማይደፋሩ፣ የተከበሩ ናቸው፡፡ በአጨዳ ጊዜም የዳራ ወጣቶች በፉከራና ቀረረቶ የሚችላቸው የለም፡፡ ሲወግዱ ኮበሌውን ሁሉ ቀድመውት እየዘለሉ ፊት ለፊት የሚመሩ መሆኑን በቃል ግጥሙ ሲያወድስ ይሠማል፡፡

### 5.2.3. ትችትን /ስድብ/ የሚገልፁ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች እንደሚያሞግሱ ሁሉ መልካም ነው ያላሉትን ተግባር ደግሞ ያወግዛሉ ይተቻሉ፡፡ ከሚያወግዟቸው ጉዳዮችም የገበሬ ስንፍና፣ ሙስና፣ ፍርሃትና መሰል ጉዳዮች ናቸው፡፡ ቀጥሎ ትንታኔውን እንመለከታለን፡፡

186፡- መገናየ /2/ አገሬ ቃርሃ ጀንጀሮ በሰልፍ
ጭላዳው በሰልፍ
ደህና ጉበዝ እንጅ አይበላም ሰነፍ
/እንጋው አብተው ፣ ጥር 12/2006 ፣ ካሴት ቁጥር1ሀ/

ቃል ግጥሙ በአንጋው አብተው የተዜመ ነው፡፡ ይህን ግጥም አገራችን ቃርሃ የጭላዳና ዝንጀሮ ቦታ ነው፡፡ ጭላዳና ዝንጀሮ ስለሚበዛበት ጠንካራ ገበሬ ካልሆነ ሰነፍ ገበሬ አርሶ አይበላም ሲል ደሴ ውበት ገልፆልኛል /ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 13/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው ቃርሃ የጭላዳና ዝንጀሮ አገር መሆኑን ነው፡፡ አገሩ ጭላዳና ዝንጀሮ የሚበዛበት መሆኑን ለመግለፅም "አገሬ ቃርሃ ዝንጀሮ በሰልፍ ጭላዳው በሰልፍ" በማለት ጭላዳና ዝንጀሮው ብዛት ያለው ፣ ከብዛቱም የተነሳ በሰልፍ ሆኖ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርቦ በመከታተል አዝመራ የሚያጠፋ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዚህ ቦታ የሚያርስና የሚያመርት በራሱ የሚተማመን ፣ ልቡን ያመነ፣ ታታሪ ገበሬ ነው፡፡ ሌት ተቀን ፀሃይና ውርጭ፣ ብርድና ዝናብ እየተፈራረቀበት ችሎ የሚጠብቅ ነው፡፡ ካልሆነ ግን ጭላዳው የተዘራውን በመጫር ይቅመዋል፡፡ በጥንካሬ መጠበቅና መንከባከብ የቻለ ጀግናው ገበሬ አምርቶ ይበላል፡፡ ከሰው ብድር አይሄድም፤ ልጆቹም አይራቡም፣ ያቀናል፣ ያበድራል፡፡ በተቃራኒው ሰነፍ ገበሬ የቦታውን አስቸጋሪነት ሲያስበው ሀሞቱ አየፈሰሰ መሬቱን አይዘራውም፡፡ ቢዘራውም ጥዋት ውርጩን፣ ቀን ፀሃዩን እየፈራ አይጠብቀውም፡፡ ገና ሲዘራ ጥሬው በጭላዳና ዝንጀሮ ይለቀማል፡፡

አልፎ አልፎ አንዳንድ ጥሬ ቢበቅልም በእሸቱ ይጨርሱታል፡፡ አይጠብቀውምና፡፡ የአራዊት መደባደቢያና መጫወቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ ለዚህም ነው "ደህና ጉበዝ እንጅ አይበላም ሰነፍ" በማለት ሰነፍ ገበሬ ጥበቃውን ሲፈራ መሬቱን ዳዋ አልብሶት ይቀራል፣ አያርሰውም፤ ቢያርሰውም፣ ቢዘራውም "ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ" እንዲሉ መሬቱ በከንቱ ሳያመርት ለአራዊት መደሰቻ ሆኖ ይቀራል ሲል የገለፀው፡፡ እጁን አይሠድም፡፡ እሸትም አያገኝም፡፡ ልጆቹ ቤተሠቦቹ በችግርና በርሃብ

ይሰቃያሉ፡፡ በጥቅሉ በግጥሙ ደሀና ጐበዝ ያርሳል፣ ይዘራል፣ ዘርቶም ይጠብቃል ጠብቆም ያመርታል፡፡ በምርቱም እንደ ልቡ ይደሰታል፡፡ ሰነፍ ግን ፀሃይና ውርጭ እየፈራ አያርስም፣ ቢያርሰውም ስለማይጠብቀው እሸት እንኳን ሳያገኝ፣ በከንቱ ዋ ብሎ ውሃ በልቶት እንደሚቀር አፅንኦት በመስጠት የገለፀው፡፡

5.2.4. ምክር የሚሰጡ

ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው እንደሚያወድሱና እንደሚተቹ ሁሉ መልካም ነው ያሉትንም ያስተምራሉ ይመክራሉ፡፡ በግጥሞቹም የስደትን አስከፊነት፣ ስለወንድም አስፈላጊነት፣ ጠንክሮ መስራት፣ በህብረት መስራትና መሰል ጉዳዮች በማንሳት ምክራቸውን ገልፀዋል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

307፡- መኸር ነው ጐበዝ እህል እንጨድ

በረዶ ሲጥል እንዳንሰደድ

/የማታው አስናቀው፣ ጥር 06/2006፣ ካሴት ቁጥር 1ሀ/

የቃል ግጥም ደረዳሪው በረዶ ሊጥል እንደሚችል በትንቢት ቃል በመንገር አስቀድሞ በወቅቱ መስራት እንደሚበጅ በማስጠንቀቅ ይመክራል፡፡ ጀግናው ገበሬ በወቅቱ አጨዶ ፣ ይከምራል፣ በወቅቱም ምርቱን ወደ ቤቱ ያስገባል፡፡ ሰነፍ ገበሬ ደግሞ አፉን ከፍቶ ወሬ ሲዘረጋ ፣ ቡና ሲያስፈላ ፣ በጥላው ሲተኛ አጨዳው ፈሶ ይቀራል /ቃለ መጠይቅ ፣ የማታው አስናቀው ፣ ጥር 06/2006/፡፡ የቃል ግጥሙ ተናጋሪ "መኸር ነው ጐበዝ እህል እንጨድ" በማለት ወንድ ልጅ በጥዋት ተነስቶ ፀሃይ ሳይበረታ እህሉን ማጨድና መከመር፣ መሸከፍ ጠንክሮ መስራት እንዳለበት ይመክራል፡፡ አዝመራ በወቅቱ ካልተሰበሰበ ወደ ፊት ተደቅኖ የሚጠብቀው ከባድ ችግር እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ለዚህም "በረዶ ሲጥል እንዳንሰደድ" በማለት በመኸር ወቅት በረዶ እንደሚጥል አስቀድሞ ያስገነዝባል፡፡ በረዶ ከጣለ ደግሞ የደረሰ፣ የደረቀ እህል ይረግፍና መሬት ላይ በመፍሰስ እዚያው በቅሎ ይቀራል፡፡ ገበሬው የሚበላው ያጣል፡፡ የሚበላው ካጣ ሲቸግረው የመጨረሻው አማራጭ መሰደድ ነው፡፡ ህይወቱ ለቤቱም ለጐረቤቱም አሰቃቂ ይሆናል፡፡ በስንፍና የሚቸገርን ገበሬ የአካባቢው ማህበረሰብ ይቃወማል እንጅ አይደግፍም፡፡ በጥቅሉ "ኋላ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" እንዲሉ ተቸግረን ወደ ሰው ሀገር ስደት ከምንሄድና ከምንሰቃይ ያለንን ንብረት በወቅቱ በሰዓቱ ጠንክረን እንሸክፍ፣ እንስራ፣ አምርተን በሀገራችን እንኑር በማለት አስቀድሞ በማስጠንቀቅ ይመክራል፡፡

305፡-ጠላ የለም እንጅ ጠላማ ቢኖር

ይህ አጨዳ ተርፎ አያድርም ነበር

/ቃለ መጠይቅ፣ ስምሙ ነጋሽ፣ ጥር 04/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ ማብራሪያ በባህላችን ጠላ ለአጨዳ ወሳኝ ነው፡፡ ጠላ ካለ ሰውነት፣ ክንድ እየበረታ ስራው ይፋጠናል፡፡ ጠላ ከሌለ ግን ሰውነት እየደከመ ፣ እየዛለ ስራው ይጓተታል፡፡ ቃል ግጥሙ ጠላ ማምጣት ያልቻለ አቅም ያነሰው ገበሬ አጨዳ ቦታ ላይ የተገጠመ ነው፡፡ ገጣሚው ጠላ ባለመኖሩ ድካም ተሰምቶታል፣ ስራው አልገፋለት ብሏል፡፡ በዚህም እየጠጣ ያጨደበትን ቀን ስራ ቅልጥፍና እያሰበ፣ እያወዳደረ ይዘፍናል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ስምሙ ነጋሽ፣ ጥር 04/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው ገበሬዎች ጠላ ሲጠጡ በስሜት ተነቃቅተው በእልልታና በሆታ ሠፊውን ቦታ አጭደው ይውላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከታሰበው አሳልፈው ያጭዳሉ፡፡ ጠላ ከሌለ ደግሞ የታሰበው አጨዳ ግማሽ ሳይታጨድ ተወዝፎ ይቀራል፡፡ ገበሬው ካልጠጣ ይፈዛል፣ ስራውም ይጓተታል፡፡ ለዚህም ነው "ጠላ የለም እንጅ ጠላማ ቢኖር" በማለት የጠላ አለመኖር የፈጠረው ችግር እንዳለ ይጠቁማል፡፡ ጠላ ቢኖር ጠንክረው ያጭዱ፣ ይበረቱና የታሰበውን ያህል ስራው ሊፋጠን ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን የጠላ አለመኖር ገበሬውን ያፈዘዘው፣ ስራውን ያጓተተው መሆኑን ገልጿል፡፡ "ይህ አጨዳ ተርፎ አያድርም ነበር" በማለት ጠላ ለስራው ቅልጥፍና ለሠዎቹም ብርታትና ጥንካሬ የሚያበረክተው አስተዋኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ አጨዳው ተርፎ ያደረውም በጠላ አለመኖር ነው፡፡ ገበሬው ጠላ ካልጠጣ ፍዝ ነው፡፡

በአጨዳ ወቅት ጠላ ማምጣት ያልቻለ ገበሬ ስራው በአግባቡ ሊከናወንለት አይችልም፡፡ ምክንያቱም ገበሬ ውሃ ጠጥቶ አያጭድም፡፡ ስሜቱ አይቀሰቀስም፣ አይጠነክርም፡፡ ስለዚህ አጨዳው በሰዓቱና በተፈለገው አቅጣጫ ይከናወን ዘንድ ጠላ አስፈላጊ ነው፡፡ ገበሬ ምንም አቅም ቢያጣ የትም የትም ብሎ ጠላ ማቅረብ ስራውን ለማቀላጠፍ መድሃኒት መሆኑን ይመክራል፡፡ "ጠላ ለገበሬ መዳህኒቱ ነው፡፡ ሲፈዝ ሲደክመው የሚያበረታው፡፡" ሲል አፅንኦት ይሰጣል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 104 ፣ 106 ይመልከቱ፡፡

308፡-ተጉዞ ተጉዞ ሰው እንደ ደመና

መመለሻው ጠፋው ያገሩ ጐዳና

/ደሴ ውበት፣ 13/2006፣ ካሴት ቁጥር 1ሀ/

እንደ ቃል ግጥም ደርዳሪው ገለፃ በሚኖርበት ቀበሌ ልጁን አረብ አገር ያልሰደደ ሰው ውስን ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ሸሃ በተባለው ጎጥ የእገሌ ልጅ አረብ አገር ሄደች ፣ ከአረብ አገር ተመለሰች ፣ ቆርቆሮ ቤት ሰራች ከተባለ ብርቅ እየመሰለው ብዙ ሰው ይሄዳል፡፡ እንደልቡ ሄዶ ገንዘብ ሰብስቦ መመለስ የሚችል ይመስለዋል፡፡ ነገር ግን እውነታው እንደዚህ አይደለም፡፡ አሁን ቅርብ ጊዜ የሄዱት እንኳን የት እንደደረሱ ወሬያቸው የለም፣ አልተመለሱም፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ደሴ ውበት፣ ጥር 13/2006/፡፡

ደሴ በቃል ግጥሙ ወደ አረብ አገር የሚጓዘውን የቃርሃ ቀበሌ ሰው ከሰማይ ደመና ጋር አነፃፅሮ አቅርቦታል፡፡ የሚጓዙትም የተቸገሩ የድሃ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ የሀብታም ልጆች ሁሉ ናቸው፡፡ ሲሄዱ እንጂ ሲመለሱ የታዩት መጀመሪያ የሄዱት ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የሚሄዱት ግን ደብዛቸው ጠፍቷል፡፡ “ተጉዞ ተጉዞ ሰው እንደደመና” በማለት የሰማይ ደመና ርቆ እንደሚጓዝ፣ እንደማያቆም፣ ሰማዩን ሙሉ እንደሚሸፍንና በዚያው እንደሚበተን ፣ እየለቀቀ ቦታው እየፀዳ ሲሄድ እንጅ ወደ ተነሳበት ቦታ ሲመለስ እንደማይታይ ሁሉ የአካባቢው ሰዎች የአረብ አገር ጉዞም ልክ እንደ ሰማይ ደመና ርቀት ያለው፣ የማያቋርጥ፣ ሀገራቱን የሸፈናት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ እልቆት የሌለው ጉዞ ውጤቱ አስከፊ መሆኑን “መመለሻው ጠፋው ያገሩ ጐዳና” በሚለው ስንኝ ወደ አረብ የተሰደዱት የአካባቢው ወጣቶች ተጉዘው ተጉዘው የሄዱበት መንገድ ጠፍቷቸው ቀልጠው ሲቀሩ ይታያል፡፡ መመለስ ቢያስቡም መንገድ ላይ በአደጋና በስቃይ መሃል የአራዊት ቀለብ ሆነው ይቀራሉ፡፡ መዳረሻቸው ሳይታወቅ እዚያው በሰው ቤት ስራ ተሰቃይተው ሳያልፍላቸው ሞተው ይቀራሉ፡፡ በመሆኑም ገጣሚው በቃል ግጥሙ በሰው ሀገር እርቀው የሚሄዱ ገንዘቡን እንጅ የሚያጋጥማቸውን ችግር አያስቡትም፡፡ እርቆ ወደ ሰው አገር ያለ አቅጣጫ መጓዝ ውጤቱ ስቃይ ፣ በደልና ሞት ነው፡፡ ስለዚህ ከሀገር ላይ ሰርቶ መኖር ይሻላል በሚል የስደትን አስከፊነት በመግለፅ ምክር ይለግሳል፡፡

### 5.2.5. ፀፀትን የማገልፁ

በዚህ ክፍል ፀፀትን የሚገልፅ ቃል ግጥም ተተንትኗል፡፡ የዳባት ገበሬዎች ሲያጭዱ በቃል ግጥማቸው እንደሚያማርሩ ፣ እንደሚተቹና እንደሚያወድሱ ሁሉ ፀፀታቸውንም ይገልፃሉ፡፡

369፡-ማጨድ ሲገባን ፀሃይ ሳይበረታ

በከንቱ አሳለፍነው በቡና ጋጋታ

/ቃለ መጠይቅ፣ ሲሳይ ጐነጠ፣ ጥር 01/2006/

በቃል ግጥሙ የተገለፀው ጊዜን በከንቱ ማሳለፍ የሚያሳድረው ቁጭት ነው፡፡ ጀግና ገበሬ በጥዋት ተነስቶ ወደ አጨዳ ይሄዳል፡፡ ፀሀይ ሳይበረታ በጥዋት በቅዝቃዜ በአደረ ጉልበት ሳይደክመው አጫጭዶ ፀሃይ ሲበረታ ወደ ቤቱ ገብቶ ምሳ በልቶ ፀሃዩ በረድ ሲልለት ይሄድና በቀዝቃዛ አየር እንዳይደክመው ያጭዳል፡፡ ሰነፍ ገበሬ አርፍዶ ይነሳል፡፡ ከዚያም በአካባቢው ባህል ቡና በህብረት ይጠጣል፡፡ የሚጠጡትም በየተራ በማፍላት ነው፡፡ ተረኛ የሆነች ሴት በጥዋት ተነስታ ቡና ታፈላለች፡፡ ሰነፍ ገበሬያችን ቡና ከልተካናት አይወጣም፡፡ ቡና ሲጠባበቅ ይቆያል፡፡ ቆይቶም አንድ ስኒ ጠጥቶ አይወጣም፡፡ ሲደጋግም እስከ መጨረሻው ይቆይና ፀሃዩ ሲበረታ ወደ አጨዳው ይገባል፡፡ ፀሀዩ አናት አናቱን እያለ ጥብቆው በላበት እየተጠመቀ ሊያጭድ ቢሞክር አይችልም፡፡ ድካም ይሰማዋል፡ እህሉም ፀሃይ እያንቃቃው ዛላው እየተበጠሰ ይወድቃል፡፡ በጥዋት ተነስቶ ማጨድ እንደነበረበት ሲገባው ይቆጨዋል ይፀፀታል /ቃለ መጠይቅ ፣ ሲሳይ ጎነጠ፣ ጥር 01/2006/፡፡

በቃል ግጥሙም እንደተገለፀው ገበሬ በጥዋት ተነስቶ በቀዝቃዛ አየር ያለ ምንም ድካም ማጨድ ሲገባው የማን ቡና ፈላ ሲል ይውላል፡፡ ስድስት ስዓት ሲሆን እንደ ደህና ጎበዝ ፎጣውን ከራሱ ላይ ጠምጥሞ ለማጨድ ይዘጋጃል፡፡ ያ የቀትር ፀሀይ አናት አናቱን ሲወቅረው ወይኔ በጥዋት ባጭድ ቡናው ቢቀርብኝ ሲል ይቆጨዋል፡፡ ለዚህም ነው "ማጨድ ሲገባን ፀሃይ ሳይበረታ" በማለት በጥዋት ተነስቶ ማጨድ ተገቢ መሆኑን የተገነዘበው፡፡ ጊዜውንም ያለ አግባብ ያሳለፈው መሆኑን "በከንቱ አሳለፍነው በቡና ጋጋታ" በማለት ቡና በመጠጣት ያባከነው ጊዜ ትክክል አለመሆኑን በመገንዘብ ሲፀፀት ይሰማል፡፡ ፀፀቱም ገበሬ በጥዋት ተነስቶ መስራት እንዳለበት ያዘክራል፡፡

## 5.3. የእርሻ ቃል ግጥሞች

እርሻ የምርትን ጥራትና መጠን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር ፣ ውጤታማ ለመሆን በቅድሚያ መሬቱን ለማለስለስ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ገበሬው በሮቹን ጠምዶ፣ እርፍ ጨብጦ፣ ጅራፍን (ጬልዳውን) እያጮኸ ግባ ብሎ ሲተልም የተለያዩ ቃል ግጥሞች ይገጥማል፡፡ ከእነዚህም ምክር ፣ ውዳሴ፣ ትችትና መሰል ሌሎች ግጥሞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የግጥሞቹን ትንታኔ እንመለከታለን፡፡

### 5.3.1. ትችትን /ስድብ/ የሚገልፁ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው የሚያዩዋቸውን የሚሰሙዋቸውን፣ የደረሱባቸውን፣ ሊደርስባቸው የሚችለውን መጥፎ ነገር ያወግዛሉ፡፡ በጥቅሉ መልካም መስሎ ያልታያቸውን እኩይ ተግባራት ይተቻሉ፡፡ በቃል ግጥማቸው ከሚያወግዟቸው ጉዳዮች ስንፍና፣ ሙስና ፣ ብድር ፣ የማዳበሪያ ብዛትና አላስፈላጊነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የግጥሞቹ ትንተኔ ይቀርባል፡፡

370 ፡-የመሬት ድልድል ወሰን ብለው
የኩታራ ዳኛ ዘርፎ ጨረሰው
/ቃለ መጠይቅ፣ አደራጀው ዱቤ ፣ ጥር 13/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ ማብራሪያ በአሁኑ ሰዓት በአካባቢያችን ስልጣን የሚሰጣቸው ወጣቶች ናቸው፡፡ መሬት ለሌላቸው ደልድሉ፣ አከፋፍሉ ሲባሉ ለራሳቸው መጠቀሚያ ያደርጉታል፡፡ እረስ በርስ ለመጠቃቀም ስልጣን የሚሰጣቸው በዝምድና ፣ በአበልጅነት ፣ በምዝነት የተቆላለፉ ናቸው /ቃለ መጠይቅ ፣ አደራጀው ዱቤ ፣ ጥር 13/2006/፡፡

ቃል ግጥሙ ወጣት ዳኛ ሚዛናዊ ስራ እንደማይሰራ ያሳያል፡፡ የአካባቢው ገበሬዎች የመሬት ባለቤት ለመሆን ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ የወረዳው ገበሬ ማህበር መሬት ለሌላቸው ገበሬዎች መሬት እንዲያከፋፍል፣ እንዲደለድል ከበላይ አካል ይታዘዛል፡፡ የሚደለድሉት ግን ለሚመለከታቸው መሬት አጥ ገበሬዎች ሳይሆን ውስጥ ለውስጥ ለራሳቸው ነው፡፡ በመሆኑም "የመሬት ድልድል ወሰን ብለው" በማለት አሰራራቸው ትክክል አለመሆኑን ያወግዛል፡፡ ችግሩ ሊፈጠር የቻለውም ከደልዳዮቹ በወጣትነት እድሜ ላይ መገኘት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ለዚህም ነው "የኩታራ ዳኛ ዘርፎ ጨረሰው" በማለት ደልዳዩቹ ኩታራ (ልጅ)፣ እበላ እበላ የሚሉ፣ ባላቸው ነገር የማይረኩ ፣ የሰውን ንብረት የሚያሚጥጡ ብልጥና አጭበርባሪ ፣ መሆናቸውን የገለፀው፡፡

እነዚህ ወጣቶች እርስ በርስ በመመሳጠር "እከክልኝ ልከክልህ" እንዲሉ ድሃን በመበደል ላበላና ላጠጣ፣ በኪስ ለሸጐጠ ለወገን ዘመድ መሬቱን የሰጡት፡፡ መሬቱ ለተቸገረ ድሃ ይሰጥ ቢባልም ድሃ እየተቸገረ ለሀብታም ሃብት ማካበቻ ሆኖ መቅረቱንና የአካባቢው ባለስልጣናት ሌቦች፣ የሙስና ስራ በውስጣቸው የታተመባቸው መሆኑን ይተቻል፡፡ ደልዳዮች በወጣትነት እድሜ ክልል መገኘታቸው ገበሬዎችን

እንደበደላቸውና ወጣት ባለስልጣን ሚዛናዊ ስራ የማይሰራ መሆኑን በማውገዝ በወጣትነት እድሜ ላይ የሚገኝ ሰው ስልጣን ሊሰጠው እንደማይገባ ያስጠነቅቃል፡፡

371፡- ማረስ ነበረ እንጅ ፀሃይ እስከሚከር
ከሰው ደጃፍ ሂዶ አንገት ከማቀርቀር
/ቃለ መጠይቅ፣ ውቤ ዘውዱ፣ ጥር 04/2006/

በቃል ግጥሙ ልመናን፣ በሰው ደጃፍ መቆምን ያወግዛሉ፡፡ ጀግናው ገበሬ ከጥዋት እስከ ማታ ግፋ ሲል ግፋ ሲል ፀሃይ ሳይፈራ፣ ብርድ ሳይበግረው ይሰራል፡፡ በስራው ተመዝኖ ውጤቱን ያገኛል፡፡ ነገር ግን ሰነፍ ገበሬ ጥዋት ፀሃይ ሞቅ ሲል ይጠምዳል፡፡ ፀሃዩ መረር ሲል ፈትቶ ይሂዳል፡፡ ከጥላው እንደተቀመጠ ፀሃይ ይገባና ሲያርስ የዋለ መስሎ እርፍና ሞፈር ቀንበሩን ጠቅልሎ ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ የዚህ ገበሬ የስራ ውጤት አንገቱን አቀርቅሮ በየሰው ደጃፍ በመቆም መለመን፣ መበደር ነው፡፡ ቢያርስ ግን ብድር አይሂድም ነበር /ቃለ መጠይቅ ፣ ውቤ ዘውዱ፣ ጥር 04/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ የምንረዳው አንገትን የሚያስደፋ፣ አሰቃቂ የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ከመግባት ፣ የሰው ፊት ከማየት ጠንክረህ መስራት ነበረብህ የሚል ነው፡፡ "ማረስ ነበር እንጅ ፀሃይ እስከሚከር" በማለት ፀሃይ ሳይፈራ፣ ከጧት እስከ ማታ ማረስ እንደነበረበት ይገልፃል፡፡ ጠንክሮ መስራት ፣ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ከልመና ቀንበር ሊያወጣ እንደሚችል "ከሰው ደጃፍ ሄዶ አንገት ከማቀርቀር" በሚለው ስንኝ እንደ ውሻ ከደጃፍ ላይ ቆሞ የሰው እጅ ከማየት፣ ራስን ከማሳቀቅ ፣ ከማዋረድ በሰዓቱ መስራት ተገቢ መሆኑን ይመክራል፡፡ "የሰው ፊት እሳቱ የሰው ፊት እሳቱ፣ አንድ ደግነቱ ለምጥ አለማውጣቱ" እንዲሉ የሰው ፊት እንደ እሳት የሚጋረፍ፣ ለምጥ የሌለው በትር ነው፡፡ በዚህ አለንጋና በትር ከመገረፍ ማረስ የተሻለ ነው፡፡ ስለዚህ ልመናና ብድርን በማውገዝ ማረስ፣ ማፈስ፣ ራስን ችሎ ማደር ተገቢ መሆኑን ያዘክራል፡፡

372፡- የአበሻ ማሽላ በጤፍ ከመበደር
እርሻ ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ነበር ማደር
/ቃለ መጠይቅ፣ ቢምር ሞላ፣ ታህሳስ 26/2006/

አንዳንድ ገበሬ ክረምት ላይ ጤፍ ፣ ምስር ፣ አብሽና አልፎ አልፎ ባቄላ ለመስጠት ማሽላ ይበደራል፡፡ ሲበደር ምንም አይመስለውም ፤ ለምዶታል፡፡ ነጋዴው ስለሚያተርፍበት በዚህ ቀን ልትመልስ ብሎ ውል አስገበብቶ ዋስ አስጠርቶ

ይሰጠዋል፡፡ ማሽላ ከቤት ሲገባ ማድና በረከት የለውም፡፡ የማሽላ ቀለብ ውሃ መጠጥ ማለት ነው አያጠግብም፡፡ ውርደትም ነው፡፡ሌት ተቀን ብሎ ማረስ ይበልጣል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ቢምር ሞላ፣ ታህሳስ 26/2006/፡፡

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ በአካባቢው ማህበረሰብ አብዛኛውን ጊዜ የሚመለከተውን ብድር አጠቃቀም ይተቻል፡፡ ደህና ገበሬ መሬቱን አለስልሶ፣ አርሶ፣ ዘርቶ፣ አርሞ፣ ኰልኩሎ ያፈራውን ምርት ከዓመት እስከ ዓመት ሳይቸገር ይጠቀማል፡፡ ከቤቱ ተርፎ ያቀናል፣ ለቸገረው ያበድራል፡፡ ያላረሰው ሰነፍ ገበሬ ከጥላው ተቀምጦ እየዋለ፣ በሰዓቱና በወራቱ ሳያርስ ይከርማል፡፡ በበጋ ወራት እንደምንም ብቂ ብቂ ብሎ ልጆቹ የመክሰስ ቆሎ ሳያገኙ ይውላሉ፤ሳይጠግቡ ያድራሉ፡፡ ግንቦት ግም ሲል ጤፍ አሰጥሃለሁ ማሽላ ስጠኝ እያለ በየነጋዴው ይዞራል፡፡ ነጋዴውም ተለምኖ ምርቱን እንዳስገባ እንዲያመጣለት ውል አስገብቶ ይሠጠዋል፡፡ ማሽላውም መጥቶ ቋት አይሞላ ፣ አያጠግብ፡፡ "የአበሻ ማሽላ በጤፍ ከመበደር" በማለት ማሽላ በጣም እርካሽ ሲሆን ጤፍ ደግሞ ሁለትና ሶሶት እጥፍ ነው፡፡ የአበሻ ማሽላ በጤፍ መበደሩን ያወግዛል፡፡ ከዚህ ይልቅ እንቅልፍ አጥቶ ሌት ተቀን መስራት የሚሻል መሆኑን "እርሻ ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ነበር ማደር" በማለት ያለ እረፍት ማረስ ማምረት እንጅ በማሽላ ጤፍ መበደር ትክክል አለመሆኑን ያስረዳል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ ክረምት ላይ የቸገረው ሰነፍ ገበሬ አራሽ ገበሬ ዝቆ ሲያቀና የነጋዴ ሚዛን ሲያጐደጉድ ይውላል፡፡ ሰነፉ ክረምቷን የሚወጣበት ማሽላ በምስር ወይም በጤፍ ይበደራል፡፡ ነጋዴውም ምስርና ጤፍ በጣም በውድ ስለሚቀና ይሰጣል፡፡ ገበሬው ለሳምንት ቀለብ የማትሆን ውሃ በቀጠነ ቁጥር የምትቀጥን ማሽላ አምጥቶ ያመረተውን የጤፍና ምስር ምርት አይኑ እየረገፈ ያስረክባል፡፡ ለእለት ቀለብ ሲያጣ ያው እንደተለመደው መልሶ ይበደራል፡፡ ዓመቱ አልፎ ዓመቱ ሲተካ ለውጥ የለውም፡፡ ስለዚህ ብድር አስከፊ፣ ኑሮን የሚያናጋ ስለሆነ ከብድር ተቆጥቦ ማረስ ተገቢ መሆኑን ሲመክር በአበሻ ማሽላ ጤፍ ለመስጠት የሚደረገውን ብድር ፊፅሞ ይቃወማል፣ ያወግዛል፡፡

### 5.3.2. ገበሬን የሚያወድሱ

በዚህ ክፍል ውዳሴ ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው የራሳቸውን፣ ሚስታቸውንና ሌሎች የአካባቢው ገበሬዎች ጀግንነት ፣ ሙያና እርሻን ያወድሳሉ፡፡ የግጥሞቹን ትንታኔ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

409፡-እርሻ ያረሰና የወንዝ ዳር ዛፍ

ዘላለም ይኖራል አበባው ሳይረግፍ

/ቃለ መጠይቅ፣ ደሴ ውበት፣ ጥር 13/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ ማብራሪያ የወንዝ ዳር ዛፍ ውሃ ዳር ስለሆነ አይደረቅም፡፡ ቅጠሉ ዘላለም እንደለመለመ ሳይረግፍ ይኖራል፡፡ ወቅቱን ጠብቆ ፍሬ ያፈራል፡፡ ያየው ሁሉ በቅጠሉ ልምላሜ ሳቢና ማራኪ መሆን እየተደሰተና እየረካ፣ በፍሬውም ይጠቀማል፡፡ ቅጠሉ ለተለያየ ጥቅም ይዉላል፡፡ አራሽ ገበሬም ቤቱ ዘላለም ሙሉ ነው፡፡ ዛፍ ውሃውን እየሳበ እንደሚለመልም ገበሬውም እርሻ በማረሱ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ጠንክሮ በመስራቱና ምርታማ በመሆኑ ቤተሠቡ ጠግቦ፣ እንግዳ ተሸኝቶበት፣ ዘላለም እያቀናና እያበደረ፣ የተራበ እያበላ፣ የተጠማ እያጠጣ ከዓመት እስከ አመት ቤቱ ሳይጐልበት ይኖራል፡፡ ስራው ራሱን አኩርቶ ቤተሠቦቹን ያሰመሰግናል /ቃለ መጠይቅ፣ ደሴ ውበት፣ ጥር 13/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ አራሽ ገበሬን ከወንዝ ዳር ዛፍ ጋር አመሳስሎታል፡፡ የወንዝ ዳር ዛፍ ከልምላሜው የተነሳ ሲያዩት ይማርካል፡፡ ቅጠሉም ሆነ ፍሬው አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ገበሬውም ጠንክሮ በማረሱ ባለፀጋ ይሆናል፡፡ ባለፀጋ በመሆኑም ሲወጣ አምሮበት፣ ሲገባ ተደስቶ፣ ሰው አክብሮት፣ ያየው ሁሉ ቀንቶበት ነው፡፡ ለዚህም ነው "እርሻ ያረሰና የወንዝ ዳር ዛፍ" በማለት እርሻ ያረሰን ሰው ዘላለም የልምላሜ ፀጋ ከተጐናፀፈው የወንዝ ዳር ዛፍ ጋር ያመሳሰለው፡፡ ሁለቱም ያገኘ የሚበላቸው ፣ የሚያርፍባቸው ጠቃሚ መሆናቸውን ነው፡፡ "ዘላለም ይኖራል አበባው ሳይረግፍ" በሚለው ስንኝ ሁለቱም እንዳማረባቸው፣ እንደተዋቡ መኖራቸውን ይገልፃል፡፡

የወንዝ ዳር ዛፍ ውሃው ካልደረቀበት እንደለመለመ ይኖራል፡፡ ውሃ ለአትክልት ዋነኛው ምግብ ነው፡፡ ያለ ውሃ መኖር አይችልም፡፡ ፀሃይና ነፋሱ ሲፈራረቅበት ቶሎ ይደርቃል፡፡ ቅጠሉም ይረግፋል፣ ፍሬም አያፈራም፡፡ ይሁን እንጅ ዘላለም እንዳበበ እንዲኖር ውሃ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ ገበሬውም እስካረሰ ድረስ በደስታና በተድላ ፣ ሳይቸገር ፣ ቤቱ ሙሉ ሆኖ ፣ አምሮበት ፣ ሽርፋና ጐተራውን አስጨንቆ ፣ ክብሩን

ጠብቆ እንዲኖር እርሻው ፣ ምርቱ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ባያርስና ባያመርት እንዲህ ደስታን ማግኘት ባልቻለ ነበር፡፡ ስለዚህ ማረስ፣ ማፈስ እንደሚያኮራ ህይወትን ሙሉ እንደሚያደርግ አፅንኦት ይሠጣል፡፡

410፡-ማረሻው ሃዲድ ሞፈሩ ወይራ

ሰርዶ አራጋፊ እንደ ጨጓራ

/ቃለ መጠይቅ፣ ጥጋቡ ፈንታቢል፣ ጥር 08/2006/

ደህና ገበሬ በሞፈሩ፣ በማረሻውና እርፍ አጨባበጡ ይለያል፡፡ ሞፈሩ ወይራ ነው፡፡ ሲያርስ ውሎ ቢያድር አይሰበርም፡፡ ማረሻው በሰፊው የተሞጠሞጠ ሰርዶውን ሁሉ የሚፈነቃቅል ነው /ቃለ መጠይቅ፣ ጥጋቡ ፈንታቢል፣ ጥር 08/2006/፡፡

በዚህ ቃል ግጥም የገበሬውን የአስተራረስ ብቃት ሲየወድሰው፣ ሲየሞግሰውና ሲያደንቀው ይደመጣል፡፡ ገበሬው ሞፈርና ቀንበሩ የተስተካከለ፣ መሬቱን እየሰነጠቀ የሚሄድ መሆኑን "ማረሻው ሃዲድ ሞፈሩ ወይራ " በሚለው ስንኝ በሠፊ ማረሻና ጠንካራ ሞፈር ማረሱን ያመለከታል፡፡ "የወይራ ሞፈር" ጠንካራና ከባድ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ለእርሻ የሚመረጥ ነው፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች ተጠቅሞ ሰርዶውን እየፈነቃቀለ እንደሚጥለው ያሳያል፡፡ መሬቱን እየሰነጠቀ፣ ሰርዶው እየተነቀለ፣ ከአፈሩ እየተለየ፣ ተራግፎ ሲወድቅ ለማሳየት "ሰርዶ አራጋፊ እንደ ጨጓራ" በማለት የገበሬውን የአስተራረስ ብልሃትና ዘዴ፣ ጀግንነት፣ ስርዶ አበጣጠር፣ አመነጣጠር ከጨጓራ ማራገፍ ጋር አነፃፅሮታል፡፡ ጨጓራ በሚገባ ተራግፎ ተልጦና ታጥቦ ሲፀዳ ለምግብነት እንደሚውል ሁሉ ገበሬውም ሰርዶውን የተለቀለቀ አውድማ እስኪመስል ሙልጭ አድርጎ መንጥሮ ዘሩን ይዘራል፡፡ ቡቃያው ምንም ሳያግደው ይበቅላል፡፡ ገበሬው በሹል ማረሻ በሰፊ ድግር ከድግሩ በላይ አፈሩን ሲያፈሰው ሰርዶው ለብቻው ቁጭ ቁጭ ይላል፡፡ ለሙያውም ያለውን ምስጋናና አድናቆት ሲቸረው ይታያል፡፡

411 ፡-ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ

አይላትም ሚስቱን ብቅል ተደበሪ

/ቃለ መጠይቅ፣ ድረስ ግርማው፣ ጥር 12/2006/

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ ድረስ ግርማው ደሴ ውበት ለተባለ ጎረቤቱ የገጠመው ነው፡፡ ደሴና ድረስ በአንድ ተቀምጠው በነበሩበት ስጠይቅ ድረስ ስለደሴ በግብርና ሙያው የተመሰገነ መሆን አብራርቶ ነግሮኛል፡፡ ደሴ ጥዋት ውርጭ፣ ቀን ፀሃይ ሳይፈራ፣ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይል ይሠራል፡፡ የሚረዳው ሎሌ በማግባት ምርቱን

ያሳድጋል፡፡ ጀግና ገበሬ በመሆኑ የራሱ መሬት አልበቃው ብሎ የሰው መሬት ገዝቶ ያርሳል፣ ሳይታረስ ወድቆ የኖረውን መሬት፣ መስኩን መንጥሮ፣ ቆፍሮ፣ ቁጥቋጦውን ቆጥቁጦ፣ እሾህና አጋሙን አፍልሶ፣ ድንጋዩን ፈነቃቅሎ፣ አለሰልሶ ይዘራል፡፡ ሚስቱ ችግር አታውቅም፡፡ ከጠንካራ ገበሬ ቤት ብቅል ተበቅሎ እንዲደርቅ ጣራ ላይ ይሰቀላል፡፡ ከቤት ጠላ አይለይም፡፡ የአካባቢው ሰውም በዚያ ጨለማ ክረምት ከችግር ማቅ የሚያወጣው አበዳሪ ስለሆነ በፈቃደኝነት ስራ ይረዳዋል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ድረስ ግርማው፣ ጥር 12/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ ደሴ ውበት ጠንክሮ በማረሱ ለራሱም ለሚስቱም ኩራት በመሆኑ ምስጋናና አድናቆት ሲቸረው ይታያል፡፡ ለዚህም ነው "ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ" ሲል ከሎሌው ጋር ሲያሻውም ሰው ለምኖ ወይም ብር ከፍሎ ታርሶ የማያውቀውን፣ ለብዙ ጊዜ የቆየውን፣ ውሃ ሲጠጣ የኖረውን (እዳሪ) መሬት ያለሰልሳል፡፡ "እዳሪ" የወጣ መሬት ለብዙ ጊዜ ድፋ ሆኖ ሳይታረስ ስለኖረ የሚያመርተው ምርት እጥፍ ድርብ ነው፡፡ ምክንያቱም እርሻ አልሠለቸምና፡፡ ጠንካራ ገበሬ በመሆኑ ያርሳል ያፍሳል፣ ጐተራውን በምርት ያስጨንቃል፡፡ ቤቱ በምርት ይትረፈረፋል፣ እንደ ልቡ ዝቆ ያቃናል፣ ለቸገርው ያበድራል፣ እንግዳ ከመጣ ጠግቦ ይመለሳል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ ብቅል መበደር እንደውርደት ይታያል፡፡ ብቅል የምትበደር ሴት ያጣች የነጣች የምታበቅለው እህል የሌላት ነች፡፡ እህል እያላት በስንፍና የምትበደር ከሆነ ሽሙጥጫውና ስድቡ አይጣል አያድርስ ነው፡፡ ያም ስለሆነ የደህና ጐበዝ ሚስት እህሉ ካላት፣ ከሞላ ከተረፈው ጐረድ ጐረድ አድርጋ ታበቅላለች፡፡ ከሀብታም ቤት ብቅል አይጠፋም፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ጠላ ይደርሳል፡፡ ከቤቱ ጠላ እንዲጠፋ አይመከርም፡፡ በመሆኑም ብቅል ተበቅሎ ከቤቱ ጣሪያ ላይ በገመድ ተንጠልጥሎ ጭስ እንዲያደርቀው ይደረጋል፡፡ ከአራሽ ገበሬ ቤት እንግዳ ሲመጣ በፍጥነት ቀና ብሎ የሚመለከተው ብቅል መሰቀሉን ነው፡፡ ብቅል መስቀል ጀግና ገበሬ መሆኑ የሚታወቅበት ሌላኛው መንገድ ነው፡፡

በመሆኑም "አይላትም ሚስቱን ብቅል ተበደሪ" በማለት አራሽ እንደፍራሽ የጠገበ ገበሬ ሰለሆነ ምርቱን እያመጣ ሰለሚረገርገው፣ የምታበቅለው አታጣምና ማብቀል ትችላለች፡፡ በተቃራኒው ሰነፍ ባል ያላት የእለት የእለቷን ንፁህ የለ ግርድ ከእጅ ወደ አፍ ሰለሚጠቀሙባት ማብቀል አትችልም፡፡ ጠላ ማድረስ ብትፈልግ

ትገዛለች ወይም ከሀብታም ቤት ትበደራለች፡፡ ጠንክሮ መስራት የሚያስመሰግንና የሚያስደንቅ ከራሱ አልፎ ለወገን ዘመድ የሚያኮራ መሆኑን አፅንኦት ይሠጣል፡፡

412፡-የነቃች ሚስት ያለው ማለዳ ቀስቃሽ
ከአንድ አንድ አውድማ ላይ መቶ መቶ አፋሽ
/ቃለ መጠይቅ፣ አዳነ የማታው፣ ጥር 13/2006/

የዚህ ቃል ግጥም ተናጋሪ አዳነ የማታው በቃል ግጥሙ ያወደሳት፣ ያሞገሳት፣ ያደነቃት ሚስቱን ነው፡፡ ሚስቴ በጥዋት ወገግ ሲል ተነሰታ ከብቱን ፊትታ ገለባ ሰጥታ እኔንም ለስራ እንድዘጋጅ ትቀሰቅሰኛለች፡፡ ወለፏን ጠራርጋ ምሳዋን አዘጋጅታ በአገልግሏ ቋጥራ ወስኮ ተሸክማ አጣምዳኝ ትመለሳለች፡፡ በአረሙ፣ በጉልጓሎው፣ በአጨዳው፣ ውቂያና እርሻው ወገቧን ታጥቃ ስትሠራ ትውላለች፡፡ ማታም ለከብት እሳር አጭዳ ተሸክማ አምጥታ ታበላለች፡፡ የቤቱን ስራም ታከናውናለች፡፡ ስራ በቀዝቃዛ ነው እንስራ ስለምትለኝ ታበረታታኛለች፡፡ አብራኝ ወጥታ ትገባለች፡፡ ተባብረን ስለምንሰራ ቤታችን ሙሉ ነው /ቃለ መጠይቅ፣ አዳነ የማታው፣ ጥር 13/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተገለፀው አዳነ በጥዋት ተነስቶ በቀዝቃዛ ፀሃይ ሳይበረታ ስራውን ገፋ ገፋ አድርጎ በጊዜ እንዲጨርስ ሚስቱ ታነሳሳዋለች፡፡ "የነቃች ሚስት ያለው ማለዳ ቀስቃሽ" በሚለው ስንኝ ሚስቱ ታታሪ፣ ስራ እንሰራ በማለት የምታበረታታው በመሆኑ በጥዋት ተነስቶ ወደስራ ሊሰማራ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ተኝቶ አያረፍድም፡፡ በእነሱ ቤት ፀሃይ ይሙቅ፣ ውርጭ ይርገፍ የለም፡፡ ጠንክረው በመሰራታቸው ምርታማ ናቸው፡፡ "ከአንድ አንድ አውድማ ላይ መቶ መቶ አፋሽ" በሚለው ስንኝ ታታሪ ሚስት ስላለችው ተባብረው ስለሠሩ በምርት መትረፍረፋቸውን ነው የገለፀው፡፡ ከአንድ አንድ አውድማ ላይ የሚይወጣው ምርት አስር አስር ኩንታል ነው፡፡ የተሻለ ምርት አገኙ ሀብታም ባለ ፀጋ ሆኑ ማለት ነው፡፡ በግጥሙ ንቁና ታታሪ ሚስት ያለው ተጠቃሚ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ሴቶች በግብርና ሙያ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ችላ ሊባል የማይገባ መሆኑን አፅንኦት ይሠጣል፡፡ ይህም "ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" የሚለውን አባዊ ስርዓት የሚገነባ አባባል የሚሽር ነው፡፡ ግጥሙ የሴቶችን እኩልነትና ተደማጭነት ያሳያል፡፡ የተሟላ ኑሮ ለመኖር በሀብትና ንብረት ለመበልፀግ ታታሪ ሚስት ማግባት ያሻል ሲል ምክሩን ይለግሳል፡፡

### 5.3.3. ምክር የሚሰጡ

ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው ይመክራሉ፣ ያስተምራሉ፣ ይገስፃሉ፡፡ ከሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች ስለ እርሻ አስፈላጊነትና ጥቅም፣ በህብረት መስራት፣ ጠንክሮ መስራት አስፈላጊነት፣ የስንፍና፣ የብድር፣ የስደት፣ የሙስና መጥፎነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

453፡- ስታርስ እደርና እዚያው ስታርስ እደር
እርኩስ የጠላውን ጓያ ከመበደር
/ቃለ መጠይቅ፣ ጥጋቡ ፈንታቢል፣ ጥር 08/2006/

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ ጓያ ከመበደር ሌት ተቀን ሲያርሱ መዋል ማደር የሚበጅ መሆኑን ይመክራል፡፡ ጓያ መበደር አብዛኛው ሰው ስለማይጠቀመውና ለፈረስና አህያ ቀለብ ሰለሚያደርገው እርኩስ ሊያሠኝ ሊያሰድብ እንደሚችል አብራርቷል፡፡ በቃል ግጥሙ ማረስ ማፈስ፣ ጀግንነት፣ ኩራት የተለካው ሌት ተቀን በመስራት ነው፡፡ "ስታርስ እደርና እዚያው ስታርስ እደር" በማለት ደከመኝ ፣ ሰለቸኝ ፣ ሳይሉ ሌት ተቀን መስራት ከውርደት ፣ ከችግር ፣ ከንቀት የሚያወጣ መሆኑን የገለፀው፡፡ ካልሆነ ግን ማጣት ነውና ሰው የማይበላውን ጓያ ይበደራል፡፡ "እርኩስ የጠላውን ጓያ ከመበደር" በማለት ጓያ መበደር ምን ያህል አዋራጅ፣ አሰዳቢ፣ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

ጓያ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ከሚያመርቷቸው የምርት አይነቶች አንዱ ነው፡፡ ጓያ ጠንካራ ሰራተኛ ስለሚፈልግ አብዛኛው ሰው አይወደውም፡፡ ጠንካራ ሰው ካልያዘው ይሠብራል፣ አካልን ያወላግዳል፡፡ በአብዛኛው ለምግብነት የሚጠቀሙት የቸገራቸው ናቸው፡፡ ከህብታም ባለፀጋ ቤት ለፈረስና ለአህያ ቀለብ ነው የሚሆነው፡፡ አህያና ፈረሰም ጠልተውት፣ አልበላው ብለው ገለባ ሲመርጡ ይታያል፡፡ ለዚህም ነው እርኩስ የጠላውን ጓያ ከመበደር በማለት ከሠው አልፎ አህያና ፈረስ የማይበሉትን፣ እንደምግብነት የማይቆጥሩትን፣ ጓያ መበደር ምን ያህል ውርደትና በአካባቢው ማህበረሰብ የሚየስተች እንደሆነ የገለፀው፡፡ እርኩሰ የማይበላውን ከዚያም አልፎ የጠላውን ጓያ መበደር "እርኩስ" የሚያሰኝ የሚያሰድብ መሆኑን ገልፆ እርሻ ማረስ፣ ሌት ተቀን ሳይሉ ጨለማ ሳይገድበው መስራት የሚሻል መሆኑን አፅንኦት ይሰጣል፡፡

454፡- ማረስ ነው እንጅ ሸንጥ እስኪቆስል
ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል

/ቃለ መጠይቅ፣ ቢምር ሞላ፣ ታህሳስ 26/2006/

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ስርቆትን በማውገዝ የማረስን አስፈላጊነት ይመክራል፡፡ በቃል ግጥሙ ማረስ የተለካው ሽንጥ እስኪቆስል እየተጐዱ ጠንክሮ በመስራት ነው፡፡ ገበሬው እርፉን በእጁ ጨብጦ ግፋ ሲል እርፉ ጐን ጐኑን ሽንጥ ሽንጡን እያለ ያቆስለዋል፡፡ "ማረስ ነው እጅ ሽንጥ እስኪቆስል" ሲል ያለውን ችግር ተቋቁሞ፣ እየታመመ፣ እየደከመ፣ መስራት የሰው ንብረት አያሳይም፣ ለውርደት አይዳርግም ሲል ነው፡፡ ገበሬ እየተልኮሰኮሰ የማያርስ፣ ወይኔ ሽንጤን አመመኝ ብሎ ምራን የሚፈታ መሆን የለበትም፡፡ "በአካባቢው ማህበረሰብ የሚሠርቀው ምርቱ ክምሩ ያነሰበት ለዓመት ቀለብ ስለማይበቃው ከሰው ክምር፣ ነዶ እያነሳ ወደ ራሱ ይጨምራል፡፡ ንብረቱ አስመስሎ ወቅቶ ያስገባል፡፡ ይህ አይነቱ ገበሬ የታወቀ ነው፡፡ ቢያመርትም አመረተ ፣ የልፋቱን ዋጋ አገኘ የሚለው የለም፡፡ የማንን አንጀት ቆረጠው እንጅ፡፡ "ውሻ ያየ በልጥ ደነገጠ" እንዲሉ ሰው ባየ ቁጥር አየደነገጠ ይኖራል፡፡ "ሰው እንኳን በስራው በወሬው ይመሰገናል" እንዲሉ ማረስ በጀግንነቱ ለዝምድና፣ ለአበልጅነት፣ አብሮ ለመብላትና ለመጠጣት ያስመርጣል፡፡/ቃለ መጠይቅ፣ ቢምር ሞላ፣ ታህሳስ 26/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ የስርቆት ህይወት አካላዊና ሰነ-ልቦናዊ ችግር ሊያደርስበት እንደሚችልና ባህሪውን ማስተካከል እንዳለበት "ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል" በማለት የሚሰርቅ ውሻ ነው እንደውሻ መስረቅን ያወግዛል፡፡ መስረቅ እንደሌለበት ምክር ይለግሳል፡፡ ሰርቆት እንደ ልብ አያናግር፣ ከሠው ፊት አያስቆምም ብሎም ቤተሠብ፣ አባት፣ ወገን ዘመድ ዘርን ያሰድባል፤ ያስገድላልም፡፡ ስለዚህ ማረስ ራስን ከውርደት ነፃ አድርጎ በሰላም ለመኖርና ህይወትን በተሻለ ሁኔታ ለመምራት ወሳኝ መሆኑን አፅንኦት ይሠጣል፡፡

455 ፡- እህል ዝሩ ዝሩ በየገደሉ ስር
በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር

/ቃለ መጠይቅ፣ ጥጋቡ ፈንታቢል፣ ጥር 08/2006/

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ገበሬው ገደሉን አፍርሶ፣ ዱሩን መንጥሮ፣ ቆፍሮ መዝራት እንዳለበት ይመክራል፡፡ ገበሬው ጥንጫውን፣ ገደሉን፣ ዱሩን መንጥሮ፣ አቃጥሎ፣ አለስልሶ ቢዘራ ምርቱን ያሳድጋል፡፡ "እህል ዝሩ ዝሩ በየገደሉ ስር" በሚለው ስንኝ በአፋፉም፣ በገደሉም በጫካውም በበሬ ባይቻል ቆፍሮ መዝራት አስፈላጊ መሆኑን

ነው የገለፀው፡፡ ምርታማና ውጤታማ ከሆነ ቤቱ ሞልቶ ከቀለብ ተርፎ አቅንቶ የጐደለውን ነገር ማሟላት ይችላል፡፡ "በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር" በማለት ገደል ደልዳላ ሳይሉ ካረሱ በቀላሉ በትንሽ ምርት በቅሎ መግዛት የሚቻል መሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በቅሎ የሚገዛው በጣም በውድ ዋጋ ነው፡፡ ጠንክሮ ያላረሰ ሰው ደግሞ እንኳን በቅሎ ዶሮ መግዛት አይችልም፡፡ ጠንክሮ ያረሰ ግን ምንም እንኳን በቅሎ በቀላል ዋጋ የማይገዛ ቢሆንም አፋፉን ገደሉን አርሶ ምስር ከዘራ በውድ ዋጋ በማቅናት መግዛት ይችላል፡፡ በአንድ ቁና ምስር በቅሎ ተገዛ ማለት ምስርም እንደ በቅሎ ተወዷል፣ ዋጋው ጨምሯል ማለት ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ በቅሎ የሚገዛ ሰው መኪና እንደገዛ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ገበሬ የትም ይሁን የት ሳያማርጥ፣ ቢችል በበሬ ባይችል በዶማ ቆፍሮ ማረስ የሚበጀው መሆኑን አፅንኦት ይሰጣል፡፡

### 5.3.4. የገበሬን ተስፋ የሚገልፁ

በዚህ ክፍል ተስፋን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ብሶትና ምሬታቸውን እንደሚገልፁ ሁሉ ተስፋቸውንም ይገልፃሉ፡፡

506፡-አምላክ ቢሻ ቢሻ ጌታ ቢሻ ቢሻ
ሳይዘራ አይቀርም የተገመሰ እርሻ
/ቃለ መጠይቅ፣ ተበጀ በየነ፣ ጥር 12/2006/

ይህ ቃል ግጥም በተበጀ በየነ ጥር 13/2006 ቤታቸው የተዜመ ነው፡፡ የገበሬ ኑሮ ሁል ጊዜም አይሟላ ዘሩ ሲኖር በሬው በሬው ሲኖር ዘሩ ይጎላል፡፡ አጣሁ ብሎ ተስፋ አይቆርጥም፡፡ አላህ አያሳጣውም፡፡ በሬም ይለምናል ፣ ዘርም ቢያጣ ቢያጣ በወለድ ተበድሮ ይዘራል /ቃለ መጠይቅ፣ ተበጀ በየነ፣ ጥር 12/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ ሁሉም ነገር የአምላክ ፈቃድ መሆኑን በተስፋ መጠበቅ ወሳኝ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ "አምላክ ቢሻ ቢሻ ጌታ ቢሻ ቢሻ" በሚለው ስንኝ "ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈፅማል" እንዲሉ የታሰበው ሁሉ፣ የታቀደው እቅድ ስኬታማ ሆኖ ከግብ የሚደርሰው አምላክ ከፈቀደ ነው፡፡ ያለ እግዚብሄር ፈቃድ ምንም መስራት እንደማይቻል ያስገነዝባል፡፡ ገበሬው አምላክን አምኖ ዘር ሳይኖረው፣ ሳያስቀምጥ መሬቱን ያለሰልሳል ፣ ያዘጋጃል፡፡ በሙሉ እምነት ተስፋውን ከአምላኩ ላይ ያደርጋል፡፡ እንደማያሳጣው ይረዳል፡፡ "ሳይዘራ አይቀርም የተገመሰ እርሻ" በማለት እግዚአብሄር ቢፈቅድ መሬቱ ውሃ ጠጥቶ፣ ዳዋ ለብሶ እንደማይከርም ተስፋ

ያደርጋል፡፡ በግጥሙም ሁሉም ነገር የአምላክ ፈቃድ መሆኑን አምላክን ተስፋ ማድረግ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል፡፡

## 5.4. የአረም ቃል ግጥሞች

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በአጨዳ፣ ውቂያና መሰል የስራ አጋጣሚዎች እንደሚያንጐራጉሩ ሁሉ በአረም ወቅትም የተለያዩ ቃል ግጥሞችን ይገጥማሉ፡፡ በቃል ግጥማቸው ከሚያነሷቸው ጉዳዮች ምሬትና ብሶት ፣ ትችት ፣ ውዳሴ፣ ምክር ፣ ፍቅርና ፀፀት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 5.4.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

በዚህ ክፍል ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው ከስራው አድካሚነት በተጨማሪ ሰነፍ ባል በማግባታቸውና መሰል ጉዳዮች ሲያማርሩ ይሠማል፡፡

507፡- የጓሮየን ስንዴ አረም ተናነቀው
እባክህ ጌታዬ ባልባሉን አላቀው
/ቃለ መጠይቅ፣ ደሴ ውበት፣ ጥር 13/2006/

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ ደሴ ውበት ግጥሙ በሁለት መልኩ ይገጠማል፡፡ አንድም የበዓላት በተከታታይ መከሠት በሰራው ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመግለፅ ሲሆን አንድም ሰነፍ ባል እንደማያስፈልግ፣ ከሰነፍ ባል ብቻን መኖር እንደሚሻል ምሬትና ብሶት የሚገልፅበት ነው፡፡ ቃል ግጥሙን የምንገጥመው አረሙን ቶሎ ቶሎ ልናርም ስንጓጓ በዓላት ስለሚዘጉት ነው፡፡ የጓሮ አዝመራ ጥዋት ማታ፣ ወጥቶ ገብቶ ከሚስት ጋር ስለሚታረም አረሙ ቶሎ ቶሎ ይሞላልና ያስቸግራል፡፡ በዓል እንዳንሸር ክልክል ነው ሲል አብራርቶልኛል /ቃለ መጠይቅ፣ ደሴ ውበት፣ ጥር 13/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው የጓሮ አዝመራ ጥዋት ማታ ወጥቶ ገብቶ ባልና ሚስት የሚያርሙት ነው፡፡ ጠንካራ ባልና ሚስት የስራ ጉጉት ስላላቸው ሁልጊዜም ስራ ቢሆን ይመርጣሉ፡፡ ከስር ከስር እየተከተሉ የሚበቅለውን አረም እህሉን ሳይጐዳው በሰዓቱ ነቃቅሎ መልካም ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ ይሻሉ፡፡ ነገር ግን የጓሮ እህል መሬቱ ወፍራም ስለሚሆን አረሙ በፍጥነት ስለሚወጣ አንድ ቀን ቢያድር እህሉን እስከ ወገቡ ይጠመጠምበታል፡፡ “የጓሮየን ስንዴ አረም ተናነቀው” በማለት እህሉ በአረም ተሸፍኖ፣ ተውጦ፣ በተከታታይ በዓል መሆኑ የፊት የፊቱን እንዳይነቅሉት

አድርጎታል፡፡ በዓል እንደማይሻር በሀይማኖት የተከለከለ ውግዝ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ቢሠሩም አንድ ቅጣት እንደሚያርፍባቸው ያስባሉ፡፡ ህግና ተዕዛዙን መጣስ አይፈልጉም፡፡ "እባክህ አምላኬ ባልባሉን አላቀው" በሚለው ስንኝ ብሶትና ምሬት በተሞላበት ድምፅ አምላካቸውን ይማፀናሉ፡፡ ተማፅኖውም ስራ እንዲሆንላቸውና አረሙን አርመው ጥሩ ምርት እንዲያገኙ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ አንዷት ሴት የማይሰራ ሰነፍ ባል ካላት እሱን ለማናደድ ትገጥመዋለች፡፡ ያገባችው ባል ጥዋት ውርጭ ማታ ብርድ የሚፈራ ሰነፍ ይሆንባታል፡፡ አያርም፣ አይኮተኩት ተኝቶ ሲያንኮራፋ ያረፍዳል፡፡ ጥዋት ማታ ወጥታ ገብታ ብቻዋን ስንዴዋን ታርማለች፡፡ ከዚህ መሃል በዓላት ይመጡና የስራ ቀን ይዘጋባታል፡፡ ስንዴውን አረሙ ሳይበላው ቶሎ ቶሎ ማረም ትፈልጋለች፡፡ ግን አልቻለችም፡፡ የሚረዳት የለም ብቻዋን ትባዝናለች፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብም ባል ካላት አይረዳም፡፡ ለምን ለሠነፍ እሰራለሁ ነው የሚለው፡፡ እስከ ወገቡ ሲተናነቀው ትናደዳለች፡፡ እርሱ ከሌለ ለምና ወይም ጀግና ባል አግብታ አንደምታሰራው ታሰባለች፡፡ ያ ካልሆነ የሚረዳት እንደማታገኝ ከባህሉ ትረዳለች፡፡ ለዚህም ነው "እባክህ አምላኬ ባል ባሉን አላቀው" ስትል በሰነፍ ባል የተመረረችው ሴት ምን ጊዜም አልሠራልይ፣ ሠርቶ አላበላይም፣ ተቀምጦ እየዋለ፣ ለምን ባል አላት ያሰኘኛል፡፡ ስሙ ባል ይሁን እንጅ ባል አይደለም አልፈለገውም ስትል ሀዘን በተሞላበት ድምፅ ብሶትና ምሬቷን ለአምላኳ ታሰማለች፡፡ ብቸኛ ሆና መኖር እንደምትችል አሁንም ብቸኛ እንደሆነች ምን ይሰራል፣ አላቀይ ስትል ትማፀናለች፡፡ በቃል ግጥሙ ሴት ልጅ ያለ ወንድ መኖር እንደምትችል በማስገንዘብ እማዊ ስርዓቱን ታፀናለች፡፡

508፡- አረ ተው አምላኬ ፊትህን አዙርልኝ
አርሜ ኮትኩቼ ጥቅሙ እንዲበዛልኝ
/ቃለ መጠይቅ፣ ውቤ ዘውዱ፣ ጥር 04/2006/

በዚህ ቃል ግጥም እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ ማብራሪያ ገበሬው አምላኩን ሲያማርር ይሠማል፡፡ ፈጣሪ ፊት እንደነሳው፣ እንዳሳጣው፣ እንደ ጨከነበት በማድረግ በምሬት "ኧረ ተው አምላኬ ፊትህን አዙርልኝ" በማለት ፊቱን እንዲመልስለት ምሬት በተቀላቀለበት ድምፅ ይለምናል፡፡ አምላክ ፊቱን አዙሮበት ሳይሆን በራሱ ድክመት ያጣውን ነገር በምክንያት በመደበቅ ለማምለጥ ነው፡፡ ገበሬው ማረም፣ መኮትኮቱን እንጅ መሬቱን አለስልሶ፣ አስልቶ በሚገባ ቢያርሰው ምርታማ መሆኑ የማይካድ ነው፡፡

ነገር ግን በስንፍናው የአካባቢው ሰው እንዳይዘባበትበት አምላክ አሳጣኝ፣ ነሳኝ ሲል ይናገራል፡፡ ልመናውም ምርታማ ሆኖ፣ የሥራው ሁሉ ረድኤትና በረከት እንዲወርድበት ነው፡፡ በመሆኑም ገበሬው ራሱ በስንፍናው ያጣውን ነገር ለማጣቱ፣ ለመቸገሬ ምክንያት አንተ ነህ በማለት የማያደላውን አምላኩን በከንቱ ሲያማርር ይደመጣል፡፡

### 5.4.2. ትችትን /ስድብ/ የሚገልፁ

በዚህ ክፍል የትችት ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው እንደሚያወድሱና እንደሚመክሩ ሁሉ ያዩትንና የሰሙትን እኩይ ተግባር ደግሞ ይተቻሉ፡፡ የግጥሞቹን ትንታኔ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

517፡- ወይ አርመህ አብላት ወይ አንተ ሙትላት

ሰነፍ ባል አግብታ ምነው ባታሰኛት

/ቃለ መጠይቅ፣ ገብሬ መንግስቱ፣ ጥር 14/2006/

የቃል ግጥሙ ደርዳሪ ተቀምጦ እየዋለ በስንፍናው ሚስቱን የአገር መዘባበቻ የሚያደርግን ገበሬ ያወግዛል፡፡ በስንፍናው ከራሱ አልፎ ሚስቱን ያሰድባልና፡፡ በስንፍና ከጥላው ቁጭ ብሎ፣ ቡና ሲያስፈላ፣ አፋፍ ላፋፍ ሲዞር ቀኑን ይገፋዋል፡፡ የዘራውን አያይም፤ የደረቀውን አያጭድም፤ አረም በእህሉ ላይ ተንሳፎበት እያየ ተቀምጦ ይውላል፡፡ ሚስቱ እጅና እግሩን አጣፍፎ አይን አይኗን ቢያያት የምታቀርበው ታጣለች፡፡ በችግር መጫኛ ትገረፋለች፡፡ "ወይ አርመህ አብላት ወይ አንተ ሙትላት" በሚለው ስንኝ ባል እያላት መቸገር የለባትም ሰርተህ አብላት ካልሆነም ራስህን አጥፋ፣ ተለያት ሲሉ ከሁለት አንዱን መምረጥ እንዳለበት ያስጠነቅቁታል፡፡

ሚስቱ የባዕድ፣ የዘመድ፣ የጐረቤት መዘባበቻ ሆና ስትሰደብ፣ የጓደኛ ታናሽ ሆና መኖር እንደሌለባት "ሰነፍ ባል አግብታ ምነው ባታሰኛት" ሲሉ የተቸገረችው፣ የተዋረደችው ሰነፍ ባል በማግባቷ ነው፡፡ እባክህ አታሰድባት፣ አታስወቅሳት በማለት ምሬቱን ይገልፃል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ አንዲት ሴት ባል ካላት ብትቸገር፣ ብትራብ፣ ብትጠማ የሚረዳት፣ የሚያዝንላት የለም፡፡ ህዝቡ የሚራራው ባል ከሌላትና ከሞተባት ነው፡፡ ሰነፍ ባል አግብታ ከተቸገረች ለምን አትፈታውም እያለ ይጐነድላታል፡፡ ሰለዚህ ጠንክረህ ካልሰራህ ፍታትና ለምና ወይም ደህና ባል አግብታ ከችግር ትላቀቅ ሲል ልመና በተቀላቀለበት ድምፅ ምሬቱን ይገለፃል፡፡

### 5.4.3. ምክር የሚሰጡ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው እኩይ ተግባራትን እንደሚያወግዙና እንደሚተቹ ሁሉ መልካም ነው፣ ይጠቅማል ለሚሉት ጉዳይ ደግሞ ምክር ይለግሳሉ፡፡ በቃል ግጥሞቹም ጠንክሮ መስራት፣ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ ተባብሮ መስራት፣ የፈተናን መቋቋም አስፈላጊነት፣ የብድርን አስከፊነትና መሰል ጉዳዮች በማንሳት በማስጠንቀቅ፣ በማስገንዘብ፣ በመገሰፅ አቀንቅነዋል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

528፡- አርመህ ኮትኩተህ ካልሠራህ በመላ
ኋላ ተቸግረህ አሉማ እንዳትበላ
/ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ተሻገር፣ ታህሳስ 26/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ በሰዓቱ ያልሠራ፣ ያልከወነ ገበሬ መጨረሻው በርሃብ መገዛት የርሃብ ሎሌ ሆኖ መሰቃየት ነው፡፡ በወቅቱ ብርዱ፣ ጭቃው፣ ጤዛው እያለ ካልሠራ፣ ያረሰውን ካላረመው፣ አረም ይውጠውና ሳያፈራ ከስሮ ይቀራል፡፡ ሲያጣም ሰው የማይበላውን አሉማ ቅጠል ይበላል፡፡ ጠንክሮ ከሰራ ግን አይቸገርም /ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ተሻገር፣ ታህሳስ 26/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው ገበሬዎች የትንቢት ቃል ግጥሞችን በመግጠም በሰዓቱ ያልሰራ ገበሬ ወደፊት ምን እንደሚጠብቀው በመጠቆም አስጠንቅቀው ይመከራሉ፡፡ ገበሬ በሰዓቱ በደንብ ጠንክሮ ካልሰራ ሊቸገር እንደሚችል "አርመህ ኮትኩተህ ካልስራህ በመላ" በማለት በብርታትና በጥንካሬ ካልሰራ ከፊቱ ተደቅኖ የሚጠብቀው በርሃብ አለንጋ መገረፍ መሆኑን "ኋላ ተቸግረህ አሉማ እንዳትበላ" በሚለው ስንኝ ካልሰሩት ችግር መምጣቱ እንደማይቀር፣ ከመቸገር፣ ከመራቡ በፊት መስራት እንዳለበት ያስጠነቅቀዋል፡፡ ጉልበቱን አጣጥፎ ለማረምና ለመኮትኮት ጭቃና ውርጭ የፈራው ገበሬ የሚበላው ሲያጣ የማይበላውን የአረም አሉማ ቅጠል ለመንቀል ይወጣል፡፡ "አሉማ" ማለት በክረምት ወራት በጣም የቸገረው፣ ጐመን ያጣ ሰው የሚበላው መራራ ቅጠል ነው፡፡ የባሰበት ካልሆነ ቢቸግረውም ጐመን ፈልጐ፣ ለቃቅሞ ይበላልእንጅ አሉማ አይበላም፡፡ ይህ ገበሬ አሉማውንም በቀላሉ አያገኘውም የሰው አዝመራ ለውሶ፣ ወይም የታረመውን አገላብጦ ለይቶ ካልሆነ" /ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ተሻገር፣ ታህሳስ 26/2006/፡፡ ገበሬ በስንፍናው በወቅቱ ካልሰራ የኋላ ኋላ እድል እጣ

ፈንታው አሉማ መብላት እንደሚሆን አስቀድሞ በማስጠንቀቅ በወቅቱ ጠንክሮ መስራት ተገቢ መሆኑን አፅንኦት ይሠጣል፡፡

529፡- አዝመራውን ሁሉ አረም እንዳይበላው
ሴትም ሆነ ወንዱ ጠንክሮ ማረም ነው፡፡
/ቃለ መጠይቅ፣ ስምሙ ነጋሽ፣ ጥር 04/2006/

በዚህ ቃል ግጥም ተባብሮ መስራት አስፈለጊ መሆኑን ይመከራል፡፡ እንደ ቃል ግጥም ደርዳሪው ማብራሪያ ገበሬ የተዘራውን እህል አረም እንዳይበላው፣ ፍሬ እንዲያፈራለት የፊት የፊቱን ማረም አለበት፡፡ "አዝመራውን ሁሉ አረም እንዳይበላው" ሲል በአረም ከመጠቃቱ ከመጥፋቱና ለችግር ከመጋለጡ በፊት ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ይጠቁማል፡፡ ለዚህም መፍትሄው ተባብሮ መስራት መሆኑን "ሴትም ሆነ ወንዱ ጠንክሮ ማረም ነው" በማለት ሴት ወንድ ሳይሉ በጥንካሬ፣ ተባብሮ መስራት ስራን እንደሚያቃልል፣ ምርታማና ውጤታማ ለመሆን እንደሚያስችል ያስረዳል፡፡ አረምን የሚያርመው ወንድ ብቻ ሳይሆን ሴትም ማረም እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡

በቃል ግጥሙ "አረምን" የሰው ባህሪይ የሆነውን መብላት በማላበስ እንደ ሰው እንደሚበላ በማድረግ በሰውኛ ዘይቤ አቅርቦታል፡፡ ከሆድ የገባ፣ የታኘከ ምግብ እንደማይመለስ አረምም አዝመራውን ከበላው ልክ ታኝኮ ከሆድ እንደገባ ምግብ ማለት ነው፡፡ አረም የበላው ያቀጨጨው አዝመራም መመለሻ የሌለው መሆኑን በመጠቆም እህሉ በአረም ከመበላቱ፣ ከመጎዳቱ በፊት ሴት ወንድ ሳይሉ ጠንክሮ መስራት ተገቢ መሆኑን አፅንኦት ይሠጣል፡፡

### 5.4.4. ገበሬን የሚያወድሱ

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ሌሎችን እንደሚተቹ ሁሉ ራሳቸውንና ሌሎች ሙያቸው፣ ባህሪያቸውና መሰል ጉዳዮቻቸው ያስደሰታቸውን ገበሬዎች ያሞግሳሉ፡፡ ቀጥሎ የግጥሞቹን ትንታኔ እንመለከታለን፡፡

520፡- አረሜን አርሜ ፈሰስ ሳስጨንቅ
የማናት ልጅ ብሎ መጣ ሊጠይቅ
/ቃለ መጠይቅ፣ ብትወጣ ኪዴ፣ ጥር 12/2006/

ዕለቱ ማክሰኞ ነበር፡፡ ሽሃ በተባለ ጎጥ ከእስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች መረጃ ስሰበስብ ከቆየሁ በኋላ ከዚያው ትንሽ ወረድ ብሎ ድረስ ግርማው የተባለ ገበሬ

መረጃ ሊሰጠኝ እንደሚችል ነገሩኝ፡፡ እርሱም የምፈልገውን መረጃ ሰጥቶኝ በጭዋታ ጭዋታ ከሴትምኮ ጠንካራ ገበሬዎች አሉ ከዚህም ከፈለግሽ ብትወጣ ኪዴ የምትባል እንደወንድ የምታርስ ሴት አለችልሽ አለኝ፡፡ ከዚያም ከመስክ ረዳቴ ጋር ወደቤቷ ይዞን ሲሄድ በሰላም ተቀብላ አስተናገደችን፣ እያሳቀች መረጃውን ስትሰጠኝ ፎቶና ቀረፃውን ከለከለችኝ፡፡

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ብትወጣ ኪዴ እንዲህ ስትል አጫውታኛለች፡፡ እኔና ባለቤቴ እኩል ነው የምንሰራው፡፡ ስሰራ የሴት የወንድ አልልም ሁሉንም ስራ አግዘዋለሁ፡፡ እሱ ንግድ ይነግዳል፡፡ ንግድ ሲሄድ ያለውን ስራ ከልጆቹ ጋር ስሰራ እቆየዋለሁ፡፡ የአካባቢው ሰው ብዙ ሴቶች ስለማያርሱ እኔን አያጅራት እያለ ያደንቀኛል፡፡ አንድ ጊዜ ባለቤቴ ንግድ ሂዶ ከልጆቹ ጋር ጤፍ ሳርም ቆየሁና ሳስበው ዝናብ ከጣለ እህሉ ሊደመሰስ ሆነብኝ፡፡ በወቅቱ ልጆቹ ለማረስ አልደረሱም ነበር፡፡ ልጆቹ በሮቹን አጣመዱኝና ውሃው ቁልቁል እንዲፈስ ገመስ ገመስ አድርጌ በሮቹን ፈታናቸው፡፡ ከርቀት ያየኝ አንድ ሰው መጣና ሰላምታ ሰጥቶኝ፣ የማን ልጅ እንደሆንኩ ጠይቀኝ፡፡ ነገርኩትና ዘርሽ ይባረክ ብሎ መርቆኝ ሄደ፡፡ ከባለቤቴ ጋር ተጋግዘን ስለምንሰራ ቤታችን ሙሉ ነው፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ብትወጣኪዴ፣ ጥር 12/2006/፡፡

ከቃል ግጥሙ እንደምንረዳው በግብርና ስራ ላይ የምትሳተፍ ሴት ተመልካቿ ብዙ ነው፡፡ ያየው ሁሉ ምስጋናና አድናቆት ይቸራታል፡፡ ጠንካራዋ የሴት ገበሬ ብትወጣ ኪዴ ባለቤቷ ቢኖር ባይኖር ከስራዋ ዘነፍ አትልም፡፡ ወገቧን ታጥቃ በጥዋት ወደ አረሟ ትገባለች፡፡ እህሉ ፍሬ እንዲያፈራ አረሙን አርማ ስትጨርስ የታረመውን እህል ዝናብ ሲዘንብ ጐርፍ እንዳይደመስስባት ልፋቷ ከንቱ እንዳይሆን ለጐርፍ መውረጃ የሚሆን ፈሰስ በመቅደድ እንደ ልቡ እንዲወርድ ታደርጋለች፡፡ “እርሜን አርሜ ፈሰስ ሳስጨንቅ” ስትል ከአረም በኋላ አብዛኞቹ ሴቶች የማይደፍሩትን በሬ ጠምዳ ግባ በማለት ፈሰሱን ሰንጠቅ ሰንጠቅ ማድረጓን ገልፃለች፡፡ ሴት ልጅ እንኳን እርሻ በአረም ትመሰገናለች፡፡ አላፊ አግዳሚው የማናት ልጅ፣ የማናት ሚስት እያለ እየጠየቀ፣ እያደነቀ ይሄዳል፡፡ ለጋብቻና ለዝምድና ትፈለጋለች፡፡ “የማናት ልጅ ብሎ መጣ ሊጠይቅ” በማለት በስራዋ፣ በጥንካሬዋ በመደነቅ ገስግሶ መጥቶ ዘሯን፣ ወላጆቿን ለማወቅ መሻቱን ትገልፃለች፡፡

በካባቢው ማህበረሰብ ለትዳር የምትፈለግ ሴት የቤት ሙያ ብቻ ሳይሆን በግብርና ስራም ተሳትፎ ያላት መሆን አለበት፡፡ ወንዶች ይበልጥ የሚፈልጉት

በግብርና ስራው ጠንካራ እንድትሆንና አብረው ወጥተው ገብተው በመስራት ምርታማ ሆነው ቤታቸው እንዲቀና ነው፡፡ የቤቱ ስራ ጠፍቷት አይቀርም ብለው ያምናሉ፡፡ በግብርና ሙያው ላይ ጠንካራ ታታሪ ሴት ከሆነች ትወደሳለች፤ አላፊ አግዳሚው አየ ዘርሽን ይባርከው እያላት ያልፋል፡፡ ያየው ሁሉ ያከብራታል፤ ተናግራ ማሰማት ትችላለች፡፡ ስለዚህ በቃል ግጥሙ ገጣሚዋ ራሷን በማወደስ ሴት ልጅ ሴትነቷ ሳይገድባት ከወንድ እኩል መስራት እንደምትችል በማሳየት የወንዶችን የበላይነት የሚገነባውን አባዊ ስርዓት ስትፈታተነው ትታያለች፡፡

521፡- ለኩትኳቶውማ አንችኑ ሰጥቶኛል
ቁጢት ከመበጠስ ይኸው ይሻለኛል፡፡
/ቃለ መጠይቅ፣ ሰይድ መሳነር፣ ጥር 13/2006/

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ሰይድ ሚስቱ በግብርና ሙያ ላይ ብቃት ያላት መሆኑን ምስጋናና አድናቆቱን ሲቸራት ይሠማል፡፡ ሚስቱ ከጐኑ ሆና ስታረምና ስትኮተኩት ጠንካራ፣ ትጉህና የምታኮራ ስለሆነች “ለኩትኳቶውማ አንችኑ ሰጥቶኛል” በማለት የኩትኳቶው መዳህኒት ሆና በስራዋ አስደስታዋለች፡፡ ስራዋ የሚያኮራ እንጅ የማያሳፍር መሆኑን ይገልፃል፡፡ ሚስቱ በፊት ልብስ ትሠራ ነበር፡፡ የሽመና ስራው ጥቅም ያን ያህል እርካታ አልሠጠውም፡፡ ሽመናውን በመተው ወደ ግብርናው ስራ ስትሰማራ በኑሮው ላይ ለውጥ ያመጣች መሆኑን “ቁጢት ከመበጠስ ይኸው ይሻለኛል” በሚለው ስንኝ ከሽመና ስራ በግብርና ስራ መሰማራቱ ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ለዚህም ነው “አንችኑ ሰጥቶኛል” በማለት ከሚስቱ ሌላ ረዳት የማያስፈልገው፣ ሁሉንም ሸካክፋ የምትሠራ፣ ጠንካራና ትጉህ ሴት መሆኗን ሲያወድሳት ሲያደንቃት ይደመጣል፡፡

### 5.4.5. ፍቅርን የሚገልፁ

546፡- አረም ለምነሽኝ ከጐንህ ዋልኩኝ
በአይኔ ስላየሁህ ደህና ከረምኩኝ
/ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታ መንግስቱ፣ ጥር 08/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ ማብራሪያ ሴት ልጅ ፍቅሯን በፈለገችው መንገድ መግለፅ አትችልም፡፡ በባህሉ የተገደበውን ህግና ደንብ፣ አጥር መዝለል አትችልም፡፡ አጥር ዘላ ብትገኝም ትወገዛለች፡፡ ልጅቷ የምትወደውን ልጅ እንደምትወደው ለመንገር ባህሉ አይፈቅድላትም፡፡ የባህል እስረኛ የሆነችው ሴት ልጅ በፍቅር ስትሠቃይ ሰላም

አጥታ ለረዥም ጊዜ በተስፋ ትኖራለች፡፡ በባህሉ ሴት ልጅ ለጋብቻ ስትደርስ በቤተሠቦቿ ታጭታ ትዳራለች፡፡ ልጅቷን በፍቅሩ የታመመችለት ልጅ አረም ይለምናታል፡፡ ወደ አረሙም ቤተሠብ ካልፈቀደ መሄድ አትችልም፡፡ ቤተሠብ ከልጁ ጋር ያላትን ፍቅር፣ ለፍቅሩ ህመምተኛ ሆና መቆየቷን ስለማያውቁ ይፈቅዱላትና ትሄዳለች፡፡

"አረም ለምነሽኝ ከጐንህ ዋልኩኝ" ስትል በአረም ምክንያት መገናኘታቸውን ከጐኑ ተቀምጣ ስታርም መዋሏን ትገልፃለች፡፡ ልጅቷ መገናኘት ቀርቶ በአይኗ ማየት ያልቻለችው፣ ፍላጐቷ ታፍኖ፣ እስረኛ ሆና የኖረችው አይን ለአይን በመተያየታቸው በውስጧ መረጋጋት ሰፍኖ፣ በተስፋ ተሞልታ፣ ከፍቅር ደዌ መታከሟንና እፎይታ ማግኘት መቻሏን "በአይኔ ስላየሁህ ደህና ከረምኩኝ" በሚለው ስንኝ በእይታ ብቻ ሰላም ማግኘቷን ከህመም መፈወሷን ትገልፃለች፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ግጥም በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 547 ይመልከቱ፡፡

### 5.4.6. ፀፀትን የሚገልፁ

548፡- ገብሱን ሳናርም ቀለባችን
ክረምቱ መጣ ውሃ በላን
/ቃለ መጠይቅ፣ ጠጋለም ካሳው፣ ጥር 08/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ ሰነፍ ገበሬ ጊዜውን በከንቱ በማሳለፍ ይፀፀታል፡፡ ባለመስራቱ ወደ ፊት ምን ሊያጋጥመው እንደሚችል አስቀድሞ ያውቃል፡፡ ገበሬው በአሉባልታ ሲዞር፣ ሲተኛ አረሙን ሳያርም ትቶ አረም ፍሬ አልባ እንዲያስቀረው ያደርገዋል፡፡ አለማረማቸውም ቀለብ እንደሚያሳጣቸው በመገንዘብ ማረም፣ መስራት እንደነበረባቸው ይፀፀታሉ፡፡ የሚበሉት ቀለብ ስለሌላቸው ከፊታቸው ተደቅኖ የሚጠብቃቸው ችግርና ስቃይ መሆኑን "ክረምቱ መጣ ውሃ በላን" በሚለው ስንኝ ካልሠሩት ምን ሊያጋጥም እንደሚችል አስቀድመው አውቀውታል፡፡ በክረምት የሚበላ ስለሌለ ወደ ልመና፣ ስደት፣ ብድር መቀላወጥ ነው፡፡ ተለምኖም አይገኝም፡፡ ብድርም የሚሠጥ አይገኝ ላረስ ይከፍለኛል ብሎ ለመነው ካልሆነ፡፡ ስለዚህ ክረምት ላይ በላይ ውሃ በታች ውሃ ሆኖባቸው ውሃ ጠጥተው፣ በርሃብ አንጀታቸው የሚያድሩ መሆኑን በመገንዘብ መስራት እንደነበረባቸው ሲፀፀታቸው ይሠማል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ግጥም በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 549 ይመልከቱ፡፡

## 5.5. የጉልጓሎ ቃል ግጥሞች

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ከሚያከውኗቸው የስራ አይነቶች አንዱ ጉልጓሎ ነው፡፡ ጉልጓሎ አድካሚና አሠልቺ ስራ ሲሆን ገበሬዎች ከዚህ አሰልቺ ስራ ለማምለጥ የተለየዩ ቃል ግጥሞችን ይገጥማል፡፡ ከእነዚህም ምሬትና ብሶትን፣ ውዳሴና ምክርን የሚገልፁ ግጥሞች ይገኙበታል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 5.5.1. ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ

በዚህ ክፍል ብሶትና ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ ገበሬዎች በጉልጓሎ ስራ ወቅት  በስራው የሚደርስባቸውን ስቃይ፣ በደልና እንግልት በቃል ግጥማቸው አማርረው ይገልፃሉ፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

550፡- ጤፉን ስጐለጉል አረሙን ሳነሳ
ምነው ከወገቤ ተቆረጥኩኝሳ
/ቃለ መጠይቅ፣ ጎሌ ደርሶ፣ ጥር 08/2006/

የዚህ ግጥም ተናጋሪ ጎሌ ደርሶ ወንድ ልጅ ሲያርምና ሲጐለጉል ሲውል ስራው ሲበዛበት ወገቡ ይጐዳል፡፡ ጉንብስ ቀና ብሎ መስራት ይሳነዋል፡፡ ሚስቱ ጠንካራ ሆና አንጀቱን የሚደግፍ ምግብ ካላበላችው /ቃለ መጠይቅ፣ ጐሌ ደርሶ፣ ጥር 08/2006/፡፡ ከቃል ግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው የጤፍ ጉልጓሎ አድካሚና አሰልቺ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ስራ የሚሠራ ሰው ወገቡን የሚደግፍ አንጀቱን የሚያቀና ደህና ምግብ መብላት አለበት፡፡ ጠንካራ ሚስት ያለው በጥዋት ተነስታ አንጀት የሚያርስ ምግብ ታበላውና ምንም ድካም ሳይሰማው ይውላል፡፡ ነገር ግን ጠንካራ ሚስት የሌለው በጥዋት ተነስቶ በሮቹን ይጠምድና ተሃ ሲል ተሃ ሲል እየተጐነበሰ ሰርዶውንና አረሙን እያራገፈ ይጐለጉላል፡፡

ለመጐልጐል ሲጐነበስ ነው ህመሙ"ጤፉን ስጐለጉል አረሙን ሳነሳ" በማለት ጉልጓሎ ችግሩ ተጐንብሶ መስራቱ ላይ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ጐንበስ ብሎ አረሙን ለማንሳት ሲሞክር ወገቡ ከሁለት ክፍል ቁርጥ ይልበታል፡፡ ተመልሶ ለመቃናት ይቸገራል፡፡ የስራውን አስቀያሚነትና አድካሚነት ሲያማርር ይሠማል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ግጥሞች በአባሪ ውስጥ ተራ ቁጥር 550፣ 551፣ 553 ይመልከቱ፡፡

## 5.5.2. ገበሬን የሚያወድሱ

በዚህ ክፍል ገበሬን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በቃል ግጥማቸው ስራው የፈጠረባቸውን ስቃይ እንደሚያማርሩ ሁሉ ሲያወድሱና ሲያደንቁ ይሠማሉ፡፡ ከእነዚህም ጕልጓይን፣ ገበሬንና መሰል ጉዳዮችን ያሞግሳሉ፡፡ የግጥሞቹን ትንታኔ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

554፡- ሲዋጋ ውሎ ሲጠልም እንደ አሳ

ምነው አነሰ የጕልጓይ ምሳ

/ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታ መንግስቱ፣ ጥር 14/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ተናጋሪ በነሃሴ ወራት ጉልጓሎው ቸበራ ይሆንና ጕልጓይ እስከ ጉልበቱ እየጠለመ ይጕለጉላል፡፡ በዚያ ቸበራ ብቅ ጥልም ሲል ጉልበቱ ሲደክም እየዋለ ደህና አንጀት የሚያቀና ምሳ ማግኘት አለበት ጉልበቱን የሚተካ / ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታ መንግስቱ፣ ጥር 14/2006/፡፡

ገጣሚው በቃል ግጥሙ የገለፀው የጉልጓሎ ስራ አድካሚ ቢሆንም ጕልጓዮቹ ወገባቸውን አስረው፣ ልብሳቸውን ከፍ ከፍ አድርገው ታጥቀው በትጋትና በጥንካሬ መስራታቸውን ነው፡፡ ጕልጓይ በዚህ ቸበራ በቦካ ጭቃ ጠልሞ ሲወጣ ጉልበቱ ይደክማል፤ አንድ እግሩን ነቅሎ አንድ እግሩን ለመንቀል ይቸገራል፡፡ “ሲዋጋ ውሎ ሲጠልም እንደ አሳ” በሚለው ስንኝ በዚያ ባህር የመሰለ ቸበራ ብቅ ጥልም ሲል፣ ልክ እንደ ጦር ውጊያ በአልሸነፍም ባይነት፣ በፉክክር ስራውን ለማሸነፍ ሲሰቃዩ መዋላቸውን ከባህር አሳ ጋር አነፃፅሮ አቅርቦታል፡፡

ለእነዚህ በብርታትና በጥንካሬ ስራውን ለማሸነፍ ወገባቸው ሲቆረጥ የዋሉት ጕልጓዮች የወጣውን ጉልበት የሚተካ ደህና ምሳ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን የመጣው ምሳ አንጀት የማያቀና ለደቂቃ እንኳን የማያሳርፍ ይሆናል፡፡ “ምነው አነሳ የጕልጓይ ምሳ” በሚለው ስንኝ ጕልጓይ በደንብ መብላት፣ ያስወጣው ጉልበት መተካትና ተመልሶ ወደ ጉልጓሎ ሲገባ በጥንካሬ መሰራት እንዳለበት ተግሳፅ በተሞላ ቃል ይናገራል፡፡ ምክንያቱም ጕልጓይ ምሳ ካልበላ ተመልሶ ወደዚያ ቸበራ አይገባም፡፡ ቢገባም ጠንክሮ መስራት አይችልምና፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ የነሃሴ ጉልጓሎ ሲሆን በአብዛኛው በበትር ተደግፎ ነው የሚጕለጎለው፡፡ ቸበራው እስከ ጉልበት ስለሚውጥ መውደቅም ስላለ ላለመውደቅ በዚህ ጉልጓሎ የዋለ ሰው ደህና ምሳ ሊበላ እንደሚገባው የታመነ ነው፡፡ ካልሆነ የተለመነው ሰው በባዶ ሆዱ፣ በራብ አንጀቱ ሲያሰቃዮኝ ዋሉ ብሎ ስም

ያጠፋል፤ ስራውም በከንቱ ይቀራል፡፡ ገጣሚው ለጕልጓዮቹ ምስጋናና አድናቆት ሲቸራቸው ለባለቤቱ ደግሞ ጕልጓይ ደህና ምግብ እንደሚያስፈልገው በተግሳፅ መልክ ያስገነዝባታል፡፡

555፡-የቀኙ በሬ ልቤን ልቤን ሲል
ልማሙ ወጥቶ ጉች ጉች ሲል
ሰባቱ ጎልጓይ ቤቴን ቤቴን ሲል
ነጭ ጤፍ አምራች ጥርስ የሚመስል
/ቃለ መጠይቅ፣ ጀጃው ደርሶ፣ ጥር 10/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ደረዳሪ ማብራሪያ ጀግና ገበሬ ጥዋት ፀሃይ ስትወጣ የጠመደ ጀንበር እስክትጠልቅ ግፋ ሲል ግፋ ሲል በሬውም ጉልጓይም ይደክማል፡፡ ያቀደውን ካላሳካ ምራን መጠቅለል አያውቅም፡፡ ገበሬው በቀኝ በኩል ደህናውን ጠንካራ በሬ በግራ በኩል ደከም ያለውን አድርጎ ይጠምዳል፡፡ የታለመውን ለመፈፀም እስከ ምሽት ያደርሳቸዋል፡፡ የማይደክመው ጠንካራው በሬም ይደክማል /ቃለ መጠይቅ፣ ጀጃው ደርሶ፣ ጥር 10/2006/፡፡

በቃል ግጥሙ ለጠንካራ ገበሬ ምስጋናና አድናቆት ሲቸረው ይታያል፡፡ "የቀኙ በሬ ልቤን ልቤን ሲል" በማለት አይበገርም የተባለው በሬም ማንፍነፉን ሊደክም መቻሉን የገለፀው፡፡ በአስተራረሱ የተደነቀው ይህ ገበሬ በሰፊ ድግር በሹል ማረሻ መሬቱን እየሰነጠቀው ሲሄድ ጭቃው ድግሩ ላይ እየንቦለቦለ ይወድቃል፡፡ "ልማሙ ወጥቶ ጉች ጉች ሲል" ያለው በሰፊው ድግር ላይ የሚጠቀለለውና በእግሩ አውርዶ ቁጭ ቁጭ የሚለው ጭቃ ነው፡፡ ገበሬውን በጉልጓሎ ከሚያደክመው ስራ ልማሙን ማውረድ ነው፤ ወገብ ይቆርጣል፡፡ ስዓቱ ሲደርስ የተለመነው ሰውም ይሁን ባለቤቱ በስዓቱ ወደ ቤት መመለስ ይፈልጋሉ፡፡ የበሬ መፈቻ 10 ሰዓት ካለፈ ጕልጓይ ልቡ ወደ ቤት ነው፡፡ "ሰባቱ ጕልጓይ ቤቴን ቤቴን ሲል" ሴት ጕልጓይ ከቤት ገብታ እራት ታበስላለችና ልቧ ይንጠለጠላል፡፡ በዚህ ጥረቱ ከጧት እስከ ማታ ሽንጡን ለጥጦ በማረሱ የተጣራ ምርት ያመታል፡፡ ቤቱ በምርት ይጨነቃል፡፡ "ነጭ ጤፍ አብቃይ ጥርስ የሚመስል" በሚለው ስንኝ ያመረተው ምርት ምን ያህል የፀዳ እንደሆነ ከጥርስ ፅዳት ንፅናህ ጋር አመሳስሎታል፡፡ የስራው ውጤትም ጀግንነቱን ያስመሰክራል፡፡ ጀግና ገበሬ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ከጥዋት እስከ ማታ እንደሚሠራ ያስገነዝባል፡፡

### 5.5.3. ምክር የሚሰጡ

በዚህ ክፍል ምክር የሚሰጡ ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡ ግጥሞቹ በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጠንክሮ መስራትና መሰል ጉዳዮችን ነው፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

563፡- መጐልጐል ነው እንጅ ወገብ አደግድጐ
እንጀራ አይገኝም ቢጥዱ ምጐጐ[7]
/ቃለ መጠይቅ፣ ቢራራ አገኘሁ፣ ታህሳስ 26/2006/

በዚህ ቃል ግጥም ጠንክሮ መስራት የሚበጅ መሆኑን ምክር ይለግሳል፡፡ ጉልጓሎ የተለካው ወገብን አደግድጐ ታጥቆ በመስራት ነው፡፡ ጉልጓሎ ሲጐለጐል ወገብን ካልታጠቁት አንድ ጊዜ ቢጐነበሱ ሁለተኛ መድገም አይቻልም፡፡ ወገብን ጠበቅ አድርገው ካሰሩት በቀላሉ ለአደጋ አያጋልጥም፤ ድካምን ለማቃለል ስራውን ለማቀላጠፍና በጥንካሬ ለመስራት ያግዛል፡፡

"መጐልጐል ነው እንጅ ወገብ አደግድጐ" በሚለው ስንኝ በጥንካሬና ብርታት ሽንጥን ለጥጦ መስራት ተገቢ መሆኑን ነው የገለፀው፡፡ ጠንክረው ካልሠሩት እንጀራ ወድቆ አይገኝም፡፡ በደንብ ካልተጐለጐለ እህሉን ገና ሲበቅል አረም ይተናነቀዋል፡፡ ተነቅሎም ስለማያልቅ አሸንፎ እንዲቀጭጭ በማድረግ ምርት አልባ ያስቀራል ሲል "እንጀራ አይገኝም ቢጥዱ ምጐጐ" በማለት "ምጣድ ብቻውን አይጮህም" እንዲሉ ምጣድ ቢጣድ የሚጋገር ነገር ከሌለ ከንቱ ድካም ነው፤ በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ጠግቦ ማደር አይቻልም፡፡ ከሠሩና ካመረቱ ነው ዋዳት ሞልቶ አቡክቶ በሰፌው ጋግሮ መብላት የሚቻለው፡፡ ስለዚህ ጠንክሮ ካልሰሩት በመቀመጥ በስንፍና እንጀራ ሊገኝ እንደማይችል በማስጠንቀቅ ይናገራል፡፡

564፡- ጉልጓሎን መጐልጐል ከስሩ መንጥቆ
ካልተጐለጐለ ቀረ ከዚያው ፀድቆ
/ቃለ መጠይቅ፣ አታክልት ዳምጤ፣ ጥር 09/2006/

እንደ ቃል ግጥሙ ደርዳሪ ማብራሪያ አረሙ ከዚያው ፀድቆ እንዳይቀር ከስሩ መንጥቆ ማረም ተገቢ መሆኑን ይመክራል፡፡ ጉልጓሎ ሲጐለጐል ከወገብ ጐንበስ ብሎ አራግፌው ካላወጡት ማረሻው ያልነቀለውን መንጥሮ በዶማ ካልፈነቀሉት ከዚያው ፀድቆ ይቀራል፤ ይለመልማል "ጉልጓሎን መጐልጐል ከሰሩ መንጥቆ" በሚለው ስንኝ የተወለወለ ሜዳ፣ የተለቀለቀ አውድማ አስመስሎ፣ አጥርቶ መንቀልና ማውጣት ነው፡፡

ካልመነጠሩት፣ ሰርዶው ካልተራገፈ ተመልሶ ድካም ነው፡፡ “ካልተጐለጐለ ቀረ ከዚያው ፀድቆ” በሚለው ስንኝ በደንብ ካልተጎለጎለ ለምልሞ፣ ፀድቆ እንደሚቀር የገለፀው፡፡ የፀደቀ አረም ደግሞ እህሉ ገና ሲበቅል አብሮ በመውጣት ያቀጭጨዋል፡፡ ለፍሬ ሳይበቃ በከንቱ ይቀራል፡፡ ስለዚህ ተጠንቅቆ በጥራት መስራት ተገቢ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

# 6. ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል የጥናቱ አጠቃላይ ገጽታና ግኝት ምን እንደሚመስል ይቀርባል፡፡

ይህ ጥናት የዳባት ወረዳ ገበሬዎች ቃል ግጥም ክዋኔና የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወት ላይ የተደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ የስራ አይነቶች (አጋጣሚዎች) ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን ቃል ግጥሞች በአውዳቸው በመሰብሰብ፣ የሚያነሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፣ የግጥሞቹን ማህበራዊ ፋይዳ መግለፅና ገበሬዎች ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ማሳየት ነው፡፡

ጥናቱ በዋናነት በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ የተቀነበበ ነው፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ገላጭ የምርምር ዘዴና የይዘት ትንተና በተግባር ላይ ውለዋል፡፡ መረጃዎችም በምልከታና ቃለ መጠይቅ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ሲሆን እንደ አስፈላጊነታቸውና እንደ መረጃ ሰጭዎቹ ፍላጎት ለመሰነድ መቅረፀ ድምፅ ወ ምስልና ማስታወሻ ደብተር አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ጥናቱ ታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ መረጃዎችም ከወረዳዋ 30 ቀበሌዎች መካከል በተመረጡ ሰባት ቀበሌዎች ከ47 ቁልፍና ረዳት መረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት በውቂያ፣ አጨዳ፣ እርሻ፣ አረምና ጉልጓሎ የስራ አጋጣሚዎች በአውድ ውስጥና ከአውድ ውጭ ሲሆን ከ580 በላይ ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ገበሬዎች በተደጋጋሚ ያነሷቸው 54 ቃል ግጥሞች ተመርጠው በተከወኑበት አውድ መሰረት በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተከፋፍለው ገለፃና የይዘት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

ከመረጃ ትንተናው ግኝት መረዳት እንደሚቻለው የዳባት ወረዳ የኦርቶዶክስና እስልምና እምነት ተከታይ ገበሬዎች ጥብቅ ግንኙነት የሚፈጥሩባቸው ተቋማት ጋብቻ፣ ተዝካር፣ ዓመታዊ ክብረ በዓላት፣ ሰንበቴ፣ ለቅሶ፣ ክርስትና፣ አበልጅነት፣ ስግደት ስዓትና ሆበራ ስራ መሆናቸው በጥናቱ ተገልጿል፡፡ ሁለቱም የእምነት ተከታይ ገበሬዎች በተለያዩ ጉዳዮች እርስ በርስ እንደሰንሰለት የተያያዙ ናቸው፡፡ ሀዘንና ደስታቸውን በመጋራት በሰላምና በፍቅር ተከባብረውና ተቻችለው ይኖራሉ፡፡

ገበሬዎች ግንኙነት የሚፈጥሩበት ተቋም የሆበራ ስራ ነው፡፡ የሆበራው አይነት ደቦ ያትና አሰና ግብር ናቸው፡፡ አንደኛው ደቦያት አንድ ገበሬ የእሱው አዝመራ ወደ ኋላ መቆየት የሚችል ሲሆን ከተለያዩ ገበሬዎች ስራ በመሄድና የደረሰ አዝመራ በማተጫጨድ፣ በማተራረምና በመሳተፍ ብድር የሚያወጣበት ነው፡፡ ሁለተኛው የአሠና

ግብር ሆበራ ነው፡፡ የአሥና ግብር ሆበራ አንድ ገበሬ ሴትም ሆነ ወንድ ስራውን ለማከናወን አቅም ሲያጥረውና አቅም እያለውም ብቻውን ሊያከናውነው የማይችል ሠፊና ብዛት ያለው አዝመራ ካለው  ለሌላ የቅርብ ቤተሠቡ ወይም ጓደኛው አሠና ግብር ቁምልኝ በማለት ስራውን የሚያስከውንበት ነው፡፡ ገበሬዎች በዚህ ወቅት ተከባብረው ስራቸውን በቅልጥፍና እንደሚያከናውኑና የበግና የጠላ ሽልማት ተሰጥቷቸው ሲዘፍኑ እንደሚያድሩ በጥናቱ ታይቷል፡፡

የዕለት ተዕለት ውሏቸውን ስንመለከትም የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በአዘቦት ቀን፣ በሰንበት ቀን (እሁድና ቅዳሜ)፣ በዓመታዊ ክብረ በዓላት ቀንና በመንግስት በዓላት ቀን የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ይውላሉ፡፡ ሁለቱም የእምነት ተከታዮች በአዘቦት ቀናት የአጨዳ፣ እርሻ፣ ውቂያ፣ አረምና ጉልጓሎ ተግባራት ሲያከናውኑ ሰንበትን፣ ቅዱስ ሚካኤልን፣ ማሪያምንና ባለእግዚያብሄር ያከብራሉ፡፡ ሙስሊሞች የሚያከብሩበት ምክንያት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች አዝዕርታቸውን በረዶ ሲደበድበውና አንዳንድ ችግሮች ሲያጋጥሟቸው የችግሩ መንስኤ አድርገው ስለሚቆጥሯቸው ከአገር ባህል ሳይወጡ ግንኙነታቸውን በማጠናከር ተቻችለው በሰላም ለመኖር መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

ቅዳሜ ለሙስሊሞች የስራ ቀን ሲሆን የእርሻ፣ አጨዳ፣ ውቂያና ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ገበሬዎች ደግሞ ገበያ በመገብየት፣ ገለባ በመከመር፣ እንጨት በመፍለጥ፣ ልብስ በማጠብና መሰል በአዘቦት ቀን ከሚያከናውኗቸው ተግባራት የተለዩ ስራዎችን ይፈጽማሉ፡፡ በዓመታዊ የአረፋና መውሊድ በዓላት ሙስሊሞች ተዛዝነው ያለው ለሌለው አካፍሎ፣ በአንድ በልተው ጠጥተው በመማማርና በመወያየት ሁሉም ተደስተው እንደሚውሉ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችም በተለያዩ በዓላት ከቅርብም ከሩቅም ያለውን ወገን ዘመድ በመጥራት ያዘጋጁትን ምግብና መጠጥ ሲያበሉ፣ ሲያጠጡ፣ ሲወያዩና በዘፈን ያሳልፉታል፡፡

በመንግስት በዓላት ቀን ሁለቱም የእምነት ተከታይ ገበሬዎች እርስ በርስ ተቀሳቅሰው ያላቸው ፈረስና በቅሎ ሸልመው፣ መሳሪያቸውን  ይዘው በፉከራ፣ ቀረርቶና ዘፈን ተሰልፈው ሲያከብሩ በሌላ በኩል አንዳንድ ገበሬዎች ቤታቸው በመቅረት ንብረታቸውን ሲቆጣጠሩ እንደሚውሉ የጥናቱ ግኝት ይጠቁማል፡፡ የሴቶችን ስራ ድርሻ ስንመለከት ሴቶች ከቤት ስራቸው በተጨማሪ የውጭ የግብርና ስራ በማከናወን

ሰፊውን ቦታ ሲይዙ ወንዶች በመስክ ስራ ብቻ ስለሚሳተፉ በሴቶች ላይ የስራ ጫና እንደሚፈጠርባቸው ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ከጓደኞቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና ከሌላ ሰው የሰሙትን ቃል ግጥም ከነዜማ አወራረዱ በመሸምደድ፣ የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀምና አውድን መሰረት አድርገው አዳዲስ የማሻሻያ ቃላት በመጠቀም ይደርሳሉ፡፡ በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ላይ የቃል፣ የሃረግ፣ የስንኝና የይዘት ለውጥ በማድረግ፣ የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም፣ ሙሉ ለውጥ በማድረግና ለውጥ ሳያደርጉ ይከውናሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜም በሸምደዳ እንደሚያቀርቡና ቃል ግጥሞችን የሚከውኑት በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን ስልት መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

ገበሬዎች በእርሻ፣ ውቂያ፣ አጨዳ፣ አረምና ጉልጓሎ የስራ አጋጣሚዎች ባዜሟቸው ቃል ግጥሞች ብሶትና ምሬት፣ ትችትን (ስድብ)፣ ውዳሴ፣ ምክር፣ የወንድም አስፈላጊነት፣ ስለበሬ የተዜሙ፣ የበሬ ጥቅም፣ የበሬ ውዳሴ፣ የበሬ ዳተኝነትና በደል፣ ፍቅር፣ ተስፋና ፀፀትን የሚያነሱ ርዕሰ ጉዳዮች አንስተዋል፡፡

በአጠቃላይ ገበሬዎች ቃል ግጥሞችን በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ከሰዎች ሰምተው በሸመደዱትም ሆነ በራሳቸው የፈጠራ ግጥም ራሳቸውንና ታዳሚን ከማዝናናት፣ ስራን ከማፋጠን አልፎ ያለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ፣ ያለፈና የወደፊት አኗኗራቸውን፣ ባህልና ታሪካቸውን፣ ድጋፍና ተቃውሟቸውን፣ ስሜትና ፍላጐታቸውን፣ ማግኘትና ማጣታቸውን፣ ብሶትና ምሬታቸውን፣ ስንፍናና ጀግንነትን፣ ድህነትና ስደትን፣ መከፋትና መደሰትን የተመለከቱና ሌሎችንም በርካታ ርዕስ ጉዳዮች ለመግለፅ እንደሚጠቀሙባቸው ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

# የተጠቀሱ ምንጮች


ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነ -ቃል መምሪያ፡፡* ኢንተርናሽናል ጀርመን ጐልማሶች ትምህርት ተቃም፣1991 ዓ.ም፡፡

_________፡፡ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አፋዊ ኪነተ ቃል፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለሴሚናር የቀረበ፣ 1970ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ *የስነ -ጽሁፍ መሠረታዊያን*፡፡ አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002ዓ.ም፡፡

ማሞ ተፈራ፣ "በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳና ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና በዳንግላ ወረዳና አካባቢው"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002 ዓ.ም፡፡

ብርሃኑ አሳዬ፣ "በባንድና አንካሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ግጥሞች፣" የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያቋንቋዎች ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ዓ.ም፡፡

ጋሻው አሻግሬ "በእብናት ወረዳ ባህላዊ ወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና"፣ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2005 ዓ.ም፡፡

Bascom, Wiliam R. *Four Functions of Folklore.The Journal of American Folklore*, Vol.67, No.266. (Oct. - Dec., 1954), pp. 333-349.

Bauman, Richard. *The Field Study of Folklore in Context*._ahand book of American Folklore. ED Richard M. Dorsen, 1983.

__________.*Verbal art as performance*. Vol. 77, No. 2, /Jan 1975/ PP. 209 - 311.

__________.*Verbal aret as performance*, waveland: University press 1977.

Ben- Amos, Dan. *"Context" in Context. Western Folklore*, Vol. 52, No. 2 Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture. (Apr. —Oct.,1993), pp. 209-226.

______________.*Toward a Definition of Folklore in Context.The Journal of American Folklore*,Vol. 84, No. 331, Toward New Perspectives

In Folklore. (Jan. - Mar., 1971), pp. 3-15.

Bronner, Simon J. *Art, Performance, and Praxis*: The Rhetoric of Contemporary Folklore Studies. Western Folklore, Vol. 47, No. 2, (Apr., 1988), pp. 75-101.

Finnegan., Ruth.*Oral literature in Africa.*_Nairobi; Oxford University press, 1970.

_____________.*Oral traditions and the verbal arts.* A guide to research practices by Routledge,1992.

____________. *Oral poetry its Nature, significance and social context*, Cambridge: Cambridge University press, 1977.

Getie Gelaye. "Peasant Poetics and State Discourse in Ethiopia: Amharic oral Poetry as Aresponse to the 1996-97 Land Distribution policy" vol.6, Michigan State university press,1999.

Goldstien,K.S.*Aguide for field Works in Folklore*. Pennsylvania hatbord, Folklor association inc,1964.

Hufford, Mary. *Context.The Journal of American Folklore*, Vol. 108, No. 430, CommonGround: Keywords for the Study of Expressive Culture. (Autumn, 1995), pp. 528-549.

Kapchan, Deborah *A. Performance ._The Journal of American Folklore*, Vol. 108, N.430, Common Ground: Keywords for the Study of Expressive Culture (Autumn, 1995), pp. 479-508.

Sims C, Martha and Marthine. S. *Living Folklore. An Introduction to the Study Of Peopleand Their Traditions*.Utah State University Press / Logan, Utah ,2005.

Okpewho, Isidore. *African Oral Literature.* BackGrounds Character and Continuity. Bloomington: Indian University Press,1992.

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተቁ | ስም | ፆታ | እድሜ | ሃይማኖት | አድራሻ ቀበሌ | ስራ | የሰጡት መረጃ አይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ድረስ ግርማው | ወ | 35 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ገበሬና ነጋዴ | ስለ ገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የእርሻ ግጥምና የቃል ግጥም ድረሳ |
| 2 | ግዛት አሠፋ | ወ | 30 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | ስለ ገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የአጨዳና ውቂያ ግጥም፣ ክዋኔ |
| 3 | ቢምር ሞላ | ወ | 35 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የአጨዳና እርሻ ግጥም |
| 4 | ቢራራ አገኘሁ | ወ | 21 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | የተማረ ገበሬ | የአጨዳና ጉልጓሎ ግጥም፣ የግጥም ለመዳ |
| 5 | ጀጃው ደርሶ | ወ | 38 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የውቂያ ግጥም፣ ክዋኔ ፣የወረዳዋ ስያሜ፣ |
| 6 | ሙሉ አለበል | ሴ | 28 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | የቤት እመቤትና ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 7 | ደሴ ውበት | ወ | 48 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ገበሬ | የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ፣የአጨዳና እርሻ ግጥም |
| 8 | አድን ዱቤ | ወ | 38 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | አናፂና ገበሬ | ስለ አጨዳና ጉልጓሎ አውድ፣ የውቂያ ግጥም |
| 9 | ተካ | ወ | 19 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ተማሪና ገበሬ | የውቂያ ግጥም |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የማታው | | | | | | |
| 10 | አዳነ የማታው | ወ | 40 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ገበሬ | የአረምና ጉልጓሎ አውድ፣ የውቂያ ግጥም፣የግጥም ለመዳ |
| 11 | ምርኩዝ በለጠ | ወ | 39 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 12 | ነጋ ብርቁ | ወ | 55 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 13 | የሽበር ካሣው | ወ | 28 | ኦርቶዶክስ | ጭላ ማሪያም | ተማሪና ገበሬ | የአጨዳና ውቂያ ግጥም |
| 14 | አበራ ብርሃኑ | | 38 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | የተማረ ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 15 | አደራጀው ዱቤ | ወ | 29 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | የተማረ ገበሬ | የአጨዳና ውቂያ ግጥም፣ የዕለት ተዕለት ውሎ |
| 16 | ሲሳይ ጐነጠ | ወ | 60 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 17 | አራጋው ተሻገር | ወ | 22 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ተማሪና ገበሬ | የአጨዳ፣ ውቂያና አረም ግጥም |
| 18 | አቸንፎ ጀጃው | ወ | 15 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ተማሪ | የአጨዳ ግጥም |
| 19 | አንጋው አብተው | ወ | 28 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 20 | አታክልት ዳምጤ | ወ | 28 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የጉልጓሎ ግጥም፣ ክዋኔና ጥቅም |
| 21 | ዋሴ ፈንቴ | ወ | 30 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የውቂያ ግጥም |
| 22 | ተበጀ በየነ | ወ | 65 | ሙስሊም | ቃርሃ | ገበሬ | የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የእርሻ ግጥም |
| 23 | ቄስ ቢምረው | ወ | 40 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የውቂያ ግጥም፣ የግጥም ለመዳና ጥቅም |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጥላየ | | | | | | |
| 24 | አበባ እንየው | ሴ | 32 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | የቤት እመቤት ገበሬ | የገበሬዎች የእለት ተዕለት ውሎና የግጥም ለመዳ፣ |
| 25 | አስናቀው ካሴ | ወ | 38 | ኦርቶዶክስ | አብጠራ | ገበሬ | የገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የእርሻ ግጥም |
| 26 | ኑርልኝ ኢሳ | ወ | 35 | ሙስሊም | ቃርሃ | ገበሬ | የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትናየዕለት ተዕለት ውሎ፣ |
| 27 | ጐሌ ደርሶ | ወ | 55 | ኦርቶዶክስ | በንከር | ገበሬ | የአጨዳናጉልጓሎ ግጥም፣ ክዋኔ |
| 28 | አለማየሁ ተዘራ | ወ | 70 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | ስለ አውድማ አውድና ግጥም |
| 29 | ብትወጣ ኪዴ | ሴ | 40 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | ገበሬና የቤት እመቤት | ስለ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ፣ የአረም ግጥም |
| 30 | ፈንታ መንግስቱ | ወ | 52 | ኦርቶዶክስ | ጭላ ማሪያም | ገበሬ | ስለአረም አውድና ግጥም፣ ጉልጓሎ ግጥም |
| 31 | ሰይድ መሳነር | ወ | 39 | ሙስሊም | ቃርሃ | ገበሬና ሸማኔ | ስለ ገበሬዎች ማህበራዊ ህይወት፣ ና የዕለት ተዕለት ውሎና አረም ግጥም |
| 32 | ምህረት ካሴ | ወ | 40 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የውቂያ ግጥምና የግጥም ለመዳ |
| 33 | የማታው አስናቀው | ወ | 45 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የአጨዳና እርሻ ግጥም፣ክዋኔ |
| 34 | ጠጋለም ካሣው | ወ | 46 | ኦርቶዶክስ | ጫርቢጣ | ገበሬ | የአረም ግጥም |
| 35 | ጥጋቡ ፈንታቢል | ወ | 52 | ኦርቶዶክስ | አብጠራ | ገበሬ | እርሻ ግጥም |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | ስምሙ ነጋሽ | ወ | 43 | ኦርቶዶክስ | ታላቅ መስክ | ገበሬ | የእርሻ፣ አጨዳ፣ አረም ግጥምና እርሻ አውድ |
| 37 | ውቤ ዘውዱ | ወ | 38 | ኦርቶዶክስ | ታላቅ መስክ | ገበሬ | የእርሻና አረም ግጥም |
| 38 | ተገኝ አማን | ወ | 28 | ሙስሊም | ቃርሃ | ገበሬ | የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ |
| 39 | አርጋው ጀንበር | ወ | 28 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | የስነ ህዝብ ባለሞያ | ስለ ወረዳዋ ገፅታ |
| 40 | አደራጀው ጌታቸው | ወ | 28 | ኦርቶዶክስ | 03 | የባህል እሴቶች የስራ ሂደት ባለሙያ | ስለ ወረዳዋ ገፅታ |
| 41 | ቢምር እንየው | ሴ | 39 | ኦርቶዶክስ | ቃርሃ | የቤት እመቤት | ስለ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ |
| 42 | ብርቂ ጫኔ | ሴ | 39 | ኦርቶዶክስ | 02 | ኮሙኒኬሽን ባለሙያ | ስለ ወረዳዋ ገፅታ |
| 43 | ንግስቱ ገብሬ | ወ | 50 | ኦርቶዶክስ | ጭላ ማሪያም | ገበሬ | የአረም ግጥም |
| 44 | ኣስማረ መልሴ | ወ | 39 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 45 | ደጀን ንጉሴ | ወ | 18 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ተማሪና ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 46 | ቢራራ ዋለ | ወ | 32 | ኦርቶዶክስ | ዳራ | ገበሬ | የአጨዳ ግጥም |
| 47 | ሲሳይ መላሹ | ወ | 39 | ኦርቶዶክስ | ተንሰ የማሪያም | ገበሬ | የአጨዳና አረም ግጥም |
| 48 | እራርቶ አለሙ | ወ | 40 | ኦርቶዶክስ | በንከር | ገበሬ | የጉልጓሎ ግጥም |

**አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች**

1. ቃል ግጥሞችን ከማን አገኛችሁ? እንዴትስ አጠናችሁት?
2. የአጨዳ ቃል ግጥሞችን በሌሎች የስራ አይነቶች ላይ ታዜማላችሁ? ለምሳሌ በአውድማ ፣ በእርሻ ወዘተ ::
3. የገበሬዎችን ስም፣ ሙያ፣ ባህሪይ፣ የትውልድ ቦታ በማንሳት ታዜማላችሁ፡፡ የዚህ አይነት ቃል ግጥም ጠቀሜታው ምንድን ነው?
4. በሆበራ ተሰባስባችሁ ታጭዳላችሁ፡፡ እንዴት ነው በሆበራ ልትሰባሰቡ የቻላችሁት? ግንኙነታችሁስ በምን መልኩ ነው? ደባያት በመመለስ ወይስ በሌላ?
5. በስራ ሰዓት የምታዜማቸው ቃል ግጥሞች ምን ጥቅም አላቸው ትላለህ? ለሥራውም ሆነ ለአንተ?
6. በአብዛኛው ጠላ ካልጠጣችሁ አታዜሙም:: ይህ ለምን ይመስልሃል?
7. አሁን ያዜምከው ቃል ግጥም የራስህ/ሽ ፈጠራ ነው ወይስ ከሌላ ሰው የሰማኸው?
8. ስራ በምታከናውኑበት ጊዜም ሆነ ስራ ስትጨርሱ በቡድን ሆናችሁ የምትጨፍሩት ለምንድን ነው? ባትጨፍሩስ?
9. በአጨዳ ወቅት እርስ በርስ በመፎካከር ግጥሞችን ታዜማላችሁ፡፡ ይህ ለምን ይጠቅማል ብለህ ታስባለህ?
10. በግል ወይም ለየብቻ የምታዜሙት ግጥም በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ከምታዜሙት ግጥም ይለያል? ልዩነት ካለው ምን ምን ?
11. የአውድማ ቃል ግጥሞችን ከአጨዳ ቃል ግጥሞችን በተለየ መልኩ በጥዋት ስራውን ስትጀምሩ አንስቶ ትገጥማላችሁ:: ይህ ለምን ይመስልሃል? ባትገጥሙስ?
12. አውድማ ላይ የሚዜሙት ቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ? በአጨዳ ፣ በእርሻ፣ በአረምና ጉልጓሎ?
13. በአብዛኛው ቃል ግጥሞችን የምታዜሙት መቸ መቸ ነው?
14. በአጨዳ ጊዜ የምታዜሟቸው ቃል ግጥሞች ከስራው ጋር ይያያዛሉ? የአውድማ የእርሻ የአረምና ጉልጓሎስ?
15. ከግብርና የስራ አይነቶች አጨዳ፣ አውድማ፣ እርሻ፣ አረምና ጉልጓሎ አድካሚና አሠልች ስራ የትኛው ነው ?
16. የገበሬዎች ማህበራዊ ህይወት ምን ይመስላል

    16.1. ኦርቶዶክስ ገበሬዎች እርስ በርስ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?

16.2. ሙስሊም ገበሬዎች እርስ በርስ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?

16.3. ሙስሊምና ኦርቶዶክስ ገበሬዎች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል?

17.የገበሬዎች የእለት ተዕለት ውሎ ምን ይመስላል

17.1. የኦርቶዶክስ ገበሬዎች የዕለት ተዕለት ውሎ ምን ይመስላል?

17.1.1. የኦርቶዶክስ ገበሬዎች በአዘቦት ቀናት ምን ይሠራሉ?

17.1.2. ኦርቶዶክስ ገበሬዎች በዓመታዊ ክብረ በዓላት ምን ይሠራሉ?

17.1.3. ኦርቶዶክስ ገበሬዎች በሰንበት ቀናት /እሁድ/ ቅዳሜ/ ውሏቸው ምን ይመስላል?

17.1.4. ኦርቶዶክስ ገበሬዎች በመንግስት በዓላት ቀን ውሏቸው ምን ይመስላል?

17.2. የሙስሊም ገበሬዎች የእለት ተዕለት ውሎ

17.2.1. ሙስሊም ገበሬዎች በአዘቦት ቀናት ምን ይሠራሉ?

17.2.2 ሙስሊም ገበሬዎች የግብርና ስራ የማይሠሩባቸው ቀናት አሉ? ካሉ መቼ መቼ? ለምን ?

17.1.2. ሙስሊም ገበሬዎች በዓመታዊ ክብረ በዓላት ምን ይሠራሉ?

17.1.3. ሙስሊም ገበሬዎች በመንግስት በዓላት ውሏቸው ምን ይመስላል?

18. ሴቶች በግብርና ሙያ ላይ ይሳተፋሉ? ከተሳተፉስ በምን በምን ስራ ላይ? የማይሳተፉበትስ የስራ አይነት አለ? ካለ ለምን ?

19. የዳባት ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ ምን ይመስላል

19.1. የወረዳዋ መልካምድራዊ አቀማመጥ ምን ይመስላል? የአየር ንብረቱስ?

19.2. የወረዳዋ የህዝብ ስርጭትና የአብዛኛው ህዝብ መተዳደሪያ ኢኮኖሚ ምንድን ነው?

19.3. ዳባት የሚለው የወረዳዋ ስያሜ ከየት የመጣ ነው?

## አባሪ ሶስት፡-ከመስክ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች

### 1. የአውድማ /የሆበሬ/ ቃል ግጥሞች

### 1.1 የገበሬን ብሶትና ምሬት የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

1. ተወይ ባለጢጋ በሬው ሆዬ

   ተወይ ባለጢጋ /2/ ክፉ መናገርከን /2/

   አገሬን ሳልገባ ወንዙን ሳልሻገር

2. ሆበሬ ሆበሬ እባክሽ እናቴ /3/ ጥሬ ቆልተሽ በገል

   ታውቂዋለሽና የሰውን ቤት ነገር

3. አንተም እንደ እኔ ነህ /2/ እሩቅ ነው አገርህ /2/

   ሰማውህ በድምጥህ /2/ በማንጐራጐርህ

4. ጐኔን ጐኔ ወጋው ጐን ይወጋል ወይም

   እባክህ ግባበት እህል ገላጋይ /2/

5. እግሬን በለው እንጅ ባለ መከራውን

   ይሄዳል እይኔማ እያዬ እንጀራውን

6. ነይማ ላሳይሽ ዶሮ ጭሮ ጭሮ /2/ ሲያለብሰኝ አመዱን

   የሰው ቤት እንጀራ ባድ የገመገመው

   በልቸው ስነሳ ጉልበቴን ደከመው

7. እህት የእናቴ ልጅ ነይ ላሳይሽ ጉዴን

   ዶሮ ጭሮ ጭሮ አልብሰኝ አመዱን

8. ወዳጀ ወዳጀ አወይ በሬው ሆዬ

   እንዴት ወዳጅ ጠፋ አዝመራ ይመስል

   ሲያዋዩት ያዋያል የላኩት ይመስል

9. አግማስ አንተን ብዬ ስድህ ውየ መጣሁ

   በርዬ አንተን ብዬ ስዞረ ውየ መጣሁ

   እንዴት ይደረጋል አንተንማ ካጣሁ

   በእግሬ እየረገጥኩኝ አበሳየን አየሁ

10. አወይ ሆዴ ሞኙ /2/ እንጀራ ዘመዱ /2/

    መታውት ወንድሜን አብሬ ለባዱ

11. እኳ ስል /2/ እኳ ስል ከርሜ እኳ ስል ልባጅ

እንደ ላም እረኛ አንደ ውሃ ቀጅ

12. እየው ምድር መሸ ልለምን እራቴን

ትልቅ ትንሽ ይሆን ማን አውቆት አባቴን

13.እባክህ አምላኬ እባክህ ፈጣሪ

እባክህ ጌታዬ እባከህ አምላኬ አብጀው ቀኑን

ያለፈው አለፈ የሚመጣውን

14. አወይ በሬ በሬ ክፉ አይናገሬ/2/

ክፉ ቢናገሩይ/2/ክፉም አልናገር

አገሬን ሳልገባ ወንዙን ሳልሻገር

15. አወይ በሬው አለም /2/ ወንድም የሌለው ሰው የወንድም አባሪ

ከትክሻው ቀረ የዱላው ስባሪ

16. ተወይ ባለጠጋ በሬው ሆዬ

ተወይ ባለጠጋ /2/ ክፉ መናገርከን /2/

እንጀራ እውር ሆኖ ሊከተህ አመልክን

17. ተወይ በሬው አለም ወዳጅ /2/

ተወይ ባለጠጋ ክፉ መናገርክን

እንጀራ ዱር ሆኖ ሊከተው አመልክን

18. የረሃብ ሎሌነህ የምትከተለኝ /2/

የኔ አለም ተመለስ የእኔም መግቢያ የለኝ /2/

19. አንተን ካላገኘሁ ጕኔን ካላገኘሁ

አያን ካላገኘሁ በሬን ካላገኘሁ

የእለት ሞቴን እንጅ ሌላም አልተመኘሁ

20. እንጀራ አለ ቢሉኝ የወረድኩበቱ

ከሾተል ይበልጣል የድንጋይ ስለቱ

21. ሲገፉኝ ሲገፉኝ ወዳጅ ሲገፉኝ

ሲገፉኝ ሲገፉኝ ደረስኩ ከገደሉ /2/

ደረስኩ ከገደሉ /2/

የኔ አለም ተመለስ በዛብኝ በደሉ /2/

22. እባክህ ተዋሰይ ጠይሙ ስንሰለት /2/

አሁን ወት ይገኛል ወንድም የለት የለት

23. አንድ ወንድም ለምኔ ይላል የተመቸው

እንኳን ወንድነቱን በትሩን አግንቸው

24. አቁም ባልከኝ እንጅ ደርሰህን ትመታኝ

አንተ ባለወንድም እኔን ሞት ሊፈታኝ

25. ወዳጀ /2/ ሊመታኝ በሽመል /2/ ታሃ ታሃ

ሊመታኝ በሽመል /2/ ብመክት ሸንበቆ

አልሠበር አለ አንድነቴን አውቆ

26. አሞራ በሰማይ ይላል ወየው ወየው

አንዱን ሁለት ሆኖ ሲመታው እያየው

27. አሁን ምን አልኩና ጠራሽው ወንድምሽን

እኔስ አንድነቴ አላሳዝንሽም

28. እባክህ በርዬ ማሽላ ውቃልኝ

ጐረቤት አልባ ነኝ እረዳትም የለኝ

**1.2 ትችትን/ስድብ/ የሚገልፁ**

29. አወይ በሬ በሬ ክፉ አይናገሬ

አምላክም እንደ ሰው በርዬም እንደ ሠው

አምላክም እንደ ሠው እግዜርም እንደሠው

ታደላለህ አሉ ሸማ ለለበሰው

30. አወይ በሬ በሬ/2/ አወይ የእንጀራ እናት ያለብሽ ኩነኔ

ትኩሱን ለልጅሽ ያደረውን ለእኔ

31. ዳር ዟሪ በሬና እናት የሌለው ልጅ

ቢበላም አይጠግብ ድሮም በሠው እጅ

32. ዳር ዟሪ በሬና እናት የለው ልጅ

ያስታውቃል በመላ

ሆዱ ገፍጠጥ ያለ እራሰ ሞላላ

33. አንድ እንጀራ በእኔ እንዴት ትኮራለህ

ከባለጠጋ ቤት ትነባበራለህ /2/

34. አንድ እንጀራ ለእኔ መሰታውቴ ነህ

ብዙ ብዙ ነገር ታሳየኝአለህ

35. አወይ ስንዴ ሞኙ በቆሎ ታልቃለህ በቂጣ ታልቃለህ /2/

ከባለጠጋ ቤት ትነባበራለህ /2/

36. አወይ ስንዴ ሞኙ ሲሰሩብህ ግፍ

ከምድጃው ደፍተው ካመድ ጨመሩህ

37. እኔና በርዬ በለፋንበቱ

ከቤቱ ቁጭ ብሎ ያራጣል ሴቱ

38. እኔና በርዬ ባቀናነው ቤት

ምድጃውን ይዞ አራጠጠ ሴት

## 1.3 ምክር የሚሰጡ ቃል ግጥሞች

39. በሬ በሬ ብዬ የምወዘወዘው

እንጀራ አይበላም አምላክ ከላዘዘው

40. አንች የእናቴ ልጅ ነይ እንሂድ ትግሬ

አንች ወጠ ሰሪ እኔ ወንዝ አሻግሬ

41. አንች የእናቴ ልጅ ነይ እንሂድ ትግሬ

አንች ወጠ ሰሪ እኔ ጋሻ ጃግሬ

42. በሬው ዙርልኝ በሬው ዙርልኝ

አዟሪም የለኝ በርባሪም የለኝ

አንተው ቀልስልኝ አንተው ዙርልኝ

43. እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ

አንዱን ለእኔ ወንድም አንዱን ለእግዜር ፈንታ

44. ወንድም የሌለው ሰው /2/ ኸይ በሬ በሬ

ወንድም የሌለው ሰው ምነው ጠብ መውደዱ

እንደ ጕዳና እሸት ቆርጠውት ቢሄዱ

45. ወዳጅ ወዳጅ አትዋል ይዋሉብህ /2/ ይዋሉብህ

አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩ /2/

በሰው የመከሩ በአንተ የመከሩ እነማን ከበሩ

ከቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ /2/

46. አወይ በርዬ ሆ /2/ አወይ /2/ ይላል ጅብ እየጐተተው

አገሩ ያልቻለው ወንዙ የልከተተው

47. በርዬ ሆበሬ በርዬ ሆበሬ

ህዳርና ታህሳስ ሁለቱ ነበሩ

ህዳር ሂደ ቤቱን /2/

ታህሳስ ሂደ ቤቱን/2/ ሂደ ቤቱን

እንደላም እረኛ አድርሶ ጊዜያቱን

48. አወይ በሬ ሆዬ እኔና በርዬ እንሂድ ምናኔ

እህል የሚሠራ ብናገኝ ሽማኔ

49. ታበላይ እንደሆን አብላይ አሁን አሁን

የማታ ማታማ እጠራን የለሁም

50. ብታበላኝማ ብታጠጣኝማ አንተን ባልተለየሁ

እከተልሃለሁ እግርህን እያየሁ

51. ተው እባክህ በሬ ተው እባክህ በሬ

ልዋል ከድንበሬ ልቀበር ከአገሬ

ከሰው አገር መሄድ ይበላኛል አውሬ

ሆበሬ ሆበሬ ወዳጀ /2/ ስራልኝ በርዬ

52. ወዳጀ /3/ በሬው ተምቧለል

እንደ ቤት ማገር እንደጠምበለል

53. ታበላኝ እንደሆን አብላኝ አሁን አሁን

የማታ ማታማ እሰራ የለሁኝ

54. አወይ በሬው አምቦ አወይ በሬው ዘገር

በሬው ዘገር አወይ በሬው አምቦ

ጠላችን በገንቦ እራታችን ደቦ ዝልሉ በገንቦ

55. በሬ ሆይ አዙር በርዬ አዙር

ጉኔ ሆይ አዙር አዙር ተሽከርከር

ምርታችንን ይዘን ገብተን እንድናድር

56. አውድማው ሠፊ ነው ነዶውን ጨምረው

በጉንጭህ ያዝና እርገጠው አትፍራው

57. በሠፊ አውድማ ካልተወራጨ

ምርት አይገኝም ፊጦ ቢረጨ

58. በሬው ሆዬ አንተ በሬው አለም

አድርገው ድቅቅ አድርገው ገለባ

ቤታችን እሩቅ ነው በጊዜ እንድንገባ

59. ወዳጄ /3/ በሬው ሆዬ በሬው አለም

በሬ ተንኮራደድ አያ ተንኮራደድ

አውድማው ሙሉ ነው እንዳሻህ ተራመድ

60. ወዳጀ በሬ በሬ /2/ በሬ በሬ

በርዬ በልና በርዬ በልና

አንተም ወደ ሳርህ እኔም ወደ ቡና

61. በሬው ዳኑ በሬው ሆዬ በሬበሬ

እንውቃ አዝመራችን እንሸከፍ በወቅቱ

አቅማችን ሳይደክም ሳይበላብን ከብቱ

62. በሬ በሬ ወዳጀ/3/ በሬው ሆዬ

በሬ ዙር በሬ ዙር አብረን እንዙር

እንደነጨረቃ እንደነ ጀንበር

63. ዙር በሬ ዙር በሬ ምረቱ የጋራ ነው

ፍሬው የኔ ቢሆን ገለባው ያንተ ነው

64. በሬ በሬ ወዳጀ /2/ በሬ በሬ

በርዬ አንተና እኔ ጐንዬ አንተና እኔ

የለብን ኩነኔ

አንተ ሳረ በላ እኔ የሰው ሎሌ

65. አወይ በሬ ሆዬ/2/ በሬና ገበሬ /2/ ቢጣሉም አይበጅ /2/

እንዲያው ሰተት ብሎ ይጠመዳል እንጅ

66. በርዬ እሹሩሩ በርዬ ኑርልኝ

ገለባውን ብላ ፍሬውን ተውልኝ

67. የመሰከ አውድማ አውጡ ለሁሉም ይበጃል

አፈር ከፉ ሰው ነው ያየውን ይፈጃል፡፡

68. የወታደር እናት ታጠቂ በገመድ

ከልጅሽ የቀረ ማን ሊሆንሽ ዘመድ

69. የወታደር እናት ላይ ላዩን እለፊ

ልጅሽ መቶልሻል የአሞራው ትራፊ

70. አለቀ መኸሩ አያየ ከበረ በርዬ ከበረ

ያበላኛል ማለት ያጠጣኛል ማለት

ውሃ ሙሽምጠጥ ነው በሚወርደው አለት

71. አልቀ መኸሩ አያ በሬው ሆዬ

ያበላኛል ማለት የጠጣኛል ማለት

ውሃ መጨበጥ ነው በሚወርደው አለት

72. አድርገው አመድ አድርገው አመድ የሚመደመድ

አድርገው ገለባ ከካባ የሚገባ

73. በሬው ስራ ቤት አያ ስራ ቤት

በሰኔ በግንቦት የምትገባበት

74. እባክህ በርዬ ቶሎ ቶሎ ዙር

ስንዴያችን ብዙ ነው እንዳያሳድር

75. ኧረ በሬው አለም አንተ በሬው ሆዬ

ኧረ በሬ ቀልስ ኧረ በሬ ግባ

በሬ ካልገባበት አይደቅም ገለባ

76. በርዬ ጉንዬ በእግርህም አሻሽ

በቀንድህም መንሽ እንጨርሰ ሳይመሽ

77. በርዬ አሸብቦ ጉንዬ አሸብቦ

እራታችን ዳቦ ጠላችን በገንቦ

78. አውርድ አውርድ በርዬን አውርድ

አባይን ያህል ምርት ጣናን ያህል ግርድ

79. በርዬ ተዋሰይ ነገ እዋስሃለሁ

መከራ በአንድ ሠው እንዳይኖር አውቃለሁ

80. በርዬ እንዙር በርዬ እንዙር /2/

ደመናው ሳይመጣ ዝናቡ ሳይጥል

81. እናቴ በራቤ ምን ያሳዝንሻል /2/

እናቴ በእድሌ ምን ያሳዝንሻል /2/

ሰውነቴን እንጅ ሀብቴንን ወልደሻል

82. እየው እዚያ ማዶ አሞራው ዶልቶ

ባላገሩን ይሆን ወታደሩ ሞቶ

አይሙት ወታደሩ ይሙት ባላገሩ

ይለቀስለታል በሰራ በባሉ

ይታረድለታል መካን ከዳብሩ

83. አወይ በሬው አለም በሬው ሆዬ

የዚያ ቤት ባለቤት የዚያ አዳራሽ ጌታ

ምንጊዜ ተጠምዶ ምንጊዜ ተፈታ

84. አሆሲል ገበሬ /2/ ገበሬ ሲዘራ ሲቋጠር በአይነት

ወደ ዜት ደርሰ የዚያ ቤት ባለቤት /2/

85. አወይ በሬው ሆዬ በሬ በሬ

ይብላይ ለተለየ በሬ በሬ /2/

ይብላይ ለተለየ አዝመራ ለለየው /2/

ይብላኝ ክንብል የርገኝ በዚህ ይከታተል

ወዳጅ ያዝናል እንጅ በአንድ አብሮን ይሞታል

86. ወዳጀ በሬ ሆ እግሬም ግፋ ግፋ በሬው ሆዬ

እግሬም ግፋ ግፋ አይኔም ሠው ተመልከት /2/

ገብተን እንድናድር እንጀራ ካለበት /2/

87. መካሬ መካሬ በሬው ሆዬ

ህዳር ሂደ ቤቱን ታህሳስ ሂደ ቤቱን

ህዳር ሂደ ቤቱን /2/ ታህሳስ ሂደ ቤቱን/2/

አንደላም እረኛ አድርሶ እራቱን

88. መካሬ መካሬ በሬው ሆየ

ታህሳስ ሂደ ቤቱን /2/ ሂደ ቤቱን

እንደ ልጃ ገርድ አደርሶ ወራቱን /2/

89. ህዳርና ታህሳስ በአንድ ላይ ነበሩ

ህዳር ሂደ ቤቱን ታህሳስ ሂደ ቤቱን

እንደላም እረኛ አድርሶ ሰዓቱን

90. አወይ አወይ ይላል ጅብ እየጐተተው

አገሩ ያልቻለው ደብሩ ያልከተተው

91. አወይ በሬ በሬ /2/ አወይ በሬ ሙዙ /2/

አወይ በሬ በሬ አጐይ በሬ መዙ /2/

አትውረድ በወንዙ /2/

አለቅት አለው አሉ የሚያመዘሙዙ

92. አወይ በሬው አለም አወይ በሬው ሆዬ

እንጀራ አለ ብለው አይነግሩም ለድሃ

ተሻገረው አሉ አርባ አራቱን ውሃ

93. ወዳጅ ወዳጅ ሁሉ አለቀ ማዕበል በላው አሉ

ያላዋቂ መሪ ወስዶት በገደሉ

94. ወዳጅ በሬ በሬ /2/ አገሬ ወዲያ ነው ደመናውን አልፎ

አመጣኝ እንጀራ በልጓሙ ጠልፎ

87 እንጀራ ሆነና የሰው ቁም ነገሩ

አልቀበር አለ ሠው ሁሉ ከአገሩ

1.4 **የወንድምን አስፈላጊነት የሚገልፁ ቃል ግጥሞች**

95. ወንድም አልኩይ እንጅ እናት የወለደው

የጥቃቱ ጊዜ እንደነሃሴ ጉም አልፎ እሚጋረደው

96. ወንድም አልኩይ እንጅ /2/ የእናት ሆድ ያበጀው

ወንድም አልኩይ እንጅ እናት የወለደው የእናት ሆድ ያበጀው

ይሄዳል ጠበቃ ነገሬን ሳይፈጀው /2/

97. ወንድም አልኩይ እንጅ አንተን አልኩኝ እንጅ

አንተን ደህናውን ሠው

እንደ ሽል ከሆዴ የምትላወሰው /2/

98. አወይ በርዬ ሆይ/2/ ወንድም አልኩይ እንጅ እናት የወለደው

የጥቃቱ ጊዜ አልፎ እሚጋረደው

99. ወንድም አልኩኝ እንጅ /2/ ኸይ በሬ ሆዬ

ወንድም አልኩይ እንጅ እናት የወለደው

እንደ ተራራ ጉም አልፎ እሚጋረደው

1.5. **እናትን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች**

100. ሚስቴ ትፍጨውና እናቴ ትጋግረው

ይህን በላ ብላ ለሠው የማትነግረው

101. እህቴ ጋግራ /2/ እናቴ ታቅርበው በሬው ሆዬ

ይህን በላ ብላ የማትገመግመው

102. እህቴ ትፍጨውና /2/ እናቴ ትጋግረው

ይህን በላ ብላ ለሠው የማትነግረው

**1.6 በሬን የተመለከቱ ቃል ግጥሞች**

**1.5.1 የበሬን አስፈላጊነት የሚገልፁ**

103. አወይ በሬ በሬ የማይልህ የለም /2/

ከዚህ አስነስቶ እስከ እየሩሳሌም

104. በርዬ አንተን ያጡ ወዳጅ አንተን የጡ

ከማህበር ወጡ ሽንጐ አይቀመጡ

105. አወይ በሬው አለም አወይ በሬው ባንተ

አወይ በሬው ሆዬ አወይ በሬው ዋሴ

አንተ ባትኖርማ ታሰረ ምላሴ

106. በርዬአንተን አልባ /2/ በሬው ሆዬ

ወዳጅ አንተን አልባ /2/

አይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሠማ

107. አወይ በሬው አለም ያኑርህ ዘላለም

ከዚህ አስደክቶ እስከ እየሩሳሌም

108. አረ በሬ ዙሬ አረበሬ ዙሬ

ጠባዬ መልካሙ ጅራተ ጉንጉኔ

አንተ ስትኖር ነው የምኖረው እኔ

109. በርዬ ምሩቁ በርዬ ምሩቁ

አውድማ ቢወድቅ ምድር ቢደልቁ

አንተ ካልሄድክበት አይሰበር ምርቁ

110. በርዬ እሹሩሩ በርዬ እሹሩሩ

በአንተ ነው ማማሩ በልግና መኸሩ

111. ወዳጀ/2/ ወዳጅ ወንድም ዋሴ በሬ ዋሴ

አንተማ ከሌለህ ታሰረ ምላሴ

112. በርዬ አንተን ያጡ ይሏቸዋል መጡ

ዘው ብለው ገቡ እየው ቀላወጡ

ጥሩም አያገኙ አተላም አያጡ

113. በሬው እሹሩሩ በሬው እሹሩሩ

ላብላህ ከድንበሩ ለጠጣህ ባህሩ

ባንተ ትክሻ ነው የቀናው አገሩ

114. አያ በሬ ምሳው አያ በሬ እራቱ

ባንተ ከጐደለ አይምላም ሌማቱ

115. በሬ ካላንተማ እያ ካላንተማ

አይጣል አውድማ አይሠራ ማማ

አይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሠማ

116. እሹሩሩ በሬ በዛብኝ ውለታህ

ቃል ገብቼ አለሁኝ በጅራፍ ላልመታህ

117. በርዬ በርዬ በርዬ ጎኔን ይሙት ያለህ ማነው

ይሙት አባቱን ጠላትህ ይረር

እንደ ጐመን ዘር እንደ አብሽ ቅጠል

አንተ ባትኖር ኑሮ ሊበላኝ ነብር

ከዱር የሚውል ከዱር የሚያድር

118. በርዬን የጠላ ጐንየን የጠላ

በገና በጥምቀት ይለምናል ጠላ

በብርጭቆም አይደል በሰባራ አንኮላ

119. በርዬ አንተን ያጣ ቢናገር ጣዕም አጣ

በሸንጐ ዋስ አጣ ከገንቦ ጠላ አጣ

ንጹህ ድሃ ሆነ ከሁሉም የነጣ

120. በሬ የሌላቸው አያ የሌላቸው

ሌባ ነው ስማቸው አዳፋ ልብሳቸው

ከሠው አገር ሄደው አሞራ በላቸው

121. በርዬ መካሬ በርዬ መከሬ መካሬ /2/

ክፉ አይናገሬ

122. አያበሬ በሬ አያበሬ በሬ

ጅራት ጉንጉኔ ቀንደ ቀጫጭኔ

አያንጐራጉሬ ክፉ አይናገሬ

123. የበሬን ውለታ እንጫወት ማታ
በዋንጫ ጋጋት በቆሎ ካካታ

1.5.2 **በሬን የሚያወድሱ**

124. በሬ እንዳንተ እሚዞር የሚሽከረከር
አያ እንዳንተ እሚሆን የሚሽከረከር
እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር

125. በርየ ሲሠራ እያየ ሲሠራ
ጐንየ ሲሠራ ይመስላል ደብተራ
ቤተክርስቲያን ገብቶ ቅኔ የማመራ

126. እንደመጋል ያለ አንድ መጋል ባገኝ
እንደ ስጠኝ ያለ አንድ ሰጠኝ ባገኝ
አርሽ በበላሁ እንዳገኝ እንዳገኝ

127. እንደዳልች ያለ አንድ ዳልች ባገኝ
አርሽ በበላሁ እንዳገኝ እንዳገኝ

128. አንድ ይልካ ያለ አንድ ባገኘማ
እርሽ በበላሁ ጉልበቴ በጠና

129. አወይ በሬ ሆዬ አወይ በሬ አለሙ
የተሠራህበት ምንድን ነው ቀለሙ

130. እንደ ቀለም ያለ አንድ ቀለም ባገኝ
አርሽ በበላሁ እንዳገኝ እንዳገኝ

131. ሆበሬ /2/ ወዳጄ ሆበሬ ሆበሬ /2/
በርየ ሲሠራ እያዬ ሲሰራ ወዳጄ ሲሰራ
ወንድም የሸለመው ይመሰላል ደብተራ /2/
ከደብተራም ደብተራ ቅኔ የሚመራ /2/

132. ክብር ደስ ይለኛል /2/ ኧይ በሬው ሆዬ
ክብር ደስ ይለኛል /2/ ሲረግጠው መሬቱን
የማይሞት ይመስላል የማይለቀው ቤቱን

133. በሬን የወለደች ወደድኳት እናትክን
አያን የወለደች ወደድኳት እናትክን
ጐኔን  የወለደች ወደድኳት እናትክን

ሃር የጐነጐነ አስመስላ ባትክን
የጠጅ ብርሌ አስመስላ አንገትክን

134. ወዳጅ በሬ /2/ በሬው በአንተ ላይ መሠለ ፀሃይ
በሬው በአንተ ጫንቃ ይመስላል ጨረቃ

135. በሬ በአንተ ላይ ይመስላል አደይ
በሬው በአንተ ጫንቃ ይመስላል ጨረቃ

136. አያበሬ ማሬ አያ በሬ ማሬ
ብላ በበርበሬ ጠጣ በብርሌ
በአንተ ላይ አይደለ ጠግቤ ማደሬ

137. ወዳጅ እልሃለሁ ወዳጅ /2/ በሬው ሆዬ
አወይ በሬ በሬ አወይ በሬው አለም
ያኑርህ ዘላለም እንደየሩሳሌም እንደ መድሀኒየለም

138. አወይ በሬ በሬ አወይ በሬው ወንድም
ብታበላኝ እንጅ ብትሞትሰ አልወድ

139. በሬው ላንተ ብዬ ቆላ ደጋ ብየ
ውሃውን ገድቤ ሳርክን ከልክዬ
እደክምልሃለሁ እንዳይጠማህ ብዬ
እንዳይርብህ ብዬ

### 1.5.3 የበሬን ዳተኝነት የሚገልፁ

140.አያዬ በሬው ሆዬ /2/ የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ
ከኋላ ተነስቶ በፊት በመድረሱ

141. የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ
ቀን ሲወቃ ውሎ ማታ በመድረሱ

142. የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ
ማልዶ በመነሳት ማልዶ በመድረሱ

### 1.5.4 የበሬን በደል የሚገልፁ

143. አወይ በሬ በሬ አወይ በሬ መሆን /2/
አስረው ደበደቡት ምን አርጓቸው ይሆን

144. ወዳጅ /2/ በሬ በሬ አወይ በሬ በሬ

ወዳጄ /2/ አያ በሬ በሬ /2/

በገዛ ቁርበቱ ገረፈው ገበሬ /2/

145. እዩት ተመልከቱ የበሬን ግፉን

አመት ሙሉ ለፍቶ አፈኑት አፉን

146. በሬው ሰራ በእጁ

በገዛ ቁርበቱ ሲገርፈው ወዳጁ

1.6 **ፀፀትን የሚገልፁ**

147. መኸር ተከወነ መኸር ተከወነ በሬው ሆዬ

ገባ በየቤቱ ገባ ብዬ ቤቱ

አውኝ አለ ጅቡ /2/ እኔ ነኝ እራቱ

148. አወይ በሬ በሬ እየው ጉሙዞረ አባሪ ከራሱ

ያምናው ባለዳዬ ሳይለቀቅ ዋሱ

ያምናው ባለዳየ መጣ በኋስ ጫማ

እንደ ቅቤ ልቅለጥ እንደጨው ልሟሟ

## 2. የአጨዳ ቃል ግጥሞች

### 2.1.ብሶት /ምሬት/ የሚገልፁ

149. ኸረ በለው/2/ የሰው አገር ወሃ ብጠጣው መረረኝ

ኸረ አገሬ ጭላ መጣሁ ተቀበለኝ

150. እማሜውና/2/ አይጣል አያድርስ የጅል ጐረቤት /2/

ፍርሃት ይመስለዋል ንቀው ሲተውት /2/

151. አንተም እኔን ንቀህ እኔም አንተን ንቄ እንዲህ ተናንቀን

እንገናኛለን ከአንዱ ጐራ ታንቀን

152. አረበለው አረደኑ /2/ አባት አረገመኝ እናት አረገመኝ

ያምናው ክራሞቴ ዘንድሮም ደገመኝ

153. እማሜውና መሬቱ አምሳ ክንድ /3/ በሬው የተውሶ

እንጀራው ሊበላ እንዲህ ብሎ ታርሶ

154. አቃጥሏት /2/ ጐጆዬን እራሷን ይዛችሁ /2/

ጐጆም አታስይዙኝ እናንተ እያላችሁ

155. ሲከፋኝ /2/ ዘንድሮ ሲከፋኝ ልጅ እየተመኘሁ

ዘወር ብየ ባየው መቻልን አገኘሁ

156. አረ ተወኝ ወንድም /3/ ስሸሽ አታባረኝ

ያንተም ግፉ በዛ እኔንም መረረኝ

157. ናልይማ /2/ ኧረ አገሬ ኧረ አገሬ ዳራ

በምንሽር አርሶ በጓንዴ ጐልጉሎ

ምናለ ቢሄዱት የአባት አገር ጥሎ

158. በአጨዳ በአጨዳው ጥብቆየ ራስ

ካምናው ክራሞቴ የዘንድሮው ባሰ

159. ኧረ ዱሩ ጥራኝ ተቀበለኝ መጣሁ

ምን ያስቀምጠኛል ባልንጀራ ካጣሁ

160. ያረባባ ጐጆ /2/ ያረባባ ጐጆ /2/ ቢቀርም ግድ የለኝ

ለእናቴም ልጅ የላት ለእኔም ወንድም የለኝ

161. ባምቀው /2/ አክብለው /3/ ባምቀው /2/ አንገቴ ደረሰ

አክ ስለው ወጣ ደም እየጐረሰ

161. የአንበሳ ልጅ ሞቶ የጅብ ልጅ ገነነ /3/

አላስተኛው አለ ፀጉሩ እየቦነነ

162. ኧረ በለው ጅል አምጥቶ አምጥቶ ራሱን አይችልም

ያነካካው የለም ያነንም ያነንም

163. የበረደ ጐኔን ሊወጋኝ ጀመረ

እስከ መጨረሻው እድሌ ባማረ

164. እማሜውና ኧረ አይጣልባችሁ የዘመመ ጐጆ የኩበት ማገዶ /3/

ሁል ጊዜ እየጤሰ ይኖራል ተለምዶ /2/

165. ኧረ በለው /2/ አመጠኛው ገደል /2/

ተንኮለኛው ገደል በሬ ያሳልፋል

ጅንጀሮ ይጠልፋል

ጅል ያመጣው ነገር ለሁሉ ይተርፋል

166. እማሜውና/2/ ግንጭሌን አቁሜ ከጉልበቴ ላይ

ልጅነት ሲያድግ ሰው ሞኝ ይባላል ወይ

167. እማሜውና /2/ አምጭልኝ በሮቹን አርጄ ልብላቸው /2/

ጉልበቴ ሳይደክም ሌባው ሳይነዳቸው

168. መሄዴ ነው /3/ ከዚችም አልገኝ /2/

እንደኔ የከፋው ምንገደኛ ባገኝ

169. ጎራው ናና/2/ ዘመናችን አልፎ አለን በሰው ዘመን

አንገታችን ደፍተን እንደጤፍ ዘመማን

170. እማሜውና /2/ እናርሳለን ብለን ሞክረን ነበረ

በሮቹም ደከሙ እኛም ተውነው ቀረ

171. ጎራው ናና/2/ ስጡኝ ምንሽሬን /2/ ታላቅ ወንድሜን

ከዚህ ደም አልገባም የማይለውን

172. ከአባቴው ባድማ ካደኩበት አገር

በሬ ጠምደውበት /2/

ቁሜም ተቀምጨም ገምቸው ጉልበቴን

ስራ ቀናችሁን ብዬ መጣሁ ቤቴን

173. ጐራውና /2/ አንተ አባይ አንተ አባይ

ሞልተህ የምትፈሰው

አታሻግርንም የተከፋውን ሰው

174. ማሜውናና /3/ ስንዴ ቆሎ መብላት ጥርስ ያነቃንቃል

ከምከም ብሎ መሳቅ ጥርስ ያነቃንቃል

የድሃ ልጅ መሆን ማደሪያው ይጨንቃል

175. እማሜውና /2/ ኸረ ልጅ ማሰሪያው ኸረ ልጅ ገመዱ

ጐጀማ ምናላት ጥለዋት ቢሄዱ

176. እማሜውና/3/ ከቤቴ በበላይ ከቁንጨጮዋ ላይ እሾህ <u>ሲበቅል</u>/2/

ወይ ተወግቶ መቻል ወይ ነቅሎ መጣል

177. ታርቀን ተለቃልቀን በሶስት ሽማግሌ /2/ በሰባት <u>እማኝ /2/</u>

አመታቱ ደርሶ ስላምታ ነሳኝ

178. የማምነው /2/ የማምነው ጊዜን ነው /2/

እሱም ትቶኝ አይሄድ እኔም አልከጅለው

179. እማሜውና /2/ ጐራውና /2/

እባክሽ እናቴ አትስጭኝ በሽሮ

እሂድብሻለሁ በድሜ ሽራሮ

180. ሱሪየ ተቀዶ ከጉልበቴ ላይ

ያነን የሚሠፋ ወንድም አለ ወይ

181. እማሜውና /2/ ጐራው ናልይ

አሞኛል ታክቶኛል ምን ቀን ጤና አግኝቼ

በሰንጣራው ካራ ጐኔን ተወግቼ

182. ጐራውና /2/ እኔስ ጃሎ ላልል እኔስ መገን ላልል ግዝት ነበረብኝ

አንጎራጉራለሁ እየጐደለብኝ

183. እማምየ ናልይማ /2/ አረጐራው

ጫማም በጠጠር ነው ልብስም በውሃ ያልቃል

ልጅ የወለደ ሠው መች ይነቃነቃል

184. ወይራ ነበርኩ ቆረጡኝ ተቆረጥኩ

ፈለጡኝ ተፈለጥኩ

አመድ ሆነኩኝና ደፉኝ በጓሯቸው ደፉኝ

አህያቸው መጥታ ልትረግጠኝ ሞከረች /2/

ልትግጠኝ ሞከረች /2/

እንዳትረግጭኝ ኦሽ እንዳትግጭኝ ኦሽ

ሰው እሆን ምናልባት ድንገት ተመልሽ /2/

185. ጐጃም ተሸምቶ አስመራ ተቀና

አታልቅሽ አገሬ ቀን ይወጣልና

2.2 **ትችትን/ስድብ/ የሚገልፁ**

186. መገናዬ /2/ አገሬ ቃርሃ ጅንጀሮ በሰልፍ

ጭላዳው በሰልፍ /2/

ደህና ጐበዝ እንጅ አይበላም ሰነፍ

187. ሁለት ወንድማማች /2/ ወደ ወንዝ ወረዱ

ወንድም የሌለውን እንደበሬ ሊያርዱ

188. አረጐራው /2/ የማትረባ ፍየል መንታ ትወልዳለች /2/

ልጆቿም አይረቡ እሷም ትሞታለች

189. እህት የለኝ ወንድም የለኝ ይላል የፈራ ሰው

ፈሪ የፈራ ሰው /2/

እህት የለኝ ይላል ዛርጢ የፈራ ሰው

ክትክታም ወንድም ነው ልቡን ላመነው ሠው

190. ጕራውናና /3/ ሰንጋ አረጀ ብለው ቢጕነዳድሉት

አመሉን አይረሳም ኮርቻ ቢጭኑት

191. አማሜውና /2/ እምም አለ ዛፉ ቀፎውን ጨነቀው

ማር ብቻ መስሎታል መርዙን ላላወቀው

192. ኧረናልይ /3/ ጅራት ጉንድል በሬ /2/ ዝንብ አይከለክልም

ያረባ ጓደኛ እሬሳ አያስጥልም

193. አረ ደኑ አረናልይ/2/እናንት ወንድሞቸ እረ አይጣልባችሁ አያድርስባችሁ

የፈሪ ጕረቤት የዛርጢ ጕረቤት

ተጋደሉ እያለ ይሮጣል ወደ ቤት

194. ናልይማ/2/ሲጨብጡት የማይነጥቅ ቢከስ የማይረታ ጠላት ተበጅቶ

አይተን አይተን ተውነው ጓዛችን በርክቶ /2/

195. አንድ አይና በሬና ነፍስ የገደለ ሠው

እንደደነበረ እድሜውን ጨረሰው

196. ደመናው /2/ ወንድ ልጅ ደመናው /2

በቀን ሰባት ጊዜ ይሠራል ልቦናው

197. ኧረ አገሬ ዳባት የጭነጫው ለምለም

ግጦ ግጦ ፈጀው የሰው አገር ላም

198. እማሜውና /3/ ሚያዚያን እረስ ቢሉት ፀሀይ እየፈራ

ግንቦት እረስ ቢሉት ካፊያን እየፈራ

ሰኔን እረስ ቢሉት ዝናብ እየፈራ ነጐዳ እየፈራ

ሃምሌን እረስ ቢሉት ጭፋናን እየፈራ

ነሃሴ እረስ ቢሉት /2/ ቸበራ እየፈራ

ልጁ እንጀሯ ቢለው በጅብ አስፈራራ

199. ጕራውናና /2/ ሰነፍ ይብላይልህ ፈሪም ይብላይልህ

እርጅናውም ገባ ሞትም አይቀርልህ

200. ጎራውናና/3/ እናንት ወንድሞቸ ልብህ ጭንቅ ጭንቅ በሎብህ እንደሆን

ሆድህ ጭንቅ ጭንቅ ብሎብህ እንደሆን

እናትህን ጠይቃት ሽል ለውጣ እንደሆን

201. ናልይማ /2/እንስቲቱን ነበር ይሏተያል ብርኪ

ጉልበታቸው ስንኩል አፋቸው ሰው ነኪ

202. እማሜውና /2/ ሄደ ንቡ መሄድ የለመደው

ጉንዳንማ ቀረ ሆዱን የወደደው

203. ጀግናው አጨጅ መጣ የተባለ ጊዜ

ለጀግናው ደስታ ነው ለሠነፍ ትካዜ

204. ጎራው ናልይ ናልይማ

ነውር ነው ነውር ነው ቅሌት ቅሌት

አልቢን ማጭድ ይዞ ከኋላ መቅረት

205. አቆራረጡን እኛ ስናውቀው

አባ ገዝግዝን ምን ደባለቀው

206. ማጭዱ እሳት ያለው እየመሰላችው

እነሱም አልመጡ እኛም ታዘብናቸው

207. በአጨዳ ጊዜ ሌት የማይወጣ

ችግር ጠበቀው ከቤት ሲመጣ

208. ለጤፍ አጨዳ አይሆንልኝም

ለስንዴ አጨዳ አይሆንልኝም

ተጋበዝ ሲሉህ ተውኝ አትልም

209. ወገቡ ከረረ

ወደ ኋላ ቀረ

210. ማጭዱን ንጠቁት

ሚስቱ ትጨድበት

አንድ ጊዜ ሳቁበት

211. የኔማ ማጭድ አለው ስለት

ያንተማ ማጭድ ሲያዩት ጉትት

212. እማምዬ /2/ አረናማ /2/

በለው በለው ሲል ነው የወንድ ልጅ ሞቱ

ሴቲቱ እናቴ እኔን ሴት ወልዳ

ወዳጀን አልጠቅም ጠላቴን አልጐዳ

213. ጐራውና ና /2/ ተልባ ዝሩ /3/ ተልባ /2/ ተልባ ወላላ ነው /2

በቀበሌ በመንደሩ የሚሠራው ሁሉ ግማሹ ሌባ ነው

214. እማሜውናና /3/ሰማይ ሙሉ ኮከብ አድማቂው ጨረቃ

ያረባ ወንድ ልጅ ለሱሪም አይበቃ

215. አረሱት /3/ መስኩን አረሱት /2/ ዘቅዝቀው እንደ ቦይ

አባትየው ቢሞት ልጅየው የለም ወይ

**2.3 ውዳሴን የተመለከቱ ቃል ግጥሞች**

**2.3.1 ገበሬን የሚያወድሱ**

216. ጐራው ናና /2/ አስር ብር ገባ አሉ መራራው አብሽ

ከሙሉየ ሌላ ማን ብየ ልጥራሽ

217. አረደኑ አረበለው/2/ከነብርቁ ጋራ ከነ አባባው ጋራ አብረው ቢሠደዱ

ከየማታው ጋራ ከነሲሴ ጋር አብረው ቢሠደዱ /2/

ከግብርና ጋራ አብረው ቢሠደዱ

ቢያገኝም ያበላል ቢያጣም ያዝናል ሆዱ /2/

218. ኸረ በለው /2/እነ ወጣት እነ ሽበር እነ ክንዱን ይዥ

እንኳን ጤፍ አጨዳ በበላሁ እጅ ይገፍ

219. አረበለው /2/ ሴትም ጃሎ አለሽ የመባቻለት የልደታለት

በነቀላው ገብታ በአጨዳውም ገብታ

ሱሪም በትታጠቅ ሽጉጥ ባይኖራት

ኸረ ሙሉ አለበል የሴት ወንድ ናት

220. በማጭዱም ቢሆን /2/ አይቀድሙኝም ባይ ነው

በጨልዳም ቢሆን አይቀድሙኝም ባይ ነው

ያግዛት አሠፋ ወደረኛህ ማነው

221. ሂደ ነጐደ ሂደ ወረደ

ማጭዱ እንደሳት እየነደደ

የቆመውን ጤፍ እየጐመደ

222. አልቢኑማ /2/ እጅን አለው ፈንጅ

ሰውየው ነው እንጅ ጠምዝዞ ቆራጭ

223. አጨዳውንማ ድረስነን ይገ፤ የማታውን ይገ፤

እጥለው አልነበር ደርቤ ደርቤ

224. አባይ ጥቁር ነበር ከሠል የመሠለ

እየቀላ መጣ ደም እየመሠለ

225. አንባጓሮ ሲሆን /2/ ከዘራው ሲደራ
መሄድ ያስፈልጋል ከነግዜ ጋራ
226. በለው /3/ በለው በለው ሲል ነው የወንድ ልጅ ሞቱ
ሴት ትማርካለች ከረጋ መሬቱ
227. አምስት ሆነው መተው አንድ ሆኖ ቆያቸው
የሸመቀው ጐበዝ አብተከተካቸው /2/
228. ተው በለው /2/ የባቄላ ምርቱ ይጣላል በማንኪያ /2/
የእነ እርጥብን ወንድም ድረስየን ነካ
229. ገዛው /2/ ግልገል በቅሎ /2/ ከዋጋ ቆጥዬ /2/
መችም የአባት በቅሎ አይገኝም ብዬ
230. ናናናና /2/ ትናንሹን በሬ ልታተላልቀው /2/
የማጭዱ ዳኛ የማታው አስናቀው /2/
231. እንዲህ ነው /2/ የእህል አሚሚት
እንጀራና ጠላ ወጥና ቅባት
232. ማሜውና /2/ ኩታው ሸበርባራ ከዘራው ድፋው
ያግዛት አሠፋ ወደርም የለው
233. ልሙት እኔ /2/ አረ ልሙት እኔ /2/
ከተጠቁ ወዲያ ምን ያደርጋል እድሜ
234. ከአልቢኑ ጋራ አለው መሃላ
ከእጁ ላይለየው ክንዱ ላይላላ
235. እረጅም ዛፍ አይቶ ይሠፍራል አሞራ
ሲያስጨንቅ ይውላል የጐበዝ አዝመራ
236. ከአቆራረጡ
አቀማመጡ
237. አልቢኑ መሪ
እጁ መርማሪ
238. አልቢኑ ስለት ሰውየው ደፋር
ይከምረዋል ነዶን እንዳፈር
239. የጐበዝ ማጭድ ታሰታውቃለች
እንደሀዘንተኛ ፊቷን ፊጅታለች

ራሷን ታማ ሻሽ ጠምጥማለች

240. በስለት አልቢን ሲያቀማጥለው

ጓደኛው ከጐን ሲከታተለው

ሚስቱ በደስታ ባሌ ምትለው

241. ከቦታ ቦታ ቦታ ተራምዶ

አቆላለፈው ነዶ በነዶ

242. አልቢኑ ስለት እጁ ሰንሰለት

ማነው ሚቆየው የተነሳለት

243. አልቢኑ ከፊት ሽውሽው ሲል

ነዶው ከኋላ ዱብ ዱብ ሲል

ቀዶት ይሄዳል አልቅት ይመስል

244. ጐበዙ ሄዶ አቆለቆለ

ሰነፉ ቀረ እያስተዋለ

245. ማጭዱ ቀና ገበሬው ቀና

አገላበጠው እንደ አቦል ቡና

246. አጭጄ አጭጄ ዘርግቸዋለሁ

ነዶ ሰብሳቢን ተከተል በለው

247.አህሉን አጭደህ ነዶውን ጥለህ

ትከምራለህ ጐበዙን ይዘህ

248. ግንቦት ዘርቸ ሰማይ ሰማይ ሳይ

ህዳር አጭጀ አገኘሁ ሲሳይ

249. ማጭዴን ይገፍ ሳጭድ ስውል

እራት ነው እንጂ ምሳም አልል

250.አጫጅን አጫጅ እንዴት ወለደው

ያዝኩህ እያለ እያናደደው

251. አጨዳ ውየ ማታ ስገባ

የገበሬው ቤት አለው አበባ

252. ማጭዱ አልቢን ጥርሱ ዘርዛራ

ማን ይወዳደር ከአጅሬ ጋራ

253. ተከታተለው የአልቢኑን ሞራጅ

አርአያ እንዲሆን ለሠነፍ አጫጅ

254. አልቢኑ ከእጁ የተዋሃደ

ጀግና ሰነፍን ጣጥሎት ሄደ

255. አጫጅ አጫጁ ይፎካከራል

የአልቢኑ እጀታ ይመሰክራል

256. የአልቢኔ ጥርሷ ተሸራመመ

ጀግና ቢይዛት ያልተዳከመ

257. አያሌ ክምር አጭዶ ከማሪ

ሚስቱ አትመኝም የሰው ቅሪሪ

258. አርገበገበው በሰላው ማጭድ

የራሱን ጨርሶ የሰው የሚያጭድ

259. የጐበዝ አሽከር እህል መድማጁ

የተስማማ ነው ማጭዱ ከእጁ

260. የአልቢኑ ጌታ የአልቢን ገበሬ

ወረዶ ገጣሚ እንደ አውራ በሬ

261. አትውረድ ቢሉት ወረዶ በግድ

አቆላለፈው እንደ በግ ቀንድ

262. ጅብ አጥንት ሲያገኝ ያደርጋል ጉርድምድም

አጨደው ከመረው የጐበዞች ወንድም

263. አቆራረጡ የሚደነቀው

ከጐበዝ መሃል የሚያስጨንቀው

መጣ ያ ጀግና ሊሸከሽከው

264. የመጣበት አገሩን እንጅ

መድምዶ ጣለው እንደ መጋጃ

265. ማጭዱ አልቢን ነው ጥርሱ ዘርዛራ

ሸክፎ አስገባው በአስር ጐተራ

266. ዘርግፎ ጣለው ችቦ ችቦውን

በረጅም አልቢን የቆረጠውን

267. አጫጅ ገበሬ የሳቱ ሳንቃ የሬት መራራ

የማይቀመስ የማይበላ

268. አጨዳም መላ ነው ደቦውም መላ ነው
የነ ወይኖን እርሻ የሚዘልቀው ማነው
269. አረጐራው ናልይ ናልይማ /2/ ኧረ አገሬ ጭላ
ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ
እንዴት አለሸ ጥቃት የሞት ባለንጀራ
270. ኧረናልኝ/2/ አረ ማሩ አረ ድረስ ማሩ /2/
ከእንጀራው ከወጡ ከጠላው ማማሩ
271. ናማ ናማ ናማ ደባት ከከተማው ይሸጣል አነሽ
የድረስ ባለቤት ጠጅ ጠመቀሽ
272. .ማጭዱ ስለት በእውቅ የተሠራ
ከተጠመደ የማያባራ
273. አልቢኑ ስለት ከውጭ የመጣ
ቆራርጦ ጣለው ሁሉ ሳይመጣ
274. የቻይና ማጭድ አፉ ስለት
ያጭድ ጀመረ የሁሉን ፊት
275. አልቢን ሽው ሽው አልቢን ሽው ሽው
በ25 ብር የተገዛሽው
276. ዛሬስ ማጭዴ ተጐማጅታለች
በጥዋት ወጥታ ጤፍ ትበላለች
277. የኔስ ማጭዴ ተጐማጅታለች
ሰነፍ ያለውን ትቆርጠዋለች
278. የአልቢኔ መስላት የእህሉ ማማር
አይሠለቸኝም ስቆርጠው ባድር
279. አረጐራው አረደኑ /2/ ፊትል ፍተይ ቢሉኝ /2/
የማላውቅበትን አጨዳ ገብቸ /2/
ለጥ አረኩት እንጅ ዋኝቸ ዋኝቸ
280. የኔስ አልቢኔ ታኮራኛለች
ከሠው ፊት ለፊት ታደርገኛለች
281. ዛሬስ አልቢኔ ምንድን ሆናለች
አንዳንዱን ችቦ ታነሳዋለች

282. ዛሬስ አልቢኔ ልቧን አሟታል

እየቆረጠ ያስቀምጣታል

283. ኧረ ተይ ማጭዴ አትበይ ገልታ ገልታ

እከፍልሽ ይሆናል ያንችንም ውለታ

284. ማጭድ ይቆርጣል እጅ ይጨብጣል

እየቆረጠ ደግሞ ለመጣል

285. ማጭዱን በቀኙ ገብሱን በግራ እጁ

ግራ ሲያዝለት ቀኝ ነው አራጁ

286. በስመ አብ ወልደ መንፈስ ቅዱስ

በመንፈስ ቅዱስ የተወለደው

እንደ ስላሴ የበረደደው

ከዚህ አንስቶ ከዚያ ቢልከው

አንጀት ጉበቱን አዝለከለከው

287. አበባ ያብባል ገና

አዲስ አበባ

አበባ ያፈራል ገና

አዲስ አበባ

288. አበባ ሸው አዲስ አበባ

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

289. አበባ ገና ነው ገና

አዲስ አበባ

አበባ የግሸ ፈረስ

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

አበባ ስሙ ነው ቡላ

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

አበባ አብደከደከው

አዲስ አበባ

አበባ አገሩን ሁላ

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

በል በለው

አዲስ አበባ

አበባ ገና ነው ገና

አዲስ አበባ

290. አይብልሃ አይብልሃ ሆበሬ

አይብልሃ

አይብልሃ ጀግንየው እንዴት ነው

አይብልሃ ሆበሬ

አሃይ ሎጋ አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ

አሃይ ሎጋ ኮበሌው ቶሎና

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ የገደልከው አውሬ

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ነፍስ አውሏልና

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ወደልሽል/2/

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ወደልሽን ማን ችሎ

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ እሱን በፍልጥ ነው

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ በመጫኛ ጥሎ

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ለቃርሃ ልጆች

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ደግሞ ለገብሬሎች

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ደግሞ ለነ ደጀን

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ እንገታችን ደፍተን

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ታመን ራሳችን

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ ለሰው በተረፍነ

አሃይ ሎጋየሆ

አሃይ ሎጋ እንኳን ለራሳችን

አሃይ ሎጋየሆ

2.3.2 አገርን የሚያወድሱ

291. አገሬ ቃርሃ አገሬ አዲስ አለም/2/

አገሬ ዋልካው ጎጥ ለዚችማ ምና

ተዛዝኖ ይበላል ጤፉንም በዝና

292. አረ አገሬ ዳራ አገሬ ዳራቦ ወይን ያብቅልብሽ

ወጣት እንደእንቦሳ የሚዘልብሽ

293. ጉፍር ጉፍር አርጐ ይተኛል ነብር

ኧረ አገሬ አብጠራ ትልቁ ደብር

294. እማሜውና /2/ መግመሻው አብራራው መጐልጐያው ጓንዴ /2/

ነጭ ጤፍ ያበቅላል አረ አገሬ አራዴ

295. አረጐራው ናልይ ናልይማ /2/ ኧረ አገሬ ጭላ

ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ

እንዴት አለሸ ጥቃት የሞት ባልንጀራ

296. ተው ናልይ /2/ አረጐራው አረ አገሬ በንከር

አገሬ ቃርሃ አረ አገሬ ዳራ

ያግድም /2/ ያግድም ያድም

ጉድቡ ጭንቅ ነው አያረማምድም

297. አገሬ ለባስጌ ወለሹ መለሹ

የዱራኛ ጠላ የሚጠጣብሹ

298. አረ በለው/2/አገሬ ቃርሃ የጥንጫው ለምለም

ካለ ጥርሰ መልካም ካለውብ የለም

299. አረናልይ ናልይማ /2/አገሬ ቃርሃ ሞፈር መቁረጥ ያውቃል

ካልተለበለበ መቸ ይታረቃል

300. አገሬ አዲስ አለም የነብላው የነቀንድል አገር

ጎድጓዳ ስትመስል

ታወጣለች ጀግና ሃረግ የሚመስል

301. አረ አገሬ ዳራ ገፋገፋ አድርገህ ውጣው አቀበቱን

ልብ ያሰበው ነገር አይገኝም ለቱን

302. ማሜውናና /2/ በመስከረም ወራት ይዘራል ሽንብራ

የበሬው መሽጫ ሞንሚናይቱ ዳራ

303. አገሬ ጉናይባ አገሬ ውልክፊት ያግድም/2/

ቦታው ከረከር ነው አያረማምድም

## 2.4 ምክር የሚሰጡ

304. እባክሽ እናቴ /2/ ውለጅልኝ መንታ /2/

ቀኝ እጀ ሲመክት ግራ እጀ ተመታ

305. ጠላ የለም እንጅ ጠላማ ቢኖር

ይህ አጨዳ ተርፎ አያድርም ነበር

306. ጠላ የለም እንጅ ጠላማ ቢኖር

አስተጫጨድማ እንዲህ አልነበር

307. መኸር ነው ጐበዝ እህል እንጨድ

በረዶ ሲጥል እንዳንሰደድ

308. ተጉዞ ተጉዞ /2/ ሰው እንደ ደመና /2/

መመለሻው ጠፋ ያገሩ ጐዳና

309. ተውናማ /2/ አገሬ ቃርሃ /3/ ካረስኩማ ከጐለጐልኩማ /2/

ይሻለኝ ነበር የአባቴን ባድማ

310. ኧረ መገን ኧረ ናልይ መገናዬ

የላዩን ታች በለው የታቹን ላይ በለው

እንዲህ አያለ አይደል ጀግና የሚባለው

311. ማሜውና /2/ አንድ ባልቴት በሬ ካላሰሩት ከቤት /2/

እንደምን ዋላችሁ አይልም ጐረቤት

312. አማሜውና /2/ በሮችን አምጭልኝ ጥቅሉን ጨምረሽ

አጣማጅም የለኝ አጣማጇ አንች ነሽ

313. ጤፍ አጨዳ ስሄድ ለምን ትቆያለሽ

ብቅ በይ ከጐኔ ማንቆርቆሪያ ይዘሽ

314. ይብላኝልህ አረ ጠላቴ አትለፍ በደጀ

እንደ ዓመት ባል ዶሮ ትጠፋለህ በእጀ

315. ጐበዝ አፍቅሮ ነው መከፋት /3/

እንዲያው ቢለኩሱት ይከብዳል ለለት

316. ኧረ ናና /2/ አረበለውአንት የሚስቴ ወዳጅ የእኔ ባልንጀራ

ጀንዴው ቀዳዳ ነው ልጆቹን አደራ

መቸም እዝነት የለህ አንዱን ሽጠህ ብላ

317. ጐራው ናና /2/ ከሠደፍ ዘቅ ዘቅ ከአፈሙዙ ቀና ያረጉት እንደሆን

ጥይት ሠው አይፈራም ባላንባራስ ቢሆን

318. እማሜውና /2/ ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው

ከአገር በፊት መግደል ነገረ ሠሪን ነው

319. እማሜውና /2/ ማሰብ ሞኝነት ነው መበሳጨት ከንቱ

እግዜር ያለው ላይቀር ሁሉም በሰዓቱ /2/

320. እንዲያም እንዲያም ብለህ /2/ ራስህ ደህና ሁን

ችግር አቧራ ነወ ይራገፋል አሁን /2/

321. እማሜውና /3/ ትልቅ ወንድም ያለው /2/ የክንድ ከዘራ ነው

የዛን ትንሽ ያለው የወንድ ሽጉጥ ነው

የዛን ትንሽ ያለው የእጅ ጓንዴ ነው

ከባዕድ ጋር ቢበሉት መለያያው ጠብ ነው፡፡

322. ትብስ ትብስ ብሎ /2/ ከባለቤቱ ጋር ከሚስቲቱ ጋራ የሰሩተይ ቤት

ትብስ ትብስ ብሎ /2/ ይሻላል ይህ ብሎ የሠሩተይ ቤት

ቢገፉት አይወድቅም ቢነቀንቁት

323. ኧረ ተወኝ ልቤ ደርሶ መደንገጡን

ሞት አይቀረም ብየ ነግሬህ እርግጡን

324. ሰማህን የሽበር ሰማህን ወንድሜ

ሁልጊዜም አይመች ጐጆና ትዕቢት /2/

አንዱን እንደመተው ካላደረጉት

325. ጐራው ናና /2/ እስኪ ሽንብራ አምጡ /2/ ጥሬው የሚበላ

እሳት ነዶ ነዶ ጢስ አይቀርምና

326. ኧረ በለው /2/ እሙየ በሮችሽ /2/ ቀኝ ናቸው ግራ

የተጠመዱለት ላኪብኝ አደራ

327. በልተወው /3/ ይቅርበት የአንድ አመት አዝመራ

በልተወው /3/ ይጥፋበት የአንድ አመት አዝመራ /2/

ቤት ስለሌለው ነው አንበሳ እሚፈራ

328. እማሜውና /2/ ማግጅበት ጀርጉጅበት ካልደመቀ አይጋግርም

መቀመጥ ነው እንጂ መሄድ አይቸግርም

329. ጐራውናና /2/ አንተ ጐራ ዘለህ ንገር ለዛ ጐራ

እንብይን አይደለም የጠብ መጀመሪያ

330. ጐራውናና /2/ አትውረዱ ኪንፍዝ ዘንጋዳ ብላችሁ

ከዚሁ ክረሙ ደረቁን በልታችሁ

331. ጐራውናና /2/ በስዓቱ በወራቱ ፈፋውም ያጐርፋል

ወንዙም ይደነፋል

ጊዜን ለጠበቀ ያነሁሉም ያልፋል

332. ጐራውናና /2/ ነገረሠሪና ፍየል ያለው መንደር /2/

ሠውየውን ትቶ ፍየሊቱን መግደል

333. ጐራው ናና /3/ አትውደዱ /2/ አትውደዱ

ገዳይ ገዳይ አለው እዳ

ያደጉበት አገር ይሆናል አንጋዳ

334. ያዝ የዝ አትበሏቸው ተው ተው አትበሏቸው /2/

ንዴትና ቂጭት ንዴት አለባቸው /2/

335. ሲሆን እንታረቅ አለዛም ፈግጠው /2/

አጥንትህ ይገኛል አሞራው ሲግጠው

336. እማሜውና /2/ ኧረ እረሱ /2/ እረሱ በጠና

ሽታው ይገልሃል የጐረቤት ጠላ

337. ጅቡ መጣ ብለህ አታሰፈራራው /2/

በደንቀዜ ዳቦ ደረቱን በለው /2/

338. አረደኑ በለው /2/ አረ ጐራው ናልይማ

በል ግፋ በል ግፋ /2/ በል ግፋ ጨምር

በአንድ ሰሞን ያልፋል ችግርና ጦር

339. ጐራውናና /2/ አንድም ካልነገዱ ምጥዋና አስመራ

አንድም ካላረሱ ሰፋ ካለ ጐራ

ኧረ እንደምን ተብሎ ይበላል እንጀራ

340. ቢነግዱም /2/ መክሰር ቢሰርቁም መታሰር

እኔማ ዘንድሮ የታየኝ ብልሃት /2/

የእኩል መሬት ባገኝ እያረሱ መብላት

341. ኧረ ጐራው /2/ ከወገቡ አትሁን አገር ይጠላሃል

ከአፋፉ ላይ አትሁን ገደል ይስዱሃል

ከደልዳላው አትሁን ቤት ይሠሩብሃል /2/

አንጓባቢ ሆነህ መኖር ይሻልሃል

342. ነገረ ሰሪና ፍየል ያለው መንደር

ፍየሊቱን ትቶ ሰውየውን መግደል

ሰውየውን ገሎ ከአገር ከመነቀል ከአገር ከመሠደድ

እልም ካለው ጐራ ፍየሊቱን ማረድ

343. ጐራውናና /2/ በሉ ጠና ጠና እናንት ወንድሞቸ

በሉ ጠና ጠና

ከነወርቁው እርሻ ተልከናልና

344. አትውደዱ /2/ ጨረቃ አትውደዱ

አትውደዱ ጨለማ ነው መውደድ

ጨረቃ አትውደዱ

ጨረቃው ሲጠፉ ይጠፋል መንገዱ

345. አይዞሽ አልቢኔ

አበላሻለሁ ገንፎ በቅቤ

346. አረ ግፋ በለው አረ ግፋ በለው

አይቀርምና የተጀመረው

347. ክንዴ ጠንክሪና በርችና መንጥሪ

አብሹን አጭደሽ እስክትከምሪ

348. አይዞሽ አልቢኔ

ከጓደኞቸ አላንስም እኔ

349. ጐበዝ እንበርታ እንጨድ ባልቢን

በአንድ ላይ ከበን በደቦ ሆነን

350. ተውናማ /2/ ገደሉን /2/ አፍርሶ ካላረጉት ሜዳ

ዱሩን መነጣጥሮ ካላረጉት እርሻ

ኧረ እንደምን ተብሎ ይሸኛል እንግዳ

351. አይዞህ ቀኙ እጀ ማጭዱን ያዘው

አይዞህ ግራ እጀ እህሉን ያዘው

ስንዴና ገብሱን እንድናግዘው

352. ጐራውናና /2/ ማጨድ ነው እንጅ እጅ እስኪቆስል

ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል

353. አጨዳን በጋራ እንተባበረው

ችግር እንዳይመጣ እንድናባርረው

354. አጨዳን ማጨድ በህብረት ሆኖ ነው

ለየብቻ ማጨድ ጊዜ ለመግደል ነው

355. ጫማ እንድገዛልህ ተው በርታ ማሙዬ

እኔ በፊት ሳጭድ ሰብስብ ከኋላዬ

356. አንች ነሽ ክንዴ አይዞሽ አልቢኔ

ሰላ  በይልኝ አላላም እኔ

357. በርትተን ተባብረን እንሂድ በጋራ

መወጣት አለብን የህዝቡን አደራ

358. ጤፍ አጨዳ ስሄድ ተከተይ ከኋላ

እቀራለሁ ብትይ እንዳንጠላላ

359. አልቢኑን አጉርሰው እስከ ላንቃው ድረስ

ካልሆነ አይገኝም አፍን ሞልቶ መጉረስ

360. አካሌ ማጭዴ እጀን አደራ

እንዳታኖረው ከነዶው ጋራ

361. አንተ ዝም ብለህ ማጭዱን ላከው

ያመጣው የለ እየጐተተው

362. አንተባበር እንጨድ ጐበዝ

ፀሃይ ሳይገባ ጨለማ ሳይዝ

363. እገሌ ጐበዝ ነው ብሎ ከማለት

አጨድ አጨድ አርጐ በወቅቱ መውቃት

364. ኸረ ሱሪ ግዙ ረጅም አጭር

አንዱን ለግብርና አንዱን ለመንደር

365. ዛሬስ ማጭዴ ማታ ልጠብሽ

ገብሱ ብዙ ነው የሚጠብቅሽ

366. ውለታ ከፋይ ነኝ እኔ ገበሬው

ለባለ እጅ ሰጥቼ አሠራኻለው

367. አረ በለው /2/ ተው ተው ተው <u>ናልይማ /2/</u>

አረ ጀግናው ናልይ አረ ጐበዝ ናልይ

አንተ ናልይ እንጅ ይቅር የቀረው

መሰናክል እንጂ እርባናም የለው

368. ገፋ ገፋ አድርገህ በጊዜ ፍታቸው

የሰው አገር በሮች እራትም የላቸው

**2.5 ፀፀትን የሚገልፁ**

369. ማጨድ ሲገባን ፀሃይ ሳይበረታ

በከንቱ አሳለፍነው በቡና ጋጋታ

**3 የእርሻ ቃል ግጥሞች**

**3.1 ትችትን/ስድብ/ የሚገልፁ**

370. የመሬት ድልድል ወሰን ብለው

የኩታራ ዳኛ ዘርፎ ጨረሰው

371. ማረስ ነበረ እንጅ ፀሃይ እስከሚከር
ከሰው ደጃፍ ሂዶ አንገት ከማቀርቀር
372. የአበሻ ማሽላ በጤፍ ከመበደር
እርሻ ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ነበር ማደር
373. ኮሌ ባንገትህ ሞልተህ ሳብበት
አይደለህ ሴት ድሪ አታስርበት
374. ሲተልሙ አይተልም ሲዘሩ አይዘራ
አሻግሮ ያያል የሠው አዝመራ
375. ረጅም ዛፍ አይቶ ይሰፍራል ጉሬዛ
ምነው በኛ ዘመን ማዳበሪያው በዛ
376. በልማ አንተ ጉበዝ እንዳሻህ ተናገር
ጀርባዬን ገብሬ ባቆየሁት አገር
377. ቦራና ወይኖ ትላለች ሚስቱ
ጭቃ ወርሶታል ከነ ጉልበቱ
ውሃ አይነካሽ ነው ልክ እንደእናቱ
378. ወይ ረስላት ወይም ሙትላት
በጣሳ ጥፊ አታሰገድላት
379. ሲያርሱ አያርሰ ሲዘሩ አይዘራ
በየሄደበት ቆሞ እያወራ
380. ገበሬው መጣ ትላለች ማታ
እሱ እሚውለው ሲያስር ሲፈታ
381. መሬቱ ለጭቁን ይኸው ተከፍሏል
እግዚያብሄር ያጥናህ ነባሩ ፈውዳል
382. መሬቱን ሳይገምስ ዘሩን ቢዘራ
ሳይበቅል ቀረ በላው አሞራ
383. የሰነፍ ቤቱ ተደረመሰች
ልጁ አለቀሰ ሚስቱም አዘነች
384. አርሶ በበላ በወይፈኖቹ
ይቀኑበታል ጐረቤቶቹ
385. ተቀምጦ ውሎ ሲሞቅ ፀሃይ

ሰው ውሎብኝ ይላል አያልቅም ጠንቋይ

386. ካልረባ ሹመት ይሻላል እርሻ

በሰፊ ድግር በሹል ማረሻ

387. በበጋ እንዳያርስ ፀሃይ እየፈራ

በክረምት እንዳያርስ ብርደን አየፈራ

ልጁ ቢያለቅስበት በጅብ አስፈራራ

388. በጅብ ቢያስፈራሩት መች ዝም ይላል ልጅ

በትኩስ እንጐቻ ደረቱን ነው እንጅ

389. እንጀራው የብድር ወጡ የልመና

አርሶ የማይበላ ያልታደለ መና

390. በጠንካራው በሬሲያርሱ አትረስና

ሲያጭዱ አትጨድና ሲውቁ አትውቃና

አሚረቱብኝ በል ከመንደር ዋልና

391. በሰኔ በግንቦት ፀሀይ የፈራሰው

ሚስቱም ጤፍ አታገኝ በሬውም ጭድ የለው

392. እነ ነጭ ለባሽ እነ እጣተ ለምለም

እቤታቸው ሲኬድ የሚቀመስ የለም

393. ሰርዶው ባለበት ነው ሳይለቅ ቦታውን

አረስኩኝ እያለ ነድቶበት ላይላዩን

394. ያላረሰማ ሰው እርፍ ያልነቀነቀ

ገና በሃምሌ ወር ወፍጮው ወላለቀ

395. ያላረሰ ጐበዝ እርፍ ያልነቀነቀ

ከነቤተሠቡ በርሃብ ተላለቀ

396. በሬ የሌላችው ምንም የሌላቸው

ከአውደማ ዳር ቆሞ ያለቅሳል ልጃቸው

397. ክረምት ዝናብ ፈርቶ በጋ ፀሃይ ፈርቶ

ሰው ዋለብኝ ይላል ከጥላው ተኝቶ

398. አበላሉ እንደጅብ ቅልጥሙ እንደውሻ

እርሱ ልመና እንጅ መች ይወዳል እርሻ

390. ጀግናው በሬ ጠምዶ ማሳ ያደርሳል

ሰነፍ ዋንጫ ይዞ ወሬ ይሰልቃል

391. ልጁም አለቀሰ እርር ትክን ብሎ
ከርሃብ የበለጠ ምን ጅብ አለ ብሎ

392. አረቄ ጠጥቶ ከመንቀዋለል
ፍየልና በጉን ማርባት ይሻላል

393. አነታፋው ለምለም እነ ጣቱ ለምለም
ታመው የተኙ ቀን የሚበሉት የለም

394. ይምጡ በሮቻችን አርደን እንብላቸው
ደግሞ እንደመሬቱ ሳይደለድሏቸው

395. አጋሙን መንጥሮ እንዳይዘራ እህል
እሾኹን መንጥሮ እንዳይዘራ እህል
አሻግሮ ይመኛል የሰውን ክምር

396. በትልልቅ ጉድጓድ ካልረገረጉላት
መች ትኖራለች ሚስት ከንፈሯን ቢስሟት

397. መሬት ተሠፈረ በትንሽ ገመድ
እንግዲህ ደህና ዋል ጠላና ዘመድ

398. ባላርስ ባልጐለጉል ምን አስጨነቀኝ
የድሆቹ ዋቢ እርዳታ አለልኝ

399. ዝናብ ሲቀር ቀረ ሲመጣ መጣ ነው
የግብርና ኑሮ አጠራጣሪ ነው

400. አረ ምን ያደርጋል የግብርና ኑሮ
ቀን የጣለ ጊዜ ተያዘ ጉሮሮ

401. እነ ኩታው ለምለም እነ ሱሪው ለምለም
አሁን ገደም ቢሉ መታከሚያ የለም

402. አሁን ኑሮ ነው ወይ የገበሬ ኑሮ
ሁልጊዜ ደተፍቶ እንደ ዶሮ ጭሮ

403. ቢያብቡ ቢያጌጡ ቢያምሩ አንደጨረቃ
የገበሬ ኑሮ ተምልሶ ጭቃ

404. ከሴት ወንድ ይሻል ብየ ባገባው
ለቁርስም አይበቃ የአመት አዝመራው

405. ሚስቱ ትለዋለች ምን አረስክ ማታ
ጊዜ እየገደለ በዛፍ ስር ምኝታ
406. እኛ ከገለባው ምን አለን ከምርቱ
መንግስት ይሠጠናል እትንከራተቱ
407. ናውጣ ናውረድ ብሎ ከማለት
የእርዳታውን ስንዴ በኬሻ መሙላት
408. ስራ እንደኮሶ እየመረረው
ጠቅልሎ መጉረስ ማን አስተማረው
**3.2 ውዳሴን የሚገልፁ**
409. እርሻ ያረሰና የወንዝ ዳር ዛፍ
ዘለለም ይኖራል አበባው ሳይረግፍ
410. ማረሻው ሃዲድ ሞፈሩ ወይራ
ሰርዶ አረጋፊ እንደጨጓራ
411. ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ
አይላትም ሚስቱን ብቅል ተበደሪ
412. የነቃች ሚስት ያለው ማለዳ ቀስቃሽ
ከአንድ አንድ ላይ መቶ መቶ አፋሽ
413. ጀግናው ገበሬ ማልዶ ገስግሷል
ዘሩን አውጥቶ በአቁማዳ ቋጥሯል
ግንቦት ሲመጣ ሳቅሳቅ ይለዋል
414. አባቱ ነበር ሞፈር አራቂ
ልጅ ደረሰ ሰረዶ ነቅናቂ
415. የወይኖ ጌታ የቀኙ በሬ
የዘገር ጌታ የግራው በሬ
እርፍ እስኪናገር አራሽ ገበሬ
416. የጥቁር በሬ ጉያ ገራፊ
የዋልካ መሬት ሠርዶ አራጋፊ
417. ቆላ ደጋ ባይ ያላንዳች እረፍት
ሲያበላ እሚኖር ዘላለም እሸት
418. አተራረሱን አገር ያውቀው

ጐተራው በጤፍ የተጨነቀው

419\. በሬና ገበሬ ሁለቱ አንድ ናቸው
ሲነጋ የወጡ ሲመሽ ነው መግቢያቸው

420\. የግራሩን ስር መንጥሮ ቢያርሰው
ነጭ ጤፍ ወጣ ጅብ የማይጥሰው

421\. ሎጋና ጐሹ የሂዱበቱ
ያረገርጋል የእርሻ መሬቱ

422\. በሬ አይደለም ወይ ያቀናው ቤቱን
እንኳን ጥሬውን ይብላው ዱቄቱን

423\. የመስቀል ጌታ ይጠምዳል ማልዶ
በረጅም ዋንጫ መቀልጠም ለምዶ

424\. በሬው ሰጋር ማረሻው ወጊ
የቤቱ ጌታ ምርት ረግራጊ

425\. በሮች ጥቋቁር ገበሬው ሙጫ
ማን ይለቀዋል ሰርዶው ቢንጫጫ

426\. የፈንዛ ጌታ ጠመደ ማልዶ
በረጅም ዋንጫ ኮረፌ ለምዶ

427\. አራሽ ገበሬ ጥዋት እስከ ማታ
ዘሩ አያልቅበት ጥማድ አይፈታ

428\. ያረሰ ሰው መልካም እርፍ የነቀነቀ
ወፍጮው እንዳጎራ መስከረም ዘለቀ

429\. በሬው ሲራመድ አንደ መኪና
ሰርዶውን ሁሉ አረገው መና

430\. አራሽ ገበሬ ምራን ቋጣሪ
በሰፊ ድግር ሠርዶ አበጣሪ
ለተቸገረ ዘር አበዳሪ

431\. ጉች ጉች ያለ ስንደዶ ፈንቃይ
ጥርስ የመሠለ ነጭ ጤፍ አብቃይ

432\. የጀንበር ጌታ የእርሻው ሚኒስቴር
የሚደባልቅ አፈሩን ካፈር

433. በሬው የቤቱ የሚጠመደው በለት በለቱ

የማይለየው ቀንበር ከአንገቱ

434. አራሽ በሃምሌ በዚያ ጨለማ

ልማሙ ወጥቶ ጉጆ ሲሰራ

በፈር በፈሩ ውሃ ሲሞላ

ወይ የዚያን ጊዜ ያለው መከራ

435. አራሽ ገበሬ ጉራ ለጉራ

ጉታ አስጨናቂ በስንዴ አዝመራ

436. ኮከብ ያንተ እናት ምነው መከነች

እንዳንተ ያለ በደጋገመች

437. የበሮቹ ቄስ የበሮች መምህር

አቆላላፊ ክምር በክምር

438. በሬ ገራፊ እስከ ቅንድቡ

ነጭ ጤፍ አብቃይ እስከወገቡ

439. የእርሻው መድሀኒት እርሻ ወዳጄ

እርፍ የሚያምርበት እንደጉራዴ

440. የሞፈሩ ስም ይባላል ወይራ

የቀንበሩ ስም ከያዘ አይላላ

በሬ ዝቅ ሲል በጅራፊ ቀና

ፈሩ ዝቅ ሲል በድግር ቀና

ምርት አገላባጭ ቤቱ የቀና

441. አራሽ ገበሬ የሳቱ ላንቃ የሬት መራራ

የማይቀመስ የማያባራ

442. ስቆፍር ውየ ስቆፍር መሽ

አይለምነኝም የትም ያመሽ

443. በእርሻ የከበረ ጥሩ ባለቤት

እንግዳ ይሸኛል በማር በወተት

444. ባሻልማ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል

ሰራ ቆርቆሮ በት ባህር የሚመስል

445. በጥቋቁር በሬ ሆብሎ ሆብሎ

ሠራ ቆርቆሮ ቤት ሳሩን ወደያ ጥሎ

446. አየ አተላለም አዬ አተራረስ

ከድግሩ በላይ አፈሩ ሲፈስ

447. አቤት አስተራረስ ምድር አመታት

የሞፈሩ መርዘም የበሬው ፅናት

448. በጐምላላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል

ቆርቆሮ ቤት ሠራ ፋኖስ የሚመስል

449. በሬውን ሲነዳው እንደ ግሪደር

ጅራፉን ሲያጮኸው እንደምንሽር

ማን ይወዳደራል ከአስማረየ ጋር

450. ገበሬው ሁሉ ጠምዶ ሲፈታ

ወርዶ ተላሚ የኮሌ ጌታ

451. ወተት ቢጠፋ አይጠፋም ጠላ

ጐበዝ ገበሬ የቤቱ ባላ

451. ጠጋብ ገበሬ ቢሞትም ገነት ነው

ሌሊትም ከበሬው ቀንም ከእርሻው ጋር ነው

452. ሰውየው ጥቁር በሮቹ ጥቁር

ሰርዶ አገላባጭ እንደነፍሰ ጡር

**3.3 ምክር የሚሰጡ**

453. . ስታርስ እደርና እዚያው ስታርስ እደር

እርኩስ የጠላውን ጓያ ከመበደር

454. ማረስ ነው እንጅ ሸንጥ እስኪቆስል

ምንድን ነው ስርቆት ውሻ ይመስል

455. እህል ዝሩ ዝሩ በየገደሉ ስር

በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር

456. በሬው ቀና በል ከጥጉ ድረስ

አርሶ የበላ አለው የደስ ደስ

457. ከሸርፋው ጐታ እፈሽ ካላሿት

ትታዘባለች ሚስትም ባዳ ናት

458. መስቀል ቀና በል ኮሌ ተራመድ

ራስ ካልቻሉት አይወድም ዘመድ

459. ማረስ ነው እንጅ እርፍ እስኪለመጥ
ይቸግር የለም ሞሰብ ሲገለጥ

460. ፎጣ መጠምጠም ራስ ይመልጣል
ሽንጥን ገትሮ ማረስ ይበልጣል

461. ወይ ካላረሱ ወይ ካልቀደሱ
ጠላ አይገኝም እንደደረሱ

462. ማረስ ነው እንጅ ከድቡ ድረስ
የመጣው ዘመድ ስቆ ይመለስ

463. አረተው ሳበኝ አታርገው ወዛ
እርሃብ ክፉ ነው ያጠፋል ለዛ

464. አረተው ሳበኝ መሸ ጀንበሩ
የዋልንበቱ ሳይታይ ሾሩ

465. ሳብሳብ አርገኝ እንደ መጠጫ
ክፉ ለምደናል በኮልባ ዋንጫ

466. በደጋግ በሬ ሃይ ሃይ ካላሉት
ችግር አይለቅም በአቡየ ቢሉት

467. ፎጣ መጠምጠም ራስ ይመልጣል
ድሪቶ ለብሶ ማረስ ይበልጣል

468. ማረስ ነው እንጅ እርፍ ነቅንቆ
ርሃብ ክፉ ነው ይገላል አንቆ

469. አታወላውል እርሻውን ድፈር
በወይራ ሞፈር በሚያዚያ ጀንበር

470. ኮሌ ተራመድ አይኤም ሰው ልመድ
ራስ ካልቻሉ አይወድም ዘመድ

471. ወይ እረስላት ወይም ሙትላት
በጣሳ ጥፊ አታስገድላት

472. ቀና በል ዘገር ቦረን ደግፌው
ወዲያና ወዲህ አታንገላታው

473. ተውረስ ደኑን ተውረስ አትኩራ

እንኳን በማረሻ ቆፍረው በዶማ
አላየኸውም ወይ የሸመቱን ተራ

474. ማረስ ነው እንጅ ማረስ ይበልጣል
ሞሰብ ሲገለጥ አካላት ያልቃል

475. ማረስ ነው እንጅ እርፍ እስኪወዛ
ሚስትን ከመንከር በጐመን ጨዛ

476. ማረስ ነው እንጅ አቧራ ለብሶ
ስርቆት ምንድን ነው ጨለማ ለብሶ

477. ወይኖ ዝቅበል ጀንበር በል ቀና
እንድናበድር እንድናቀና

478. ካረስን እንረስ በነሶረን
ትግር ባድማ አያድርገን

479. ሰነፍ ገበሬ እረስ አታማር
ከደግ ገበሬ ተበድረህ ዘር
አዝመራው ሲደርስ ክፈለው በጥር

480. ገበሬ ገበሬ እረስ አትተኛ
እንዳትተበተብ በችግር መጫኛ

481. ተውረስ ገበሬ ዘር ተበድረህ
መስከረም ሲመጣ ትከፍለዋለህ

482. ኧረ እረሱ ረሱ በእርሻ አትመለሡ
ቡና እንኳን ሲፈላ ይቸግራል ቁርሱ

483. እርሻን ማረስ በጥንድ በሬ ነው
በወቅቱ አለስልሶ በወቅቱ እንዲዘራው

484. ተውረስ ተውረስ ተውረስ ቀርበህ
የሰው ቤት ቅራሪ አያስብ ልብህ

485. እርሻውን እረሰው ግፋ በል ገበሬ
ሀገር እንድትለማ እንድትሆን ፍሬ

486. በሬውን ግረፈው ደሙ እስኪንዘረዘር
ከከበርቴ ደጃፍ ቁና ከመሠንዘር

487. ማረስ ነው ማረስ ነው ሞፈር እስኪለመጥ

ሃምሳ ሳንቲም ይዞ ጠንቋይ ቤት ከመሮጥ

488. በሬውን ግረፈው ደሙ እስኪንዘረዘር

ሽመታ ሰንት ነው እያልክ ከመዞር

489. ጉበዝ እርሻ እረሱ /2/ ካልሆንም መንኩሱ

እየወለዳችሁ ልጅ አታስለቅሱ

490. ትንሽ ሳህን ይዞ ጓያ ከመበደር

ማሳውን እረሰው ይሸፈናል በዘር

491. የአበሻ ማሽላ በጤፍ ከመበደር

እርሻ ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ነበር ማደር

492. ማረስ ብቻ አይደለም የገበሬ ሰራው

ከብቶችን ያረባል ለወተት ለስጋው

493. አገር ጥሎ መሄድ ምን ያደርግልሃል

ጠንክሮ መስራቱ ለአንተ ይሻልሃል

494. እርሻ ረስ እርሻ ረስ እርሻ ረስ ይበጃል

ሚስትም ትኮራለች ቤትም ይደረጃል

495. ወይ ፈትተህ ስደዳት ወይ እረስላት

የጐረቤት ሽታ አንገሸገሻት

496. ሰነፍ አትቸገር አትዋል ከጥላ

ከሀብታም ገበሬ ተበድረህ ዝራ

497. እረሰ ይሻልሃል እረስ ይሻልሃል

የጐረቤት ጠላ ሽታው ይገልሃል

498. ገበሬው እርሻ እረስ አትዋል በከንቱ

ማረስ አይደለም ወይ የእህል መሠረቱ

499. ወይ እረስ ወይ ነግድ ትዳር ይመርብህ

ሚስትህ አለቀሰች አማረረችብህ

500. ማረስ ነው እንጅ እጅ እስኪተላ

አሻግረው ቢያዩት የሰው ጐተራ

ዝንብ አይከለክል ርሃብ አይከላ

501. ማረስ ነው እንጅ እጅ እስኪቆስል

ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል

502. ማረስ ነው እንጅ ድቡን አዙሮ
አሻግሮ ቢያዩት አይሆንም ኑሮ
503. እስኪ ዘርን ዝራ አምላክን አምነህ
የሚሠጥህ እሱ አንተ ምን አውቀህ
504. ማረስ ያስፈልጋል ሞፈሩ እስኪለመጥ
እንግዳ ሲመጣ ሚስትን ከማጋለጥ
505. እርሻ እረሱ /2/ በእርሻ አትመለሡ
ባውንድ አየገኝም ኪስን ቢዳስሱ

**4.5 ተስፋን የሚገልፁ**

506. አምላክ ቢሻ ቢሻ ጌታ ቢሻ ቢሻ
ሳይዘራ አይቀርም የተገመሰ እርሻ

**4 የአረም ቃል ግጥሞች**

**4.1 ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች**

507. የጓሮየን ስንዴ አረም ተናነቀው
እባክህ ጌታዬ ባል ባሉን አላቀው
508. አረ ተው አምላኬ ፊትህን አዙርልኝ
አርሜ ኮትኩቼ ጥቅሙ እንዲበዛልኝ
509. ተጐንበሽ ውዬ ላረሙ ነቀላ
እኔ እልፍ ሳልል መጣብኝ ከኋላ
510. እህህ /እህህ ልቀመጥ በቂጤ
ልመልከታት ጤፌን ባገኝ ትንሽ ቢጤ
511. እህል ተዘርቶ አረም ባይኖር
ደሰታ ነበር አርሶ መኖር
512. ይህ አረም የሚሉት በጣም አደገኛ
ጥዋት ማታ ቢነቅሉት አሁንም አፍለኛ
አፍለኛስ ያረጃል አርጅቶም ይሞታል
አረም ግን አይጠፋም ቢጠፋም ይተካል
513. ሳምር ስጐለጉል ስዘራ ከረሜ
እሸት እሸት አልኩኝ ከመሃሉ ቁሜ
514. አርሜ ኮትኩቼ አደላድየሽ

ምን ተንኮለኛ ነው ያየ የበላሽ

515. አረሙን ለመንቀል ጤዛንም አልፈራ

እባክህ አምላኬ ዝናብ ስጠው ያፍራ

516. አረሙን አርሜ ጣቴን ደከመኝ

እህል ነበርኮ እኔን የሚያድነኝ

4.2 **ትችትን/ስድብ/ የሚገልፁ**

517. ወይ አርመህ አብላት ወይ አንተ ሙትላት

ሰነፍ ባል አግብታ ምነው ባታሰኛት

518. እንዳይኮተኩተው ዝናብ እየፈራ

በሃምሌ እንዳያርም ብርዱን እየፈራ

ልጁ ቢያለቅስበት በጅብ አስፈራራ

519. ጥዋት አረም ሲሄዱ አንች ተኝተሻል

የእኔንስ ጨረስኩኝ የአንች ፈንታ ቀርቷል

4.3 **ውዳሴ ቃል ግጥሞች**

520. አረሜን አርሜ ፈሰስ ሳስጨንቅ

የማናት ልጅ ብሎ መጣ ሊጠይቅ

521. ለኩትኳቶውማ አንችኑ ሰጥቶኛል

ቁጢት ከመበጠስ ይኸው ይሻለኛል

522. አረም ታርሞ እህል ሲያፈራ

አጨዳው ብዙ ሸክሙ ተራራ

523. አረሙ ሲታረም እዚያ በነበርኩኝ

የፊት የፊትህን ይገፍ በበረርኩኝ

524. ገዳይ በሃምሌ ዘንቦ ሲያባራ

አረም አራሚ ከሚስቱ ጋራ

525. ያርሳል በጠራራ ያርማል በጤዛ

ቁጭ ሲል አያፍርም በዚያ ጠረጴዛ

526. አጣጥና አጋም ጨብጦ ነቃይ

ከሰው ማሳ ላይ ነጭ ጤፍ አብቃይ

527. እርም እርም አርጎ ይገባል ከቤቱ

ገበሬ ገበሬ ገበሬ ገነቱ

4.4 ምክር የሚሰጡ

528. አርመህ ኮትኩተህ ካልሠራህ በመላ
ኋላ ተቸግረህ አሉማ እንዳትበላ

529. አዝመራውን ሁሉ አረም እንዳይበላው
ሴትም ሆነ ወንዱ ጠንክሮ ማረም ነው

530. ንቀይው አረሙን ሰርዶውን ለይተሽ
ከርሞ ነጭ ስንዴ ተበይበታለሽ

531. አጥርተሽ አርሚው ሁሉንም አዝመራ
እንድታስቀምጭው በመልካም ጐተራ

532. አረሙን አርሙ በጣም ተጣጣሩ
ችግርን በፍጥነት እንድታባርሩ

533. ሲያርሙ ተው አርም ሲሰሩ ተው ስራ
በግንቦት አይገኝ የሠው ቤት እንጀራ

534. ኸረ ጓዴ ጓዴ ቶሎ ቶሎ እረም
በወጣት አራሚ አነዳትቀደም

535. አረምን በጊዜው ካልነቃቀሉት
ጐጥጉጦ ይወጣል እንደቆንጆ ጡት

536. ሲያርሙ እማያርም ሲበሉ እማይበላ
ከሀገራችን ይውጣ እንዳይሠርቀን ኋላ

537. አንች አምስት ጣቴ አርሚ እባክሽ
ታጥቦ መቀመጥ ነው አንች የፈለግሽ

538. ንቅልቅል አድርጊው መጭና እንዶየውን
ማነው የዋለበት እንዳታስብይን

539. ባለቤቴ ድረሽ በጓሮ በኩል
አረሙን በቶሎ ከስሩ እንንቀል

540. ማረም ነው እንጅ ጤፍን ደህናአድርጐ
እንጐቻው ሲበሉት ይጥማል እንደ እርጐ

541. ምነው በባል ቢያርሱ ቅዳሜ ቢያርሙ
ከባለፀጋው ደጅ ሂዶ ከመቆሙ

542. አረም ሳይታረም ሳይወጣ አራሙቻ

አሁን የት ይገኛል የመኸር እንጉቻ

543. አረምን ካረሙት ከስሩ ነቅሎ ነው

ከቆረጡትማ ያው መተካቱ ነው

544. ማረም ነው እንጅ ስንፍና አይጠቅምም

አቁማዳ ይዞ ቢንከረፈፉ እሚያቀምስ የለም

545. ማረም ነው እንጅ ውርጭ ሳይፈሩ

ከችግር ነፃ ይሁን አገሩ

**4.5 ፍቅርን የሚገልፁ**

546. አረም ለምነሽኝ ከጕንህ ዋልኩኝ

በአይኔ ስላየሁህ ደህና ከረምኩኝ

547. አረሙን አርሜ ከዳሩ ስደርስ

ሽጋ ልጅ መጣልኝ ሆድ የሚያላውስ

ሽጋ ልጅ ሽተተኝ ሽጋ ሽጋ ገብስ

**4.6 ፀፀትን የሚገልፁ**

548. ገብሱን ሳናርም ቀለባችን

ክረምቱ መጣ ውሃ በላን

549. ሳላርመው ውዬ ሳልጐለጉለው

ገብሱን አራሙቻ እንክርዳድ በላው

**5.የጉልጓሎ ቃል ግጥሞች**

**5.1 ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች**

550. ጤፍን ስጐለጉል አረሙን ሳነሳ

ምነው ከወገቤ ተቆረጥኩኝሳ

551. አየህ ደስ ሲል የጤፍ ጉልጓሎ

ሲጐነበሱ ባይደክም ቶሎ

552. ጉልጓሎ ሲያዩሽ ቀላል መስለሽ

ሲጐነበሱ ታንቋቂያለሽ

553. እስኪ ልማለደው ልንገረው ለገብርኤል

የዘራሁት ሁሉ በሙሉ እንዲበቅ

**5.2 ውዳሴን የሚገልፁ**

554. ሲዋጋ ውሎ ሲጠልም እንደአሳ
ምነው አነሰው የጐልጓይ ምሳ
555. የቀኙ በሬ ልቤን ልቤን ሲል
ልማሙ ወጥቶ ጉች ጉች ሲል
ሰባቱ ጐልጓይ ቤቱን ቤቱን ሲል
556. እሰይ አደይ እርገጭው ወለላ
አንችንስ አልሠጥም በፍፁም ለሌላ
557. አጥለቀለቀችው
ደባይ የዋለችው
558. ላም አንችን የሸጠ
አይኑ ፈጠጠ
አንችን የገዛ
ግንባሩ ወዛ
559. መች ይመለሳል የላም ውለታ
ስታበራይ ውላ ስትታለብ ማታ
560. አማረ ሠመረ
ዳቦው ተከመረ

ነጭ ጤፍ አምራች ጥርስ የሚመስል
561. አሪበት ሽኝበት
ወርቅ እንዲበቅልበት
562. በሃምሌ ጐልጉዬ መስከረም አርሜ
በዘርዛራ ማጭድ በህዳር አጭጄ
መኸሩን ሸክፌ እበላለሁ እኔ
ጥርስ የመሰለ ነጭ ጤፍ አብቅዬ

**5.3 ምክር የሚሰጡ**

563. መጐልጐል ነው እንጅ ወገብ አደግድጐ
እንጀራ አይገኝም ቢጥዱ ምጐጐ
564. ጉልጓሎን መጐልጐል ከስሩ መንጥቆ
ካልተጐለጐለ ቀረ ከዚያው ፀድቆ

565. እህሉ ሲበቅል አረም እንዳይኖረው
አረሙ እንዲጠፋ ጐልጉሎ መጣል ነው
566. እንውረድ እንጅ ከጉልጓሎው
ያረባው አረም እንዳይበላው
567. የገበሬ ሚስት ጐልጉይ ዝቅ በይና
ዋደት ሞልቶ ማቡካት አይገኝምና
568. ሰዎች ዝቅ ዝቅ በሉ ጉቶውን እናንሳ
አምርተን አድርሰን እንብላ ዳጉሳ
569. በል ዝናቡም ዝነብ ካፊያውም አካፋ
የጐለጐልነው ጤፍ ተዘርቶ እንዳይጠፋ
570. አንተም ጠንክር እረስ እኔም ልጐልጉል
ምሳችን ይመጣል በአዲስ አገልግል
571. እንደ ጤፍ እንጀራ ያዘኝ በአገልግል
አንተ እያረስክልኝ እኔ ልጐልጉል
572. ካልጐለጐሉት ካልመጠነጠሩት
አዝመራ አይገኝ ጫካ ቢረጩት
573. እማ በራይ
ደረሰብሽ ጐልጓይ
ይበጃል ያንች እበት
በአግድመት ጣይበት
574. እሸው እናቴ እግር በእግር
እንዳያነፋ እንዳይፎገር
575. ከደረሱ ይመለሱ
ካልደረሱ ይድረሱ
576. ተው ጐልጉል ገበሬ ተው ወጥረህ ስራ
ካልተጐለጐለ አይገኝ እንጀራ
577. ደፋ ደፋ አድርጉት አረሙን ከስር
የተወለወለ መደብ እንዲመስል
578. ላሜ ቦራ እሪበት ሽኝበት
ነጭና ቀይ ጤፍ እንድናበቅልበት

579. ጤፉ በቅሎ እንድናየው

ጕበዝ በርቱ እንጕልጉለው

580. ተው ወጥረህ ስራ ተው ጕልጉል ገበሬ

ካልተጕለጕለ አይገኝም ጥሬ


581. ጕልጉለን አምላክን እንማ

እሱ ይሰጠናል ያሰብነውን ሁላ

582. ወንድም ሆነ ሴቱ ወጥቶ መጕልጕል ነው

ካደጋ በኋላ ለእህል ደመኛ ነው

# አባሪ አራት፡- ካርታ




የዳባት ወረዳ ካርታ




ምስል 1 ፡ የአማራ ክልል ካርታ /ከወረዳዉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘ/

# አባሪ አምስት፡- ፎቶ ግራፎች



ምስል 2. አቶ አድን ዱቤ ጤፍ ሲወቁ



ምስል 3. አቶ አድን ዱቤ ከዮሀንስ አድን ጋር ጤፉን ከገለባው በእጃቸው ሲለዩ



ምስል 4. አቶ ግዛት አሰፋ፣ የሽበር ካሳው፣ ወ/ሮ ሙሉ አለበል፣ ዋሴ ፈንቴ የጤፍን ገለባ በመሽን ሲያራግፉ



ምስል 5. አቶ አለማየሁ ተዘራ ሆበሬ እያሉ ግጥም በመደርደር ላይ




ምስል 6. አቶ ምህረት ካሴ የምስር አውድማ በመጥረግ ላይ



ምስል 7. አቶ ግዛት አሰፋ ሆበሬ እያሉ ግጥም በመደርደር፣ አጥኝዋ እህሉን በመቆስቆስ ላይ



ምስል 8. የሽበር ካሳው ሆበሬ እያለ ግጥም በመደርደር፣ ግዛት አሰፋ እህሉን በመቆስቆስ ላይ



ምስል 9. ከግራ ወደ ቀኝ መክት ትዛለ፣ አስማረ መልሴ፣ ምህረት መልሴ፣ ነጋ ብርቁ፣ ምርኩዝ በለጠና ሌሎች በጤፍ አጨዳ ላይ



ምስል 10. ከግራ ወደ ቀኝ የማታው አስናቀው፣ ሲሳይ ጎነጠ፣ የሽበር ካሳው፣ አበራ ብርሃኑና ሌሎች በጤፍ አጨዳ ላይ



ምስል11. ከግራ ወደ ቀኝ ደጀን ንጉሴ፣ አቸንፎ ጀጃው ፣ቢራራ አገኘሁና አራጋው ተሻገር፣ቢምር ሞላ፣ ቢራራ ዋለ በአጨዳ ላይ ሲዘፍኑና ሲፎክሩ




ምስል12. ከግራ ወደ ቀኝ አራጋው ተሸገር፣ ቢራራ ዋለ፣ ቢምር ሞላና ሌሎች በአብሽ አጨዳ ላይ ሲፎካከሩ



ምስል13. ከግራ ወደ ቀኝ የማታው አስናቀው ፣ምህረት ካሴ፣ አደራጀው ዱቤ፣ ድረስ ግርማውና ሌሎች በጤፍ አጨዳ ላይ



ምስል14. ከአጨዳ በኋላ ገበሬዎች ጠላ በመጠጣትና አቶ ቢራራ ዋለ በመመረቅ ላይ



ምስል15. አቶ ስምሙ ነጋሽ እርሻ በማረስ ላይ

## መግለጫ

ይህ ጥናት የእኔ  ኦርጅናል ስራ ሲሆን ከዚህ በፊት ለሌላ ዲግሪ ማሟያ በየትኛውም ዩኒቨርስቲ አልቀረበም፡፡ የተጠቀምኩባቸው ምንጮች በተገቢው መንገድ በትክክል የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም  ሀብታም ግዛት

ፊርማ ----------------------------------

የተረከበበት ቦታና ጊዜ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሰኔ 2006 ዓ.ም

አማካሪ ዘሪሁን  አስፋው

ፊርማ -------------------------------------